

# FSC የኢትዮጵያ ጊዜያዊ የደን አስተዳደር ደረጃ

*FSC-STD-ETH-01-2024 AM*

FSC FORESTS™ FOR ALL FOREVER

**የፎቶ ባለመብት:**

ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በካፋ የባዮስፊር ጥብቅ ደን ውስጥ የሚገኝ ጥቁር እና ነጭ *ኮሎቡሰ ጉሬዛ* © አብዱራዛክ ሣህሌ ሙሳ

**በዚህ የአማርኛ ትርጉም ላይ የሚገኝ ማስታወሻ:-**

ይህ የ FSC ጊዜያዊ የደን አስተዳደር ደረጃ መመዘኛ ለኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ (እንግሊዝኛ) ቅጂ የአማርኛ ትርጉም ነው። ኦፊሴላዊው የእንግሊዝኛ ስሪት እና የተተረጎሙት የአማርኛ ቅጂዎች በ connect.fsc.org ይገኛሉ። በፀደቀው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስሪት እና በተተረጎመው ቅጂ መካከል ልዩነት ወይም አለመጣጣም ካለ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስሪት የበላይነት ይኖረዋል።

**® 2024 Forest Stewardship Council, A.C. ሁሉም መብት የተጠበቀ ነዉ።**

**FSC® F000100**

በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኙትን የቅጂ መብት ያለ አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ለሕዝብ ወይም ለንግድ ዓላማዎች ማሰራጨት ፣ መለወጥ ፣ ማስተላለፍ ፣ እንደገና መጠቀም ፣ ማባዛት፣እንደገና መለጠፍ ወይም መጠቀም አይቻልም። በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኙትን ገጾች ለመመልከት፣ ለማውረድ፣ ለማተም እና ለማሰራጨት ለመረጃነት ብቻ እንዲያገለግል ፈቃድ ተሰጥቶዎታል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| **ርዕስ** | FSC የኢትዮጵያ ጊዜያዊ የደን አስተዳደር ደረጃ | |
| **የዶክመንቱ መለያ ኮድ** | FSC-STD-ETH-01-2024 AM | |
| **የሰነዱ ሁኔታ** | የጸደቀ | |
| **የተፋጻሚነት ወሰን**[1] | ለሁሉም የደን ዓይነቶች (ዝርዝሮች በዚህ ደረጃ ክፍል ‘’B.2 ወሰን’’ ተቀምጧል) | |
| **አጽዳቂ አካል** | የፖሊሲ መማክርት ቡድን | |
| **ቀን** | **የጸደቀበት ቀን** | እ.ኤ.አ ሐምሌ 19/2024 |
| | **የታተመበት ቀን** | እ.ኤ.አ መስከረም 3/2024 |
| | **የሚፀናበት ጊዜ** | እ.ኤ.አ ጥር 15/2024 |
| **የጊዜ ወሰን** | **የሽግግር ጊዜ:** | ስራ ላይ ከዋለበት እሰከ 12 ወራት |
| | **ሰነዱ የሚያገለግልበት ጊዜ:** | እስኪታደስ፣ በአዲስ እስኪተካ ወይም እስኪሰረዝ |
| **ደረጃው የተዘጋጀው** | Soil Association Certification Limited<br>Janette McKay<br>Email: jmckay@soilassociation.org<br>Severinus Jembe;<br>Email: sjembe@soilassociation.org. | |
| **አስተያየት ለመስጠት** | FSC International – Performance and Standards Unit<br>Adenauerallee 134<br>53113 Bonn<br>Germany<br><br>**Phone:** +49 -(0)228 -36766 -0<br>**Fax:** +49 -(0)228 -36766 -65<br>**Email**: psu@fsc.org | |

## የሰነድ ስሪት መከታተያ

| የሰነድ ስሪት | መግለጫ | የፀደቀበት ቀን |
|---|---|---|
| **V1.0** | የመጀመሪያ ሰነድ ፣ FSC-STD-ETH-01-2024 የኢትዮጵያ ደን አስተዳደር ደረጃ፣ በ P&C V5-3 ላይ የተመሠረተ | እ.ኤ.አ. 19/07/2024 |

[1] የሽግግር ጊዜው በተመሳሳይ ጊዜ አዲሱ የስሪት ደረጃ የሚተገበርበት እና የቀድሞው ስሪት ደረጃ የሚወገድበት የጊዜ ሰንጠረዥ ነው። የሽግግር ጊዜው ካበቃ ከስድስት (6) ወራት በኋላ በአሮጌው ስሪት ላይ የተሰጡ የምስክር ወረቀቶች ዋጋ ቢስ እንደሆኑ ይቆጠራሉ ።

# ማውጫ


**ማውጫ** **3**

**ሀ መቅድም** **5**

ሀ-1. የደን አስተዳደር ምክር ቤት (FSC) 5

ሀ-2. የFSC መርሆች እና መሥፈርቶች 5

**ለ መግቢያ** **6**

ለ.1. ዓላማ 6

ለ.2 የተፈፃሚነት ወሰን 6

ለ.3. የማስፈጸም ኃላፊነት 6

ለ.4. በደረጃው ውስጥ መደበኛ ለሆኑና ላልሆኑ መሰረታዊ ነገሮች በተመለከተ የአጠቃቀም ማስታወሻ 7

ለ.5 ትርጓሜዎች እና ክርክር 8

**ሐ አውድ** **9**

ሐ-1 አጠቃላይ የደን ዘርፍ መግለጫ 9

ሐ-2 ደረጃ ለማውጣት መነሻ መረጃዎች 11

**መ. ማጣቀሻ** **13**

**ሠ. መርሆዎች, መስፈርቶች እና አመላካቾች** **14**

መርሀ-1: ህግን ማክበር 14

መርሀ 2: የሰራተኞች መብት እና የቅጥር ሁኔታ 17

መርሀ-3፡ የነባር ሕዝቦች/Indigenous peoples/ መብቶች 21

መርሀ 4: የማህበረሰብ ግንኙነቶች 24

መርሀ -5: የደን ጠቀሜታዎች 28

መርሀ-6: የአካባቢያዊ እሴቶች እና ተጽዕኖዎች 30

መርሀ 7: የደን አስተዳደር ዕቅድ ዝግጅት 36

መርሀ-8: ክትትልና ግምገማ 39

መርሀ-9: ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች 41

መርሀ-10: የአስተዳደር ተግባራት አፈጻጸም 44

**ረ. አባሪዎች 49**

| | | |
|---|---|---|
| አባሪ ሀ. | ቢያንስ የሚመለከታቸውን ህጎች፣ ደንቦች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የየጸደቁ ዓለም አቀፍ ኮንቨንሽን እና ስምምነቶችን የያዘ ዝርዝር (መርህ 1.) | 49 |
| አባሪ ለ. | ለሠራተኞች የሚያስፈልጉ ሥልጠናዎች (መርህ 2) | 55 |
| አባሪ ሐ. | የጥበቃ ቦታ መረብ (Conservation Area Network) ጽንሰ-ሀሳባዊ ንድፍ (መርህ6) | 56 |
| አባሪ መ. | በአገሪቱ ወይም በክልሎች ውስጥ የሚገኙ ብርቅዬ እና ለመጥፋት በአስጊ ሁኔታ ላይ ያሉ ዝርያዎች ዝርዝር (መርህ 6) | 57 |
| አባሪ ሠ. | የደን አስተዳደር እቅድ መሰረታዊ ነገሮች (መርህ7) | 60 |
| አባሪ ረ. | የእቀድና ክትትል የጽንሰ-ሀሳብ ማዕቀፍ (መርህ 7) | 62 |
| አባሪ ሰ. | የክትትል ቅድመ ሁኔታዎች (መርህ 8) | 64 |
| አባሪ ሸ. | ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታ ዋና ቦታዎች የሚመለከቱ አመልካቾችን ለማዘጋጀት ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ (መርህ 9) | 66 |
| አባሪ ቀ. | ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስልቶች (መርህ 9) | 68 |
| አባሪ በ. | ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ማዕቀፍ (መርህ 9) | 69 |
| አባሪ ተ. | መዝገበ ቃላት | 103 |

# ሀ መቅድም

(መረጃ ሰጪ ክፍል)

## ሀ-1. የደን አስተዳደር ምክር ቤት (FSC)

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካባቢና ልማት ኮንፈረንስ (የምድር ጉባዔ/Earth summit እ.አ.አ. በ 1992 በሪዮ ዴ ጄኔሮ) ከተካሄደ በኋላ እ.አ.አ. በ1993 የደን አስተዳደር ምክር ቤት ኤ.ሲ. /The Forest Stewardship Council A.C (FSC) የተቋቋመ ሲሆን ተልእኮውም በዓለም ላይ ያለዉን ደን ለአካባቢ ተስማሚ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘላቂ ጥቅም የሚያስገኝ አስተዳደር ማስፋፋት ነዉ።

FSC በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ዕውቅና እና ገለልተኛ የሆነ የሶስተኛ ወገን ማረጋገጫ ስርዓት ይዘረጋል። ይህ ስርዓት የምስክር ወረቀት ባለቤቶች ምርቶቻቸውን እና አገልግሎቶቻቸውን ለአካባቢ ተስማሚ፣ ማህበራዊ ጠቀሜታ እና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ያለውን የደን አስተዳደር በመከተል ለገበያ እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል።FSC እንዲሁም በFSC መርሆዎች እና መመዘኛዎች ላይ የተመሠረቱ ብሔራዊ የደን አስተዳደር ደረጃዎች እና ጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃዎች ለማዘጋጀት እና ለማፅደቅ ደረጃዎችን ያወጣል። በተጨማሪም የ FSC መስፈርቶች መሟላታቸውን የሚያረጋግጡ የተስማሚነት ምዘና አሰጣጥ አካላት /conformity assessment bodies (የማረጋገጫ አካላት ተብሎም ይጠራሉ) እውቅና ለመስጠት የ FSC ደረጃዎችን ያወጣል።

ለአካባቢ ተስማሚ የሆነ የደን አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት እንጨት፤ እንጨት ነክ ያልሆኑ ምርቶች እና የስነ ምህዳር አገልግሎቶች፣ የደን ብዝሃነት፣ ምርታማነት እና ስነ ምህዳራዊ ሂደቶች መጠበቃቸዉን ያረጋግጣል።

ማኅበራዊ ጥቅም ያለው የደን አስተዳደር ለአካባቢው ነዋሪዎችም ሆነ በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ የረጅም ጊዜ ጥቅም እንዲያገኙ ይረዳል፤ እንዲሁም የአካባቢውን ነዋሪዎች የደን ሀብትን ለመጠበቅ እና የረጅም ጊዜ የአስተዳደር ዕቅድ ለማክበር ጠንካራ ማበረታቻ ይሰጣል።

ከኢኮኖሚ አንፃር አዋጭ የሆነ የደን አስተዳደር ማለት ማንኛውም የደን ልማት ስራዎች የሚዋቀሩት እና የሚተዳደሩት እንዲሁም በበቂ ሁኔታ ትርፋማ የሚሆኑት የደን ሀብት፣ የስነ-ምህዳር ወይም የአከባቢዉ ማህበረሰብን በማይጎዳ መልኩ ትርፋማ ሲሆን ነው፡፡ በቂ የገንዘብ ትርፍ የማግኘት ፍላጎት እና ኃላፊነት የሚሰማው የደን ሥራ መርሆዎች መካከል ያለው ውጥረት ሊቀነስ የሚችለዉ በተሟላ መልኩ የደን ምርቶች እና አገልግሎቶችን በተሻለ ዋጋ ለገበያ ለማቅረብ በሚደረጉ ጥረቶች ነዉ ።

## ሀ-2. የFSC መርሆች እና መሥፈርቶች

የFSC መርሆዎችን እና መስፈርቶችን FSC ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳተመዉ እ.ኤ.አ በ1994 በአፈጻጸም ላይ ተመስርቶ፣ በውጤት ተኮር እና አለምአቀፋዊ ደረጃን በጠበቀ መልኩ ነዉ። መርሆዎቹ እና መስፈርቶቹ የሚያተኩሩት ከመስክ ትግበራ አስተዳደር ስርአት ይልቅ  በደን አስተዳደሩ የመስክ ትግበራ አፈጻጸም ላይ ነው።

በመርሆዎች ወይም በመስፈርቶች መካከል የተዋረድ ልዩነት የለም። በእያንዳንዱ የደን አስተዳደር አሃድ (ዩኒት) ዉስጥ እኩል ደረጃን፣ ተቀባይነትን እና ስልጣንን ይጋራሉ፣ እና በጋራ እና በተናጠል ይተገበራሉ።

የFSC መርሆዎች እና መስፈርቶች ከInternational Generic Indicators /IGI/ ጋር በመሆን ለብሔራዊ የደን አስተዳደር ደረጃዎች እና ጊዜያዊ ብሄራዊ ደረጃዎችን (INS)  ለመቅረጽ መሰረት ይሆናሉ።

# ለ መግቢያ

## ለ.1. ዓላማ

(መረጃ ሰጪ ክፍል/Informative section)

የዚህ ደረጃ ዓላማ የመስፈርቶችን ስብስብ የሚያቀርበው፡-

1. ድርጅቱ ኃላፊነት የሚሰማው የደን አያያዝ በደን አስተዳደር አሃድ ውስጥ እንዲተገበር ማድረግ እና ስምምነትን ለማሳየት፤
2. የደን አስተዳደር ምክር ቤት (FSC) እውቅና የተሰጣቸው የምስክር ወረቀት ሰጪ አካላት (CBs) ከዚህ መስፈርት ጋር የተመዘነ የደን አስተዳደር የምስክር ወረቀት ለመስጠት፣ ለማቆየት ወይም ለማደስ እንዲያስችል፤

## ለ.2 የተፈፃሚነት ወሰን

(መደበኛ ክፍል/Normative section)

ይህ ደረጃ በሚከተለው የተፈፃሚነት ወሰን ውስጥ የሚተገበር ይሆናል፡-

| | |
|---|---|
| ጂኦግራፊያዊ ክልል | **በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ** |
| የደን ዓይነቶች | **ሁሉም የደን ዓይነቶች** |
| የባለቤትነት ዓይነቶች | **ሁሉም የባለቤትነት ዓይነቶች የህዝብ፣ የግል እና ሌሎችን ጨምሮ** |
| የመጠን እና የጥንካሬ ምድቦች<br>**(According to section 6 of FSC-STD-60-002)** | **ሁሉም የደን አስተዳደር አሃዶችን፣ አነስተኛና ዝቅተኛ የደን አያያዝ ወይም አጠቃቀም ያላቸዉን ጨምሮ (SLIMFs)**<br>**(See section B.4 for the applicable SLIMF eligibility criteria)** |
| የደን ዉጤቶች<br>**(According to FSC-STD-40-004a)** | **እንጨትና የእንጨት ነክ ያልሆኑ ምርቶች (NTFPs): ፍራፍሬዎች (የጫካ ቡና እና የዱር ኮረሪማ); ማር** |

## ለ.3. የማስፈጸም ኃላፊነት

(መደበኛ ክፍል/Normative section)

በዚህ ደረጃ ውስጥ ያሉት መስፈርቶች ከድርጅቱ የደን አስተዳደር አሃድ ጋር የተያያዙትን ሁሉንም የአስተዳደር ተግባራት ይሸፍናል ፣ በአስተዳደር አሃዱ ውስጥም ሆነ ውጭ፣ በቀጥታ የተከናወኑም ወይም በኮንትራት የተሰጡን ያካትታል።

ከጂኦግራፊያዊ ቦታ አንፃር በዚህ ደረጃ ውስጥ ያሉት መስፈርቶች በአጠቃላይ ለ(ዳግም) ሴርተፊኬት (ምሥክር ወረቀት) ማረጋገጫ በሚቀርብበት የደን አስተዳደር አሃድ ወሰን ውስጥ ላለው አጠቃላይ የጂኦግራፊያዊ ቦታ ይሠራል። ይሁን እንጂ አንዳንድ መስፈርቶችና አመላካቾች ከአስተዳደር አሃዱ ወሰን ውጭ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ይህ በFSC መርሆዎች እና መስፈርቶች እንደተገለጸው የደን አስተዳደር አሃድ አካል የሆኑትን የመሠረተ ልማት መገልገያዎችን ያካትታል።

የደን አስተዳደር ደረጃዎች ከዓለም አቀፍ፣ ከብሔራዊ እና ከአከባቢዊ ህጎች እና ደንቦች ጋር በጥምረት መተግበር አለባቸው።

በዚህ ደረጃ እና ሕጎች ውስጥ ባሉ መስፈርቶች መካከል ግጭት ሊኖር በሚችልበት ጊዜ ልዩ የ FSC አሰራር ሂደት ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

በዚህ መስፈርት ውስጥ ካሉት የደረጃ መመዘኛ ጋር የሚጣጣም መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው (ዎች) ወይም አካላት የእውቅና ማረጋገጫ አመልካች ወይም ባለቤት ናቸው ። ለFSC ምሥክር ወረቀት ዓላማ እነዚህ ግለሰቦች ወይም አካላት "ድርጅት" ተብለው

ይጠራሉ።

ድርጅቱ ከደን አስተዳደር አሃዱ ጋር በተያያዙ ውሳኔዎች፣ ፖሊሲዎች እና የአስተዳደር እንቅስቃሴዎች ተጠያቂ ነው።

በተጨማሪም ድርጅቱ ሌሎች ሰዎች ወይም አካላት በድርጅቱ ፈቃድ ወይም የኮንትራት ውልየተሰጣቸው ወይም ለደን አስተዳደሩ አሃድ ጥቅም እንዲሠሩ የተፈቀደላቸው በዚህመስፈርት ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን የማሳየት ኃላፊነት አለበት።

በዚህ ደረጃ ውስጥ ካሉት መስፈርቶች ጋር የማይጣጣሙ ሰዎች ወይም አካላት ሲኖሩ ድርጅቱ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅበታል።

## ለ.4. በደረጃው ውስጥ መደበኛ ለሆኑና ላልሆኑ መሰረታዊ ነገሮች በተመለከተ የአጠቃቀም ማስታወሻ

(መደበኛ ክፍል/Normative section)

በደረጃ ውስጥ ያሉ መደበኛ የሆኑመሰረታዊ ነገሮች ማለት፡

በሌላ መልኩ እስካልተገለጸ በስተቀር የሰነዱ ትግበራ ወሰን፣ የሚፀናበት ቀን እና ጊዜ፣ የቃላት መፍቻ፣ መርሆዎች፣ መስፈርቶች ፣ አመላካቾች፣ ሠንጠረዦች እና አባሪዎች ያካትታል፤

**ማስታወሻ:-** የአባሪዎችን ኦዲት በሚመለከት፣ አመላካች አባሪን ሲያመለክት፣ የተስማሚነት ግምገማው ሁለቱንም አመላካች እና ተዛማጅ መስፈርቶችን አባሪውንም ማካተት አለበት ፤ አባሪው በግልፅ 'መረጃ ሰጪ' ተብሎ ካልተገለጸ በስተቀር፤

<u>በደረጃ ውስጥ መደበኛ ያልሆኑ መሰረታዊ ነገሮች</u> ለመመሪያ ብቻ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉት፡

የዚህን መስፈርት ትግበራ ለመደገፍ የሚረዱ ማረጋገጫዎች፣ የመመሪያ ማስታወሻዎች እና ምሳሌዎች ተካተዋል።

ኦዲተሮች አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሌሎች የማረጋገጫ ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ። በተጨማሪም ድርጅቱ የሚጠበቅበትን የማረጋገጫዎች ተስማሚነት እንደ መመሪያ ለማሳየት ማቅረብ ይችላል።

<u>በግራጫ ቀለም የተለዩ መሰረታዊ ደንቦች</u> በሀገሪቱ ውስጥ የማይተገበሩ ነገር ግን ለግልፅነት ሲባል ደረጃ ውስጥ ተካተዋል።

ለአነስተኛና ዝቅተኛ የደን አያያዝ ወይም አጠቃቀም (SLIMF) ብቁ የሆኑትን የደን የአስተዳደር ክፍሎችየሚያሰተዳድሩት የአስተዳደር አሃድ ድርጅቶች በደረጃዉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም አመልካቾች ማሟላት አለባቸው ፣ የተወሰኑ የSLIMF አመልካቾች ካልሆኑ በስተቀር (ለምሳሌ ፣ SLIMF 1.7.1)፣ ከዚህ በላይ ያሉ ድርጅቶች ከነእሱ ጋር መስማማመት አለባቸው፡

| SLIMF የብቃት መስፈርት | ብሄራዊ ገደብ |
|---|---|
| **አነስተኛ የአስተዳደር አሃድ(management unit)** | እስከ 100 ሄክታር |
| **ዝቅተኛ መጠን ያለዉ የ አስተዳደር አሃድ** | ከአጠቃላይ የደን ምርት ቦታዎች በየዓመቱ የሚሰበሰበዉ መጠን ከአመታዊ አማካይ የምርት ጭማሪ (MAI) 20% ያነሰ ሲሆን፣ እና<br>ወይም ከአጠቃላይ የደን ምርት ዓመታዊ የምርት መጠኑ 5000 ኪዩቢክ ሜትር ያነሰ ሲሆን፣<br>ወይም በሪፖርቶች እና ተቆጣጣሪ ኦዲቶች በተረጋገጠው የምስክር ወረቀት በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ የዓመታዊ አማካይ የምርት መጠን ከአጠቃላይ የደን ይዞታ በዓመት ከ5000 ኪዩቢክ ሜትር በታች ሲሆን ነው፤ |

የእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶችን (የNTFPsን) በማረጋገጫ ደረጃ ውስጥ የሚያካትቱ ድርጅቶች በመደበኛ ውስጥ ሁሉንም አመልካቾች ማሟላት አለባቸው።

የተወሰኑ NTFP አመላካቾች ካሉ (ለምሳሌ፣ "NTFP 1.2.1" የሚል ምልክት የተደረገባቸው) ፣ እነዚህ ድርጅቶች በተጨማሪ ከእነሱ መስፈርቶች ጋር መስማማት አለባቸው።

| ድንጋጌዎችን ለመግለጽ የቃል ቅጾች<br>[Adapted from *ISO/IEC Directives Part 2: Rules for the structure and drafting of International Standards*] | |
|---|---|
| ይሆናል / **shall** | : ከደረጃው ጋር ለማጣጣም በጥብቅ መከተል ያለባቸውን መስፈርቶች ያመለክታል፤ አይሆንም 'shall not' የሚለው መከልከልን ያመለክታል |
| **"መሆን አለበት"/ "should"** | : በርካታ አማራጮች መካከል አንዱ በተለይ ተስማሚ እንደሆነ የሚመከር መሆኑን ፣ ሌሎችን ሳይጠቅሱ ወይም ሳይካትቱ ፣ ወይም የተወሰነ ድርጊትን ተመራጭ እንደሆነና ግን የግድ አስፈላጊ አለመሆኑን ያመለክታል።<br>ድርጅቱ እነዚህን መስፈርቶች በተመጣጣኝ መንገድ ሊያሟላ የሚችለው ይህ ሊገለጽ እና ሊረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ነው። |
| **"ሊሆን ይችላል"/ "may"** | : በደረጃው ወሰን ውስጥ የሚፈቀደውን የእርምጃ አካሄድን ያመለክታል; የማያስፈልገው (Need not) የሚያሳየው የተወሰነ የእርምጃ አካሄድ መስፈርት ካልሆነ ነው። |
| **"ይችላል"/ "can"** | : የምንጠቀመው ቁሳዊ ፣ አካላዊ ወይም ምክንያታዊ የመሆን እድልና የችሎታ መግለጫ አረፍተ-ነገሮች ናቸው፣ |

በመሠረታዊ መርሆዎች እና መስፈርቶች በF(በኤፍ) የጽሑፍ ክፍል ውስጥ ያለው በሰያፍ (in italics) የተጻፉ እና በኮከብ ምልክት(asterisk) የተለዩ ቃላትን ይይዛል ። እነዚህ ቃላት በ "የቃላት-መፍቻ" ክፍል ውስጥ ተገልጸዋል።

ይህ ሰነድ በFSC-PRO-60-007 EN መዋቅር ፣ ይዘት እና የጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃዎች መ በተገለጸው መሠረት ለግምገማ እና ለክለሳ ክፍት ነው ።

## ለ.5 ትርጓሜዎች እና ክርክር

(መደበኛ ክፍል/Normative section)

የጊዜያዊ የደን አስተዳደር ደረጃዎችን በተመለከተ የትርጉም ጥያቄዎች ሲነሱ በቀጥታ ለFSC ለአፈጻጸም ሂደት እና ለማፅደቅ ይቀርባሉ፡፡ ተቀባይነት ያገኙ (የጸደቁ) ትርጓሜዎች በአለም አቀፍ የ FSC ድር ገጽ ላይ ታትመዋል (See፡ INT-STD-60-006_01) ።

በባለድርሻ አካላት መካከል የምስክር ወረቀት መስፈርቶችን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች በFSC የክርክር አፈታት ስርዓት ይስተናገዳሉ፡፡ (See፡<FSC-PRO-01-008-Processing Complaints in the FSC Certification Scheme Procedure>).

# ሐ አውድ

## ሐ-1 አጠቃላይ የደን ዘርፍ መግለጫ

(መረጃ ሰጪ ክፍል /Informative section)

ኢትዮጵያ እጅግ አስደናቂ የሆኑ ጂኦሎጂካዊ ታሪክ፣ ሰፊ የሆነ ላቲቲዩድ እና የመሬት ከፍታ ልዩነት ያላት ሀገር ስትሆን በዓለም ላይ ከሚገኙት ሰፊ ስነ ምህዳራዊ አካባቢዎች መካከል አብዛኛውን ይዛለች። እነዚህ አካባቢዎች ከአፋር 115 ሜትር ከባህር ጠለል በታች ከሚገኙት ዝቅተኛ ቦታዎች ጀምሮ በሰሜን በኩል ከሚገኘው የራስ ዳሽን ተራራ ጫፎች እና በደቡብ ምስራቅ ከሚገኘው የባሌ ተራሮችን ያካትታል። እነዚህ የተለያዩ አካባቢዎች ደግሞ ለሀገሪቱ አጠቃላይ ባዮሎጂያዊ ብዝሃነት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱትን የተለያዩ ዝርያዎችን ለመያዝ ችሏል።

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ብርቅዬ እንስሳትና እፅዋት ያሏት አገር ናት፤ ነገር ግን እነዚህ እንስሳትና እፅዋት አከባቢያቸው ከመጠን በላይ ጥቅም ላይ በመዋሉ እና የተፈጥሮ መኖሪያቸው በመነሳቀሉ ምክንያት እስከ መጨረሻው ከዓለም ላይ የመጥፋት አደጋ ተጋርጦባቸዋል። በFAO የደን ሀብት ዳሰሳ ጥናት (FRA) ውስጥ የቅርብ ጊዜ የተዘረዘሩት የኢትዮጵያ የደን ሀብት መረጃዎች ኢትዮጵያን ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ከ10 እስከ 30 በመቶ የሚደርስ የደን ሽፋን ካላቸው አገራት መካከል አስቀምጧታል።

በFRA (FAO, 2015) መሠረት የኢትዮጵያ የደን ሽፋን 12.4 ሚሊዮን ሄክታር (11.5 በመቶ) ነው። ከ1990 እስከ 2010 ባለው ጊዜ ውስጥ በአገሪቱ ውስጥ የእፅዋት ሽፋን ማሽቆልቆል እንዲፋጠን አስተዋፅኦ ካደረጉት ምክንያቶች ከፍተኛ የድህነት መጠን ፣ የህዝብ ብዛት መጨመር ጋር ተያይዞ የደን ምርቶች ፍላጎት እንደ ማገዶ ያሉ እና ከዚያ በኋላ ደኖችን እና የደን ቦታዎችን ወደ እርሻ መሬቶች እና ሰፈራዎች መቀየር ናቸው። እ.ኤ.አ. ከ1990 እስከ 2000 ባለው ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ደኖች (መጠን ደንና ዘርዛራ ደን ጨምሮ (woodland)) በ1.4 ሚሊዮን ሄክታር ቀንሷል። እ.ኤ.አ. በ 2005 የደን ሽፋኑ የበለጠ እየቀነሰ እና 13.0 ሚሊዮን ሄክታር እንደሚሸፍን ተገምቷል:: በሌላ አገላለጽ ኢትዮጵያ ከ1990 እስከ 2005 ባለው ጊዜ ውስጥ በአማካይ በአመት 140,000 ሄክታር ደን (FAO, 2015) በመጨፍጨፉ ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር በላይ ደን አጥታለች።

በአሁኑ ወቅት በደን የተሸፈነው ቦታ 12.4 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ነው ተብሎ ይገመታል፤ ይህም ከጠቅላላው የመሬት ስፋት 11.4 በመቶውን ይሸፍናል። የደን መጨፍጨፍ ዋነኛ ምክንያቶች ለግብርና ዓላማዎች የሚውሉ ደኖችን እና ዘርዘር ያሉ ደኖችን መመንጠር፣ የማገዶ እንጨት ፣ የከሰል ምርት እና የግንባታ ቁሳቁሶች ናቸው። ሰው ሰሥራሽ ደን የሀገሪቱን የእንጨት ፍላጎት ከማሟላት በጣም የራቀ በመሆኑ የደን መጨፍጨፍ የማይቀር መሆኑን ያመለክታል። የደን መጨፍጨፍ ዋነኛ መንስኤዎች እንደ ድህነት፣ የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ደካማ የኢኮኖሚ እድገት እና የአካባቢ ሁኔታ የመሳሰሉ እርስ በእርስ የሚደጋገፉ ምክንያቶች ከሚፈጥሩት አስከፊ አዙሪት ጋር የተቆራኙ ናቸው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ችግኝ በመትከል ሁኔታውን ለማስተካከል የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፏል። እ.ኤ.አ ከ2008 ጀምሮ በመላ ሀገሪቱ የችግኝ ተከላ ዘመቻው በየዓመቱ ሲካሄድ የቆየ ሲሆን የደን ሽፋን እየጨመረ መምጣቱን የመንግስት መረጃ ያመለክታል። እ.ኤ.አ ከ2010 እስከ 2015 ባለው ጊዜ ውስጥ የደን ሽፋን መጨመሩ ተመዝግቧል፡፡ ይህም በዓመት 40000 ሄክታር እንደሚጨምር ይገመታል (FAO, 2015)። ኢትዮጵያ የደን ሀብት ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ በቁጥር 80 የሚጠጉ እና በአጠቃላይ 26 879.15 ስኳር ኪ.ሜ ስፋት ያላቸውን ጥብቅ የደን ቦታዎችን አቋቁማለች።

በኢትዮጵያ የደን ምርት ለአካባቢው ኑሮና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም፣ ነገር ግን በአብዛኛው አልተመዘገበም፣ በዚህም ምክንያት እውቅና አላገኘም። በኢትዮጵያ ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ሥነ ምህዳራዊ ጠቀሜታ ካላቸው በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች መካከል አንዱ የደን ሀብቷ ነዉ። የደን ሀብት አስፈላጊነትና በብዝሃ ህይወት፣ በስነ-ምህዳር አገልግሎቶች እና በሰዎች ደህንነት መካከል ያለውን ትስስር በተመለከተ ግንዛቤ እያደገ መጥቷል (EFS፣ 2014)።

ደኖች የእንጨት እና እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶች (NTFPs) ምንጭ ናቸው። የኢትዮጵያ ደኖች የገጠርን አኗኗር የሚያስቀጥሉ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶችን (NTFPsን) ጨምሮ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ምንጮች ቢሆኑም፣ ተገቢውን ትኩረት አልተሰጣቸውም። በኢትዮጵያ ለገጠር ቤተሰቦች ከፍተኛ ገቢ እና የውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚያስገኙት በጣም አስፈላጊዎቹ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFPs) ቡና፣ ማር ፣ የተፈጥሮ እጣን እና ሙጫዎች ናቸው። በኢትዮጵያ ከ1997 ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ የአካባቢ ፖሊሲና ብሔራዊ የጥበቃ ስትራቴጂ አላት (EPA,1997) ። እንዲሁም የክልል መንግስታት የትግራይ፣ የአፋር፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የሶማሌ፣ የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ የጋምቤላ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስታትን ጨምሮ የራሳቸውን "የክልል ጥበቃ ስትራቴጂዎች" አዘጋጅተዋል።

በኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ከ2005 እስከ 2010 ባለው ጊዜ ውስጥ አጠቃላይ የእንጨት ምርት ከ100 718 ወደ 107 943 ሺህ ሜትር ኪዩብ

($m^3$) አድጓል። ከጠቅላላው የእንጨት ምርት 97 በመቶ ገደማ የሚሆነው እንጨት ለማገዶና ለከሰል ምርት ሲሆን ቀሪው 3 በመቶ ብቻ ለግንባታና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ናቸው። በኢትዮጵያ የደን ምርት በተለያዩ ንዑስ ዘርፎች የተከፋፈሉ ሲሆን እያንዳንዳቸው ለጠቅላላው ብሔራዊ ምርት (GDP) ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። እነዚህ ንዑስ ዘርፎች ሙጫ፣ እጣን፣ ማር፣ የዛፍ ዘርና ችግኝ፣ የጫካ ቡና፣ ቅመማ ቅመም፣ ቀርከሃ፣ የእንጨትና የመድኃኒት ተክሎች ናቸው፡፡ (African Business Association - ABDAS). ። እንጨት ለግንባታ፣ ለቤት እቃዎች እና ለከሰል ምርቶች ዋና የጥሬ ዕቃ ምንጭ ነው።

የኢትዮጵያ ደኖችና ዘርዘር ያሉ ደኖች ለበርካታ የቤት እና/ወይም አስፈላጊ የተላመዱና የጫካ እፅዋት ፣ የዱር ተዛማጆች (wild relatives) ማከማቻዎችና የጂን (የዘር) ክምችት ምንጭ ናቸው። ለምሳሌ ቡና (*Coffee arabica*) በሀገሪቱ ደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ በሚገኙ እርጥብ አረንጓዴ ተራራማ ደኖች ውስጥ ይገኛል።

የደን መጨፍጨፍ ፣ መጠለያ አካባቢዎች መጥፋት እንዲሁም የተፈጥሮ ደን ዳግም ብቅለት መቀነስ፣ በዱር እሳት እና በእርሻ / በሰፈራ መቋቋም ምክንያት የእጽዋት መጨፍጨፍ የተነሳ የደን ሀብቶች በከፍተኛ ሁኔታ አደጋ ላይ ናቸው። የእርሻ ደን ልማት (የጥምር ደን ግብርና) እና ከመሬት እና ከዛፍ ባለቤትነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች እና ህጎች አለመኖራቸውም ለፍራፍሬዎች እና የለውዝ ዝርያዎች ዘር መጥፋት/genetic erosion/ አስተዋፅዖ አድርገዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ በጠቅላላው 277 አጥቢ የእንስሳት ዝርያዎች  የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 29ኙ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ዝርያዎችና ከፍተኛ ጥበቃ የሚሹ ለምሳሌ እንደ ዋሊያ አይቤክስ *Walia Ibex (Capra walie)*፣ ጭላዳ ባቡን *Gelada Baboon (Theropithecus gelada)*, ተራራ ኒያላ *Mountain Nyala (Tragelaphus buxtoni)* ፣ የኢትዮጵያ ተኩላ *Ethiopian Wolf (Canis simensis)* ፣ ስታርክስ ሃሬ *Starck's Hare (Lepus starcki)* ያጠቃልላል። ከእነዚህ አደጋ ላይ የሚገኙ ዝርያዎች መካከል አንዳንዶቹ በጣም የተገደቡ ቦታዎች ብቻ የሚኖሩ ናቸው፤ ከእነዚህም መካከል ዋሊያ አይቤክስ የተባለው በዓለም ላይ በጣም አደጋ ላይ የወደቀ አጥቢ ዝርያ ነው።

ኢትዮጵያ የበለፀገ የአእዋፍ ዝርያዎች ያሏት ሲሆን በጠቅላላው 861 ዝርያዎች (ከአፍሪካ አጠቃላይ 40%)ቱን ትይዛለች፣ከዚህ ውስጥ 29ኞቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ (endemic) ናቸው፡፡በተጨማሪም 16ቱ በኢትዮጵያ ጂኦግራፊያዊ ድንበር ላይ ብቻ የተገደቡ ሲሆኑ 13ቱ ደግሞ ከኤርትራ ጋር የተጋሩ ናቸው፣

። እንዲሁም ለመጥፋት የተጋለጡ 14 የወፍ ዝርያዎች(በመቶ ዓመታት ውስጥ 10%ቱ የመጥፋት አደጋ ሊያጋጥማቸው ይችላል) የሃርትውድ ፍራንኮሊን/Hartwood's Francolin/ ፣ ፕሪንስ ሩፖሊስ ቱራኮ /Prince Ruspoli's Turaco/፣ ታላቁ ነጠብጣብ ንስር/Greater Spotted Eagle/ ፣ አነስተኛ ካስትል/Lesser Kestrel/ ፣ ቢጫ አንገት ያለው ሴሪን/Yellow-throated Serin/ ፣ የቅርብ ሌሊት ጃር/Nechisar Nightjar/ ፣ ዋትልድ ክሬን /Wattled Crane/፣ ዲጎዲ ላርክ /Degodi Lark/ ፣ ነጭ ጅራት ስዋውላ /White-tailed Swallow/ ፣ ሲዳማ ረዥም ክላቭ ላርክ /Sidamo Long-clawed Lark/ ፣ ላፔት-ፊት ቫልቸር /Lappet-faced Vulture/ ፣ አቢሲኒያን ቡሽ /Abyssinian Bush Crow/፣ ኮርኒክሬክ እና ኢምፔሪያል ንስር /Corncrake and Imperial Eagle/፡ ፡ 16 ዝርያዎች ደግሞ ለከፋ አደጋ የተቃረቡ ናቸው።

የኢትዮጵያ የንጹህ ውሃ አካላት ከ180 በላይ የዓሣ ዝርያዎች እንዳሏቸው ይታወቃል። ከእነዚህ ውስጥ ከ37-57 የሚሆኑት በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ (endemic) እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ (Golubstov and Mina, 2003) በተጨማሪአባሪ ሰንጠረዥ 8 ተመልከት ።

የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ ከ25 በላይ የዓሣ ዝርያዎች ያሉት ሲሆን ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ የዓሣ ምርት 50 በመቶውን ይይዛል። እንዲሁም በጣም አስፈላጊና ለንግድ ጠቃሚ የሆኑት የዓሣ ዓይነቶች ቆሮሶ /ቲላፒያ/፣ ናይል ፐርች እና ካትፊሽ /አምባዛ/ እንደሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል።

ነፍሳትን ጨምሮ የኢትዮጵያ አርትሮፖድ እንስሳት እምብዛም አይታወቁም። ብዙ ነፍሳት ለሰው ልጆች በጣም ጠቃሚ ናቸው። የእጽዋት የአበባ ዘርን በማዳቀል ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ፥ በመሆናቸው እና በአብዛኛዎቹ ማህበረሰቦች ውስጥ በምግብ ሰንሰለት ውስጥ መካከለኛ ቦታዎችን ስለሚይዙ ለሰው ልጅ ትልቅ ጥቅም አላቸው። አንዳንዶቹ ለሰዎችና ለቤት እንስሳት በሽታ የሚያስተላልፉ በመሆናቸው ጎጂ ናቸው። ነፍሳት በንጹህ ውሃ ውስጥ በጉልህ ይራባሉ፤ እናም በምድር ላይ ሊታሰቡ የሚችሉትን ሁሉንም መኖሪያ ቦታዎችን ይይዛሉ። ነገር ግን፣ የነፍሳት ስርአተ-ምህዳሮች በሰፊው በሶስት ዋና ዋና ስርአተ-ምህዳሮች ሊከፈሉ ይችላሉ፣ እነሱም የውሃ ውስጥ ስርአተ-ምህዳር፣ እርሻ እና የደን ስርአተ-ምህዳር ናቸው። አብዛኛዎቹ ሁሉም ማለት ይቻላል የነፍሳት ዝርያዎች ከደን ስርዓተ-ምህዳር ጋር የተቆራኙ ናቸው።

ከ277 አጥቢ እንስሳት መካከል 29ኙ፣ ከ862 አእዋፍ 16ቱ፣ ከ201 በደረት ከሚሳቡ እንስሳት መካከል 10ሩ፣ እና ከ63ቱ አምፊቢያን እንስሳት መካከል 34ቱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ናቸው። ከአእዋፍ ዝርያዎች ውስጥ 31ዱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስጋት አለባቸው፣ ከእነዚህ መካከል 5ቱ በአደገኛ ሁኔታ ላይ ያሉ፣ 12ቱ ለአደጋ የተጋለጡ እና 14ቱ የተጋለጡ ዝርያዎች ተብለው ተመድበዋል። በአለም አቀፍ ደረጃ

ለአደጋ ተጋልጠዋል ተብለው የሚታሰቡ የተለያዩ ፍልሰተኛ/ስደተኛ አእዋፍ በኢትዮጵያ በየዓመቱ ወደ ሃምሳ የሚጠጉ ቦታዎችን ይጎበኛሉ ወይም ያርፋሉ።

የተጠበቁ አካባቢዎች ዋነኛ ስጋት የሚመነጨው በፓርኮች ውስጥ ወይም በአቅራቢያቸው ካለው ሰፈራ፣ ከእርሻ ልማት፣ ከግጦሽ፣ ከደን መጨፍጨፍና ከማዕድን ማውጣት ጋር ተያያዥነት አለው። የኢትዮጵያ መንግስት እ.ኤ.አ እስከ 2030 ድረስ 22 ሚሊዮን ሄክታር የተጎዱ መሬቶችን እና ደኖችን የመመለስ ራዕይ አለው። ይህን በማድረጉ አገሪቱ የዛፍ ሽፋንን ማሳደግ እና የተጎዱ ደኖችን መልሶ ማቋቋም ብቻ ሳይሆን የደን ልማት ዘርፍ ለግብርና ምርት ስርዓቶች ፣ ለውሃ እና ለኃይል የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ በከፍተኛ ሁኔታ ለማሳደግ ፣ የምግብ እና የሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ለማሻሻል እና ለሥራ እና ለቤተሰብ ገቢ ተጨማሪ ዕድሎችን ለመፍጠር ነው።

ቀርከሃ በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች አንዱ ሲሆን ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች እምቅ ምንጭ በመሆን ለባዮ ኢኮኖሚ አስተዋፅዖ ያደርጋል። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ትልቁን የቀርከሃ ሀብት ያላት ሲሆን ከሁለት ዋና ዋና የአገር በቀል ዝርያዎች ይመደባሉ፣ እነሱም የደጋ ቀርከሃ (*Yushania alpina*) እና የቆላ ቀርከሃ (*Oxytenanthera abyssinica*) የተባሉት በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች እና በትግራይ ክልላዊ ግዛቶች በብዛት ይገኛሉ። በተጨማሪም የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት (EEFRI) ፣ ዓለም አቀፉ የቀርከሃ እና ራታን ድርጅት (INBAR) እና ሌሎች የልማት ኤጀንሲዎች ከ40 በላይ የቀርከሃ ዝርያዎችን በማስገባት እድገታቸው፣ ምርታቸውና በመስክ ላይ ተስማሚነታቸው እየተረጋገጠ ነው። በኢትዮጵያ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ላይ የቀርከሃ ዓመታዊ ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ 56,250,000 የኢትዮጵያ ብር (ETB) የሚገመት ሲሆን ወደ 750,000 የሚጠጉ ሰዎች በቀርከሃ ላይ የሚተዳደሩ ናቸው (EEFCCC, 2017)።

እ.ኤ.አ በ2018 መጀመሪያ ላይ ብሔራዊ የደን ሕግ ተሻሽሏል፤ እናም አሁን የማህበረሰብ መብቶችን በግልፅ እውቅና የሰጠና እንዲሁም ሰነ-ምህዳራዊ አገልግሎቶችን ወይም የብዝሃ ሕይወትን ሳያበላሹ የተፈጥሮ ደኖችን በማስተዳደር እና ሰዉ ሰራሽ ደኖችን በማቋቋም ረገድ ትልቅ ሚና እንዲላቸው ያስገነዘበ ነዉ። አዲሱ የደን ህግ የሚከተሉትን ሶስት ቁልፍ ለውጦች ይዟል:- የአሳታፊ የደን አስተዳደርን በማስተዋወቅ የተፈጥሮ ደኖችን በተስማሙ የአስተዳደር ዕቅዶች መሠረት የማስተዳደር ኃላፊነቶች እና ጥቅሞችን በማካፈል የማህበረሰቦችን ሚና ለማጎልበት፣ ለግል ደን አልሚዎች እንደ ከኪራይ ሊዝ ነፃ መሬት ፣ የመሬት አጠቃቀም እና የደን ባለቤትነት የምስክር ወረቀቶች የተሻለ ተደራሽነት እና እስከ መጀመሪያው ምርት (ለግል ባለሀብቶች እና ማህበራት) እና እስከ ሁለተኛው ምርት (ለማህበረሰቦች) ድረስ የግብር ዕፎይታ ጊዜ ማቅረብ፤ እና ድንበሮች: እርሻን ወደ ደኖች በማስፋት ፣ የደን ድንበሮችን በማዛባት ፣ ሰደድ እሳትን በማስነሳት ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን በመጉዳት ፣ በመንግስት ፣ በማህበረሰብ ፣ በማህበር ወይም በግል ደኖች ውስጥ እንስሳትን በማደን ወይም በሚያሰማሩት ላይ ከባድ ቅጣቶችን ያካተተ ነው። ይህ ማለት የኢትዮጵያ መንግስት እና ሌሎች አጋሮች የተፈለገውን የFSC INS ግብ ለማሳካት በተሻለ ሁኔታ ውስጥ ይሆናሉ ማለት ነው።

## ሐ-2 ደረጃ ለማውጣት መነሻ መረጃዎች

(መረጃ ክፍል/ Informative section)

በደን አስተዳደር ምክር ቤት (FSC) የአፈጻጸም እና ደረጃዎች ክፍል (PSU) Soil Association Certification (SA Cert) ለኢትዮጵያ ጊዜያዊ የደን አስተዳደር ደረጃን (IFSS) ለማዘጋጀት አጠቃላይ የደን አስተዳደር ደረጃን (GFSS) በመጠቀም ከዓለም አቀፍ የቀርከሃ እና ራታን ድርጅት (INBAR) እና Forest of the World (FoW) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በአካባቢው ከሚሰራ አጋራቸው በኢትዮ ዌትላንድስ (Ethio Wetlands) በኩል እ.ኤ.አ በሚያዚያ 2022 ተመዝግቧል። እንደ አለመታደል ሆኖ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት እ.ኤ.አ በመስከረም 2022 ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረው በመጀመሪያው የጊዜ ሰሌዳ ሊከናወን አልቻለም።

በደረጃው ላይ ሁለት ዙር የባለድርሻ አካላት ምክክር ተካሂዷል፤ የመጀመሪያው ምክክር በበይነ መረብ ላይ የተካሄደው በሁለቱም የSoil Association እና በደን አስተዳደር ምክር ቤት (FSC) ድህረ-ገጾች ምክክር መድረክ ላይ ሲሆን እ.ኤ.አ ከየካቲት 23 እስከ መጋቢት 30 ቀን 2023 ነበር ። ሁለተኛው ምክክር እ.ኤ.አ ከግንቦት 23 እስከ ግንቦት 30 ቀን 2023 ተካሂዷል። በሁለተኛው ዙር ምክክር ወቅት ከባለድርሻ አካላት ጋር ሶስት ስብሰባዎችን በአካል በመገናኘት ተካሂደዋል። እ.ኤ.አ ከግንቦት 23-24 ቀን 2023 የተካሄደው የመጀመሪያ ስብሰባ *በጌሜቺሳ እና በሑዋቀበሌ* ያሉ የደን ማህበረሰቦችን አካቷል ።

ቀበሌ በኢትዮጵያ ትንሹ አስተዳደራዊ አሃድ የሆነው ሲሆን በሸካ ዞን የሚኖሩ የኦሮሞ እና የሸካ ማህበረሰቦች ተወካዮችን ያካተተ ነው ። በመቀጠልም እ.ኤ.አ ከግንቦት 27 እስከ 28 ቀን 2023 በጂማ ከተማ የሀኒ ላንድ ሆቴል (Honey Land Hotel) የሁለት ቀን ስብሰባ ተካሂዶ ከአራት የኢትዮጵያ ክልሎች ጋምቤላ ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ እና ሲዳማ የተውጣጡ ተሳታፊዎችን አሰባስቧል።

በስብሰባው ላይ የተገኙት የማኅበረሰቡ ተወካዮች፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትና በእነዚህ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ነበሩ።

ሶስተኛው እና የመጨረሻው የባለድርሻ አካላት ስብሰባ በአዲስ አበባ ከተማ በስዊስ ኢን ኔክሰስ ሆቴል እ.ኤ.አ ግንቦት 30 ቀን 2023 እንደ ብሔራዊ ምክክር ተጠርቷል። ከ12ቱ የኢትዮጵያ ክልሎች የተውጣጡ 45 ተሳታፊዎች የተገኙ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ከኦሮሞ፣ ከአፋር፣ ከማጃንጊር፣ ከሼካ እና ከዳሰነች የተወጣጡ አሥር ማህበረሰብ አባላት ናቸው። በስብሰባው ወቅት የተወያዩባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች የከፍተኛ የጥበቃ እሴት(HCV) ማዕቀፍ ፣ ነባር ህዝቦች (Indigenous People) እና እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (ማር ፣ ኮሮሪማ፣ የኢትዮጵያ ቁንዶ በርበሬ ፣ የጫካ ቡና) ዙሪያ ያተኮሩ ናቸው ።

በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ ማጠቃለያ ላይ ተሳታፊዎች በርካታ ማረጋገጫዎችን አቅርበዋል ፣ በመቀጠል ሁሉም በIFSS ረቂቅ ውስጥ ተካተዋል። በተጨማሪም ባለድርሻ አካላት የኢትዮጵያ ቁንዶ በርበሬ (*Piper capense)* በIFSS ውስጥ ካሉ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFPs) ዝርዝር ውስጥ እንዳይካተትበጋራ ወስነዋል፤ እንዳይካተት የተደረገበት ምክንያት አሁን ያለው የኢኮኖሚ አዋጭነት ማጣት ነው። ከሰዓት በኋላ በተካሄደው ክፍለ ጊዜ፣ መርሕ 3 (P3) በኢትዮጵያ ሁኔታ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን ለመገምገም ውይይት የSA Cert አስተባባሪ መርቷል። ምንም እንኳን ስምምነቱ ለኢትዮጵያ ተገቢነት እንደሌለው ቢገልጽም ፣ መርሁ ግን ለወደፊቱ ሊከሰቱ ለሚችሉ ለዉጦች ለማስተናገድ እንዲቻል እንዲቆይ ተደርጓል።

ጊዜያዊ የደን አስተዳደር ስታንዳርድ (IFSS) ሁሉንም የደን ዓይነቶች ለመገምገም እንደ አጠቃላይ ማዕቀፍ የሚያገለግል ሲሆን ይህም ሰው ሰራሽ ፣ የተፈጥሮ እና የቀርከሃደኖችን ያጠቃልላል።

# መ. ማጣቀሻ

(መረጃ ክፍል/Informative section)

ይህን ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ እነዚህ የማጣቀሻ ማስረጃዎች የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ የስራት ቁጥር የሌላቸው ማጣቀሻዎች፣ የማጣቀሻ የሆነው ሰነድ የቅርብ ጊዜው እትም (ማስተካከያዎችን ጨምሮ) ይተገበራል፡፡

| | |
|---|---|
| **FSC-POL-20-003** | FSC Policy on the Excision of Areas from the Scope of Certification |
| **FSC-POL-30-001** | FSC Pesticides Policy |
| **FSC-STD-30-005** | FSC Standard for Group Entities in Forest Management Groups |
| **FSC-PRO-01-008** | Processing Complaints in the FSC Certification Scheme |
| **FSC-PRO-30-006** | Ecosystem Services Procedure: Impact Demonstration and Market Tools |
| **FSC-DIR-20-007** | FSC Directive on FSC Forest Management Evaluations |
| **FSC-GUI-30-003** | FSC Guidelines for the implementation of the right to Free, Prior and Informed Consent (FPIC) |

**ማስታወሻ፡** ይህን ደረጃ ተግባራዊ ሲደረግ፣ ከFSC የአካባቢው ተወካዮች ጋር በመጠየቅ ወሳኝ የሆኑ ትርጓሜዎችን ለማኘንት (የFSC ብሔራዊ ቢሮ ወይም ተወካዮች፣ ወይም የFSC አፈጻጸም እና የደረጃ ክፍል፣ ምንም ዓይነት ብሔራዊ FSC ተወካይ ካልተገኘ) ፣ ወይም በእናንተ አረጋጋጭ አካል፡፡ በFSC ሰነድ ማዕከል አማካኝነት አለም አቀፍ ትርጓሜዎች ይገኛሉ (https://fsc.org/en/document-centre) ፡፡

# ሠ. መርሆዎች, መስፈርቶች እና አመላካቾች

(መደበኛ ክፍል/ normative section)

## መርህ-1: ህግን ማክበር

**ድርጅቱ ከሁሉም ተፈጻምነት ካላቸው ህጎች፣ደንቦች፣ በሀገር ደረጃ የጸደቁ አለም አቀፍ ስምምነቶች፣ የድርድር ሃሳቦች እና ስምምነቶችን ያከብራል፡፡**

**1.1 ድርጅቱ ህጋዊ ሰውነት ያለውና፣ በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ ግልጽ የሰነድና የማያጠራጥር ህጋዊ ምዝገባ ያለው፣ ለተወሰኑ ተግባራት ከሚመለከተው ህጋዊ ከሆነ አካል በጽሁፍ ማረጋገጫ ያገኘ፤**

1.1.1 በምስክር ወረቀቱ ወሰን ውስጥ ሁሉንም ተግባራት ለማከናወን በሰነድ የተደገፈ እና የማያከራክር ህጋዊ ምዝገባ አለው፤

***ማረጋገጫዎች፡-*** የምዝገባ ምስክር ወረቀት፡ አሳታፊ የደን አስተዳደር ስምምነት (PFM Agreement)

1.1.2 ህጋዊ ምዝገባ በህጋዊ መንገድ በተደነገጉት ሂደቶች መሰረት ተወዳዳሪ በሆነ ህጋዊ ባለስልጣን ተሰጥቷል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ አስተዳደር ዕቅድ፣ ከፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የምስክር ወረቀት ወይም በክልል ደረጃ ከተቋቋመው የሕብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅን ለማስፈጸም ከሚመራና ከሚቆጣጠር አካል ፤ ከፍትህ ቢሮ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤

**1.2 ድርጅቱ ለአስተዳደር አሃድ የተለዩ ቦታዎች ህጋዊ ሁኔታ፣ የይዞታ ጊዜ እና የመጠቀም መብቶች እንዲሁም ድንበር በግልጽ የተቀመጡ መሆናቸውን ያሳያል።**

1.2.1 በህግ የተመዘገቡ ሀብቶችን በይዞታ ባለቤትነት የማስተዳደር እና የመጠቀም በምስክር ወረቀት አሰጣጥ ወሰን ውስጥ ተመዝግቧል።

እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFP) 1.2.1 የአስተዳዳር አሃድ ህጋዊ የሆነ የመሬት ስሪት የተፈጥሮ ሃብቱንና፤ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን (NTFP) ለመጠቀምና ለማስተዳደር ህጋዊ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፡፡

***<u>መምሪያ ማስታወሻ፡-</u>*** እዚህ ላይ የዛፍ ሀብት ባለቤትነት አከራካሪ አለመሆኑን ማረጋገጥ ማስታወሱ አስፈላጊ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች የመሬት ባለቤቶች በእርሻቸው ላይ ዛፎችን የተከሉ አይደሉም፣ በተለይም በቤተሰብ ሁኔታዎች ውስጥ ፣ ስለሆነም በቤተሰብ ውስጥ ያለ ሌላ ሰው ለማረጋገጫ በተሰጡት ዛፎች ላይ የይገባኛል ጥያቄ አለመኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ።

1.2.2 የመሬት ባለቤትነት ምስክር ወረቀት በህጋዊ መንገድ በተደነገጉት ሂደቶች መሰረት በህጋዊ ባለስልጣን ተሰጥቷል፡፡

1.2.3 በምስክር ወረቀት አሰጣጥ ወሰን ውስጥ ያሉ ሁሉም በአስተዳደር አሃድ የተለዩ ቦታዎች ወሰን በግልጽ ምልክት የተደረገባቸው ወይም የተመዘገቡ እና በካርታዎች ላይ በግልፅ የሚታዩ ናቸው።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የሊዝ ስምምነት፣ የመሬት ኪራይ ስምምነት፣ የመሬት ስጦታ ስምምነት፣ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ፣ ከቀበሌ (ከክልል መንግስት) ካርታና የመሬት አጠቃቀም ፕላን፣ ካርታዎች፣ የመሬት አሰተዳደር ክፍል፣ የአሳታፊ ደን አስተዳደር ስምምነት (PFM Agreement) ፣ የአስተዳደር ፕላን፤ የስራ ፈቃድ፤ የክፍያ ሰነዶች፣ ኮቦ ሲስተም፤

**1.3. የአስተዳደር አሃዱ ወይም ድረጅቱ በያዘው አስተዳደር ወሰን ውስጥ ስራ ለመስራት ህጋዊ ፍቃድ መያዝ ሲኖርበት፣ ይህ የስራ ፍቃድ ድርጅቱ ከተፈቀደለት የስራ አይነት ጋር የተመሳከረ መሆኑ፣ በተጨማሪም የተሰጠው የስራ ፈቃድ ከአካባቢበው የአስተዳዳር እና መንግስት ካወጣው ህግ ጋር የተመሳከረ እና የሚጣጣም መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ሕጋዊ ፈቃድ ማንኛውንም የደን ውጤት እና የደን ውጤት ያልሆኑ ምርት እና/ወይም ስነ ምህዳራዊ አገልግሎትን በአስተዳደር አሃዱ ይዞታ ውስጥ ምርት ለመሰብሰብ የሚፈቅድ መሆን አለበት፡፡ ድርጅቱ ከሙብትና ግዴታዎች ጋር በተያያዘ በህጋዊ መንገድ የተወሰኑ ክፍያዎችን ይፈጽማል፤**

1.3.1 በአስተዳደደር አሃድ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በሙሉ ማክበር የሚገባቸው፡-

1) ተቀባይነት ያለው ህግና ደንብ እና የአስተዳደር መስፈርቶች፣

2) ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶችን እና

3) አስገዳጅ የአሰራር ደንቦች፤

እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFP) 1.3.1. እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን (NTFP) ለሰው ልጅ ጥቅም ላይ ለማዋል ከታሰበ፣ ሁሉም የሚመለከታቸው ህጋዊ እና አስተዳደራዊ የንፅህና እና የምግብ ደህንነት መስፈርቶች ያሚላ መሆን አለበት፤

1.3.2. ማንኛውም ከደን አስተዳደር ጋር የሚጠበቅ ህጋዊ ክፍያ ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ለሚመለከተው አካል መከፈል አለበት፤

1.3.3. አስተዳደር እቅድ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ሁሉንም ተቀባይነት ያላቸው ህጎች ለማክበር የተዘጋጁ መሆን አለባቸው።

**ማረጋገጫዎች:** የኢትዮጵያ ፌድራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር፡ 456/2005 (እ.ኤ.አ)፤ የፌደራል የደን ልማት፡ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር፡ 1065/2018 (እ.ኤ.አ)፤ የማህበረሰብ ጤና አዋጅ ቁጥር፡ 200/2000 (እ.ኤ.አ)፣ ማህበራዊ ስምምነቶች አሳታፊ የደን አስተዳደደር ስምምነት ሰነድ፡፡

**1.4 ድርጅቱ ካልተፈቀደ ወይም ህገወጥ የሀብት አጠቃቀም፣ አሰፋፈር እና ሌሎች ህገ-ወጥ ድርጊቶችን ስልታዊ በሆነ መንገድ የአስተዳደር አሃዱን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን ያዘጋጃል፣ ይተገብራል እና/ወይም ከተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች ጋር ያስፈጽማል።**

1.4.1. ካልተፈቀደላቸው ወይም በህገወጥ መንገድ ምርት መሰብሰብ፣ የአደን፣ አሳ ማስገር፣ ማጥመድ፣ መሰብሰብ እና ህገወጥ ሰፈራን ለመከላከልና ለመጠበቅ እርምጃዎች ተወስዷል፡፡

1.4.2 ጥበቃ የተቆጣጣሪ አካላት ሕጋዊ ኃላፊነት ሲሆን ከነዚህ ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በመሆን ለመለየት፣ ሪፖርት ለማድረግ፣ ያልተፈቀዱ ወይም ህገወጥ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር እና እንዳይቀጥል የሚያስችል አሰራር ተዘርግቷል።

1.4.3. ህገወጥ ወይም ያልተፈቀደላቸው ተግባራት ሲገኙ ለመቋቋም እርምጃዎች ተወስዷል፡፡

**ማረጋገጫዎች:-** የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1065/2018 (እ.ኤ.አ)፣ አዋጅ ቁጥር 456/2005 (እ.ኤ.አ)፣ የኢትዮጵያ ፌድራላዊ ዲሞክራቲክ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም፣ ደንብ ቁጥር 151/2012 (እ.ኤ.አ)፣ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ደንብ፤

**1.5. ድርጅቱ የደን ዉጤቶችን በአስተዳደር አሃድ ውስጥ እና ከአስተዳደር አሃዱ እስከ መጀመሪያው ሽያጭ ጣቢያ ድረስ ለማጓጓዝና ለመነገድ የሚመለከታቸውን ብሄራዊ ህጎች፣ የአካባቢ ህጎች፤ የጸደቁ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና የግዴታ የአሰራር ደንቦች ማክበር አለበት።**

1.5.1 ተፈጻሚነት ካላቸዉ ብሔራዊ ህጎች፣ የአካባቢ ህጎች፣ የፀደቁ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና የግዴታ የአሰራር ደንቦች ጋር በተጣጣመ መልኩ የደን ምርቶች ማጓጓዝና ንግድ እስከ መጀመሪያው የሽያጭ ቦታ ድረስ ባከበረ መልኩ ተተግብሯል።

1.5.2 በማንኛውም ለአደጋ የተጋረጡ ዝርያች አለም አቀፍ ንግድ ኮንቬንሽን(CITES) ድንጋጌዎች ላይ ያሉ ዝርያዎች ውስጥ የመሰብሰብ እና የንግድ የምስክር ወረቀቶችን መያዝን ጨምሮ የCITES ድንጋጌዎችን አክብሯል፡፡

እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFP) 1.5.2 በሁሉም የእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFP) ዝርያዎችን መሰብሰብ እና ንግድ የምስክር ወረቀቶችን ጨምሮ የCITES ድንጋጌዎችን አክብሯል።

**ማረጋገጫዎች:** የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1065/2018 (እ.ኤ.አ)፣ አዋጅ ቁጥር 575/2008 (እ.ኤ.አ) የኢትዮጵያ የዱር እንሰሳት ልማትና ጥበቃ፣ ለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ለማቅረብ የወጣ አዋጅ ቁጥር 541/2007 (እ.ኤ.አ)፤ አዋጅ ቁጥር 1223/2020 (እ.ኤ.አ) የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት፣ አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ፤

**1.6. ድርጅቱ ወይም የአስተዳደር አሃድ ማንኛውምን ባለድርሻ አካል በደን ውስጥ ለሚነሳ የይዞታ እና ይገባኛል ክርክር በመለየትና በህጋዊ ወይም የተለመደ ሕግ መሰረት ከፍርድቤት ውጭ በሰዓቱ መፍታት ይኖርበታል፡፡**

1.6.1. ይፋ በሆነ መንገድ ግጭት መፍቻ ስርአት ለባለድረሻ አካለት አገልግሎት ተዘርግቷል፡፡

1.6.2. ንኛውም ባለድርሻ አካል በደን ውስጥ ለሚነሳ የይዞታ እና ይገባኛል ክርክር በመለየትና በህጋዊ ወይም በተለመደ ሕግ መሰረት ከፍርድ ቤት ውጭ በሰዓቱተፈቷል፡፡ ይህ የተፈታ ክርክርን ወይንም በመፈታት ሂደት ላይ ያለ ክርክርን ይመለከታል፡፡

1.6.3. ወቅታዊ የተሰነደ የይገባኛል ክርክር በህጋዊ ወይም ልማዳዊ ሕግ ተካሂድዋል፤ የሚያካትታቸውም፡-

1) ክርክሩን ለምፍታት የተሄደበት ሂደት የሚሳይ መረጃ
2) የክርክሩን ውጤት ሚያሳይ ሰነድ
3) ያልተፈቱ የክርክር ሃሳቦች ካሉ ለምን እነዳልተፈቱ የሚሳይ መረጃ እና እንዴት ወደፊት መፈታት እንደሚችሉ የሚሳይ

1.6.4. ክርክሩ በተፈጸመበት ቦታ የቆመ ስራ እንቅስቃሴ የሚያሳይ

1) በከፍተኛ ደረጃ ስራ ማቆም ወይም
2) ለረጅም ጊዜ ስራ ማቆም ወይም
3) በከፍተኛ ደረጅ የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት የሚንጸባርቅ ከሆነ

***ማረጋገጫዎች፡*** ክልል የግጭት መፍቻ ህግ ወይም አዋጅ ቁጥር፡240/2021(እ.ኤ.አ)፡ ደንብ ቁጥር 10/2021 (እ.ኤ.አ) የመሬት አጠቃቀም ካርታ እና የአካባቢ እይታ ሰነድ፤

**1.7. ድርጅቱ ወይም የአስተዳደር አሃድ ማንኛውም ሙስና እና ጉቦን የተመለከተ አሰራረርን ለመከላለከል ተነሳሽነት ማሳየት እና ሙስናን የመለላከል ህግና መመሪያ በመተግበር ስራ ላይ ማዋል፡፡ ሙስናን ለመለላከል ህግና መመሪያ  በሌለበት ድርጅቱ ወይም የአስተዳደር አሃድ ማንኛውም እርምጃ በአባቢው ህግ ወይም ባይሎው መሰረት ተግባራዊ ማድረግ፡፡**

1.7.1. ሙስናን ያለመስጠትና ጉቦ ያለመቀበል ፖሊሲ ድርጅቱ ወይም የአስተዳደር አሃድ ማንኛውም አሰራር ተግብሯል፡፡

SLIMF1.7.1. ድርጅቱ ወይም የአስተዳደር አሃድ ውስጥ የታወቀ በቃል ለሁሉም አባላት የተላላፈ መመሪያ ተተግብሯል፡፡

1.7.2. የሙስና መከላለከል ፖሊሲው ከተጻፈ ህግ በላይ በተግባር ላይ ውሏል፡፡

1.7.3. የሙስና መከላለከል ፖሊሲው ለሁሉም አካል በነጻ ማህበራዊ ሚዲያ ተደራሽ ሆኗል፡፡

1.7.4. ጉቦ እና ማንናውም የሙስና መገለጫዎች ድርጅቱ ወይም የአስተዳደር አሃድ ውስጥ አይፈጸምም፡፡

1.7.5 በድርጅቱ ወይም አስተዳደር አሃድ ውስጥ ሙስና ቢከሰት ፈጥኖ የማረም እና የማስተካካል ተተግብሯል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡*** የኢትዮጵያ ፌድራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ መንግስት ሙስና መከላከል ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር፡ 1236/2021 (እ.ኤ.አ).

**1.8. ድርጅቱ ወይም የአስተዳደር አሃድ ማንኛውም የFSC መርህ እና መመሪያ ለረጅም ጊዜ መተግበርና ጠብቆ ማቆየት ፡፡ በተጨማሪም ተያያዥ የFSC ፖሊሲዎች እና ደረጃዎችን መተግበር ፡፡ እነዲሁም እነዚህን መርህ እና መመሪያ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በግልጽ የሚየሳይ እና ተደራሽ የሚደርግ አሰራር ተዘርግቷል፤**

1.8.1 ድርጅቱ ወይም የአስተዳደር አሃድ ማንኛውም የFSC መርህ እና መመሪያ ከዘላቂ ደን አያያዝ እና አጠቃቀም ጋር አዛምዶ በጽሁፍ እና በሰነድ አዘጋጅቶ መኖር አለበት፡፡

1.8.2 የፖሊሲ ሰነዱ በነጻ ለሁሉም ተደራሽ ሆንዋል፡፡

## መርህ 2: የሰራተኞች መብት እና የቅጥር ሁኔታ

**ድርጅቱ የሰራተኞችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን ይጠብቃል ወይም ያጎለብታል።**

**2.1. ድርጅቱ በዓለም አቀፍ የሠራተኛ ድርጅት በ (ILO) መሠረታዊ መርሆዎች እና በሥራ ላይ ያሉ መብቶች (1998 እ.ኤ.አ) እንደተገለጸውና በስምንቱ ILO ዋና የስራ ስምምነቶች ላይ በመመስረት በ ዓለም አቀፍ የሠራተኛ ድርጅት (ILO) ውስጥ የተገለጹት እና በሥራ ላይ ያሉትን መርሆዎች እና መብቶችን ያከብራል፡፡**

2.1.1. ድርጅቱ የሕፃናት ጉልበት አይጠቀምም።

2.1.1.1 ድርጅቱ ከ2.1.1.2 ከተጠቀሰው ሁኔታ በስተቀር ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሠራተኞችን ወይም በብሄራዊ ወይም በአካባቢ ህጎች ወይም ደንቦች ውስጥ ከተጠቀሰው ዝቅተኛ ዕድሜ በታች የሆኑ ሠራተኞችን መቅጠር የለበትም።

2.1.1.2 አንዳንድ ሀገራት በብሔራዊ ህግ ወይም ደንብ ውስጥ ከ13 እስከ 15 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሰዎች በቀላል ሥራ እንዲሰማሩ ቢፈቅድም በትምህርታቸው ላይ ተጽዕኖ ሳይፈጥር እና በጤናቸው ወይም በእድገታቸው ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆን አለበት፡፡ በተለይም ልጆች አስገዳጅ የትምህርት ህጎች ተገዢ ሲሆኑ ከትምህርት ሰዓት ውጭ መደበኛ የቀን የሥራ ሰዓት ውስጥ ብቻ እንዲሰሩ ይፈቀድላቸዋል ፡፡

2.1.1.3 በጸደቁ ብሄራዊ ህጎች እና ደንቦች መሰረት እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ለስልጠና ዓላማ ካልሆነ በስተቀር በአደገኛ ወይም በከባድ ስራ ውስጥ አይቀጥርም ፡፡

2.1.1.4 ድርጅቱ አሰከፊ የህጻናት ጉልበት ሥራ ይከለክላል።

2.1.2 ድርጅቱ ሁሉንም ዓይነት አስገዳጅ እና የግዴታ ስራዎችን አስወግዷል፡፡

2.1.2.1 የቅጥር ግንኙነቶች ያለምንም የቅጣት ማስፈራሪያ በፈቃደኝነት እና በጋራ ስምምነት ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

2.1.2.2 ማንኛውንም አስገዳጅ ወይም የግዴታ ሥራን የሚያመለክት ማስረጃ የለም፤ የሚከተሉትን ጨምሮ፣ ነገር ግን ከታች በተጠቀሱት ብቻ ሳይወሰን ፡-

1) አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት
2) ለሌላ ውለታ ማካካሻ የጉልበት ሥራ
3) የሰራተኛ ደመወዝ መከልከል/የስራ ቅጥር ክፍያ እና/ወይም ስራ ለመጀመር የሚያስችል ማስያዢያ ክፍያን ጨምሮ
4) የመንቀሳቀስ ገደብ
5) ፓስፖርት እና የመታወቂያ ሰነዶችን ይዞ ማቆየት
6) የባለሥልጣናት ዛቻ እና ማስፈራሪያ

2.1.3 ድርጅቱ በቅጥር እና በሥራ ላይ ምንም ዓይነት አድልዎ አለመኖሩን ያረጋግጣል።

2.1.3.1 የቅጥርና የሙያ ተግባራት አድሎአዊ አይደሉም (የብሄር መድልዎን ጨምሮ ) በኢትዮጵያ የሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 (እ.ኤ.አ) እንደተገለጸው።

2.1.4 ድርጅቱ የመደራጀት ነጻነት እና በጋራ የመደራደር መብትን ያከብራል።

2.1.4.1 ሠራተኞች በራሳቸው የመረጡትን የሠራተኞች ድርጅቶችን ማቋቋም ወይም መቀላቀል ይችላሉ።

2.1.4.2 ድርጅቱ የሰራተኞችን ማህበር ከመመስረት፣ ከመቀላቀል ወይምከማገዝ ጋር በተያያዙ ህጋዊ ተግባራት ውስጥ መሳተፍ ወይም ይህንኑ ከማድረግ የመቆጠብ መብታቸውን ያከብራል። እነዚህን መብቶች በመጠቀማቸው ሠራተኞችን አያገልም ወይም አይቀጣቸውም፤

2.1.4.3 ድርጅቱ በህጋዊ መንገድ ከተመሰረቱ የሰራተኞች ማህበር እና/ወይም በአግባቡ ከተመረጡ ተወካዮች ጋር በመልካም እምነት እና ከፍተኛ ጥረት በማድረግ የጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ ይደራደራል፡፡

2.1.4.4 የጋራ ድርድር ስምምነቶች ባሉበት ይተገበራሉ።

**2.2 ድርጅቱ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በቅጥር ሁኔታዎች፣ በስልጠና እድሎች፣ ውሎችን በመስጠት፣ በተሳትፎ ሂደቶች እና በአስተዳደር ተግባራት ያበረታታል።**

2.2.1 የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን የሚያበረታቱ እና በቅጥር ተግባራት፤ በስልጠና እድሎች፤ ውሎችን መስጠት፤ የተሳትፎ ሂደቶች እና የአስተዳደር ተግባራት ላይ የሥርዓተ-ፆታ መድልዎን የሚከላከሉ ስርዓቶች ተተግብረዋል።

2.2.2 የስራ እድል ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች በተመሳሳይ ሁኔታ ክፍት ሲሆን ሴቶች በሁሉም የስራ ደረጃዎች በንቃት እንዲሳተፉ ይበረታታሉ።

2.2.3 በተለይም በሴቶች የሚከናወን ሥራ (ችግኝ ጣቢያዎች፣ ሲሊቪካልቸር፣ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች ምርቶች መሰብሰብ፣ መመዘን፣ ማሸግ፣ ወዘተ.) በተመሳሳይ በወንዶች ከሚከናወን ስራ ጋር በስልጠና፤ በጤና እና ደህንነት መርሃ ግብሮች እኩል ተካተዋል።

2.2.4 ሴቶች እና ወንዶች አንድ አይነት ስራ ሲሰሩ ተመሳሳይ ምንዳ ይከፈላቸዋል፡፡

2.2.5 በኢትዮጵያ የሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011(እ.ኤ.አ) በምእራፍ 2 አንቀጽ 57 ላይ እንደተገለጸው ሴቶች ምንዳቸውን ዋስትና ባለው ሁኔታ እንዲቀበሉ እና እንዲያቆዩ ለማድረግ በጋራ ስምምነት በተደረገባቸው ዘዴዎች (ለምሳሌ ቀጥታ የባንክ ዝውውር፣የትምህርት ቤት ክፍያ ወዘተ) በመጠቀም እና በቀጥታ ይከፈላቸዋል።

2.2.6 በኢትዮጵያ የሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2019(እ.ኤ.አ) ምዕራፍ 1 አንቀጽ 88 ላይ እንደተገለጸው የወሊድ ፈቃድ ከወሊድ በፊት ከ30 ተከታታይ ቀናት ያላነሰ እና ከወሊድ በኋላ ለ90 ተከታታይ ቀናት ከክፍያ ጋር የሚቆይ ቀናትን ያጠቃልላል።

2.2.7 በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር1156/2019 (እ.ኤ.አ) ምዕራፍ 2 ክፍል 81 ላይ እንደተገለጸው የአባትነት ፈቃድ ከክፍያ ጋር ለ3 ቀናት የሚቆይ እና ተጨማሪ 5 ተከታታይ ቀናት ያለክፍያ ልዩ እና ከባድ የሆኑ ክስተቶች ሲከሰት ይኖራል።

2.2.8 በኢትዮጵያ የሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 (እ.ኤ.አ) እንደተገለጸው የስብሰባዎች፣ የአመራር ኮሚቴዎች እና የውሳኔ ሰጭ መድረኮች ሴቶችና ወንዶችን ለማካተት እና የሁለቱም ንቁ ተሳትፎ እንዲኖር ተመቻችቷል ።

2.2.9 በኢትዮጵያ ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 (እ.ኤ.አ) በተደነገገው መሠረት በሥርዓተ-ጾታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በወላጅነት ወይም በፆታዊ ዝንባሌ ላይ የተመሰረቱ ጾታዊ ትንኮሳ እና አድሎአዊ ጉዳዮችን ሪፖርት ለማድረግ እና ለማስወገድ ሚስጥራዊ እና ውጤታማ አሰራሮች አሉ።

***ማረጋገጫዎች፦*** የክፍያ ደረሰኞች፤ የደመወዝ ክፍያ ዝርዝር ፤ የወሊድ ፈቃድ ድንጋጌዎች በቅጥር ውል እና በድርጅቱ የሰው ኃይል ፖሊሲ፤ ከሠራተኞች ጋር የተደረጉ ቃለመጠይቆች፤ የአባትነት ፈቃድ ድንጋጌዎች፤ በሥራ ስምሪት ውል እና በድርጅቱ የሰው ኃይል ፖሊሲ፤ የስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎች፤ በቦታው ላይ የሪፖርት ማቅረቢያ ሥርዓቶች እና የአደጋ ጊዜ ዘገባዎች።

**2.3 ድርጅቱ ሰራተኞችን ከሥራ ደህንነትና ጤና አደጋዎች ለመጠበቅ የጤናና ደህንነት አሰራሮችን ተግባራዊ ያደርጋል ። እነዚህ አሰራሮች ከአስተዳደር ተግባራት መጠን ፣ ጥንካሬ እና ስጋት ጋር ተመጣጣኝ መሆንና የILO የደን ደህንነት እና የጤና የተግባር ደንብ ምክሮችን ማሟላት ወይም ማለፍ አለባቸው፡፡**

2.3.1 በደን ስራ የጤና እና የደህንነት ተግባራት በILO የደህንነት እና የጤና የተግባር ደንብ እና መመሪያ በሚያሟላ ወይም በተሻለ መልኩ ይዘጋጃሉ/ ይተገበራሉ፡፡

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 2.3.1.1 ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (ከNTFPs) አስተዳደር እና ከምርትመሰበሰብ ጋር ተያይዘው የሚመጡ የጤና እና የደህንነት ስጋቶች ተለይተዋል እና ተገምግመዋል እናም ለአደጋዎቹ የጤና እና የደህንነት ተስማሚ ልምዶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሆነዋል።

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 2.3.1.2 ድርጅቱ ከምግብ ወለድ በሽታዎች ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን በመለየት በእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (በ NTFPs) አሰባሰብ እና ማቀነባበር ሂደት ላይ አደጋን ለመቀነስ ተገቢውን የጤና እና የደህንነት መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል።

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 2.3.1.3 በሕዝብ ጤና አዋጅ ቁጥር 200/2000 (እ.ኤ.አ) የምግብ ጥራት ቁጥጥር እና የምግብ ደረጃ መስፈርቶችን ያሚሉ ሁሉንም እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን (NTFPs) ለሰው ልጆች ለመሰብሰብ እና ለማሸግ የተሰነዱ አሠራሮች ተዘርግቷል፡፡

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 2.3.1.4 ለምግብነት የሚውሉ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን (NTFPs) ለማቀነባበር የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ንፁህ እና ቀደም ሲል ከተሰበሰቡ ቁሳቁሶች ትራፊዎች የፀዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የንፅህና አጠባበቅ ሂደት አለ።

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 2.3.1.5 በማቀነባበሪያ ቦታዎች ለምግብነት ከሚውሉ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFP) አይነቶችናሙናዎችን ለመውሰድ እና እነሱን ለመመዝገብ እና ለማከማቸት አሰራር ተዘጋጅቷል፡፡

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 2.3.1.6 የምርት አሰባሰብ ሥራ አስኪያጅ ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFPs) አሰባሰብ ጋር የተያያዘ አግባብነት ያለው የጤና እና የደህንነት መመሪያዎችን ያውቃል።

SLIMF 2.3.1 እያንዳንዱሠራተኛ ከሚሰራው ተግባር ጋር ስለሚዛመዱ የጤና እና የደህንነት እርምጃዎች ተነግሮታል/ ተነግሯታል እና እነዚህም የ ILO የደህንነት እና ጤና በደን ስራ ላይ የተግባር መመሪያን ያሟላሉ ወይም ከዚያ በላይ ያልፋሉ።

2.3.2 ሠራተኞች ለተመደቡበት ሥራ ምቹ የሆኑ የግል መከላከያ መሣሪያዎች አሏቸው

2.3.3 የግል መከላከያ መሳሪያዎችን መጠቀም ግዴታ ነው

2.3.4 በጤና እና በደህንነት ተግባራት የአደጋዎች ድግግሞሽ እና በአደጋዎች ምክንያት የባከነ ጊዜን ጨምሮ ተመዝግበው ተቀምጠዋል

2.3.5 የአደጋዎች ድግግሞሽ እና ክብደት ከብሔራዊ የደን ኢንዱስትሪ አማካይ አደጋ ጋር ሲነፃፀር ያለማቋረጥ ዝቅተኛ ናቸው

2.3.6 የጤና እና የደህንነት ጥንቃቄ ተግባራት ከትላልቅ ክስተቶች ወይም አደጋዎች በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ ይገመገማሉ እና ይሻሻላሉ።

***ማረጋገጫዎች፡-*** *ወቅታዊ የአደጋ መዝገቦች፤*

**2.4 ድርጅቱ ዝቅተኛው የደን የኢንዱስትሪ ደረጃዎች የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ወይም ሌሎች እውቅና የተሰጣቸው የደን የኢንዱስትሪ ምንዳ ስምምነቶች ወይም የኑሮ ምንዳ ይህም ከህጋዊ ዝቅተኛ ምንዳ በላይ ከሆነ ምንዳ ይከፍላል፣ ከእነዚህ መካከል አንዳቸውም በማይኖሩበት ጊዜ ድርጅቱ ከሠራተኞች ጋር በመገናኘት የኑሮ ምንዳ ለመወሰን ዘዴዎችን ያዘጋጃል።**

2.4.1 በኢትዮጵያ የሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 (እ.ኤ.አ) ምዕራፍ 2 ክፍል 55.2 እንደተደነገገው ድርጅቱ በማንኛውም ሁኔታ የሚከፍለው ምንዳ ህጋዊ ዝቅተኛ የደመወዝ መጠንን ያሟላል ወይም ይበልጣል።

2.4.1.1 ድርጅቱ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት፤የሥራ ገበያ እና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን ባስገቡ ጥናቶች ላይ በመመስረት በየጊዜው ዝቅተኛ የደመወዝ መጠን ይከልሳል፡፡

2.4.2 የሚከፈለው ምንዳ ያሚላል ወይም ይበልጣል፡-

1) ዝቅተኛ የደን ኢንዱስትሪ ደረጃዎች ወይም
2) ሌሎች የታወቁ የደን ኢንዱስትሪ ምንዳ ስምምነቶች; ወይም
3) ከህጋዊ ዝቅተኛ ምንዳ በላይ የሆነ የኑሮ ምንዳ
4) በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ 1156/2019 (እ.ኤ.አ) ምዕራፍ 2 ክፍል 55 እንደተደነገገው ብሔራዊ ዝቅተኛ ምንዳ ።

2.4.3 ሚስጥራዊነትን በጠበቀ መልኩ የክፍያ እርከን እና የክፍያ ደረሰኞች ለሠራተኞች ግልጽ ይደረጋሉ።

2.4.4 ምንዳ፣ ደመወዝ እና የውል ክፍያዎች የሚከፈላቸው በወቅቱ ነው2.5 ድርጅቱ የአስተዳደር ዕቅዱን እና ሁሉንም የአስተዳደር ተግባራትን በአስተማማኝ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ለሠራተኞች ሥራ-ተኮር ሥልጠና እና ቁጥጥር ያሳያል።

**2.5 ድርጅቱ የአስተዳደር ዕቅዱን እና ሁሉንም የአስተዳደር ተግባራትን በአስተማማኝ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ለሠራተኞች ሥራ-ተኮር ሥልጠና እና ቁጥጥር ያሳያል።**

2.5.1 ሰራተኞች ለአመራር እቅድ እና ለሁሉም የአመራር ተግባራት አፈፃፀም በአስተማማኝ እና ውጤታማ አስተዋፅዖ ለማድረግ ከአባሪ ለ እና ከክትትል ጋር የተጣጣመ የስራ ተኮር ስልጠና አላቸው።

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 2.5.1 እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFPs) በመሰብሰብ እና በማቀነባበር ላይ ያሉ ሠራተኞች ወይም ወኪሎቻቸው (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ ተወካዮች) ፣ ምን እንደሚሰበሰብ እና እንዴት እንደሚከናወን ስምምነት ያካተተ የተፈረመ ውል አላቸው፡፡

2.5.2 ወቅታዊ የሥልጠና መዝገቦች ለሁሉም የሚመለከታቸው ሠራተኞች ተቀምጠዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** *የሥልጠና መዝገቦች፣ የሥልጠና ሰርተፊኬቶች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሠራተኞች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፡፡*

**2.6 ድርጅቱ ከሠራተኞች ጋር በመገናኘት ለሠራተኞች በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ውድመት ፣ ለድርጅቱ በሚሰሩት ሥራ ጋር በተያያዘ በሥራ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች ወይም በስራ ላይ ለደረሰ ጉዳት ቅሬታዎችን ለመፍታት እና ፍትሃዊ ካሳ የመስጠት ዘዴዎች ይኖረዋል።**

2.6.1 ከሠራተኞች ባሕል ጋር አግባብ ባለው ግንኙነት የዳበረ የግጭት አፈታት ሂደት ተዘርግቷል፡

2.6.2 የሰራተኞች ቅሬታዎች ተለይተው ምላሽ ተሰጥተዋል ወይም ተፈትተዋል ወይም በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ ናቸው፡፡

2.6.3 የሰራተኞች የንብረት መጥፋት ወይም ጉዳት፣ በሥራ ላይ ለሚከሰት በሽታ ወይም የአካል ጉዳት ጋር የተያያዙ የሰራተኞች ቅሬታዎች በወቅታዊ መዝገቦች ተይዘዋል የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

1) ቅሬታዎችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች
2) ፍትሃዊ ካሳን ጨምሮ የሁሉም አለመግባባቶች አፈታት ሂደት ውጤቶች፤
3) ያልተፈቱ አለመግባባቶች ያልተፈቱበት ምክንያቶች እና ወደ ፊት እንዴት እንደሚፈቱ

2.6.4 ለሠራተኞች ከሥራ ጋር በተገናኘ ለሚደርስ የንብረት መጥፋት ወይም ጉዳት እና በሥራ ላይ ለሚከሰት በሽታ ወይም ጉዳት ፍትሃዊ ማካካሻ ተሰጥቷል።

## መርህ-3፡ የነባር ሕዝቦች/Indigenous peoples/ መብቶች

**ድርጅቱ በአስተዳደር ተግባራት የተጎዱትን የነባር ሕዝቦች መሬቶች፣ ግዛቶች እና ሀብቶች የባለቤትነት፣ የመጠቀምና የማስተዳደር ሕጋዊና ልማዳዊ መብታቸውን ይለያል እንዲሁም ይጠብቃል።**

**3.1 ድርጅቱ በአስተዳደር አሃዱ(Management Unit) ውስጥ ያሉትን ወይም በአስተዳደር ተግባራት የተጎዱትን ተወላጆች ይለያል። ድርጅቱ ነባር ሕዝቦችን በማሳተፍ የይዞታ መብቶቻቸውን፣ የደን ሃብትና ስርአተ-ምህዳር አገልግሎት የማግኘትና የመጠቀም መብቶቻቸውን፣ ልማዳዊ መብቶቻቸውንና ህጋዊ መብቶቻቸውን እና ግዴታዎቻቸውን በአስተዳደር አሃዱ ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው። በተጨማሪም ድርጅቱ እነዚህ መብቶችን አስመልክቶ የሚከራከሩባቸውን ቦታዎች ይለያል።**

3.1.1 በአስተዳደር ተግባራት ሊጎዱ የሚችሉ በአከባቢዉ ነባር ህዝቦች ተለይተዋል።

1) በግለሰብ ደረጃ ራሱን እንደ ነባር ተወላጅ መለየት እና በማህበረሰቡ እንደ አባላቸው መቀበል፤
2) ከቅኝ ግዛት በፊት/ከቅድመ-ሰፋሪ ማህበረሰቦች ጋር ታሪካዊ ቀጣይነት፤
3) ከግዛቶች እና ከአካባቢው የተፈጥሮ ሀብቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት፤
4) የተለየ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ሥርዓቶች፤
5) የተለየ ቋንቋ፣ ባህል እና እምነት፤
6) የበላይ ያልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፤
7) እንደ ልዩ ህዝቦች እና ማህበረሰቦች የአባቶቻቸውን አካባቢዎችና ስርዓቶች ለመጠበቅና ለማስቀጠል ቁርጥ ውሳኔ

***<u>የመመሪያ ማስታወሻ፡-</u>*** በአንዳንድ ሁኔታዎች የነባር ሕዝቦች እንደ ነባር ተወላጅ መብቶቻቸውን ለመለየት እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ይህንን ሂደት ለመደገፍ FSC በተባበሩት መንግስታት የተቀመጡትን የሚከተሉትን የባህሪዎች ዝርዝር ያስተዋውቃል፡ ድርጅቶች ከሀገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ነባር ህዝቦች፣ ድርጅቶች ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር መማከር አለባቸው።

3.1.2 በ3.1.1 ከተጠቀሱት የነባር ሕዝቦች ጋር በባህላዊ አግባብ ባለው ተሳትፎ የሚከተሉት ተመዝግበዋል እና/ወይም ካርታዎች ተቀርፀዋል፤

1) ህጋዊ እና ባህላዊ የይዞታ መብቶቻቸው፤
2) የደን ሃብት እና የስነ-ምህዳር አገልግሎቶችን የማግኘት እና የመጠቀም ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶቻቸው፤
3) ተፈጻሚ የሚሆኑ ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶቻቸው እና ግዴታዎቻቸው፤
4) እነዚህን መብቶች እና ግዴታዎች የሚደግፉ ማስረጃዎች፤
5) ህጋዊ እና/ወይም ልማዳዊ መብቶችን በያዙባቸው ቦታዎች ላይ ምኞታቸው እና ግቦቻቸው፤
6) በነባር ሕዝቦች፣ መንግስታት እና/ወይም ሌሎች መካከል ስለመብቶች የሚከራከሩባቸው አካባቢዎች፤
7) ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች እና የተከራካሪ መብቶች በድርጅቱ የሚስተናገዱባቸው መንገዶች ማጠቃለያ፤ እና
8) ከFPIC, FSC፣ የደን አስተዳደር ተግባራት፣ ያልተነካ የደን መልክአ ምድሮች እና አገር በቀል ባህላዊ መልክአ ምድሮች ጋር የተገናኘ የግንዛቤ ደረጃቸው።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የነባር ሕዝቦች የመለየት ሂደት፣ በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ ተለይተው የሚታወቁት የአከባቢዉ ነባር ተወላጆች እና አጎራባች ቦታዎችን የሚገልጹ ሪፖርቶች፤ ከነባር ሕዝቦች ጋር የተደረገ የምክክር እና የውይይት ማስረጃ፤ በአመላካቾች 3.1.2 እና በተዘረዘሩት ጉዳዮች 1-8 ላይ ያለው መረጃ።

**3.2 ድርጅቱ ለአስተዳደር አሃዱ በተለዩ ቦታዎች ውስጥ ወይም ከእሱ ጋር በተያያዘ በሚከናወኑ የአስተዳደር ተግባራት ላይ ቁጥጥርን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ሕጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች እውቅና ለነባር ሕዝቦች ይሰጣል እንዲሁም ያከብራል። የነባር ሕዝቦች የአስተዳደር ተግባራትን ለመቆጣጠር የሶስተኛ ወገን ውክልና ለመስጠት ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት ያስፈልጋል።**

3.2.1 ባህላዊ አግባብ ባለው ተሳትፎ የነባር ሕዝቦች መቼ ፣ የት እና እንዴት መብቶቻቸውን፣ ሀብቶቻቸውን፣ መሬቶቻቸውንና ግዛቶቻቸውን ለመጠበቅ በሚያስፈልገው መጠን የአስተዳደር ተግባራትን እንዴት አስተያየት እንደሚሰጡና ማሻሻያዎችን እንደሚጠይቁ መረጃ ያገኛሉ።

3.2.2 የነባር ሕዝቦች ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶቻቸው በድርጅቱ አይጣሱም።

3.2.3 ከአስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ የነባር ሕዝቦች ሕጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች የተጣሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ሲኖር ሁኔታው አስፈላጊ ከሆነ በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ በሆነ ተሳትፎ እና/ወይም በመስፈርት 1.6 ወይም 4.6 በተጠቀሰው የክርክር መፍቻ ሂደት ይስተካከላል።

3.2.4 ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት በነባር ሕዝቦች የሚሰጥ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን የሚያካትት ሂደት በመጠቀም የተለዩ መብቶቻቸውን የሚነኩ የአስተዳደር ተግባራትን ከማካሄድ በፊት ነው፡-

1) የነባር ሕዝቦች ሀብታቸውን በሚመለከት መብታቸውን እና ግዴታቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፤
2) በኢኮኖሚያዊ ፣ በማህበራዊ እና በአካባቢያዊ ሁኔታዎች የሀብቱን እሴት ለነባር ሕዝቦች በሚገባ ማሳወቅ፣
3) የነባር ሕዝቦች መብታቸውን፣ ሀብታቸውን፣ መሬታቸውንና ግዛታቸውን ለመጠበቅ በሚያስፈልገው መጠን ለታቀዱት የአስተዳደር ተገባራት ፈቃዳቸውን የመከልከል ወይም የመቀየር መብታቸውን ማሳወቅ፤ እና
4) ለአካባቢው ተወላጆች ወቅታዊ እና የወደፊት የታቀዱ የደን አስተዳደር ተግባራትን ማሳወቅ።

3.2.5 በነፃ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት ሂደት እስካሁን ድረስ የFPIC ስምምነት ካልተደረገ ድርጅቱ እና የተጎዱት ነባር ህዝቦች በጋራ በስምምነት፣የFPIC ሂደት ውስጥ ገብተዋል፤ ይህ ሂደት በመልካም እምነት* እየተከናወነ ሲሆን

ማህበረሰቡም በዚህ ስምምነት ረክቷል።

***ማረጋገጫዎች:-*** በግልጽ የተመዘገቡ የነባር ሕዝቦች መብቶች፤ በአከባቢዉ ለነባር ተወላጆች በመብታቸው ላይ የግንዛቤ ፈጠራ መዝገብ፤ በግልጽ የተመዘገበ የFPIC ሂደት እና ስለ ተወላጆች ተመሳሳይ ግንዛቤ

**3.3 በአስተዳደር ተግባራት ላይ የቁጥጥር ውክልና በሚሰጥበት ጊዜ በድርጅቱ እና በነባር ሕዝቦች መካከል ያለው አስገዳጅ ስምምነት በነጻ፣ በቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት ይጠናቀቃል። ስምምነቱ የቆይታ ጊዜውን፣ ለዳግም ድርድር ዕድል የሚሰጥ፣ የእድሳት፣ የማቋረጥ፣ የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን እና ሌሎች ውሎችን እና ሁኔታዎችን ይገልፃል። ስምምነቱ የድርጅቱን የነባር ሕዝቦች የስምምነቱን ውሎችና ሁኔታዎች መፈጸማቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል።**

3.3.1 አግባብ ባለው ባህላዊ ተሳትፎ ላይ በመመስረት የአስተዳደር ስራዎችን መቆጣጠር፣ በነጻ ቅድመ እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነት ሲሰጥ፣ አስገዳጅ ስምምነቱ ቢያንስ የሚይዘው፡-

1) የአሁኑ ስምምነት የሚቆይበት ጊዜ፤
2) ስምምነት የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች፤
3) እገዳ፣ መቋረጥ፣ እንደገና መደራደር እና የእድሳት ድንጋጌዎች፤
4) የጋራ ስምምነት የተደረገበት ተነሳሽነት ያለው የግጭት አፈታት ሂደት የሚካሄድባቸው ሁኔታዎች ፤
5) የስምምነቱ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች።

***<u>የመመሪያ ማስታወሻ:</u>*** የተነካ መብት ያገኘው ከመንግስት ጋር ለሚደረገው ማንኛውም የህግ አቋም ወይም የድርድር ሁኔታ መዘዝ እንዳለው ስለሚታሰብ ከድርጅቱ ጋር በህጋዊ መንገድ የሚያዝ ስምምነት ላይገባ ይችላል። በነዚህ ሁኔታዎች፣ ተዋዋይ ወገኖች FPIC የመስጠት፣ የመከልከል ወይም የመሰረዝ መብትን ለማክበር በግልፅ ከተቀመጡ አላማዎች ጋር የተለየ የስምምነት አይነት ለመጠቀም ሊወስኑ ይችላሉ። በስምምነቱ ሂደት ልማት ከመጀመሩ በፊት ስለዚህ ሁኔታ መወያየት ጠቃሚ ነው።

3.3.2 አስገዳጅ የስምምነት መዝገቦች ተጠብቀዋል።

3.3.3 አስገዳጅ ስምምነቱ የድርጅቱን የነባር ሕዝቦች ከውሎቹና ሁኔታዎቹ ጋር መከበራቸውን የመከታተል ድንጋጌን ይዟል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የFPIC በስራ ላይ ያሉ አስገዳጅ ስምምነቶች

**3.4 ድርጅቱ በተባበሩት መንግሥታት የነባር ሕዝቦች መብቶች መግለጫ (2007) እና በአለም አቀፍ የስራ ድርጅት ስምምነት 169 (1989) የተገለጹትን በአካባቢዉ የነባር ተወላጅ ሕዝቦች መብቶች፣ ልማዶች እና ባህል እውቅና ይሰጣል እንዲሁም ይደግፋል።**

3.4.1 በUNDRIP እና ILO ስምምነት 169 የተገለጹት የነባር ሕዝቦች መብቶች፣ ልማዶች እና ባህል በድርጅቱ አልተጣሱም፤

3.4.2 በUNDRIP እና ILO ኮንቬንሽን 169 በተገለጸው መሰረት በአካባቢዉ የነባር ሕዝቦች መብቶች፣ ልማዶች እና ባህል በድርጅቱ እንደተጣሱ የሚያሳይ ማስረጃ በሚገኝበት ጊዜ፣ እነዚህን ነባር ሕዝቦች መብቶች፣ ልማዶች እና ባህል ወደነበረበት ለመመለስ የተወሰዱ እርምጃዎችን ጨምሮ፣ የመብት ባለቤቶችን በሚያረካ መልኩ በሰነድ ቀርቧል፤

***ማረጋገጫዎች፡-*** ከነባር ሕዝቦች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ።

**3.5 ድርጅቱ ነባር ሕዝቦችን በማሳተፍ ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች እና የነባር ህዝቦች ህጋዊ ወይም ልማዳዊ መብቶች ያሏቸው ቦታዎችን ይለያል። እነዚህ አካባቢዎች በድርጅቱ እውቅና የተሰጣቸው ሲሆኑ አስተዳደራቸው እና/ወይም ጥበቃቸው ከነዚህ ነባር ሕዝቦች ጋር በመግባባት ይስማማል።**

3.5.1 የነባር ሕዝቦች ሕጋዊ ወይም ልማዳዊ መብቶች ያላቸውን ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች በባህል አግባብነት ባለው ተሳትፎ ተለይቷል፤

3.5.2 እንዲህ ያሉ ቦታዎችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እርምጃዎች ከባህል አንጻር ተገቢ በሆነ መንገድ ነባር ህዝቦች ጋር በመተባበር ተስማምቷል፣ ተመዝግቧ እንዲሁም ተተግብረዋል። የነባር ሕዝቦች በዶክመንት ወይም በካርታ ላይ የተገለጹ ቦታዎችን አካላዊ መለያ መስጠት የቦታዎቹን እሴት ወይም ጥበቃ አደጋ ላይ እንደሚጥል ሲወስኑ ሌሎች መንገዶች ተጠቅመዋል፤

3.5.3 ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች አዲስ በታዩበት ወይም በተገኙበት አካባቢ የጥበቃ እርምጃዎች ከነባር ሕዝቦች ጋር እስኪስማሙ ድረስ እና በአከባቢው እና በብሔራዊ ህጎች እንደተደነገገው የአስተዳደር ተግባራት ወዲያውኑ ተቋርጠዋል፤

***ማረጋገጫዎች፡-*** ካርታዎች፤ የቦታዎች ምርመራና ከነባር ሕዝቦች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ።

**3.6 ድርጅቱ የነባር ሕዝቦች ባህላዊ እውቀታቸውን የመጠበቅና የመጠቀም መብታቸውን ይጠብቃል፤ እንዲሁም የአካባቢው ማህበረሰቦች እንዲህ ዓይነቱን እውቀትና የአዕምሯዊ ንብረታቸውን በመጠቀም ካሳ ይከፍላቸዋል። እንደ መስፈርት 3.3 መሠረት አንድ አስገዳጅ ስምምነት ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በድርጅቱ እና በነባር ሕዝቦች መካከል እንዲህ ዓይነቱ አጠቃቀም በነፃ፣ በቅድሚያ እና በመረጃ በተደገፈ ስምምነት እንዲካሄድ ይደረጋል፤ ይህ ስምምነት የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ ጋር የሚስማማ ይሆናል።**

3.6.1 ባህላዊ እውቀት እና አእምሯዊ ንብረት ተጠብቋል፣እንዲሁም የእነዚህ ባህላዊ እውቀት እና አእምሯዊ ንብረት ባለቤቶች ነፃ ፣ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ በውል ስምምነት በመስጠታቸው ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

3.6.2 የነባር ሕዝቦች ባህላዊ ዕውቀትንና የአዕምሯዊ ንብረት መብትን ለመጠቀም በነጻ፣ በቅድሚያና በቅድመ መረጃ ስምምነት በተደረሰው አስገዳጅ ስምምነት መሠረት ካሳ ተከፍሏቸዋል፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** በግልጽ የተመዘገበ የFPIC ሂደት፣ በሥራ ላይ ያሉ አስገዳጅ ስምምነቶች ።

## መርህ 4: የማህበረሰብ ግንኙነቶች

**ድርጅቱ የአካባቢ ማህበረሰቦችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ለማሻሻል አስተዋፅኦ ያደርጋል።**

**4.1 ድርጅቱ በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ ያሉትን የአካባቢ ማህበረሰቦችን እና በአስተዳደር ተግባራት የተጎዱትን ይለያል። ድርጅቱ ከእነዚህ ማህበረሰቦች ጋር በመገናኘት የይዞታ መብቶቻቸውን፣ የደን ሃብትና የስነ-ምህዳር አገልግሎት የማግኘትና የመጠቀም መብቶቻቸውን፣ በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ የሚተገበሩ ልማዳዊ መብቶቻቸውን፤ ህጋዊ መብቶቻቸውን እና ግዴታዎቻቸውን ይለያል።**

4.1.1 በአስተዳደር አሃዱ የሚገኙ እና በአስተዳደር ተግባራት ሊጎዱ የሚችሉ የአከባቢ ማህበረሰቦች ተለይተዋል።

4.1.2 በ4.1.1 ውስጥ በተገለፀው መሠረት፣ ከአከባቢው ማህበረሰቦች ጋር አግባብነት ባለው ባህላዊ መስተጋብር የሚከተሉት በሰነድ እና/ወይም በካርታ ተለይተዋል፡-

1) የይዞታ ህጋዊ እና ባህላዊ መብቶቻቸው፤
2) ህጋዊ እና ልማዳዊ የደን ሀብት እና የስርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች የማግኘትና የመጠቀም መብት፤
3) ህጋዊ እና ባህላዊ መብቶቻቸው እና ተፈጻሚነት ያላቸው ግዴታዎች፤
4) እነዚህን መብቶች እና ግዴታዎች የሚደግፉ ማስረጃዎች፤
5) በአከባቢው ማህበረሰቦች ፣ መንግስታት እና/ወይም ሌሎች መካከል የመብት ክርክር የሚካሄድባቸው አካባቢዎች፤
6) ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች እና አከራካሪ መብቶች በድርጅቱ የሚቀርቡበት መንገዶች ማጠቃለያ፤ እና
7) ከአስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ የአከባቢው ማህበረሰቦች ምኞቶች እና ግቦች።

***ማረጋገጫዎች:-*** የማህበረሰብ መለያ ሂደት መዝገብ ዝርዝር፤ ተለይተው የታወቁ ማህበረሰቦች ዝርዝር፤ በአመልካች 4.1.2 ከተዘረዘሩት 1-7 ጉዳዮችን እንዴት መፍታት እንደሚቻል የሚያሳይ በግልፅ የተመዘገበ የተሳትፎ ሂደት፣ አሳታፊ የደን አስተዳደር (PFM) ስምምነት።

**4.2 ድርጅቱ የአከባቢው ማህበረሰቦች ለአስተዳደር በተለዩ አሃዶች ውስጥ ወይም ከእዚዉ ጋር በተያያዘ በሚከናወኑ የአስተዳደር ተግባራት ላይ ቁጥጥርን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ሕጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች እውቅና ይሰጣል እንዲሁም ያከብራል። የባህላዊ ህዝቦች የአስተዳደር ተግባራትን ለመቆጣጠር የሶስተኛ ወገን ውክልና ለመስጠት ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት (FPIC) ያስፈልጋል።**

4.2.1 ባህላዊ አግባብ ባለው ተሳትፎ አማካኝነት የአካባቢው ማህበረሰቦች በአስተዳደር ተግባራት ላይ መቼ፣ የት እና እንዴት አስተያየታቸውን ሊሰጡና መብቶቻቸውን ለመጠበቅ በሚያስፈልገው መጠን ማሻሻያዎችን እንደሚጠይቁ እንዲያዉቁ ተደርጓል።

4.2.2 የአከባቢው ማህበረሰቦች የአስተዳደር ተግባራትን የመቆጣጠር ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች በድርጅቱ አልተጣሱም።

4.2.3 ከአስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ የአካባቢው ማህበረሰቦች ሕጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች የተጣሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ሲኖር ሁኔታው አስፈላጊ ከሆነ በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ በሆነ ተሳትፎ እና/ወይም በመስፈር 1.6 ወይም በ4.6 በተጠቀሰው የክርክር መፍቻ ሂደት ተስተካክሏል።

4.2.4 የአስተዳደር ተግባራት ከመጀመራቸው በፊት በባህላዊ ሕዝቦች የተለዩና መብቶቻቸውን የሚጎዱ የሚከተሉትን በሚያካትት ሂደት ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት ተሰጥቷል፡-

1) የባህላዊ ሕዝብ ሀብቱን በሚመለከት መብታቸውን እና ግዴታቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፤
2) በኢኮኖሚያዊ ፣ በማህበራዊ እና በአካባቢያዊ ሁኔታዎች የሀብቱን ዋጋ ለባህላዊ ሕዝቦች በደንብ ማሳወቅ፣
3) የባህላዊ ሕዝቦች መብታቸውን እና ሀብታቸውን ለመጠበቅ በሚያስፈልገው መጠን ለታቀዱት የአስተዳደር ተገባራት ፈቃዳቸውን የመከልከል ወይም የመቀየር መብታቸውን ማሳወቅ፤ እና

4) ለባህላዊ ሕዝቦች ወቅታዊ እና የወደፊት የታቀዱ የደን አስተዳደር ተግባራትን ማሳወቅ፡፡

4.2.5 ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት (FPIC) ሂደቱ እስካሁን ወደ FPIC ስምምነት ካልመራ ድርጅቱ እና የተጎዱት ባህላዊ ሕዝቦች በጋራ ስምምነት በተደረገበት፣ በመልካም እምነት እየተራመደ ባለው እና ማህበረሰቡም በሚረካበት የ FPIC ሂደት ውስጥ ተሳትፈዋል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** ከማኅበረሰቦች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፣ የአለመግባባቶች የተመዝገቡበት መረጃ፣ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ የ FPIC ሂደት መዝገብ፤ ከባህላዊ ሕዝቦች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፡፡

**4.3 ድርጅቱ ለአካባቢው ማህበረሰቦች፣ ለሥራ ተቋራጮችና ለአቅራቢዎች በአስተዳደራዊ ተግባራት ስፋት እና ክብደት ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ዕድል፣ የሥልጠናና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡**

4.3.1 ለአካባቢዉ ማህበረሰቦች፣ ለአካባቢዉ ተቋራጮች እና ለአካባቢዉ አቅራቢዎች የሚከተሉትን ምክንያታዊ እድሎች ተላልፈዉ ተሰጥቷል፡

1) የሥራ፤

2) የስልጠና፤ እና

3) ሌሎች አገልግሎቶች፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአከባቢውን ማህበረሰብ ያስቀደመ የግዥ እና የሥራ ስምሪት ፖሊሲ፣ የኮንትራክተሮች ዝርዝር፣ ለህብረተሰቡ የሥራ ዕድሎችን የማስተላለፍ መዝገብ፣ የሥልጠና መዝገቦች፣ የሥራ ስምሪት መዝገቦች፣ ለህብረተሰቡ የሥራ ዕድሎችን የማስተላለፍ መዝገብ፣ ከሠራተኞች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

**4.4 ድርጅቱ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በመተባበር በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገታቸው ላይ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ተጨማሪ ተግባራትን በማከናወን የአስተዳደሩ ተግባራት ስፋት፣ ክብደት፣ እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖን የሚመጥን ተግባር ይሰራል፡፡**

4.4.1 ለአካባቢያዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚሆኑ ዕድሎች በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ በሆነ መንገድ ከየአካባቢው ማህበረሰቦች እና ከሌሎች አግባብነት ያላቸው ድርጅቶችን በማሳተፍ ተለይተዋል፡፡

4.4.2 ለአካባቢያዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶች እና ተጨማሪ ተግባራት የሚተገበሩ እና/ወይም የሚደገፉ ሲሆን እነዚህም የአስተዳደር ተግባርት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖን ያገናዘቡ ናቸዉ፡፡

SLIMF 4.4.2 ድርጅቱ የአካባቢ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለመጠቀም ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡*** እድሎችን የመለየት ሂደት ሰነድ; ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮጀክቶች መዝገብ እና የተጠቃሚዎች ቁጥር፣ የአስተዳደር ዕቅድ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ተፅእኖ ግምገማ (ESIA) ሪፖርት፣

**4.5 ድርጅቱ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በመተባበር፣ በአካባቢው ማህበረሰቦች ላይ የሚደርሰውን ከፍተኛ አሉታዊ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመለየት፣ ለማስወገድና ለመቀነስ እርምጃ ይወስዳል፡፡ የተወሰደው እርምጃ ከነዚህ ተግባራት ስፋት፣ ክብደትና ስጋት እንዲሁም ከአሉታዊ ተፅዕኖዎች ጋር ተመጣጣኝ ነው፡፡**

4.5.1 ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር ባህልን በሚመጥን መልኩ በመሳተፍ የአስተዳደር ተግብራት ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን ለመለየት፣ ለማስወገድና ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** ወቅታዊ የክትትል ሪፖርቶች፤ የተመዘገቡ የመቀነስ/mitigation/ እርምጃዎች፤ የተሰነዱ የመቀነስ እርምጃዎች፣ የአፈፃፀም መዝገብ፣ ESIA ሪፖርት፡፡

**4.6 ድርጅቱ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በመተባበር ቅሬታዎችን ለመፍታት እና የአስተዳደር ተግባራት የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ በተመለከተ ለአካባቢው ማህበረሰቦች እና ለግለሰቦች ፍትሃዊ ካሳ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ይኖረዋል፡፡**

4.6.1 በአካባቢው ካሉ ማህበረሰቦች ጋር በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ በሆነ ተሳትፎ የተገነባ በይፋ የሚገኝ የክርክር አፈታት ሂደት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

4.6.2 የአስተዳደር ተግባራት ተፅዕኖዎች ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች በወቅቱ ምላሽ ተሰጥቷቸዋል እና መፍትሄ አግኝተዋል ወይም በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ ይገኛሉ።

4.6.3 የአስተዳደር ተግባራት ተፅዕኖን የሚመለከቱ ቅሬታዎች ወቅታዊ መዝገብ ተይዟል፣ ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡

1) ቅሬታዎችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች፤

2) ለአካባቢ ማህበረሰቦች እና ግለሰቦች ፍትሃዊነትን ጨምሮ የሁሉም አለመግባባቶች የመፍታት ሂደት ውጤቶች ማካካሻ ፤ እና

3) ያልተፈቱ አለመግባባቶች፤ ያልተፈቱበት ምክንያቶች እና እንዴት ይፈታሉ።

4.6.4 አለመግባባቶች ባሉባቸው አካባቢዎች ክዋኔዎች ይቆማሉ፤ እለመባባቶቹ፡-

1) ከፍተኛ መጠን፤

2) ከፍተኛ ቆይታ፤ ወይም

3) ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ፍላጎቶች ያካተተቱ ሲሆኑ

***ማረጋገጫዎች፡-*** በስራ ላይ ያለ የተሰነደ የግጭት አፈታት ሂደት ፤ ወቅታዊ የሆነ የቅሬታ መዝገብ፤ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፣ የግጭት አፈታት ሂደት ቃለ ጉባኤ መዝገብ፣ የካሳ ስምምነት።

**4.7 ድርጅቱ የአካባቢው ማህበረሰቦችን በማሳተፍ ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች እና የአካባቢው ማህበረሰቦች ህጋዊ ወይም ልማዳዊ መብቶች ያሏቸው ቦታዎችን ይለያል። እነዚህ ልዩ ቦታዎች በድርጅቱ እና በአስተዳደሩ እውቅና ያገኛሉ እና/ወይም ከእነዚህ ማህበረሰቦች ጋር በመገናኘት የጥበቃ ስምምነቶች ይደረጋሉ።**

4.7.1 የአካባቢ ማህበረሰቦች ሕጋዊ ወይም ልማዳዊ መብቶች ያላቸውን ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች በባህል ተገቢ ተሳትፎ ተለይተው በድርጅቱ እውቅና ተሰጥቷቸዋል።

4.7.2 እንዲህ ያሉ ቦታዎችን ከባህል አንጻር ተገቢ በሆነ መንገድ ለመጠበቅ የሚያስችሉ እርምጃዎች ለመዉሰድ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በመተባበር ስምምነቶች ተደርገዋል፣ ተመዝገበዋል እንዲሁም ተተግብረዋል። የአካባቢ ማህበረሰቦች በዶክመንት ወይም በካርታ ላይ የተገለጹ ቦታዎችን አካላዊ መለያ በመስጠት የቦታዎቹን ዋጋ ወይም ጥበቃ አደጋ ላይ እንደሚጥል ሲወስኑ ሌሎች መንገዶች ጥቅም ላይ ይውላሉ።

4.7.3 ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች አዲስ ሲታዩ ወይም ሲገኙ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር የጥበቃ እርምጃዎች ላይ እስኪስማሙ ድረስ የአካባቢው እና ብሔራዊ ሕጎች ዉስጥ በተመላከተዉ መሠረት በአካባቢዉ የሚደረግ የማስተዳደር ተግባራት ወዲያውኑ ቆመዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** በካርታዎች ላይ በግልፅ የተከለሉ ባህላዊ ቦታዎች ፤ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ የባህላዊ ቦታዎች፤ በግልጽ ተመዘገቡ የተሳትፎ ሂደቶች ፤ ካርታዎች፤ የተሰዱ የጥበቃ እርምጃዎች፤ ፤ አዲስ የታወቁ ቦታዎች መዝገብ፣

**4.8 ድርጅቱ የባህላዊ ሕዝቦች ባህላዊ እውቀታቸውን የመጠበቅና የመጠቀም መብታቸውን ይጠብቃል፤ እንዲሁም እንዲህ ዓይነቱን እውቀትና የአዕምሯዊ ንብረታቸውን ለመጠቀም ለእነርሱ ካሳ ይከፍላቸዋል። እንደ መስፈርት 3.3 መሠረት አንድ አስገዳጅ ስምምነት ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በድርጅቱ እና በባህላዊ ሕዝቦች መካከል እንዲህ ዓይነቱ አጠቃቀም ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ በተደገፈ ስምምነት እንዲካሄድ ይደረጋል፤ ይህ ስምምነት የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች ጥበቃ ጋር የሚስማማ ይሆናል።**

4.8.1 የባህላዊው ሕዝቦች ባህላዊ እውቀት እና አዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ተደርጎላቸዋል እና ጥቅም ላይ የሚዉሉት የዚያ ባህላዊ እውቀት እና አእምሯዊ ንብረት ባለቤቶች ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነታቸዉን በማያያዝ ስምምነት ሲሰጡ ብቻ ነው።

4.8.2 የባህላዊው ሕዝቦች በባህላዊ እውቀት እና አዕምሯዊ ንብረት አጠቃቀም ላይ ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ በተደገፈ አስገዳጅ ስምምነት መሠረት ካሣ ተከፍሏቸዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** በስራ ላይ የዋለ አስገዳጅ ስምምነት ተቀምጧል፤ በግልጽ የተመዘገበ የነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ (FPIC) ሂደት፤ ከአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር የተደረገ ቃለ-ምልልስ።

## መርህ -5: የደን ጠቀሜታዎች

**ድርጅቱ የረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነትንና ማህበራዊ እንዲሁም አካባቢያዊ ተጠቃሚነትን ለማስጠበቅ ወይም ለማሻሻል በአስተዳደር አሃድ ውስጥ መጠነ ሰፊ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በተሻለ ብቃት ያስተዳደራል፡፡**

**5.1. ድርጅቱ የአስተዳደር ተግባራትን መጠን እና ጥንካሬ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ የአካባቢውን ኢኮኖሚ ለማጠናከር እና ለማስፋት በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ ያሉትን ሀብቶች እና የስርአተ-ምህዳር አገልግሎቶች ስብስብ ላይ በመመርኮዝ የተለያዩ ጥቅሞችን እና/ወይም ምርቶችን መለየት ፣ ማምረት ወይም እንዲመረት ማድረግ አስችሏል፡፡**

5.1.1 የአካባቢውን ኢኮኖሚ ለማጠናከር እና ለማስፋት የሚያግዙ የሀብት መጠን እና የስርዓተ ምህዳር አግልጋሎቶች ተለይተዋል፤

5.1.2 ከአስተዳደር አላማዎች ጋር በሚስማማ መልኩ የተለዩ ጥቅሞች እና ምርቶች በድርጅቱ የሚመረቱ እና/ወይም ለሌሎች እንዲመረቱ የአካባቢውን ኢኮኖሚ ለማጠናከር እና ለማሻሻል እንዲገኙ ተደርገዋል፡፡

SLIMF 5.1.2.1 ድርጅቱ በአስተዳደር አሃድ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ሀብቶች እና የስርአተ-ምህዳር አገልግሎቶችን በመጠቀም የተለያዩ ጥቅሞችን እና ምርቶችን ያመርታል፡፡

SLIMF 5.1.2.2 በ 5.1.1 ውስጥ የተገለጹት ጥቅሞች እና ምርቶች ከድርጅቱ የአስተዳደር ዓላማ ውጭ ከሆኑ ሌሎች እንዲመረቱ ፣ የአከባቢውን ኢኮኖሚ ለማጠናከር እና ለማዛባት እንዲገኙ ተደርገዋል ።

5.1.3. ድርጅቱ የFSC ስርአተ-ምህዳር አገልግሎቶችን ሲጠቀም ድርጅቱ የFSC PRO-30-006 ውስጥ የሚመለከታቸው መስፈርቶችን ማክበር አለበት፡፡

*ማረጋገጫዎች፡- ተመዝግበው ያሉ ሀብት እና የስርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች፣ የአስተዳደር ዕቅድ፣ የቅድመ-ትግበራ ጥናቶች፣ የሀብት ዝርዝር እና በአካባቢው ላይ በሚገኙ ድርጅቶች ጥቅም ላይ የዋለ ስርዓተ ምህዳር ግልጋሎቶች፣ የአካባቢውን ሀብት እየተጠቀሙ የሚገኙ ድርጅቶች ዝርዝር እና እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤት ሀብቶች ካርታ እና ሰነድ፣ የገበያ ትንተና ሪፖርት፡፡*

**5.2. ድርጅቱ በተለምዶ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ከአስተዳደር አሃዱ በቋሚነት ሊቆይ በሚችል ደረጃ ወይም ከዚያ በታች ይሰበስባል፡፡**

5.2.1. እንጨት መሰብሰብ ደረጃዎች አሁን ባለው ተሸሎ የተገኘ መረጃ ላይ በመመርኮዝ የእድገት እና ምርታማነት፤ የደን ክምችት፤ የምርት ምጣኔ እና የስርአተ-ምህዳር ተግባራት መልሶ ማገገም ላይ የተመሰረቱ ናቸው ።

5.2.2. ለደን ዛፍ የሚፈቀደው ከፍተኛ ዓመታዊ ቆረጣ የሚወሰነው የደን ዛፍ መሰብሰብ ደረጃ ትንተና ላይ መሰረት በማድረግ የደን ዛፍ መሰብሰብ ደረጃን በማረጋገጥ ጭምር በቋሚነት ማቆየት የሚችለውን የደን ዛፍ መሰብሰብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን ነው ።

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 5.2.2 የ NTFPs ዘላቂ የምርት መሰብሰብ መጠን በእድገቱ እና በማምረት ላይ ባለው ተሸሎ በተገኙ ወቅታዊ መረጃ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡

5.2.3 የደን ዛፍ ትክክለኛ ዓመታዊ ምርት መጠን ተመዝግበው የሚወሰዱ ሲሆን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚገኘው ምርት በተመሳሳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በ5.2.2 ውስጥ የተወሰነውን የቆረጣ መጠን መብለጥ የለበትም ፡፡

5.2.4. በድርጅቱ ቁጥጥር ስር ለንግድ አገልግሎት የሚውሉ እና ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን ለማምረት ዘላቂ የሆነ የመሰብሰብ መጠን ይሰላል እና ይተገበራል፡፡

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 5.2.4.1 የ NTFP መሰብሰብ የሚከናወነው አመቱን በተገቢው ጊዜ ነው።

1) የእፅዋት ሀብት ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም
2) የአካባቢ ተጽዕኖን መቀነስ
3) የሚሰበሰቡት ክፍሎች በተሟላ መልኩ መድረሳቸውን ማረጋገጥ

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 5.2.4.2 የNTFP መልቀም/መሰብሰብ በአስተዳደር ዕቅዱ መሰረት በተመረጡ ዛፎች ወይም የደን ክፍሎች ላይ ብቻ የተገደበ ነው

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 5.2.4.3. ለ NTFPs እድገትና ዳግም ብቅለት አስተማማኝ መረጃ ባለመኖሩ ለወደፊቱ አያያዝ ዝርዝር መረጃ ለመሰብሰብ ፕሮግራም አለ።

***ማረጋገጫዎች፡-*** *ወቅታዊ የእድገትና ምርት መረጃ፣ ወቅታዊ የደን ቆጠራ መረጃ፣ የይዘትና ስፋት መቀነስ በመሞት እንዲሁም በተፈጥሮ ክስተቶች ለምሳሌ እሳት፣ ተባይ እና በሽታ ምክንያቶች፣ እና በዚህ ደረጃ የተቀመጡ ሌሎች መስፈርቶች ጋር የተያያዙ ምክንያቶች ይዘትና ስፋት መቀነስ፣ የተመዘገበ የወቅቱ ዓመታዊ ምርት፣ ዓመታዊ ለመቁረጥ የሚፈቀድ መጠን፣ የአመራረት መረጃዎች፣ ይዘት/ዛፎች/ሄክታር፣ ከተመረተ በኋላ የእድሜ ስብጥር የመስክ ሪፖርት፣ የማምረት ጊዜውን የሚገልጽ በዕድሜ ስብጥሩና የአሰራር ዘዴውን መሰረት ያደረገ ፤ የአመራረት ስርዓት ዓመታዊ የምርት ጥናት ሪፖርት፤ የአመራረት ዕቅድ፣ የአስተዳደር ዕቅድ፣ የመስክ ቅኝትና ጥናት ሪፖርት፣ የባለድርሻ አካላት ምክክር፣ የማምረቻ ቦታ ካርታ፣ የደን ውጤቶች ዝርዝር፡፡*

**5.3 የድርጅቱ አዎንታዊ እና አሉታዊ ውጫዊ ተፅዕኖዎች በአስተዳደር ዕቅድ ውስጥ የተካተቱ መሆናቸውን ማሳየት አለበት፡፡**

5.3.1. የአስተዳደር ተግባራት አሉታዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል፣ ለመቀነስ ወይም ለማካካስ የሚደረጉ ወጪዎች በአስተዳደር ዕቅድ ውስጥ በቁጥር የተገለጹና የተሰነዱ ናቸው።

SLIMF 5.3.1 ድርጅቱ የአስተዳደር ተግባራት አሉታዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል፣ ለመቀነስ ወይም ለማካካስ የሚውል በጀት የሚመድብ ሲሆን በአስተዳደር ዕቅድ ውስጥም ተመዝግበው ይገኛሉ።

5.3.2. የአስተዳደር ተግባራት አዎንታዊ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ተፅእኖዎች ጋር የተያያዙ ጥቅሞች ተለይተው በአስተዳደር ዕቅድ ውስጥ ተካተዋል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** *ዓመታዊ በጀት፣ የአስተዳደር ዕቅድ፣ የማህበረሰብና አካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሪፖርት* (ESIA report).

**5.4 ድርጅቱ የድርጅቱን ፍላጎቶች ለማሟላት በአካባቢያዊ ማቀነባበሪያ፣ በአካባቢያዊ አገልግሎቶች እና በአካባቢያዊ እሴት ለመጨመር የሚገኙ እና የሚጠቀሙ ከሆነ፣ መጠኑን፣ ጥንካሬውን እና ስጋት በሚመጥን መልኩ መሆን አለበት። እነዚህ በአካባቢው የማይገኙ ከሆነ ድርጅቱ እነዚህን አገልግሎቶች ለማቋቋም የሚረዳውን ሁሉ ያደርጋል።**

5.4.1. አካባቢያዊ ያልሆኑ እና አካባቢያዊ አማራጮች በወጪ፣ በጥራት እና በአቅም ተመጣጣኝ በሚሆኑበት ጊዜ የአካባቢያዊ ሸቀጦች፣ አገልግሎቶች፣ ማቀነባበሪያ እና እሴት የተጨመረባቸው መገልገያዎች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

5.4.2 በአካባቢው የሚገኙ ሸቀጦች፣ አገልግሎቶች፣ ማቀነባበሪያ እና እሴት ተቋማት የተጨመረባቸው መገልገያዎች በማይገኙበት ቦታ አቅም ለመፍጠር እና ለማበረታታት ምክንያታዊ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** *የአካባቢያዊ ማቀነባበሪያ እና እሴት የሚጨምሩ ተቋማት መዝገብ፤ የተከናወኑ የአቅም ግንባታ ተግባረት መዝገብ፤ በድርጅቱ የአቅም ግንባታ ተነሳሽነት የተደገፉ የአካባቢው ሰዎች እና ተቋማት ስሞች፤ የኮንትራክተሮች እና የአገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር፤ የሥልጠና መዝገቦች፤ የስራ ቅጥር ፖሊሲ* (HR-Policy) *እና የስራ ቅጥር መዝገቦች፣ የአስተዳደር ዕቅድ፣ የዋጋ ሰንሰለት ግምገማ ሪፖርት፣ የመስክ ክትትል ሪፖርት፡፡*

**5.5 ድርጅቱ በዕቅድ አወጣጥ እና በሚያወጣቸው ወጪዎች መጠን፣ ጥንካሬና እና ስጋት ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ለረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል።**

5.5.1 ይህንን ደረጃ ለማሟላት እና የረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነትን ለማረጋገጥ የአስተዳደር ዕቅዱን ለመተግበር በቂ ገንዘብ ተመድቧል፡፡

5.5.2 ይህንን ደረጃ ለማሟላት እና የረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነትንለማረጋገጥ የአስተዳደር ዕቅድን ለመተግበር ወጪዎች እና ኢንቨስትመንቶች ተደርገዋል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** *የአስተዳደር እቅድ፤ ዓመታዊ በጀት፤ የተሟላ ወጪና ኢንቨስትመንት መዝገብ፤ የድርጅቱ ኦዲት የተደረገ ሂሳብ*

## መርህ-6: የአካባቢያዊ እሴቶች እና ተጽዕኖዎች

**ድርጅቱ በአስተዳደር አሃድ ውስጥ የሥነ-ምህዳራዊ አገልግሎቶች እና የአካባቢ እሴቶች በመጠበቅ እና/ወይም መልሶ በማቋቋም እንዲሁም አሉታዊ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን ማስወገድ፣መጠገን ወይም መቀነስ አለበት።**

**6.1 ድርጅቱ በአስተዳደር አሃድ ውስጥ እና ውጭ አካባቢያዊ እሴቶችን የሚጎዱ የአስተዳደር ስራዎችን መመልከትና መቆጣጠር ይኖርበታል፡፡ ይህ ዳሰሳ የሚካሄደው በዝርዝር፣ በመጠን፣ በድግግሞሽ ሆኖ ከአስተዳደር ተግባራት በመጠን፣ በጥንካሬና በስጋት ተመጣጣኝ የሆነና አስፈላጊውን የጥበቃ እርምጃዎችን ለመወሰንና ሊከሰቱ የሚችሉ የእነዚህን ተግባራት አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመለየትና ለመቆጣጠር በቂ ነው፡፡**

6.1.1 የአካባቢ እሴቶችን ለመለየት እና በአስተዳደር ተግባራት ተጽዕኖ ሊያሳድሩ በሚችሉበት ጊዜ ተሸሎ የሚገኝ መረጃ ከአስተዳደር አሃዱ ውጭምጥቅም ላይ ውሏል ።

***<u>የመመሪያ ማስታወሻ፡-</u>*** *ተሸሎ የሚገኝ መረጃ  የሚያካትተው፡-*

1) የአካባቢ እሴቶችን ተፈጥሮአዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ወካይ የናሙና ቦታዎች
2) የመስክ ጥናቶች
3) ለአካባቢያዊ እሴቶች አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ ቋቶች ለምሳሌ የአከባቢው የደን መዝገብ እና የተፈጥሮ መጠባበቂያ ስትራቴጂካዊ መረጃ ከስተት ወይም ከዚያ በላይ ደረጃ
4) ከአካባቢያዊ እና ክልላዊ ባለሙያዎች ጋር ምክክር ማድረግ
5) ከባህላዊ አግባብነት ጋር በተያያዘ ኢንዲጂነስ ፒፐል፣ ከአካባቢው ማህበረሰቦች እና ከተጎዱ ባለድርሻ አካላት እና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት።

SLIMF 6.1.1 ድርጅቱ በአስተዳደር አሃድ ውስጥ ያሉ የአካባቢ ጥበቃ እሴቶችን ይለያልነገር ግን ከአስተዳደር አሃድ ውጭ ባሉ የአስተዳደር ተግባራት ተጽዕኖ ሊያሳድሩ በሚችሉበት ጊዜ ከአካባቢ ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ጋር በመመካከር ይለያል።

6.1.2 የአካባቢ እሴቶች ግምገማ በዝርዝር እና በተደጋጋሚ ሁኔታ ተካሂዷል ስለዚህ:

1) በመስፈርት 6.2 መሰረት የአስተዳደር እንቅስቃሴዎች በተለዩት የአካባቢ እሴቶች ላይ የሚያሳድሩት ተፅእኖ ሊገመገም ይችላል፤
2) የአካባቢ እሴቶች ስጋቶች  በመስፈርት 6.2 መሰረት ሊታወቁ ይችላሉ፤
3) በመስፈርት 6.3 መሰረት እሴቶችን ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ የጥበቃ እርምጃዎች  ሊታወቁ ይችላሉ፤ እና
4) በመርህ 8 መሰረት የአካባቢ ለውጦችን እና ተፅእኖዎችን  መከታተል ይቻላል፤

SLIMF 6.1.2 የአካባቢ ጥበቃ እሴቶች ግምገማ በዝርዝር  እና ድግግሞሽ ይከናወናል፤  ስለዚህም በተለዩት የአካባቢ ጥበቃ እሴቶች ላይ የአስተዳደር ተግባራትተፅእኖዎች እንደ መስፈርት 6 መሰረት ይዳሰሳል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** *የመጀመሪያ የአካባቢ ግምገማ ሪፖርት፤* Annex I HCV Framework፤ *የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ* (EIA) *ሪፖርት እና የአካባቢ ባለሥልጣናት ያፀደቁት አጠቃላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ቅነሳ ዕቅድ*

**6.2. ድርጅቱ የአስተዳደር ተግባራት ከመጀመራቸው በፊት በቦታው ላይ የሚያስተጓጉሉ ተግባራት በተለዩት የአካባቢ እሴቶች ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተፅእኖዎች መጠን፣ ጥንካሬ እና አደጋ ይለያል እንዲሁም ይገመግማል።**

6.2.1 የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የአስተዳደር ተግባራት ከአካባቢያዊ ደረጃ/ stand level/ እስከ የመሬት ገጽታ ደረጃ/ landscape level/ ድረስ በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ የአሁኑን እና የወደፊቱን ተፅእኖዎች አቅም ይለያል፤

6.2.2 የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማው የቦታውን የሚረብሹ ተግባራት ከመጀመራቸው በፊት የአስተዳደር እንቅስቃሴዎች የሚያስከትሉትን ተፅእኖ ይለያል እንዲሁም ይገመግማል።

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 6.2.2. ጉልህ የሆነ የ NTFPs የመሰብሰብ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት እንቅስቃሴዎች በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ተፅእኖ ይገመገማል ።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሪፖርት/ሰርቲፊኬት፤ የአካባቢ ጥበቃ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፤ የአካባቢ ጥበቃ ሪፖርት፤ የአስተዳደር ዕቅድ፤ በአካባቢ ጥበቃ እሴቶች ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ ተፅዕኖዎች መዝገብ፤ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል፤ የልዩ ቦታ ግምገማ አሰራር፤ በአካባቢ ጥበቃ እሴቶች ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ ተፅዕኖዎች መዝገብ።

**6.3 ድርጅቱ የአስተዳደር እንቅስቃሴዎች በአካባቢያዊ እሴቶቹ ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል እና የተከሰቱትን ተፅዕኖዎች ለመቀነስ እና ለማስተካከል ውጤታማ እርምጃዎችን በመለየት እና ተግባራዊ በማድረግ የእነዚህን ተፅዕኖዎች መጠን፣ ጥንካሬ እና ስጋቶችን በማመጣጠን ይለያል።**

6.3.1 የአስተዳደር ተግባራትን አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለመከላከል እና የአካባቢ እሴቶችን ለመጠበቅ ታቅደዋል እንዲም ተተግብረዋል ፡፡

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 6.3.1.1 ድርጅቱ በአስተዳደር አሃድ ውስጥ የNTFPs አያያዝ፣ የመሰብሰብ እና አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለመከላከል እና ለመቀነስ ውጤታማ እርምጃዎችን በመውሰድ፤ ምርት በመሰብሰብ እና በማቀነባበር ያዘጋጃል እንዲሁም ይተግብራል ።

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 6.3.1.2. ከ ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (NTFPs) ዝርያዎች ጋር የተያያዙት ዘአካል(organism) ብዝሃነት ተጠብቋል ወይም ጨምሯል የሚለውን ለማሳየት ክትትል ተድርጓል ።

6.3.2 የአስተዳደር ተግባራት በአካባቢ እሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ይከላከላል ።

6.3.3 በአካባቢ እሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎች ሲከሰቱ ፣ ተጨማሪ ጉዳቶችን ለመከላከል እርምጃዎች ተወሰደዋል እና አሉታዊ ተፅእኖዎች ቀንሰዋል እና/ወይም ተስተካክለዋል፡፡

ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች NTFP 6.3.3. በአካባቢ እሴቶች እና በ NTFP ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎች ሲከሰቱ ተጨማሪ ጉዳቶችን ለመከላከል እርምጃዎች ተወስደዋል እንዲሁም አሉታዊ ተፅእኖዎች ቀንሰዋል እና/ወይም ተስተካክለዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የክትትል ሪፖርቶች፣ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል፣ የመጀመሪያ የአካባቢ ግምገማ ሪፖርት፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ (EIA) ሪፖርት፣ የአካባቢ ጥበቃ ህግ ተከባሪነት የምስክር ወረቀት፣ የህግ ተከባሪነት ሪፖርት፣ የጣቢያ-ተኮር ግምገማ አሰራር፣ ለአካባቢ እሴቶች ሊያስከትሉ የሚችሉ ተፅእኖዎች መዝገብ፣ የአስተዳደር ዕቅድ፤

**6.4 ድርጅቱ ብርቅዬ ዝርያዎችን እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎችን እና መኖሪያዎቻቸውን በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ በጥበቃ ዞኖች፣ በጥበቃ አካባቢዎች፣ ግንኙነቶች እና/ወይም (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ) ለህልውናቸው እና ለኑሮአቸው የሚረዱ ሌሎች ቀጥተኛ እርምጃዎችን በመውሰድ ይከላከላል። እነዚህ እርምጃዎች ከአስተዳደር ተግባራት ስፋት፣ ጥንካሬ እና ስጋት እንዲሁም ብርቅዬ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች የጥበቃ ሁኔታ እና ሥነ ምህዳራዊ መስፈርቶች ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው። ድርጅቱ በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ የሚወሰዱትን እርምጃዎች በሚወስንበት ጊዜ ከአስተዳደር አሃድ ወሰን ውጭ ያሉ ብርቅዬ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎችን ጂኦግራፊያዊ ክልል እና ሥነ ምህዳራዊ መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባል።**

6.4.1 ተሸለው የሚገኙ መረጃዎች ጥቅም ላይ የሚውሉት ብርቅዬ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎችን እና መኖሪያዎቻቸውን ለመለየት ሲሆን ይህም ሲአይቲኢስ ዝርያዎችን /CITES species/ (አግባብነት ካለው) እና በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ የሚገኙ ወይም ሊገኙ የሚችሉ እና ከአስተዳደር አሃዱ ጋር አጎራባች በመሆኑ በብሔራዊ ፣ በክልላዊ እና በአካባቢያዊ ብርቅዬ ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች ዝርዝር ውስጥ የተዘረዘሩትን ጨምሮ ነው።

6.4.2 የአስተዳደር ተግባራት ብርቅዩ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች እና በመከላከያ ሁኔታቸው እና በመኖሪያ ስፍራዎቻቸው ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ ተፅእኖዎች ተለይተዋል እና አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለማስወገድ የአስተዳደር ተግባራት ተሻሽለዋል፡፡

SLIMF 6.4.2 ብርቅዬ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች እና መኖሪያዎቻቸውን ከአሉታዊ ተፅእኖዎች ለመከላለከል የአስተዳደር ተግባራት ተነድፈዋል ወይም ተሻሽለዋል፡፡

6.4.3 ብርቅዬ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች እና መኖሪያዎቻቸው ተጠብቋል፡፡ ይህም የጥበቃ ዞኖችን ፣ የጥበቃ ቦታዎችን፣ ግንኙነቶችን እና እንደ ዝርያዎች ያሉ ለህልውናቸው እና ለህይወታቸው ሌሎች ቀጥተኛ መንገዶችን የመልሶ ማቋቋም ፕሮግራሞች በመስራት ነው።

6.4.4 ብርቅዬ ወይም ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎችን ማደን፣ ማስገር፣ ማጥመድ እና መሰብሰብ ተከልክሏል፡፡

SLIMF 6.4.4 የብርቅዬ ወይም ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎችን ማደን፣ ማስገር፣ ማጥመድ እና መሰብሰብን መከላከል የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቷል፡፡

**6.5 ድርጅቱ ነባር የሆኑ ሥርዐተ ምህዳሮችን የሚወክሉ ናሙና አካባቢዎችን ወደ ተፈጥሯዊ ሁኔታቸው እንዲመለሱ በመለየት ይጠብቃል፡፡ወካይ ናሙና አካባቢዎች ከሌሉ ወይም በቂ ካልሆኑ ድርጅቱ የአስተዳደር አሃድጋር የተመጣጠነ መልኩ ወደ ተፈጥሯዊ ሁኔታ ይመልሰዋል። የቦታው መጠንና በዕፅዋት ውስጥ ያሉትን ጨምሮ ለጥበቃቸው ወይም ለመልሶ ማቋቋማቸው የተወሰዱ እርምጃዎች በባህር ደረጃ ካለው የሥርዐተ ምህዳሮች ጥበቃ ሁኔታ እና እሴት እንዲሁም ከአስተዳደር ተግባራት መጠን ፣ ጥንካሬ እና ስጋት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው።**

6.5.1 በአስተዳደር አሃድ ውስጥ ያሉ ወይም በተፈጥሮ ሁኔታዎች ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ነባር ሥርአተ-ምህዳሮችን ለመለየት ተሸለዉ የሚገኙ መረጃዎች ጥቅም ላይ ዉሏል።

6.5.2 ነባር ሥርአተ-ምህዳሮች ተወካይ ናሙና አካባቢዎች በሚኖሩበት ቦታ ጥበቃ ተደርጎላቸዋል፤

6.5.3 ወካይ የናሙና አካባቢዎች ከሌሉ ወይም ነባር ናሙና አካባቢዎች በበቂ ሁኔታ ነባር ሥርአተ-ምህዳሮች የማይወክሉ ወይም በሌላ መልኩ በቂ ካልሆኑ የአስተዳደር አሃዱ አንድ ክፍል ወደ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ይመለሳል።

6.5.4 የንፅፅር ናሙና ወካይ ቦታዎች እና/ወይም የመልሶ ማቋቋም አካባቢዎች መጠናቸው በአካባቢው የአካባቢ ጥበቃ እና የሥርአተ-ምህዳሮች እሴት በመሬት ገጽታ ደረጃ የአስተዳደር አሃድ መጠን እና የደን አስተዳደር ጥንካሬ ጋር ተመጣጣኝ ነው።

6.5.5 የነባር ሥርአተ-ምህዳሮች ከሌሎች የጥበቃ አካባቢዎች በይነ መረብ አካላት ጋር ተጨምረዉ የሚካተቱ ወካይ የናሙና ቦታዎች ቢያንስ 10% የአስተዳደር አሃዱን ይይዛሉ።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአካባቢው ሥነ ምህዳሮች በግልጽ የተለዩ እና ካርታ የተቀረጹ ናቸው፤ Annex I HCV Framework; የተቀመጡ የመከላከያ እርምጃዎች አዲስ የተመለሱ የአካባቢው ሥነ ምህዳሮች በግልጽ የተለዩ እና ካርታ የተቀረጹ ናቸው፤ የአስተዳደር ዕቅድ ተካቷል፡፡

**6.6 ድርጅቱ በተፈጥሮ የሚኖሩ ነባር ዝርያዎች እና የዘረመል ዓይነቶች ህልውና እንዲቀጥል ውጤታማ በሆነ መንገድ በማስጠበቅ እንዲሁም በተለይም በአስተዳደር አሃድ ውስጥ የመኖሪያ ቦታዎች በመንከባከብ የባዮሎጂያዊ ብዝሃነት መጥፋትን ይከላከላል። ድርጅቱ አደንን፣ ማስገርን፣ ማጥመድን እና መሰብሰብን ለማስተዳደር እና ለመቆጣጠር ውጤታማ እርምጃዎች መኖራቸውን ማሳየት አለበት።**

6.6.1 የአስተዳደር አሃዱ በሚገኝበት ነባር ስነ ምህዳር ዉስጥ የአስተዳደር ተግባራት በአካባቢዉ የሚገኙትን የዕፅዋት ስብስብ እና የመኖሪያ ቦታ ገጽታዎች ይጠብቃሉ፡፡

6.6.2 ቀደም ሲል በተደረገው አያያዝ የዕፅዋት ስብስብ ወይም የመኖሪያ ቦታ ገጽታዎች ካጠፋ እነዚህን መኖሪያዎች መልሶ ለማቋቋም የታቀዱ የአስተዳደር ተግባራት ተተግብረዋል ።

6.6.3 አስተዳደሩ በተፈጥሮ የሚኖሩ ዝርያዎችን እና የዘረመል ብዝሃነታቸውን ለመደገፍ ከአካባቢያዊ ነባር ሥርአተ-ምህዳሮች ጋር የተያያዙ የመኖሪያ ቦታ ገጽታዎች ይጠብቃል ፣ ያሻሽላል መልሶ እንዲያገግም ያደርጋል፡፡

6.6.4 ዱር እንስሳት ጥበቃና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 163/2008 እ.ኤ.አ መሰረት በተፈጥሮ የሚከሰቱት የአካባቢው ዝርያዎችን ፣ የዘር ልዩነታቸው እና ተፈጥሯዊ ስርጭታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ የዓሣ ማስገር፣ ውጥመድ ማስቀመጥ እና የመሰብሰብ ተግባራትን ለማስተዳደር እና ለመቆጣጠር ውጤታማ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

6.6.5 የዱር እንስሳትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ አሰራሮች ተዘርግተዋል፡- በጥበቃ፣ በአደን እና በእንስሳት ወይም የአካል ክፍሎቻቸው (ቀንዶች) ንግድ በብሔራዊ እና/ወይም ዓለም አቀፍ የጥበቃ ደንቦች ላይ የሚታወቁና የሚከበሩ መሆን አለባቸው።

6.6.6 በድርጅቱ መገልገያዎችና ተሽከርካሪዎች ውስጥ የዱር እንስሳት ሥጋ እና የተኩስ መሳሪያዎችን ማጓጓዝ እና ንግድ የሚከለክል እና የሚቀጣ የውስጥ ደንብ ተቀምጧል።

6.6.7 የአደን ፖሊሲዎች መከበሩን ለማረጋገጥ መደበኛ እና ወቅታዊ ቁጥጥር የሚደረግበት ስርዓት ተግባራዊ ሆኗል።

6.6.8 ሰራተኞች የዱር እንስሳት ሥጋን ወይም የዱር ዓሣዎችን ማደንን ወይም መሰብሰብን ከተፈቀደዉ በላይ እንዳይጨምሩ ለማድረግ ውጤታማ የማጣጣም እርምጃዎች ተቀምጠዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የእሳት አደጋ መከላከያ ዕቅድ፤ ወራሪ አረም መከላከያ ዕቅድ፤ የግጦሽ መከላከያ ዕቅድ፤ የአስተዳደር ዕቅድ፤ የአካባቢ ጥበቃ ዕቅዶች፤ በአስተዳደር ክፍል ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ ሕገወጥ ተግባራት ሪፖርቶች፤ ነባር ሥርዓት- ምህዳሮች ስርጭት በግልጽ የሚሳይ ካርታ፡፡

**6.7 ድርጅቱ ተፈጥሯዊ የውሃ መስመሮችን፣ የውሃ አካላትን፣ የባህር ዳርቻ ዞኖች እና ግንኙነቶቻቸውን ይጠብቃል ወይም ያድሳል። ድርጅቱ በውሃ ጥራት እና ብዛት ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ያስወግዳል እንዲሁም የሚከሰቱትን ይቀንሳል ያስተካክላል።**

6.7.1 የተፈጥሮ የውሃ መስመሮችን፣ የውሃ አካላትን፣ የወንዝ ዳርቻ ዞኖች እና የውሃውን ብዛት እና ጥራት ጨምሮ ግንኙነታቸውን ለመጠበቅ የመከላከያ እርምጃዎች ይተገበራል።

6.7.2 የተተገበሩ የጥበቃ እርምጃዎች የውሃ መስመሮችን፣ የውሃ አካላትን፣ የወንዝ ዳርቻ ዞኖች እና ግንኙነታቸውን፣ የውሃ መጠንን ወይም የውሃ ጥራትን ከደን አያያዝ ተፅእኖዎች የሚከላከሉ ካልሆኑ የመልሶ ማቋቋም ተግባራት ይተገበራሉ።

6.7.3 የተፈጥሮ የውሃ መስመሮች፣ የውሃ አካላት፣ የባህር ዳርቻ ዞኖች እና ተያያዥነታቸውን፣ የውሃ ብዛት ወይም የውሃ ጥራት በድርጅቱ ቀደም ሲል በመሬት እና ውሃ ላይ በተከናወኑ ተግባራት ጉዳት በደረሰበት ቦታ የመልሶ ማቋቋም ተግባራትን ይተገበራል።

6.7.4 በቀደሙት ሥራ አስኪያጆች እና በሶስተኛ ወገኖች ተግባራት የተከሰቱ የውሃ መስመሮች ፣ የውሃ አካላት ፣ የውሃ መጠን እና የውሃ ጥራት ቀጣይነት ያለው ጥፋት ሲኖር ይህንን ጥፋት የሚከላከሉ ወይም ለማቃለል የሚያስችሉ እርምጃዎች ይተገበራሉ።

***ማረጋገጫዎች:*** የአስተዳደር ዕቅድ፤ የውሃ መስመሮችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ አሰራሮች፤ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ፤ የአፈር መሸርሸር ቁጥጥር፡ የመልሶ ማቋቋም ዕቅዶች፤ የውሃ ጥራት እና ብዛት መቆጣጠሪያ ሪፖርቶች፤ የውሃ መስመሮች በግልጽ በካርታ ተቀርፀዋል እንዲሁም የመከላከያ ቀጠናዎቻቸው በግልጽ ተለይቷል።

**6.8 ድርጅቱ በተጠቀሰው ክልል ውስጥ ላሉት የመሬት ገጽታ እሴቶች ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ ዝርያዎችን፣ መጠን፣ ዕድሜን፣ የመገኛ ቦታን እና የመልሶ ማቋቋም ዑደት ለማቆየት እና/ወይምበማደስ እንዲሁም የአካባቢ እና ኢኮኖሚያዊ የመቋቋም አቅምን ለማጎልበት በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ የመሬት ገጽታውን ያስተዳድራል።**

6.8.1 የተለያዩ ዝርያዎች፣ መጠን፣ ዕድሜ፣ የቦታ ሚዛኖች እና የመልሶ ማቋቋም ዑደት ለአካባቢው ተስማሚ ሆነው ተጠብቀዋል።

6.8.2 የተለያዩ ዝርያዎች ፤መጠን፣ ዕድሜ፣ የቦታ መጠን እና የመልሶ ማቋቋም ዑደት ለአካባቢው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ተስማሚ በሆነ መንገድ ካልተስተካከለ እንደገና ይገነባል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአስተዳደር ዕቅድ፤ የምርት መሰብሰቢያ መዝገቦች፤ የመልሶ ማቋቋም ዕቅዶች

**6.9** **ድርጅቱ የተፈጥሮ ደን ወይም ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ቦታዎችን ወደ ሰው ሠራሽ ደን አይቀይርም፤ እንዲሁም የተፈጥሮ ደን ወይም ሰው ሠራሽ ደን ወይም ለደን ያልሆነ የመሬት አጠቃቀም ወይም የተፈጥሮ ደን ወደ ደን ያልሆነ የመሬት አጠቃቀም በቀጥታ በተቀየሩ ቦታዎች ላይ ሰው ሠራሽ ደን መለወጥ የለበትም፣ ሆኖም ግን የሚቀየረው፡-**

**ሀ) በጣም ውስን የሆነ ክፍል ከአስተዳደር አሃዱ ቦታዎች ላይ የሚነካ ሲሆን እና**

**ለ) በአስተዳደር አሃዱ ቦታዎች ውስጥ ግልጽ፣ ጉልህ፣ ተጨማሪና አስተማማኝ የረጅም ጊዜ የጥበቃ ጥቅሞችን ሲያስገኝ፣**

**ሐ) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ፣ እንዲሁም እነዚህን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ቦታዎችን ወይም ሀብቶችን የማይጎዳ ወይም አደጋ ላይ የማይጥል ሲሆን ።**

6.9.1 የተፈጥሮ ደን ወይም ከፍተኛ የጥበቃ ዋጋ ያላቸው አካባቢዎች ወደ ሰው ሠራሽ ደን አይቀየርም፣ የተፈጥሮ ደኖችን ወደ ደን ያልሆነ የመሬት አጠቃቀም አይቀየርም፣ ከተፈጥሮ ደን ወደ ደን ያልሆነ የመሬት አጠቃቀም በቀጥታ በተለወጡ ቦታዎችን ወደ ሰው ሠራሽ ደን አይቀየርም፣ሆኖም ግን የሚቀየረው፡-

1) በጣም ውስን የሆነ ክፍል ከአስተዳደር አሃዱ ቦታዎች ላይ የሚነካ ሲሆን እና

2) በአስተዳደር አሃዱ ቦታዎች ውስጥ ግልጽ፣ ጉልህ፣ ተጨማሪና አስተማማኝ የረጅም ጊዜ የጥበቃ ጥቅሞችን ሲያስገኝ፣

3) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ፣ እንዲሁም እነዚህን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ቦታዎችን ወይም ሀብቶችን የማይጎዳ ወይም አደጋ ላይ የማይጥል ሲሆን።

**6.10** **እ.ኤ.አ ከታህሳስ 1 ቀን 1994 እና ከታህሳስ 31 ቀን 2020 መካከል ከተፈጥሮ ደን ወደ ሰው ሰራሽ ደን ተለውጠው የያዙ የአስተዳደር አሃዶች፣ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካልተከተሉ በስተቀር ለዕዉቅና ማረጋገጫ ወረቀት የበቁ አይደሉም፤ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በስተቀር፡-**

**ሀ) ለውጡ በጣም ውስን በሆነ የአስተዳደር አሃዱ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ እና በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ ግልፅ፣ ጉልህ፣ ተጨማሪ፣ አስተማማኝ የረጅም ጊዜ ጥበቃ ጥቅሞችን እያስገኘ እንደሆነ፣ ወይም**

**ለ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በለውጡ ውስጥ የተሳተፈው ድርጅት በሚመለከተው የ FSC የመፍትሄ ማዕቀፍ በተገለጸው መሠረት የሁሉም ማህበራዊ ጉዳቶች መመለስ እና የአካባቢ ጉዳቶች በተመጣጣኝ ሁኔታ ማካካሱን ሲያሳይ፣ ወይም**

**ሐ) በለውጡ ያልተሳተፈ ነገር ግን ለውጡ የተከናወነበትን የአስተዳደር አሃዶች ያገኘ ድርጅት በ FSC የመፍትሄ ማዕቀፍ ውስጥ በተገለጸው መሠረት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ማህበራዊ ጉዳቶች መልሶ ማቋቋም እና የአካባቢ ጉዳቶችን በከፊል ማስተካከሉን ሲያሳይ**

6.10.1 ተሽሎ በሚገኝ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ትክክለኛ መረጃ እ.ኤ.አ ከታህሳስ 1 1994 እና 31 ታህሳስ 2020 መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ በሁሉም ለውጦች ላይ ተሰብስቧል፡፡

6.10.2 እ.ኤ.አ ከታህሳስ 1 ቀን 1994 እና ከታህሳስ 31 ቀን 2020 መካከል ከተፈጥሮ ደን ወደ ሰው ሰራሽ ደን ለዉጥ የተደረገባቸው ቦታዎች ለዕዉቅና ማረጋገጫ የበቁ አይደሉም፤ ከሚከተሉት በስተቀር፡-

1) ለውጡ በጣም ውስን በሆነ የአስተዳደር አሃዱ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ እና በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ ግልፅ ፣ ጉልህ ፣ ተጨማሪ ፣ አስተማማኝ የረጅም ጊዜ ጥበቃ ጥቅሞችን እያስገኘ እንደሆነ ፣ ወይም

2) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በለውጡ ውስጥ የተሳተፈው ድርጅት በሚመለከተው የ FSC የመፍትሄ ማዕቀፍ በተገለጸው መሠረት የሁሉም ማህበራዊ ጉዳቶች መመለስ እና የአካባቢ ጉዳቶች በተመጣጣኝ ሁኔታ ማካካሱን ሲያሳይ፣ ወይም

3) በለውጡ ያልተሳተፈ ነገር ግን ለውጡ የተከናወነበትን የአስተዳደር አሃዶች ያገኘ ድርጅት በ FSC የመፍትሄ ማዕቀፍ ውስጥ በተገለጸው መሠረት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ማህበራዊ ጉዳቶች መልሶ ማቋቋም እና የአካባቢ ጉዳቶችን በከፊል ማስተካከሉን ሲያሳይ

4) ድርጅቱ አነስተኛ መጠን ያለው አነስተኛ ይዞታነትን ሲያሟላ

**6.11 እ.ኤ.አ ከታህሳስ 31 ቀን 2020 በኋላ የተለወጡ የተፈጥሮ ደኖችን ወይም ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸውን አካባቢዎች የያዙ የአስተዳደር አሃዶች ከሆነ ለምስክር ወረቀት ለማግኘት ብቁ አይሆኑም፡፡ ከእነዚህ ለውጦች በስተቀር**

**ሀ) በአስተዳደር አሃዱ በጣም ውስን ክፍል ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል ፣**

**ለ) በአስተዳደር አሃድ ውስጥ ግልፅ ፣ ጉልህ ፣ ተጨማሪ ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የረጅም ጊዜ ጥበቃ እና ማህበራዊ ጥቅሞችን ፈጥሯል ፣ እና**

**ሐ) እነዚህን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ለማቆየት ወይም ለማሻሻል፣ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ፣ ወይም ለማንኛውም አስፈላጊ ጣቢያዎች ወይም ሀብቶች አደጋ ላይ የማይጥሉ መሆን አለባቸው**

6.11.1 እ.ኤ.አ ከታህሳስ 31 ቀን 2020 በኋላ በተፈጥሮ ደኖች እና ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ባላቸው አካባቢዎች ላይ የተደረጉ ለውጦች በአስተዳደር አሀዱ ውስጥ በሙሉ ትክክለኛ መረጃ ተሸሎ በተገኘው መረጃ ላይ ተመስርቶ ተሰብስቧል፡፡

6.11.2 እ.ኤ.አ ከታህሳስ 31 ቀን 2020 በኋላ የተፈጥሮ ደኖች ወይም ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸው ቦታዎች የተለወጡባቸው አካባቢዎች የምስክር ወረቀት አይሰጣቸውም፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ከተለወጡ በስተቀር ፤

1) በአስተዳደር አሃዱ በጣም ውስን ክፍል ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል ፣
2) በአስተዳደር አሃድ ውስጥ ግልፅ ፣ ጉልህ ፣ ተጨማሪ ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የረጅም ጊዜ ጥበቃ እና ማህበራዊ ጥቅሞችን ፈጥሯል ፣ እና
3) እነዚህን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ለማቆየት ወይም ለማሻሻል፣ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ፣ ወይም ለማንኛውም አስፈላጊ ጣቢያዎች ወይም ሀብቶች አደጋ ላይ የማይጥሉ መሆን አለባቸው

## መርህ 7: የደን አስተዳደር ዕቅድ ዝግጅት

**ድርጅቱ ከፖሊሲዎቹ እና አላማዎቹ ጋር የሚስማማ እና ከአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬ እና ስጋቶች ጋር የሚመጣጠን የአስተዳደር እቅድ ይኖረዋል። የተጣጣመ አስተዳደርን ለማራመድ የማኔጅመንት ፕላኑ ተግባራዊ መሆን እና በክትትል መረጃ ላይ ተመስርቶ ወቅታዊ መሆን አለበት.፡፡ ተያያዥነት ያለው የዕቅድ እና የሥርዓት ሰነድ ሠራተኞችን ለመምራት፣ የተጎዱ ባለድርሻ አካላትን እና ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት ለማሳወቅ እና የአስተዳደር ውሳኔዎችን ለማመሳከር በቂ መሆን አለበት።**

**7.1 ድርጅቱ የአስተዳደር ተግባሮቹን መጠን፣ ጥንካሬ እና ስጋት በተመጣጣኝ ሁኔታ፣ ለአካባቢ ጥበቃ ተስማሚ የሆኑ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የአስተዳደር ፖሊሲዎች (ራዕዮች እና እሴቶች) እና ግቦች* ያስቀምጣል። የእነዚህ ፖሊሲዎች እና ዓላማዎች ማጠቃለያዎች በአስተዳደር እቅድ ውስጥ ይካተታሉ ፣ ይፋ ይሆናሉ።**

7.1.1 የዚህን ደረጃ ለማሟላት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ፖሊሲዎች (ራዕይ እና እሴቶች) ተብራርቷል።

7.1.2 የዚህ ደረጃ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ልዩ፣ የተግባር አስተዳደር ዓላማዎች ተገልጸዋል።

7.1.3 የተገለጹት ፖሊሲዎች እና የአስተዳደር ዓላማዎች ማጠቃለያ በአስተዳደር እቅድ ውስጥ ተካተዋል ፣ ይፋ ሆነዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአስተዳደር እቅድ፣ የመሰብሰብ ሂደቶች(harvesting procedures)፣ የአሠራር እቅዶች፣ የመሰብሰብ እቅድ(harvesting plan)፣ የተለየ የአሠራር አስተዳደር እቅድ፣ መተዳደሪያ ደንቦች

**7.2 ድርጅቱ በመስፈርት 7.1 የተቀመጡትን የፖሊሲዎች እና የአስተዳደር ዓላማዎች ሙሉ በሙሉ የሚስማማ የአስተዳደር እቅድ ለአስተዳደር አሃዱ ይኖረዋል እንዲሁም ይተገብራል፡፡ የአስተዳደር ዕቅዱ በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ ያሉትን የተፈጥሮ ሀብት ይገልጻል እንዲሁም ዕቅዱ የ FSC የምስክር ወረቀት መስፈርቶችን እንዴት እንደሚያሟላ ያብራራል። የአስተዳደር ዕቅዱ የታቀዱትን ተግባራት ስፋት፣ ጥንካሬ እና ስጋት በሚመጥን መልኩ የደን አስተዳደር ዕቅድ እና የማህበራዊ አስተዳደር ዕቅድ ያካትታል።**

7.2.1 ድርጅቱ የአስተዳደር አላማውን የሚያሳካው በአመራር እቅድ ውስጥ የተገለጹትን ተግባራት፣ ሂደቶች፣ ስልቶች እና እርምጃዎች በመተግበር ነው።

SLIMF 7.2.1 የአስተዳደር እቅዱ የአስተዳደር አላማዎችን ለማሳካት የአመራር ዉሳኔዎችን፣ ሂደቶችን ስልቶችን እና እርምጃዎችን ያካትታል።

7.2.2 የአስተዳደሩ እቅድ በአባሪ ሠ (E) ውስጥ የተዘረዘሩትን ነገሮች ተደራሽ በማድረግ ፣ተተግብሯል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአስተዳደር እቅድ፣ ሂደቶች (አሰራሮች)

**7.3 የአስተዳደር እቅዱ ወደ እያንዳንዱ የተቀመጡ የአስተዳደር አላማዎች ያለውን እድገት ሊያረጋግጡ የሚችሉ ኢላማዎችን ያካትታል።**

7.3.1 ሊረጋገጡ የሚችሉ ኢላማዎች፣ እና የሚገመገሙበት ድግግሞሽ፣ ወደ እያንዳንዱ የአስተዳደር አላማ የሚደረገውን ሂደት ለመከታተል ተቋቁሟል ።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአስተዳደር እቅድ።

**7.4 ድርጅቱ የክትትልና ግምገማ ዉጤት፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወይም አዲስ ሳይንሳዊ እና ቴክኒካል መረጃ ለማካተት እንዲሁም የአካባቢ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ለሚለዋወጡ ለውጦች ምላሽ ለመስጠት የአስተዳደር እቅድ እና የአሰራር ሰነዶችን በየጊዜው ያሻሽላል ፣ ይከልሳል።**

7.4.1 የአስተዳደር እቅዱ ተሻሽሎ በየጊዜው ከአባሪ ረ (F) ጋር የሚስማማ ሆኖ ተሻሽሏል፣ ለከልሷል፡-ለማካተት፡

1) የምስክር ወረቀት ኦዲት ውጤቶችን ጨምሮ የክትትል ውጤቶች፣
2) የግምገማ ውጤቶች፣
3) የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ውጤቶች፣

4) አዲስ ሳይንሳዊ እና ቴክኒካዊ መረጃ እና

5) የአካባቢ፣ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ለወጥ ሁኔታዎች ።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአስተዳደር ዕቅድ፤ የክትትል ሪፖርቶች፤ የባለድርሻ አካላት ምክክር ሪፖርቶች፤ ሳይንሳዊ ሪፖርቶች፤ የመሰበሰብ ዕቅዶች (harvesting plan) እና ህትመቶች፣ የተሻሻለው የአስተዳደር ዕቅድ፣ የስብሰባ ቃለ ጉባዔ

**7.5 ድርጅቱ የአስተዳደር እቅዱን ማጠቃለያ በነጻ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል። ሚስጥራዊ መረጃን ሳይጨምር፣ ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው የአስተዳደር ዕቅድ ለተጎዱ ባለድርሻ አካላት ሲጠየቁ እና የማባዛት እና የማስተናገድ ወጪዎች በመሸፈን እንዲገኙ ይደረጋል።**

7.5.1 የአስተዳደር እቅድ ማጠቃለያ ካርታዎችን ጨምሮ እና ሚስጥራዊ መረጃዎችን ሳይጨምር ለባለድርሻ አካላት ለመረዳት በሚያስችል መልኩ ያለምንም ወጪ ለህዝብ ይፋ ሆኗል።

7.5.2 ሚስጥራዊ መረጃን ሳይጨምር የአስተዳደር ዕቅድ አግባብነት ያላቸው ክፍሎች ለባለድርሻ አካላት በተጠየቁበት ጊዜ ትክክለኛ የማባዛት እና የማስተናገድ ወጪዎች በመሸፈን ይገኛሉ።

***ማረጋገጫዎች፡-*** ሚስጥራዊ መረጃን ሳይጨምር የአስተዳደር እቅድ ማጠቃለያ።

**7.6 ድርጅቱ በአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬና ስጋት ላይ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ የተጎዱ ባለድርሻ አካላትን በደን አስተዳደር ዕቅድ እና ክትትል ሂደቱ ውስጥ በንቃት እና በግልፅ ያሳትፋል፤ እንዲሁም ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት ሲጠይቁ ያሳትፋል።**

7.6.1 ለባህል ተስማሚ በሆነ ተሳትፎ የሚመለከተው ተጎጂ ባለድርሻ አካላት* በሚከተሉት ሂደቶች ውስጥ በንቃት እና በግልፅ እንዲሳተፉ ለማድረግ ጥቅም ላይ ውሏል፡-

1) የግጭት አፈታት ሂደቶች (መስፈርት 1.6፣ መስፈርት 2.6፣ መስፈርት 4.6)፤)፤

2) የኑሮ ምንዳ ትርጉም (መስፈርት 2.4)፤

3) መብቶችን መለየት (መስፈርት 3.1, መስፈርት 4.1), ነባር ባህላዊ መልከዓ ምድሮች (መስፈርት 3.1) ቦታዎች (መስፈርት 3.5, መስፈርት 4.7) እና ተፅእኖዎች (መስፈርት 4.5);

4) የባህላዊ ማህበረሰቦች ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ የልማት ተግባራት (መስፈርት 4.4) እና

5) የከፍተኛ ጥበቃ እሴቶች ግምገማ, አስተዳደር እና ክትትል (መስፈርት 9.1, መስፈርት 9.2, መስፈርት 9.4)

7.6.2 በባህላዊ አግባብነት ያለው ተሳትፎ ጥቅም ላይ የሚዉለዉ፡-

1) አግባብነት ያላቸው ተወካዮችን እና የግንኙነት አካል መወሰን (አስፈላጊ ከሆነ የአካባቢ ተቋማትን, ድርጅቶችን እና ባለስልጣናትን ጨምሮ)፣

2) መረጃ በሁለቱም አቅጣጫዎች እንዲፈስ የሚያስችሉ በጋራ የተስማሙበትን የግንኙነት መስመሮችን መወሰን፣

3) ሁሉም ባለድርሻ አካላት (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ አናሳ ቁጥር ያላቸው) በፍትሃዊነት ተወክለዋል፣ ተሳትፈዋል ፣

4) ሁሉንም ስብሰባዎች ፣ የተወያዩባቸው ነጥቦች እና ሁሉም ስምምነት የተደረሰባቸውን መመዝገባቸዉን ማረጋገጥ።

5) የስብሰባ ቅጂዎች ይዘት መጽደቁን ማረጋገጥ፣ እና

6) የሁሉንም ባህላዊ አጋባብነት ያለዉ የተሳትፎ ተግባራት ውጤት ለተሳታፊዎች መጋራቱን ማረጋገጥ።

7.6.3 የተጎዱ የመብት ባለቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጥቅማቸውን በሚነኩ የአመራር ተግባራትን በመከታተል እና በማቀድ ሂደት ውስጥ በባህላዊ አግባብነት ያለዉ ተሳትፎ እንዲሳተፉ እድል ተሰጥቷቸዋል ።

SLIMF 7.6.3 ከተጎዱ ባለድርሻ አካላት እና ከነባር ህዝቦች ጋር የእነርሱ አሳሳቢ ጉዳዮች በአስተዳደር እና በክትትል ተግባራት ልማት እና ትግበራ ውስጥ እንዲስተናገዱ ተገቢ በሆነ ባህላዊ ሁኔታ ተሳትፎ ተጠናቋል።

7.6.4 በጥያቄያቸው መሰረት ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት ፍላጎቶቻቸውን በሚነ የአስተዳደር ተግባራት ላይ በክትትል እና በማቀድ ሂደቶች ውስጥ እንዲሳተፉ እድል ተሰጥቷቸዋል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** በምክክሩ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት መዝገብ; የባለድርሻ አካላት የምክክር ሪፖርት, የአስተዳደር እቅድ, የክትትል መዝገቦች.

## መርህ-8: ክትትልና ግምገማ

**ከሁኔታዎች ጋር የሚስማማ አስተዳደር ለመተግበር ድርጅቱ የአስተዳደር ግቦችን ለማሳካት የሚደረገው እድገት፣ የአስተዳደር ተግባራት ተፅእኖዎች እና የአስተዳደር አሃዱ ሁኔታ ከአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬ እና ስጋት ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ክትትል እና ግምገማ እየተደረገ መሆኑን ማሳየት ይኖርበታል።**

**8.1 ድርጅቱ የፖሊሲዎቹን እና የአመራር ዓላማቹን፣ የታቀዱ ተግባራት የሄዱበትን ሂደት፣ እና ሊረጋገጥ የሚችል ዒላማዎችን ጨምሮ የአመራር እቅዱን አፈፃፀም ለማሳካት የአስተዳደር አሃዱን ክንዉን ይከታተላል።**

8.1.1 የአስተዳደር ዕቅዱን አፈፃፀም ፣ ፖሊሲዎቹን እና የአስተዳደር ዓላማዎችን ጨምሮ እና ሊረጋገጡ የሚችሉ ዒላማዎችን ለማሳካት የሚያስችሉ አሰራሮች በሰነድ ተይዘዋል፣ ተከናውነዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የተመዘገቡ የክትትል አሰራሮች፣ የክትትል እና የግምገማ እቅድ፣ለክትትል እና ግምገማ (M&E) የበጀት እቅድ፤ የቁጥጥር ሂደቶች ሰነድ።

**8.2 ድርጅቱ በአስተዳደር አሃድ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን አካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን እንዲሁም የአካባቢያዊ ሁኔታ ለውጦችን ይከታተላል፣ ይገመግማል።**

8.2.1 ከአባሪ ሰ ጋር በሚስማማ መልኩ የአስተዳደር ተግባራትን ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎች ክትትል ተደርጓል።

8.2.2 ከአባሪ ሰ ጋር በሚስማማ መልኩ የአካባቢያዊ ሁኔታ ለውጦች ላይ ክትትል ተደርጓል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የክትትል ሪፖርቶች፣ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርቶች፤ የክትትል አሰራሮች፣ የESIA ሰነድ፣ ከESIA አካል ጋር የውል ስምምነት፣ የአስተዳደር እቅድ።

**8.3 ድርጅቱ የክትትል እና የግምገማ ውጤቶችን ይተነትናል እናም የዚህን ትንተና ውጤቶችን እንደግብዓት በእቅድ አወጣጥ ሂደት ዉስጥ ያካትታል።**

8.3.1 ከሁኔታዎች ጋር የሚስማሙ የአስተዳደር ሂደቶች ተተግብረዋል። ለነዚህም የክትትል ውጤቶች እንደግብዓት በእቅድ አወጣጥ ሂደት እና የተገኘዉ አስተዳደር ዕቅድ ዉስጥ በየጊዘው እየተሻሻሉ ተካትተዋል።

8.3.2 የክትትል ውጤቶች ከ FSC ደረጃ ጋር ካልተጣጣሙ፤ ከዚያ የአስተዳደር ዓላማዎች፣ ሊረጋገጥ የሚችሉ ዒላማዎች እና/ወይም የአስተዳደር ተግባራት ተሻሽለዋል።

***ማረጋገጫዎች፡*** የክትትል ሪፖርቶች፤ የተተነተኑ የክትትል መረጃዎች፤ የተሻሻለ (የዘመነ) የአስተዳደር ዕቅድ።

**8.4 ከሚስጢራዊ መረጃዎች ዉጪ ድርጅቱ የክትትል ውጤቶችን ማጠቃለያ በነፃ ለህዝብ ያቀርባል።**

8.4.1 የክትትል ውጤቶች ማጠቃለያ ለባለድርሻ አካላት ለመረዳት በሚያስችል መልኩ ካርታዎችን ጨምሮ እና ሚስጥራዊ መረጃዎችን ሳይጨምር ከአባሪ ሰ ጋር በሚስማማ መልኩ ያለክፍያ ለሕዝብ ይፋ ተደርጓል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የተጠቃለለ የክትትል ሪፖርት

**8.5 ድርጅቱ የFSC ማረጋገጫ የተሰጣቸው ሆነው ለገበያ የሚቀርቡትን ሁሉንም የአስተዳደር አሃድ ምርቶች ምንጭና መጠን በየዓመቱ ከሚገመተው ምርት ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ለማሳየት የአስተዳደር ተግባራትን መጠን፣ ጥንካሬና ስጋት የሚመጥን የመከታተያና የማረጋገጫ ስርዓት ይኖረዋል እንዲሁም ይተገብራል።**

8.5.1 የFSC ማረጋገጫ የተሰጣቸውን ምርቶች ሁሉ ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት ተተግብሯል ። የዚያ አካል እንደመሆኑ:

1) የዕዉቅና ሰጪው አካል በጠየቀዉ መሠረት የግብይት ማረጋገጫው በ FSC የግብይት መረጃን በማቅረብ ተደግፏል።
2) የዕዉቅና ሰጪው አካል በጠየቀዉ መሠረት የፋይበር ምርመራው ናሙናዎችን እና የቁሳቁሶችን ንዑስ ናሙናዎች እና ስለ ዝርያዎች ስብጥር ለማጣራት መረጃን በመስጠት ተደግፏል ።

8.5.2 ስለተሸጡ ምርቶች ሁሉ መረጃ ተሰብስቧል፣ተመዝግቧል፤ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

1) የተለመደ እና ሳይንሳዊ የዝርያ ስም
2) የምርት ስም ወይም መግለጫ
3) የምርት መጠን (ወይም ብዛት)
4) ቁሳቁሱን ከደን ምርት የሚሰበሰብበት ብሎክ መነሻ ምንጭ ጋር ለማመሳከረ የተወሰደ መረጃ
5) ዛፎች ተቆርጠው የተጓጓዙበት ቀን
6) መሰረታዊ የማምረት ሂድት ስራዎች በደኑ ውስጥ ተከናዉነዉ ከሆነ ቀኑን እና የተመረተዉን የምርት መጠን፣ እና
7) ቁሳቁሱ የFSC የምስክር ወረቀት ያለው ሆኖ የተሸጠ መሆን አለመሆኑ

NTFP 8.5.2 የ FSC ማረጋገጫ ከመሰጠቱ በፊት ማር (እና/ወይም ሌሎች የንብ ስብስብ ምርቶች እና ፍሳሾች በሙሉ) በ FSC ማረጋገጫ ከመሸጡ በፊት ቢያንስ 50% የሚሆነው የተሰበሰበው የአበባ ዱቄት ከ FSC ማረጋገጫ ከተሰጠው የአስተዳደር አሃድ (MU) ውስጥ የመነጨ መሆኑን ከሁሉ ተሽሎ በተገኘው መረጃ ወይም በአበባ ዱቄት ትንተና ላይ ተመስርቶ ሲረጋገጠ በFSC ይገባኛል ጥያቄ የFSC 100% ምርት ተብሎ ሊሸጥ ይችላል።

8.5.3 ከFSC የይገባኛል ጥያቄ ጋር ለተሸጡ ምርቶች ሁሉ የሽያጭ ደረሰኞች ወይም ተመሳሳይ ሰነዶች ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ይቀመጣሉ፤ የሚከተሉትን መረጃዎች በትንሹ ያካትታል፡-

1) የገዢው ስም እና አድራሻ
2) የሽያጭ ቀን፤
3) የተለመደ እና ሳይንሳዊ ዝርያ ስም
4) የምርት መግለጫ
5) የተሸጠው መጠን (ወይም ብዛት)
6) የምስክር ወረቀት ኮድ፣ እና
7) የFSC የይገባኛል ጥያቄ ‘’FSC 100%’’ ተብለዉ የተሸጡ ምርቶችን የሚለይ FSC የምስክር ወረቀት

***ማረጋገጫዎች፡-*** የማረጋገጫ አሰራር፣ የሁሉም ግብይት መረጃ (የሂሳብ ሰነዶች፣ የግዢ ትዕዛዞች፣ የማስረከቢያ ማስታወሻዎች፣ የጭነት መረጃ የያዙ ሰነዶች (waybills) ፣ ደረሰኞች)።

## መርህ-9: ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች

**ድርጅቱ በአስተዳደር አሃድ ዉስጥ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ጥንቃቄ በተሞላበት ዘዴ በመጠቀም ይጠብቃል ወይም ያሻሽላል።**

**9.1 ድርጅቱ ከተጎዱ እና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ሌሎች አማራጭ ምንጮችን በማሳተፍ የሚከተሉትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ መኖራቸውንና ሁኔታቸውን ይገመግማል እንዲሁም ይመዘግባል። የአስተዳደር ተግባራት ከሚያስከትሉት ተፅእኖዎች መጠን፣ ጥንካሬ እና ስጋት እና ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች የመከሰታቸው ዕድል ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው።**

**ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች-1 (HCV 1) - የዝርያዎች ብዝሃነት ማለት በዓለም፣ በቀጠና ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጉልህ የሆኑ የአካባቢያዊ ዝርያዎችን እንዲሁም ብርቅዬ-ብቸኛ ዝርያ፣ ብርቅዬ፣ በመጥፋት ወይም አደጋ ላይ ያሉ ዝርያዎችን ጨምሮ የሥነ-ሕይወት ብዝሃነት መከማቸት ነዉ።**

**ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች-2 (HCV 2) - የመሬት ገጽታ ደረጃ ሥርዓተ ምህዳሮች ሕብር ማለት ያልተነኩ የደን ገጽታዎች እና ትላልቅ የመሬት ገጽታ ደረጃ ሥርዓተ ምህዳሮች እና በዓለም፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጉልህ የሆኑና በተፈጥሮ የስርጭትና የብዛት ንድፍ ውስጥ የአብዛኛው በተፈጥሮ ውስጥ የሚገኙትን ሊኖሩ-የሚችሉ ዝርያዎችን/ viable population/ የሚይዙ።**

**ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች-3 (HCV 3) - ሥርዓተ ምህዳሮች እና መኖሪያ ቦታዎች ማለት ብርቅዬ፣ በመጥፋት ወይም አደጋ ላይ የወደቁ ሥርዓተ ምህዳሮች፣ መኖሪያ ቦታዎች ወይም መጠጊያዎች።**

**ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች-4 (HCV 4) - ወሳኝ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ማለት የውሃ ተፋሰሶችን መከላከል እና የተጋለጡ የአፈር እና ተዳፋትነት ያለው መሬት መሸርሸርን መቆጣጠርን ጨምሮ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ መሠረታዊ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች።**

**ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች-5 (HCV 5) - የማህበረሰብ ፍላጎቶች ማለት ከአካባቢው ማህበረሰቦች ወይም ከነባር ህዝቦች ጋር በመተባበር የተለዩትን የአካባቢው ማህበረሰቦች ወይም የነባር ህዝቦችመሠረታዊ ፍላጎቶች (ለኑሮ፣ ለጤና፣ ለምግብ፣ ለዉሃ ወዘተ) ለማሟላት ወሳኝ የሆኑ ቦታዎችና ሀብቶች።**

**ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች-6 (HCV 6) - ባህላዊ እሴቶች ማለት ለአካባቢያዊ ማህበረሰቦች ወይም ለነባር ህዝቦች ባህላዊ ባህሎች ወሳኝ ባህላዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ሃይማኖታዊ/ቅዱስ ጠቀሜታ ያላቸውን ዓለም አቀፍ ወይም ብሔራዊ ባህላዊ፣ አርኪኦሎጂያዊ ወይም ታሪካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ጣቢያዎች፣ ሀብቶች፣ መኖሪያ ቦታዎች እና የመሬት ገጽታዎች፣ ከእነዚህ አካባቢያዊ ማህበረሰቦች ወይም ከነባር ህዝቦች ጋር በመነጋገር ተለይተዋል።**

9.1.1 በመስፈርት 9.1 ላይ በተገለጸው ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ምድብ 1-6 አካባቢን እና ሁኔታን የሚይዝ ከሁሉ ተሸሎ የተገኘ መረጃን በመጠቀም ነው፤ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸው ቦታዎች የሚተማመኑባቸው እና ሁኔታቸው መሠረት ዳሰሳው ተጠናቋል።

9.1.2 ይህ ዳሰሳ እ.ኤ.አ ከጥር 1 ቀን 2017 ጀምሮ ያልተነኩ የደን ገጽታዎች መለየትን ያጠቃልላል።

9.1.3 ዳሰሳው በከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ጥበቃ ላይ ፍላጎት ካላቸው ከተጎዱት የመብት ባለቤቶች ፣ ከተጎዱት እና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በባህል ተገቢ በሆነ መልኩ የተደረገውን ተሳትፎ ውጤቶችን ተጠቅሟል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የ HCV ማዕቀፍ፣ የ HCV ግምገማ ሪፖርት፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ዘዴዎች፤ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት እና ስጋታቸውን የሚያሳይ መዝገብ፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ውጤቶች፤ HCV በግልጽ በካርታ ተቀምጧል።

**9.2 ድርጅቱ የተጎዱ ፣ ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎችን በማሳተፍ የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን የሚጠብቁ እና/ወይም የሚያሻሽሉ ውጤታማ ስልቶችን ያዘጋጃል።**

9.2.1 ከሁሉ ተሸሎ የተገኘ መረጃዎች በመጠቀም ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን አደጋ ላይ የምጥሉ ስጋቶች ተለይተዋል።

9.2.2 የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል እና ሊጎዱ የሚችሉ የአስተዳደር ተግባራትን ከመተግበር በፊት ተያያዥ የሆኑ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸውን ቦታዎች ለመጠበቅ የአስተዳደር ስልቶችና እርምጃዎች ተዘጋጅቷል።

9.2.3 የተጎዱ የመብት ባለቤቶች፣ የተጎዱና ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎች የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል የአስተዳደር ስልቶችን እና እርምጃዎችን በማዘጋጀት ላይ ተሳትፈዋል።

9.2.4 ዋና ጥብቅ ቦታዎችን ለመጠበቅ የአስተዳደር ስልቶች ተዘጋጅተዋል።

9.2.5 አብዛኛው ያልተነኩ የደን መሬት ገጽታ እንደ ዋና ጥብቅ ቦታ ተወስኗል።

9.2.6 የተቀረጹ ስልቶች ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለማቆየት እና/ወይም ለማሻሻል ውጤታማ ናቸውኑ

9.2.7 የአስተዳደር ስልቶች በዋና ጥብቅ ቦታዎች ውስጥ የሚፈቅዱት የተወሰኑ የኢንዱስትሪ ተግባራትን ነው። ፣ ይህም ሁሉም የኢንዱስትሪ ተግባራት ተፅእኖዎችና የተበታተኑ ቦታዎችን ጨምሮ፡-

1) በዋና ጥብቅ ቦታዎች በጣም ውስን በሆነ ክፍል ውስጥ የተገደቡ ሲሆኑ፤
2) ዋና ጥብቅ ቦታ* ከ50 ሺህ ሄክታር በታች መቀነስ በማይቻልበት ሲሆኑ እና
3) ግልጽ፣ ጉልህ፣ ተጨማሪ፣ የረጅም ጊዜ የጥበቃ እና ማህበራዊ ጥቅሞችን የሚያስገኝ ከሆነ ነው።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የደን አስተዳደር ዕቅድ፤ አባሪ **ቀ**-HCV ማዕቀፍ፤ የባለድርሻ አካላት የምክክር ሪፖርት፤ የ(**ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች)** HCV ክትትል መዝገቦች፤

**9.3 ድርጅቱ የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን የሚጠብቁ እና/ወይም የሚያሻሽሉ ስትራቴጂዎችን እና እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋል። እነዚህ ስትራቴጂዎችና እርምጃዎች የጥንቃቄን አቀራረብ ተግባራዊ የሚያደርጉ ከመሆኑም በላይ ከአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬና ስጋት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው።**

9.3.1 ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች እና ጥገኛ የሚሆኑባቸው ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸው አካባቢዎች የተዘጋጁትን ስትራቴጂዎች በመተግበር ጨምሮ ተጠብቀዋል እና/ወይም ተሻሽለዋል።

9.3.2 ሳይንሳዊ መረጃው ያልተሟላ ወይም አሳማኝ ባልሆነበት ጊዜም ቢሆን እና ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ተጋላጭነት እና በጣም ጥንቃቄ መፈለጉ እርግጠኛ ባልሆነበት ጊዜም ቢሆን ስልቶቹ እና እርምጃዎቹ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ጉዳቶችን ተከላክሏል እና ስጋቶች ተወግደዋል።

9.3.3 ዋና ጥብቅ ቦታዎች በመስፈርት 9-2 በሚስማማ መልኩ የተከለሉ ናቸው።

9.3.4 በዋና ጥብቅ ቦታዎች ያለው አነስተኛ የኢንዱስትሪ ተግባራት ከአመልካች 9.2.7 ጋር የሚስማማ ነው።

9.3.5 ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን የሚጎዱ ተግባራቶች ወዲያውኑ ያቆማሉ እናም ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመመለስ እና ለመጠበቅ እርምጃዎች ተወስደዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የክትትል ሪፖርቶች፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ቃለ ምልልሶች፤ የመስክ ጉብኝቶች

**9.4** **ድርጅቱ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ባሉበት ሁኔታ ላይ የተከሰቱ ለውጦችን ለመገምገም በየጊዜው ክትትል መደረጉን የሚያሳይ ሲሆን ውጤታማ ጥበቃቸውን ለማረጋገጥ የአስተዳደር ስልቶቹን ያላምዳል። ክትትሉ ከአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬ እና ስጋት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት እና ከተጎዱ ባለድርሻ አካላት፣ ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት እና ከባለሙያዎች ጋር መግባባትን ያካትታል።**

9.4.1 የወቅታዊዉ ክትትል ፕሮግራም የሚከተሉትን ይገመግማል፡-

1) የስልቶች አፈፃፀም
2) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ያሉበት ሁኔታ እና ጥገኛ የሚሆኑባቸው ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ቦታዎች ጨምሮ እና
3) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ሙሉ በሙሉ ለመጠበቅ እና/ወይም ለማጎልበት፣ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚረዱ የአስተዳደር ስልቶች እና እርምጃዎች ውጤታማነት

9.4.2 የክትትል ፕሮግራሙ የተጎዱ የሙብት ባለቤቶችን፣ የተጎዱ እና ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎችን አካትቷል።

SLIMF 9.4.2 የክትትል ፕሮግራሙ የተጎዱ እና ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎችን አካትቶ አሳትፏል።

9.4.3 ለእያንዳንዱ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ከመጀመሪያው ግምገማ እና ሁኔታ አንፃር የክትትል ፕሮግራሙ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለውጦች ለመለየት በቂ ስፋት፣ ዝርዝር እና ድግግሞሽ አለው።

9.4.4 ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል በቂ አለመሆናቸውን የሚጠቁም ክትትል ወይም ሌሎች አዳዲስ መረጃዎች ሲገኙ የአስተዳደር ስልቶች እና እርምጃዎች ተሰተካክለዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የ አስተዳደር ዕቅድ፤ የክትትል ሂደቶች; የክትትል ሪፖርቶች; የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሪፖርቶች፤ የመስክ ጉብኝቶች፣ ከባለድርሻ አካላት የተደረጉ ቃለ መጠይቆች፤ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት መዝገብ።

## መርህ-10: የአስተዳደር ተግባራት አፈጻጸም

**በድርጅቱ ወይም ለድርጅቱ አስተዳደር አሃድ የሚከናወኑ የአስተዳደር ተግባራት ከድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎችና ግቦች ጋር በሚስማማ መልኩ እንዲሁም መርሆውንና መስፈርቱን በጋራ በማክበር ይመረጣሉ እንዲሁም ይተገበራሉ።**

**10.1 ምርቱ ከተሰበሰበ በኋላ ወይም በአስተዳደር እቅድ መሰረት ድርጅቱ በተፈጥሯዊ ወይም በሰው ሰራሽ ዳግም ብቅለት ዘዴዎች የእፅዋትን ሽፋን በወቅቱ ወደ ቅድመ ምርት ወይም የበለጠ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎችን ያድሳል።**

10.1.1 ምርት የተሰበሰበባቸው ቦታዎች ዳግም ብቅለት በወቅቱ ታይተዋል፤ ይህም፡-

1) የተጎዱ የአካባቢያዊ እሴቶችን ይጠብቃል፤ እና
2) በአጠቃላይ ቅድመ መሰብሰብ ወይም የተፈጥሮ ደን ስብጥር እና አወቃቀር እንዲያገግሙ ለማድረግ አመቺ ነው፤

10.1.2 የዳግም ብቅለት ተግባራት በሚከተለው አግባብ ተተግበረዋል፡-

1) ነባር ሰው ሰራሽ ደኖችን ምርት ለመሰብሰብ፣ ምርት ከመሰብሰቡ በፊት ወደነበረው የእፅዋት ሽፋን እንደገና ለማብቀል ወይም ከሥነ ምህዳር አንፃር በደንብ የተላመዱ ዝርያዎችን በመጠቀም ይበልጥ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎችን ማከናወን፣
2) የተፈጥሮ ደኖችን ምርት ለመሰብሰብ፣ ምርት ከመሰብሰቡ በፊት ወደነበረው ዳግም ብቅለት ወይም ይበልጥ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎችን ማከናወን፣
3) የተራቆቱ የተፈጥሮ ደኖችን ምርት ለመሰብሰብ፣ ይበልጥ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች የያዘ ዳግም ብቅለት ማከናወን፣

***ማረጋገጫዎች፡-*** መልሰው የበቀሉ ቦታዎች ስፋት መዝገብ እና ጥቅም ላይ የዋለ የዛፍ ዝርያ፣ አሁናዊ የአካባቢያዊ እሴቶች፣ የመስክ ጉብኝቶች፤

**10.2 ድርጅቱ ስነ ምህዳሩን በጥሩ ሁኔታ የተላመዱና ከአስተዳደር ዓላማው ጋር የሚስማሙ የዛፍ ዝርያዎችን ለዳግም ብቀለት ተግባር ይጠቀማል፤ ድርጅቱ ሌሎችን ዝርያ ለመጠቀም ግልጽ እና አሳማኝ ማረጋገጫ ከሌለ በስተቀር የነባር ዝርያ እና የአካባቢውን ዘረመል ዓይነት ለዳግም ብቀለት ይጠቀማል።**

10.2.1 የአካባቢው ያልሆኑትን ዘረመል ዓይነት ወይም ነባር ዝርያ ያልሆኑትን ለመጠቀም ግልጽና አሳማኝ ማረጋገጫ እስካልተሰጠ ድረስ ለዳግም ብቀለት የሚመረጡ ዝርያዎች ከስነ ምህዳሩ አንጻር የተሻለ ከአካባቢው ጋር ተላምደዋል፤ ነባር ዝርያዎች እና በአካባቢው የታወቁ ናቸዉ።

10.2.2 ለዳግም ብቀለት የሚመረጡ ዝርያዎች ለዳግም ብቀለት ዓላማዎችና ከአስተዳደር ዕቅዶች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፤

***ማረጋገጫዎች፡-*** ዝርያውን ለመምረጥ መሰረታዊ ምክንያት፣ ጥቅም ላይ የዋሉ ዝርያዎች መዝገብ፣ የአስተዳደር ዕቅድና የመስክ ጉብኝቶች፣ በዕድሜ አወቃቀር የተደረገ የምርት አሰባሰብ ስርዓት መዝገብ፣ ድህረ ተካለ እንክብካቤ ስራዎች ሪፖርቶች፣ የመስክ ዳሰሳ ሪፖርቶች (በዳግም ብቀለት አቅም፣ የእጅብ ያሉ ቁጥቋጦዎች በፍጥነት ማደግ፣ የሚሰበሰበው ይዘት፣ የማበልጸግ ተከላ፣ ሲያብቡ እና የዘር ለቀማ ወቅት አያያዝ)፣ ዓመታዊ የመስክ መዝገቦች፤

**10.3 ድርጅቱ ባዕድ ዝርያዎችን የሚጠቀመው ዕውቀቱ እና/ወይም ልምዱ ማንኛውም ወራሪ ተፅዕኖ መቆጣጠር እንደሚቻል እና ውጤታማ የማጣጣሚያ እርምጃዎች መኖራቸውን ካሳየ ብቻ ነው።**

10.3.1 ባዕድ ዝርያዎችን በቀጥተኛ ልምድ እና/ወይም የሳይንሳዊ ምርምር ውጤቶች የወራሪነት ተጽዕኖውን መቆጣጠር እንደሚቻል በማሳየት ብቻ ጥቅም ላይ ዉለዋል፤

10.3.2 ባዕድ ዝርያዎች ከተመሰረቱበት አካባቢ ውጪ የመስፋፋት ሂደቱን ለመቆጣጠር ውጤታማ የማጣጣሚያ እርምጃዎች መኖራቸዉን በማሳየት ብቻ ጥቅም ላይ ዉለዋል፤

10.3.3 በድርጅቱ የተዋወቁ ወራሪ ዝርያዎች እንዳይስፋፉ ቁጥጥር ተደርጓል፤

10.3.4 በድርጅቱ ያልገቡ የወራሪነት ተጽዕኖ ያላቸውን ባዕድ ዝርያዎች ለመቆጣጠር ዓላማ ይዞ በተለይም በሚገኙበት ከተለዩ የቁጥጥር አካላት ጋር በመተባበር የአስተዳደር ተግባራት ተከናዉነዋል።

***ማረጋገጫዎች፡-*** የምርምር ሪፖርቶች፣ ከውጭ የማስመጣት ፈቃዶች፣ የእጽዋት ደህንነት ምስክር ወረቀቶች፣ የማጣጣሚያ እርምጃዎች፣ የዝርያ መዝገብ፣ ለዝርያ ምርጫው ምክንያት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ የቃለመጠይቅ፣ መስክ ጉብኝቶች፣ አስተዳደር ዕቅድ፣ የባዕድ ዝርያዎች መስፋፋት መቆጣጠሪያ የማጣጣሚያ እርምጃዎች መከናወናቸው፣ የዳሰሳ መዝገብ፣ ESIA በተመለከተ ከመንግስት አካል የተስማሚነት ደብዳቤ፣ ውጤታማ የማጣጣሚያ እርምጃዎችን ለባዕድ ዝርያዎች የሚያሳይ የህግ ሰነዶችና አደረጃጀት፣ ቁጥጥር የተደረገባቸው ቦታዎች ካርታ፣ የመስክ ምልከታና መዝገብ፣ ተደጋጋሚ የመስክ ክትትልና ማረጋገጫ ሪፖርቶች፣ የቁጥጥር ደረጃውን የሚያሳይ ካርታ፣ የተቆጣጣሪው አካል ሪፖርት፣ የጥናት ሪፖርት፣ ከተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ፤

**10.4 *ድርጅቱ* በዘረመል የተሻሻሉ ተህዋሳትን በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ አይጠቀምም፤**

10.4.1 በዘረመል የተሻሻሉ ተህዋሳት ጥቅም ላይ አልዋሉም

***ማረጋገጫዎች***፡- ጥቅም ላይ የዋሉ ዝርያዎች መዝገብ፣ የአስተዳደር ዕቅድ

**10.5 *ድርጅቱ* ለእፅዋቱ፣ ለዝርያው፣ ለቦታው እና *ለአስተዳደሩ ዓላማዎች* ከስነ ምህዳራዊ አንጻር ተገቢ የሆነ ድህረ ተከላ እንክብካቤ ወይም የደን ልማት ተግባራት/Silvicultural practices/ ልምዶችን ይጠቀማል፤**

10.5.1 ከስነ ምህዳሩ አንጻር ተገቢ የሆነ ለእፅዋቱ፣ ለዝርያው፣ ለቦታው እና ለአስተዳደሩ ዓላማዎች የድህረ ተከላ እንክብካቤ ወይም የደን ልማት ተግባራት /Silvicultural practices/ ልምዶች ተተግብረዋል፤

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአስተዳደር ዕቅድ፣ የመስክ ጉብኝቶች፣ የዕድሜ አወቃቀርን መሰረት ያደረገ የማሳሳት ተግባር መዝገብ፣ ምርት የመሰብሰቢያ ጊዜ እና ዘዴዎችን የሚያሳዩ ሪፖርቶች፤

**10.6 ድርጅቱ የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትንሹ ይጠቀማል ወይም ሙሉ በሙሉ ያስወግዳል። ማዳበሪያዎችን በሚጠቀምበት ጊዜ ድርጅቱ ማዳበሪያዎችን የማይጠይቁ የደን ልማት ተግባራት/Silvicultural practices/ ከመጠቀም ጋር እኩል ወይም የበለጠ ሥነ-ምህዳራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳለው እና የአፈርን ጨምሮ ለአካባቢያዊ እሴቶች የሚደርሰውን ጉዳት እንደሚከላከል ፣ እንደሚቀንስ እና / ወይም እንደሚጠግን ያሳያል።**

10.6.1 ማዳበሪያዎችን መጠቀም ቀንሷል ወይም ተወግዷል፤

10.6.2 ማዳበሪያዎችን በሚጠቀምበት ጊዜ የስነ-ምህዳራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ማዳበሪያዎችን የማይጠይቁ የደን ልማት ስርዓቶችን /Silvicultural system/ ከመጠቀም ጋር እኩል ነዉ ወይም ይበልጣል፤

10.6.3 ማዳበሪያዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ ዓይነታቸው፣ መጠናቸው፣ ድግግሞሻቸው እና የመተግበሪያ ቦታ ተሰንዷል፤

10.6.4 ማዳበሪያዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ ጉዳትን ለመቀነስ የሚተገበሩ እርምጃዎችን ጨምሮ፣ አካባቢያዊ እሴቶች ተጠብቀዋል፤

10.6.5 ማዳበሪያ በመጠቀም የሚመጡ የአካባቢያዊ እሴቶች ጉዳት ቀንሷል ወይም ተስተካክሏል፤

***ማረጋገጫዎች፡-*** ማዳበሪያ ለመጠቀም በቂ ምክንያት፣ የአስተዳደር ዕቅድ፣ የማዳበሪያ አጠቃቀምና ድግግሞሽ መዝገብ፣ አሉታዊ ተጽዕኖዎችና የተወሰዱ የማጣጣሚያ እርምጃዎች መዝገብ፣

**10.7 ድርጅቱ የኬሚካል ፀረ-ተባይ መድሃኒቶችን መጠቀምን የሚያስቀሩ ወይም ለማስወገድ ያለሙ የተቀናጁ የፀረ ተባይ እና የደን ልማት ስርዓቶችን /silviculture system/ ይጠቀማል። ድርጅቱ በ FSC ፖሊሲ የተከለከሉ ኬሚካላዊ ፀረ ተባይ መድኃኒቶችን አይጠቀምም። ፀረ ተባይ መድኃኒቶች ጥቅም ላይ ሲውሉ ግን ድርጅቱ በአካባቢያዊ እሴቶች እና በሰው ጤና ላይ የሚደርሰውን ጉዳት መከላከል፣ መቀነስ እና/ወይም ማደስ ይኖርበታል።**

10.7.1 የተቀናጀ የፀረ ተባይ አያያዝ፣ የደን ልማት ስርዓቶችን (silviculture systems) መረጣን ጨምሮ ጥቅም ላይ ዉሏል፤ የኬሚካል ፀረ-ተባይ አጠቃቀም ድግግሞሽ፣ ስፋት እና መጠን ለማስወገድ ወይም ለማጥፋት ታልሞ እና አለመጠቀምን ወይም አጠቃላይ ቅነሳን እንደ ግብ በማድረግ ተፈጽሟል።

NTFP 10.7.1.1.የንብ በሽታ ለመከላከል ቀፎዎች በአካላዊ መንገድ ለምሳሌ በእንፋሎት ወይም በእሳት አማካኝነት ታክሟል።

NTFP 10.7.1.2 ሸረሪትን ( varroa mites) ለመከላከል የሚከተሉት ንጥረ ነገሮች ጥቅም ላይ ዉለዋል።

1) ፎርሚክ አሲድ (formic acid), ላክቲክ አሲድ (lactic acid), አሴቲክ አሲድ (acetic acid) እና ኦክሳሊክ አሲድ (oxalic acid);
2) ሜንቶል (menthol), ኢውካሊፕቶል (eucalyptol) እና ካምፎር (camphor).

10.7.2 ኬሚካላዊ ፀረ-ተባይ መድሃኒቶችን ከመጠቀማቸው በፊት ድርጅቶች ማሟላት ያለባቸዉ የአካባቢያዊ እና ማህበራዊ አደጋ ግምገማ ማዕቀፍ (FSC-POL-30-001 V3-0 FSC ፀረ-ተባይ ፖሊሲ አንቀጽ 4.12) ተሟልቷል፡፡

10.7.3 የተጎዱ የመብት ባለቤቶች እና ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት በአካባቢያዊ እና ማህበራዊ አደጋ ግምገማ ልማት ውስጥ ተስማሚ በሆነ በባህላዊ መንገድ እንዲሳተፉ እድል ተሰጥቷቸዋል።

10.7.4 የአካባቢና ማህበራዊ ስጋት ዳሰሳ ተገምግሟል እና አስፈላጊ ሲሆን በምስክር ወረቀቱ ዑደት ውስጥ ተሻሽሏል፤

10.7.5 ተባይ፤ አረም ወይም በሽታን ለመቆጣጠር የሚስችል አማራጮችን ለመተግበር የተወሰደ የመወሰኛ ሂደት እና አመክንዮ አለ፤ ይህም አነስተኛውን ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ጉዳት፣ የበለጠ ውጤታማነት እና እኩል ወይም የበለጠ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ጥቅሞችን ያሳያል፡፡

10.7.6 የፀረ ተባይ መድሃኒት አጠቃቀም መዝገቦች ተጠብቀዋል ፣ የንግድ ስምን ጨምሮ ፣ ንቁ ንጥረ ነገር ፣ ጥቅም ላይ የዋለው ንቁ ንጥረ ነገር መጠን ፣ የአጠቃቀም ጊዜ ፣ የመተግበሪያዎች ብዛት እና ድግግሞሽ ፣ የአጠቃቀም ቦታ እና አካባቢ እና የአጠቃቀም ምክንያት ተመዝግበዋል፡፡

10.7.7 የፀረ ተባይ መድሃኒቶች አጠቃቀምን በተመለከተ ለማጓጓዝ ፣ ለማከማቸት ፣ ለማስተናገድ በአደጋ ጊዜ የአሠራር መስፈርቶችን ለመተግበር የ ILO ሰነድ ኬሚካሎችን በሥራ ላይ መጠቀምን በተመለከተ አክብሯል፡፡

10.7.8 ፀረ-ተባይ መድኃኒቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ የአጠቃቀም ዘዴዎች መጠኑን በቀነሰ መልኩ ውጤትን ለማምጣት ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው እንዲሁም በአከባቢው ያሉትን የመሬት ገጽታዎች ውጤታማ ጥበቃ አድርገዋል፡፡

10.7.9 በፀረ ተባይ መድኃኒቶች አጠቃቀም ምክንያት በአካባቢያዊ እሴቶች እና በሰው ጤና ላይ ጉዳት ሲደርስ የመከላከል እና የመቀነስ ወይም ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ የመከላከል ስራ ተሰርቷል፡፡

10.7.10 የጸረ-ተባይ መድሃኒቶች ጥቅም ላይ ሲውሉ፡-

1) የተመረጠው ፀረ-ተባይ የአተገባበር ዘዴ፣ ጊዜ እና የአጠቃቀም ንድፍ ለሰዎች እና ዒላማ ላልሆኑ ዝርያዎች አነስተኛውን ስጋት ያቀርባል፤እና
2) ተጨባጭ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት ፀረ-ተባይ መድሃኒቱ ተባዩን ለመቆጣጠር ውጤታማ፣ ተግባራዊ እና ወጪ ቆጣቢው ብቸኛው መንገድ ነው።

***ማረጋገጫዎች፡-*** ጥቅም ላይ የዋሉ የተቀናጁ የፀረ-ተባይ መከላከያ ስርዓቶች፤ ጥቅም ላይ የዋሉ የኬሚካል ፀረ-ተባይ መድሃኒቶች ንቁ ንጥረ ነገሮች ዓይነቶች፤ የፀረ-ተባይ መድሃኒቶች አጠቃቀም መዝገቦች፤ የቦታ ጉብኝቶች፣ ከሠራተኞች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች፤ ጥቅም ላይ የዋሉ የደህንነት ዘዴዎች፤ የፀረ-ተባይ መድሃኒቶች፣ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የተወሰዱ እርምጃዎች፤ የኬሚካል አጠቃቀም ሂደቶች፤ የኬሚካል አጠቃቀም መዝገቦች፤ የፀረ-ተባይ መድሃኒት የመምረጥን ሚያሳይ ምክንያት።

**10.8 ድርጅቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን ሳይንሳዊ ፕሮቶኮሎች በመከተል የባዮሎጂካል መቆጣጠሪያ ንጥረነገሮችን አጠቃቀም ወደ ዝቅተኛ መጠን እንዲቀንስ ማድረግ ፣ መከታተል እና በጥብቅ መቆጣጠርን ያከናውናል። የባዮሎጂያዊ የቁጥጥር ዘዴዎችን ጥቅም ላይ ሲውሉ ድርጅቱ የአካባቢ እሴቶችን ጉዳት መከላከል፣ መቀነስ እና/ወይም ማደስ አለበት፡፡**

10.8.1 የባዮሎጂካል መቆጣጠሪያ ንጥረነገሮች አጠቃቀም ቅነሳ፣ ክትትል እና ቁጥጥር ተደርጎበታል

10.8.2 የባዮሎጂካል መቆጣጠሪያ ወኪሎች አጠቃቀም የቢዮሎጂካል ብዝሃነት ስምምነትን (CBD) እና ተጓዳኝ ሳይንሳዊ ፕሮቶኮሎችን ያከብራል

10.8.3 የባዮሎጂካል መቆጣጠሪያ ንጥረነገሮች አጠቃቀም ዓይነት፣ ብዛት፣ ጊዜ፣ ቦታ እና የአጠቃቀም ምክንያት ጨምሮ ተመዝግበዋል።

10.8.4 በባዮሎጂካል መቆጣጠሪያ ንጥረ ነገሮች አጠቃቀም ምክንያት በአካባቢ እሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በመከላከል እና በመቀነስ ወይም ጉዳቱ በተከሰተበት ቦታ እርምጃ ተወስዷል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-***_የቦታ ጉብኝት፣ የአስተዳደር ዕቅድ፣ ከሰራተኞች ጋር የተደረጉ ቃለ ምልልሶች፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ቃለ ምልልሶች፣ የአጠቃቀም መዝገቦች፣ የመከላከያ እና የማጣጣሚያ እርምጃዎች፣ የአደጋ ግምገማ ሪፖርቶች፣ መደበኛ የክትትል ሪፖርት

**10.9 ድርጅቱ አደጋዎችን ይገመግማል እንዲሁም ከተፈጥሮ አደጋዎች (*Natural Hazards*) ሊመጡ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የሚረዱ ተግባራትን በመጠን፣ በጥንካሬ እና በስጋት ላይ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ይተገብራል።**

10.9.1 በአስተዳደር አሃዱ ዉስጥ በመሠረተ ልማት፣ በደን ሀብቶችና በማኅበረሰቦች ላይ አደጋ ሊያስከቱትሉ የሚችሉ የተፈጥሮ አደጋዎች አሉታዊ ተፅዕኖዎች ተገምግመዋል

10.9.2 የአስተዳደር ተግባራት እነዚህን ተጽዕኖዎች ይቀንሳሉ፤

SLIMF 10.9.2 አቅም እና ሀብት በሚፈቅዱበት ጊዜ የአስተዳደር ተግባራት የተፈጥሮ አደጋዎች ሊሆኑ የሚችሉ ተቀባይነት የሌላቸውን አሉታዊ ተፅእኖዎች ይቀንሳሉ። አቅም ወይም ሀብት የማይፈቅድ ከሆነ ድርጅቱ ወይም ሥራ አስኪያጁ ከመንግስት ወይም አግባብነት ካላቸው የአካባቢ ድርጅቶች ጋር ስለ ቅነሳ አቅም እና አማራጮች ይነጋገራሉ።

10.9.3 የአስተዳደር ተግባራት የተፈጥሮ አደጋዎችን ድግግሞሽ፣ ስርጭት ወይም ክብደት እንዲጨምሩ የሚያደርጉት አደጋ በአስተዳደር ሊነኩ የሚችሉትን አደጋዎች በተመለከተ ተለይቷል፤

10.9.4 የአስተዳደር ተግባራት ተለውጠዋል እና/ወይም የተለዩትን አደጋዎች የሚቀንሱ እርምጃዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ተደርገዋል፤

***ማረጋገጫዎች፡-*** የተፈጥሮ አደጋዎች ግምገማ ሪፖርቶች; የአስተዳደር ዕቅድ; የተፈጥሮ አደጋዎች ክስተት መዝገብ; ከሠራተኞች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች; አደጋን ለመቀነስ የሚረዱ እርምጃዎች; አስተዳዳሪዎች ከመንግስት ወይም ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ጋር የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመቀነስ የግንኙነት መዝገቦች፡፡

**10.10 ድርጅቱ የመሠረተ ልማት፣ የትራንስፖርት ተግባራት እና የደን ልማት ስራዎችን ያስተዳድራል፤ በዚህም የውሃ እና አፈር ሀብቶች ተጠብቀዋል፣ እንዲሁም ለዝቅተኛ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች፣ መኖሪያዎች፣ ስርአተ-ምህዳሮች እና የመሬት ገጽታ እሴቶች ላይ የሚደርስ ጉዳት ተከላክሏልል፣ ቀንሷል እና/ወይም ተጠግኗል።**

10.10.1 የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ ጥገናና አጠቃቀም እንዲሁም የትራንስፖርት ተግባራት በ6.1 መስፈርት ውስጥ የተገለጹትን የአካባቢ እሴቶች ለማስጠበቅ ተተግብረዋል።

10.10.2 የደን ልማት ተግባራት በ6.1 መስፈርት ውስጥ የተለዩትን የአካባቢ እሴቶች ጥበቃን ለማረጋገጥ ተከናዉነዋል፤

10.10.3 የውሃ መስመሮች፣ የውሃ አካላት፣ አፈር፣ ብርቅዬና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች፣ የመኖሪያ አካባቢዎች፣ ሥነ ምህዳሮችና የመሬት ገጽታ እሴቶች ላይ የሚደርሰውን መረበሽ ወይም ጉዳት በወቅቱ የመከላከል፣ መቀነስ እና መጠገን እርምጃዎች ተተግብረዋል እንዲሁም ተጨማሪ ጉዳትን ለመከላከል የአስተዳደር ተግባራት ተሻሽለዋል፤

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአስተዳደር ዕቅድ፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ልማት እና ጥገና አሰራሮች፣የደን ልማት አያያዝ ደንብ፣ ከመሠረተ ልማት ገንቢዎች ጋር የውል ስምምነት፣ የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ሪፖርት፤

**10.11 ድርጅቱ የአካባቢ ጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ ፣ የሚሸጡ ተረፈ ምርቶችን ለመቀነስ እና በሌሎች ምርቶች እና አገልግሎቶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የእንጨት እና እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶችን ከመሰብሰብ እና ከማውጣት ጋር የተያያዙ ተግባራትን ያስተዳድራል።**

10.11.1 የእንጨት እና እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶችን የመሰብሰብ እና የማውጣት ልምዶች በመስፈርት 6.1 እና በመስፈርት 9.1 እና 9.2 የተገለጹትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች በሚጠብቅ መልኩ ተከናዉነዋል።

10.11.2 የምርት የመሰብሰብ አሠራሮች፣ የደን ምርቶችን እና የሚሸጡ ቁሳቁሶችን አጠቃቀምን ያሻሽላሉ

10.11.3 በቂ መጠን ያለው የሞተ እና የሚበሰብስ ባዮማስ (biomass) እና የደን አወቃቀር የአካባቢያዊ እሴቶችን ለመጠበቅ ተቀምጠዋል፤

10.11.4 የመሰብሰብ ተግባራት ሳይቆረጡ የቀሩ ዛፎች ላይ፣ በመሬት ላይ ያሉ እንጨት ነክ ብስባሽ እና ሌሎች የአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ያስቀራል፣

***ማረጋገጫዎች፡-*** የአስተዳደር ዕቅድ፣ የአሰባሰብ ሂደቶች፣ መስክ ጉብኝቶች፣ ከሰራተኞች ጋር ቃለመጠይቅ፣ የመሰብሰቢያ መዝገብ፣ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (EIA) ሪፖርት፤

**10.12 ድርጅቱ ቆሻሻን ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ ያስወግዳል**

10.12.1 በመስፈርት 6.1 የተመለከተውን የአካባቢ እሴቶችን ለመጠበቅ ሁሉንም ቆሻሻዎች መሰብሰብ፣ ማጽዳት፣ ማጓጓዝ እና አወጋገድ ለአከባቢዉ ተስማሚም በሆን መልኩ ተደርጓል፡፡

***ማረጋገጫዎች፡-*** የቆሻሻ አሰባሰብ መዝገቦች፤ የቆሻሻ አያያዝ አሰራር፤ የቦታ ጉብኝት፤ ከሰራተኞችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ቃለ ምልልሶች

# ፈ. አባሪዎች

(መደበኛ ክፍል )

## አባሪ ሀ. ቢያንስ የሚመለከታቸውን ህጎች፣ ደንቦች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የየጸደቁ ዓለም አቀፍ ኮንቨንሽን እና ስምምነቶችን የያዘ ዝርዝር (መርህ 1.)

**የሚከተለው በFSC-STD-60-004 (አለምአቀፍ አጠቃላይ አመላካቾች) ውስጥ ቢያንስ የሚመለከታቸውን ህጎች፣ ደንቦች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የየጸደቁ ዓለም አቀፍ ኮንቨንሽን፣ ስምምነቶችን የያዘ ዝርዝር ነው፡፡**

**ማስታዎሻ፡-** ይህ የህግ ድንጋጌ የተሟላ ዝርዝር ሆኖ የቀረበ አይደለም፡፡ ማንኛውም ተጨማሪ ህግ ተፈጻሚ ከሆነ፣ የምስክር ወረቀቱ የተሰጣቸው ድርጅቶች (Certificate Holders-CHs) እንዲሁ ማክበር አለባቸው፡፡

### 1. ምርትን ለማምረት ህጋዊ መብቶች

| | |
|---|---|
| 1.1 የመሬት ይዞታ እና አስተዳደር መብቶች | ○ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት 1994 ዓ.ም. ፡፡<br>○ አዋጅ ቁ. 1223/2020 የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት፤አስተዳደር እና አጠቃቀም፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር 85/2010 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳትን ልማት ጥበቃና አጠቃቀምን ስለማቅረብ አዋጅ፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም፡፡<br>○ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135.12007 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለንብረት ማካካሻ ክፍያ ደንብ ለሕዝብ ዓላማዎች በተዘረጉ የመሬት ይዞታዎች ላይ የሚገኝ፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር. 197/2000 የኢትዮጵያ የውሃ ሃብት አስተዳደር አዋጅ፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር 1161/2019 ለሕዝብ ዓላማ ሲባል የመሬት ይዞታዎችን መውረስ፣ የካሳ ክፍያ እና መልሶ ማቋቋምን መወሰን፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር 240/2021፡፡<br>○ ደንብ ቁጥር 10/2021 የኦሮሚያ ክልል የጉምሩክ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ ደንብ፡፡<br>○ አዋጅ ቁ. 89/1199 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር 769/2012 የኢንቨስትመንት አዋጅ፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር 839/2004 የባህል ቅርሶችን ለሀገር አቀፍ እና ክልላዊ የባህል ቅርሶች ስለ ክፍፍል ስለማቅረብ፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር 575/2008 የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ምስረታ አዋጅ፡፡<br>○ የ1980 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 192 የደን እና የዱር እንስሳትን ጥበቃና ልማት አዋጅ፡፡<br>○ አዋጅ ቁጥር 66/2000 ታህሣሥ 24/2007 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ፡፡ |

| | |
|---|---|
| | ○ አዋጅ ቁጥር 1236/2021 የተሻሻለው የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ።<br>○ ደንብ ቁጥር 151/2012 የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም።<br>○ ደንብ አዋጅ ቁጥር 133/2006 የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጣ አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 147/2010 የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም።<br>○ አዋጅ ቁጥር 456/2005 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም።<br>○ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም።<br>○ አዋጅ ቁ. 545/2007 ሙስናን በመከላከል እና በመዋጋት ላይ የአፍሪካ ህብረትን ስምምነትን ማፅደቂያ አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 8911997 የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ። |
| **1.2 የኮንሴሽን ፍቃዶች** | ○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም።<br>○ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳትን ልማት ጥበቃና አጠቃቀምን ስለማቅረብ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 8911997 የገጠር መሬት አስተዳደር።<br>○ አዋጅ ቁጥር 456/2005 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ። |
| **1.3 የአያያዝና የምርት መሰብሰብ እቅድ** | ○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም።<br>○ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 8911997 የገጠር መሬት አስተዳደር።<br>○ አዋጅ ቁጥር 456/2005 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ። |
| **1.4 ምርትን የመሰብሰብ ፍቃድ** | ○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም።<br>○ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም። |
| **2. ግብር እና ክፍያዎች** | |
| **2.1 የሮያሊቲ እና ምርት የመሰብሰቢያ ክፍያዎች** | ○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፡፡ |
| **2.2 የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሌሎች የሽያጭ ግብሮች** | ○ አዋጅ ቁ. 1180/2020 የኢንቨስትመንት አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 የሠራተኛ አዋጅ። |
| **2.3 የገቢ እና የትርፍ ግብሮች** | ○ አዋጅ ቁ. 1180/2020 የኢንቨስትመንት አዋጅ ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 የሠራተኛ አዋጅ ። |

| 3. የእንጨት ምርት መሰብሰብ ተግባራት | |
|---|---|
| 3.1 የእንጨት ምርት መሰብሰብ ደንቦች | ○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም |
| 3.2 ጥብቅ ቦታዎች እና ዝርያዎች | ○ አዋጅ ቁጥር 993/2017 የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ የፓሪስ ስምምነትን ለማጽደቅ አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 634/2009 በዱር እንስሳት ፍልሰት ላይ ያለውን ስምምነት ለማጽደቅ አዋጅ። |
| 3.3 አካባቢያዊ መስፈርቶች | ○ አዋጅ ቁጥር 482/2006 የጄኔቲክ ሀብቶችን፤ የማህበረሰቡን እውቀት እና የማህበረሰቡን መብት ተደራሽነት ለማቅረብ የወጣ አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 575/2008 የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ምስረታ አዋጅ።<br>○ ለደን እና የዱር እንስሳት ጥበቃ እና ልማት ለማቅረብ የወጣው አዋጅ ቁጥር 192 የ1980 ዓ.ም. ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ።<br>○ አዋጅ ቁ. 197/2000 የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር።<br>○ አዋጅ ቁጥር 1090/2018 አደገኛ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ቁጥጥር የወጣ አዋጅ፤<br>○ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 327/2014 የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ አካባቢ እና የደን ምርምር ተቋም ማቋቋሚያ ደንብ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 300/2002 የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር።<br>○ አዋጅ ቁጥር 674/2010 ፀረ ተባይ ምዝገባ እና ቁጥጥር የወጣ አዋጅ፤<br>○ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጨረር መከላከያ አዋጅ ቁጥር 79/1993፤<br>○ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ 299/2002፤<br>○ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ ፖሊሲ፣1997 ዓ.ም።<br>○ አዋጅ ቁጥር 29912002 የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ። |
| 3.4 ጤና እና ደህንነት | ○ አዋጅ ቁጥር 690/2010 የማህበራዊ ጤና ኢንሹራንስ አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 200/2000 የምግብ ጥራት ደረጃዎች ቁጥጥር።<br>○ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 ሰራተኛ አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 377/2003 ሠራተኛ አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 513/2007 ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 661/2009 የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር።<br>○ የህዝብ ጤና አዋጅ ቁጥር 200/2000። |
| 3.5 ሕጋዊ የሥራ ቅጥር | ○ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 ሰራተኛ አዋጅ።<br>○ አዋጅ ቁጥር 377/2003 ሠራተኛ አዋጅ።<br>○ ዋጅ ቁጥር 1237/2021 የግሌግሌ ዲኝነት እና የዕርቅ አሠራር ሥርዓት አዋጅ። |

- አዋጅ ቁጥር 515/2006 የፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ።
- አዋጅ ቁጥር 1113/2019 የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች አዋጅ።
- አዋጅ ቁጥር 715/2011 የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ።
- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587-2008

## 4 የሶስተኛ ወገን መብቶች

### 4.1 የተለመዱ መብቶች

- የኢትዮጵያ ክልል ባሕላዊ ሕጎች እና ፍርድ ቤቶች።
- አዋጅ ቁጥር 85/2010 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ።
- የኦሮሚያ ክልል ባሕላዊ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ ደንብ አዋጅ ቁጥር 240/2021፣ ደንብ ቁጥር 10/2021።
- አዋጅ ቁጥር 66/2000 ታህሣሥ 24/2007 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ።
- የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2012።
- አዋጅ ቁጥር 133/2006 የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጣ አዋጅ።
- አዋጅ ቁጥር 147/2011 የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ።

### 4.2 ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት

- የኢትዮጵያ ክልል ባሕላዊ ሕጎች እና ፍርድ ቤቶች።
- አዋጅ ቁጥር 85/2010 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ።
- የኦሮሚያ ክልል ባሕላዊ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ ደንብ አዋጅ ቁጥር 240/2021፣ ደንብ ቁጥር 10/2021።
- አዋጅ ቁጥር 66/2000 ታህሣሥ 24/2007 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ።
- የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2012።
- አዋጅ ቁጥር 133/2006 የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጣ አዋጅ።
- አዋጅ ቁጥር 147/2011 የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ።
- አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ።

### 4.3 የነባር ሕዝቦች መብቶች

- የኢትዮጵያ ክልል ባሕላዊ ሕጎች እና ፍርድ ቤቶች፣
- አዋጅ ቁጥር 85/2010 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ፤
- የኦሮሚያ ክልል ባሕላዊ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ ደንብ አዋጅ ቁጥር 240/2021፣ ደንብ ቁጥር 10/2021፤
- አዋጅ ቁጥር 66/2000 ታህሣሥ 24/2007 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ፤

| | |
|---|---|
| | ○ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2012፤<br>○ አዋጅ ቁጥር 133/2006 የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጣ አዋጅ፤<br>○ አዋጅ ቁጥር 147/2011 የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤<br>○ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤<br>○ አዋጅ ቁጥር 482/2006 የጄኔቲክ ሀብቶችን፣ የማህበረሰቡን እውቀት እና የማህበረሰቡን መብት ተደራሽነት ለማቅረብ አዋጅ። |
| **5. ንግድ እና ትራንስፖርት**<br><br>**ማስታዎሻ፡-** ይህ ክፍል ለደን አስተዳደር ስራዎች እንዲሁም ለምርት ማምረት ሂደት እና ለንግድ ስራ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ይሸፍናል። | |
| **5.1 የዝርያዎች፣ መጠኖች እና ጥራቶች ምደባ** | ○ አዋጅ ቁጥር 769/2012 የኢንቨስትመንት አዋጅ፤<br>○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም። |
| **5.2 ንግድ እና ትራንስፖርት** | ○ አዋጅ ቁጥር 769/2012 የኢንቨስትመንት አዋጅ፤<br>○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም፤<br>○ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587-2008። |
| **5.3 የባህር ዳርቻ ንግድ እና የዝውውር ዋጋ** | ○ አዋጅ ቁጥር 1236/2021 የተሻሻለው የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ፤<br>○ አዋጅ ቁጥር 545/2007 ሙስናን በመከላከል እና በመዋጋት ላይ የአፍሪካ ህብረትን ስምምነትን ማፅደቂያ አዋጅ |
| **5.4 የጉምሩክ ደንቦች** | ○ የኢትዮጵያ ጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859-2014፤<br>○ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587-2008። |
| **5.5 በመጥፋት አደጋ ላይ የሚገኙ ዝርያዎች ዓለም አቀፍ ንግድ ስምምነት(CITES)** | ○ አዋጅ ቁጥር 575/2008 የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ምስረታ አዋጅ፤<br>○ የ1980 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 192 የደን እና የዱር እንስሳትን ጥበቃና ልማት አዋጅ፤<br>○ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ። |
| **6. ተገቢ ጥንቃቄ /ተገቢ እንክብካቤ** | |
| **6.1 ተገቢ ጥንቃቄ / ተገቢ እንክብካቤ አሰራሮች** | ○ የኢትዮጵያ ጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859-2014፤<br>○ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587-2008፤ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤<br>○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ ። |

## 7. የስርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች

- ○ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ፤
- ○ አዋጅ ቁጥር. 197/2000 የኢትዮጵያ የውሃ ሃብት አስተዳደር አዋጅ፤
- ○ የ1980 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 192 የደን እና የዱር እንስሳትን ጥበቃና ልማት አዋጅ፤
- ○ አዋጅ ቁጥር 300/2002 የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ዋጅ፤
- ○ አዋጅ ቁጥር 513/2007 ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ፤
- ○ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ።

## አባሪ ለ. ለሠራተኞች የሚያስፈልጉ ሥልጠናዎች (መርህ 2)

ሠራተኞቹ የሚከተሉትን ማድረግ እንዲችሉ:-

1) የሚመለከታቸው የሕግ መስፈርቶችን ባሟላ መልኩ የደን ተግባራትን ማከናወን (መስፈርት 1.5)፤
2) ስምንቱን ዓለም አቀፍ የሰራተኞች ድርጅት (ILO) ዋና የስራ ስምምነቶችን ይዘት፣ ትርጉም እና ተፈጻሚነት መረዳት (መስፈርት 2.1)፤
3) የፆታዊ ትንኮሳ እና የፆታ መድልዎ ሁኔታዎችን ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ (መስፈርት 2.2)፤
4) አጠቃቀሙ ለጤንነት ስጋት እንዳይፈጥር ለማረጋገጥ አደገኛ ንጥረ ነገሮችን በአስተማማኝ ሁኔታ መያዝ እና ማስወገድ* (መስፈርት 2.3)፤
5) በተለይም አደገኛ ለሆኑ ወይም ልዩ ኃላፊነት ለሚጠይቁ ሥራዎች ኃላፊነትን መወጣት (መስፈርት 2.5)፤
6) የነባር ህዝቦች ከደን አስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ ሕጋዊና ልማዳዊ መብቶች ያሉባቸውን ቦታዎች መለየት (መስፈርት 3.2)፤
7) የUNDRIP እና ILO ኮንቬንሽን 169 የሚመለከታቸው ነገሮች መለየት እና መተግበር (መስፈርት 3.4)፤
8) ለነባር ህዝቦች ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች መለየት እና አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለማስወገድ የደን አስተዳደር ተግባራት ከመጀመራቸው በፊት እነሱን ለመጠበቅ አስፈላጊውን እርምጃ መተግበር (መስፈርት 3.5 እና መስፈርት 4.7)፤
9) የአካባቢ ማህበረሰቦች ከደን አስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶቻቸውን መለየት (መስፈርት 4.2)፤
10) የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማዎችን ማካሄድ እና ተገቢውን የመከላከል እርምጃዎችን ማዘጋጀት (መስፈርት 4.5)
11) የFSC ሥርዓረ-ምህዳር አገልግሎቶች የይገባኛል ጥያቄዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ ከሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ጥገና እና/ወይም ማሻሻል ጋር የተያያዙ ተግባራትን ማከናወን (መስፈርት 5.1)፤
12) የፀረ ተባይ መድኃኒቶችን አያያዝ፣ አጠቃቀም እና ማከማቸት (መስፈርት 10.7)፤
13) የቆሻሻ ፍሳሾችን ለማጽዳት የሚያስችሉ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ (መስፈርት 10.12)፤

## አባሪ ሐ.  የጥበቃ ቦታ መረብ (Conservation Area Network) ጽንሰ-ሀሳባዊ ንድፍ (መርህ6)




ሥዕላዊ መግለጫው በአካባቢ ጥበቃ ቦታ መረብ ውስጥ የተካተተው ለደን አስተዳደር የተለየ ቦታ በአጠቃላይ ከ 10% ዝቅተኛው መጠን ጀምሮ በመጠን ፣ የአስተዳደር ጥንካሬ እና/ወይም በመሬት ገጽታ ደረጃ የሥርዓተ ምህዳሮች ሁኔታ እና እሴት በእያንዳንዱ ጭማሪ እንደሚጨምር ያሳያል። ቀስቶቹና አቅጣጫቸው እነዚህን እድገቶች ይወክላሉ።

በስተቀኝ በኩል ያለው "የሥርዓተ-ምህዳሮች ያሉበት ሁኔታ/በመሬት ገጽታ ውስጥ ያለው እሴት" የተሰኘው አምድ ነባር ሥርዓተ-ምህዳሮች በመሬት ገጽታ ደረጃ የተጠበቁበትን ሁኔታ እና ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ ለተጨማሪ ጥበቃ የሚያስፈልጉትን ተዛማጅ መስፈርቶች ያሳያል።

ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ መጠን የተሰኘው የግራው በኩል ያለው አምድ እንደሚያሳየው ለደን አስተዳደር የተለየው ቦታ ስፋት እየጨመረ ሲሄድ ለደን አስተዳደር የተለየው ቦታ ራሱ በመሬት ገጽታ ደረጃ ላይ እንደሚሆን እና ስለሆነም በዚያ መሬት ገጽታ ውስጥ በተፈጥሮ የሚከሰቱትን ሁሉም ሥርዓተ- ምህዳሮች ተግባራዊ ምሳሌዎችን የያዘ የጥበቃ አካባቢ መረብ እንደሚኖር ይጠበቃል።

# አባሪ መ. በአገሪቱ ወይም በክልሎች ውስጥ የሚገኙ ብርቅዬ እና ለመጥፋት በአስጊ ሁኔታ ላይ ያሉ ዝርያዎች ዝርዝር (መርህ 6)

| ዕፅዋት |
|---|

- *Hagenia abyssinica* - African Redwood, ኮሶ
- *Juniperus procera* - African Pencil Cedar, ፅድ
- *Acacia bricchettiana*, **የግራር ዘር**
- *Acacia prasinata*, **የግራር ዘር**
- *Podocarpus falcatus* , *ዝግባ*
- *Taverniera abyssinica*
- *Cordeauxia edulis*

| አጥቢዎች |
|---|

- *Capra walie* - Walia Ibex, ዋሊያ አይቤክስ
- *Tragelaphus buxtoni* - Mountain Nyala, የተራራ ኒያላ/የደጋ አጋዘን
- *Tragelaphus scriptus* - meneliki Menelik's bushbuck, የምኒሊክ ቡሽባክ
- *Alcelaphus buselaphus swaynei* - Swayne's Hartebeest, ቆርኪ
- *Canis simensis* - Ethiopian Wolf, የኢትዮጵያ ተኩላ/የዱር ውሻ
- *Chlorocebus djamdjamensis* - Bale monkey, የባሌ ጦጣ
- *Cercopithecus mitis boutourlinii* - Boutourlini's Blue Monkey, ሰማያዊ ጦጣ
- *Graphiurus* sp. "B", ግራፊዩረስ sp. "ለ"
- *Lophuromys brevicaudus* - Short-tailed Brush-furred Rat, የኢትዮጵያ ብሩሽ ጸጉራማ አጭር ጭራ አይጥ
- *Lophuromys brunneus* -Thomas's Ethiopian Brush furred Rat, የኢትዮጵያ ብሩሽ ጸጉራማ አይጥ
- *Lophuromys chercherensis* - Mount Chercher Brush-furred Rat, የጨርጨር ተራራ ብሩሽ-ጸጉራማ አይጥ
- *Lophuromys chrysopus* - Ethiopian Forest Brush furred Rat, የኢትዮጵያ የደን ብሩሽ -ጸጉራማ አይጥ
- *Lophuromys flavopunctatus* - Ethiopian yellow-spotted Brush-furred Rat, ኢትዮጵያዊ ቢጫ-ነጠብጣብ ብሩሽ-ጸጉራማ አይጥ

**Order: Rodentia →Family: Nesomyidae**

- *Dendromus lovati* - Lovat's Climbing Mouse, ዛፍ ላይ መውጣት የሚችል አይጥ
- *Megadendromus nikolausi* - Nikolaus's Mouse
- *Dendromus mystacalis* - Chestnut Climbing Mouse, በደረት ዛፍ ላይ መውጣት የሚችል አይጥ
- *Arvicanthis abyssinicus* - Abyssinian Grass Rat, አቢሲኒያ የሳር አይጥ
- *Arvicanthis blicki* - Blick's Grass Rat, ሣር አይጥ
- *Arvicanthis saturatus*
- *Desmomys harringtoni* - Harrington's Desmomys
- *Dasymys griseifrons* - Grayish brown shaggy rat, ግራጫና ቡናማ ረዥም ፀጉር ያለው ወፍራም አይጥ
- *Desmomys yaldeni* - Yalden's Desmomys
- *Theropithecus gelada* – Gelada, ጭላዳ ዝንጀሮ
- *Colobus guereza gallarum* - Neumann's black-and-white colobus, ጉሬዛ ጋላረም - የኒውማን ጥቁር እና-ነጭ ኮሎባስ

**Order: Eulipotyphla → Family: Soricidae**

- *Crocidura baileyi* - Bailey's Shrew
- *Crocidura bottegoides* - Bale Shrew
- *Crocidura glassi* - Glass's Shrew
- *Crocidura harenna* - Harenna Shrew

- *Lophuromys melanonyx* - Black-clawed Brush-furred Rat, ጥቁር ጥፍር ያለው ብሩሽ - ባለ ጠጉር አይጥ
- *Lophuromys menageshae* - North Western Rift Brush-furred Rat, ሰሜን ምዕራባዊ ስምጥ ብሩሽ-ጸጉራማ አይጥ
- *Lophuromys simeinsis*
- *Lophuromys pseudosikapusi* - Sheko Forest Brush-furred Rat, የሼኮ ጫካ ብሩሽ-ፀጉራማ አይጥ
- *Mylomys rex* - Ethiopian Mylomys, የኢትዮጵያ ማይሎሚስ
- *Mastomys awashensis* - Awash Mastomys አዋሽ ማስቶሚስ
- *Mus imberbis* - Striped-back Mouse
- *Mus proconodon*
- *Mus mahomet* - Mahomet Mouse
- *Mus* sp. “Harena”
- *Mus* sp.1 (M. cf. triton)
- *Nilopegamys plumbeus* - Ethiopian Water Mouse, የኢትዮጵያ ውሃ አይጥ
- *Otomys typus* - Ethiopian Vlei Rat
- *Otomys fortiori* - Ethiopian Vlei Rat
- *Otomys helleri* - Ethiopian Vlei Rat
- *Otomys yalden* - Ethiopian Vlei Rat
- *Otomys cheesmani* - Ethiopian Vlei Rat
- *Otomys simiensis* - Ethiopian Vlei Rat
- *Stenocephalemys* sp. A
- *Crocidura thalia* - Thalia's Shrew
- *Crocidura afeworkbekelei* - Sanetti Shrew
- *Crocidura yaldeni* - Beletta Shrew
- *Crocidura Lucina* - Lucina's Shrew
- *Crocidura macmillani* - Macmillan's Shrew
- *Crocidura phaeura* - Guramba Shrew
- *Stenocephalemys albipes* - White-footed Stenocephalemys, ነጭ እግር
- *Stenocephalemys albocaudata* - Ethiopian Narrow-headed Rat
- *Stenocephalemys griseicauda* - Gray-tailed Narrow-headed Rat
- *Stenocephalemys “pseudogriseicauda”*
- *Stenocephalemys ruppi* - Rupp’s Stenocephalemy

**Family → Spalacidae**

- *Tachyoryctes macrocephalus* - Big-headed Mole Rat

**Order: Chiroptera →Family: Vespertilionidae**

- *Myotis scotti* - Scott's Mouse-eared Bat
- *Plecotus balensis* - Ethiopian Big-eared Bat
- *Scotophilus ejetai* - Ejetas’s house mouse

**Order: Lagomorpha → Family: Leporidae**

- *Lepus starcki* - Ethiopian Highland Hare

## አዕዋፍ

- Harwood's Francolin - *Pternistis harwoodi*
- Moorland Francolin - *Scleroptila psilolaema*
- Blue-winged Goose - *Cyanochen cyanoptera*
- Nechisar Nightjar - *Caprimulgus solala*
- Brown-faced Go-away-bird - *Corythaixoides personatus*
- Ruspoli's Turaco - *Tauraco ruspolii*
- Spot-breasted Lapwing - *Vanellus melanocephalus*
- Abyssinian Catbird - *Parophasma galinieri*
- Red-billed Pytilia - *Pytilia lineata*
- Abyssinian Longclaw - *Macronyx flavicollis*
- Yellow-throated Seedeater - *Crithagra flavigula*
- Salvadori's Seedeater - *Crithagra xantholaema*
- Ankober Serin - *Crithagra ankoberensis*
- Ethiopian Siskin - *Serinus nigriceps*
- Abyssinian Woodpecker - *Dendropicos abyssinicus*

- Yellow-fronted Parrot - *Poicephalus flavifrons*
- Ethiopian Bushcrow - Zavattariornis stresemanni
- White-tailed Swallow - *Hirundo megaensis*
- Sidamo Lark - *Heteromirafra sidamoensis*.

## አባሪ ሠ. የደን አስተዳደር እቅድ መሰረታዊ ነገሮች (መርህ7)

1) የግምገማ ውጤቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

i. በመርህ 6 እና በመርህ 9 ተለይቶ እንደተገለፀው የተፈጥሮ ሀብት እና የአካባቢ እሴቶች፤

ii. በመርህ 6 ፣ መርህ 2 እስከ መርህ 5 እና በመርህ 9 ላይ ተለይቶ እንደተገለፀው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ሀብት እና ሁኔታዎች፤

iii. በመርህ 9 ተለይቶ እንደተገለጸው ያልተነኩ ደኖች መሬት ገፅታዎች እና ዋና ቦታዎች፤

iv. በመርህ 3 እና በመርህ 9 ላይ ከተጎዱት የመብት ባለቤቶች ጋር የተለዩት ነባር ባህላዊ ገጽታዎች፤

v. በቦታው ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ማህበራዊ እና አካባቢያዊ አደጋዎች በመርህ 6፣ በመርህ 2 እስከ 5 እና በመርህ 9 የተገለጹ ናቸው፣ እና

vi. በመስፈርት 5.1 መሠረት የማስተዋወቂያ የይገባኛል ጥያቄዎች የሚቀርቡባቸው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች መጠበቅ እና/ወይም ማሻሻል፡፡

2) የሚከተሉትን ፕሮግራሞች እና ተግባራት በተመለከተ፡-

i. በመርህ 2 እንደተገለጸው የሰራተኞች መብት፣ በስራ ላይ ጤና እና ደህንነት፣ የፆታ እኩልነት፤

ii. በመርህ 3፣ መርህ 4 እና መርህ 5 የተገለጹት የነባር ህዝቦች፣ የማህበረሰብ ግንኙነቶች፣ የአካባቢው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት፤

iii. በመርህ 1፣ መርህ 2 እና መርህ 7 እንደተገለፀው የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና አለመግባባቶች እና ቅሬታዎች ስለመፍታት፤

iv. በመርህ 10 ላይ እንደተገለጸው የታቀዱ የደን አያያዝ ተግባራት እና የጊዜ ሰሌዳዎች፣ ጥቅም ላይ የዋሉ የደን ልማት /silvicultural systems/ ሥርዓቶች፣ የተለመዱ የምርት መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና መሳሪያዎች፤

v. በመርህ 5 ላይ እንደተገለጸው የእንጨት እና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብት የመሰብሰቢያ መጠን ምክንያታዊነት፡፡

3) ጥበቃ ለማካሄድ እና/ወይም ወደነበረበት ለመመለስ የሚወሰዱ እርምጃዎች፡-

i. ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች እና መኖሪያዎቻቸው፤

ii. የውሃ አካላት እና የወንዝ ዳርቻዎች ዞኖች፤

iii. የዱር እንስሳት መተላለፊያዎች ጨምሮ የመሬት ገጽታ ግንኙነት፤

iv. በመስፈርት 5.1 ላይ እንደተገለጸው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የ FSC የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የይገባኛል ጥያቄዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ፤

v. በመርህ 6 ላይ እንደተገለጸው የሚወክሉ ናሙና ቦታዎች፤ እና

vi. በመርህ 9 እንደተገለጸው ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች፡፡

4) በደን አስተዳደር ተግባራት ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለመገምገም፣ ለመከላከል እና ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች፡-

i. በመርህ 6 እና በመርህ 9 እንደተገለፀው የአካባቢ እሴቶች፤

ii. በመስፈርት 5.1 ላይ እንደተገለጸው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የ FSC ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የይገባኛል ጥያቄዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ፤

iii. ከመርህ 2 እስከ መርህ 5 እና መርህ 9 ላይ እንደተገለጸው ማህበራዊ እሴቶች እና ነባር ባህላዊ የመሬት ገፅታዎች፤ እና

iv. በመርህ 9 ተለይቶ እንደተገለጸው ያልተነኩ ደኖች መሬት ገፅታዎች እና ዋና ቦታዎች፡፡

5) በመርህ 8 ላይ የተገለጸውን የክትትል መርሃ ግብር መግለጫ፤ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

i. እድገት እና ምርት፣ በመርህ 5 እንደተገለፀው፤

ii. በመስፈርት 5.1 ላይ እንደተገለጸው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የ FSC ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የይገባኛል ጥያቄዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ፤

iii. በመርህ 6 ላይ እንደተገለፀው የአካባቢ እሴቶች፤

iv. በመርህ 10 ላይ እንደተገለጸው የአሠራር ተፅእኖዎች፤

v. በመርህ 9 ላይ እንደተገለጸው ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች፤

vi. በመርህ 2 እስከ መርህ 5 እና መርህ 7 እንደተገለጸው በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ላይ የተመሰረቱ የክትትል ስርዓቶች የታቀዱ ወይም በሥራ ላይ ያሉ፤

vii. የአስተዳደር አሃድ በተለየ ቦታ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት እና የመሬት አጠቃቀም አከላለል የሚገልፁ ካርታዎች፤

viii. የጥንቃቄ አካሄድን ለመተግበር ውጤታማነታቸውን ጨምሮ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች እና ዋና ቦታዎች ውስጥ የሚፈቀዱትን ማንኛውንም የልማት እና የመሬት አጠቃቀም አማራጮችን ለመገምገም እና ለመከታተል የሚያስችል ዘዴ መግለጫ፤

ix. ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ ለመተግበር ውጤታማነታቸውን ጨምሮ የነባር ባህላዊ የመሬት ገፅታዎች ላይ የሚፈቀዱትን ማናቸውንም የልማት እና የመሬት አጠቃቀም አማራጮች ለመገምገም እና ለመከታተል የሚያስችል ዘዴ መግለጫ፣ እና

x. ግሎባል ፎረስት ዎች / Global Forest Watch / ወይም ይበልጥ ትክክለኛ የሆነ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ካርታ፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን እና የመሬት አጠቃቀምን ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ላይ ያብራራል፣ ይህም ያልተነኩ የደን የመሬት ገፅታዎች ዋና ቦታዎችን ያጠቃልላል።

## አባሪ ረ. የእቀድና ክትትል የጽንሰ-ሀሳብ ማዕቀፍ (መርህ 7)

| ማሳያ የአስተዳደር ዕቅድ ሰነድ (መግለጫ: ይህ በ SIR እና በክልሉ ይቀያየራል) | የአስተዳደር ዕቅድ የሚከለስበት የጊዜ ገደብ | ክትትል የሚደረግባቸው ጉዳዮች (በከፊል ዝርዝር) | የክትትል ጊዜ ገደብ | ማን ይህን ጉዳይ ይከታተለዋል? (መግለጫ: ይህ በ SIR እና በክልሉ ይለያል) | FSC መርሆች/ መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| የቦታ ፕላን (የሚሰበሰብ ዕቅድ) | ዓመታዊ | የጅረት መሻገሪያ | በመስክ ላይ እና በየዓመቱ | ተግባሪ ሰራተኛ | P10 |
| | | መንገዶች | በመስክ ላይ እና በየዓመቱ | ተግባሪ ሰራተኛ | P10 |
| | | ማቆያ ትንሽ ቦታ | በየዓመቱ ናሙና | ተግባሪ ሰራተኛ | P6, P10 |
| | | ብርቅዬ ሊጠፉ የተቃረቡ እና አደጋ ላይ ያሉ ዝርያዎች | በየዓመቱ | የስነህይወት አማካሪ | P6 |
| | | ዓመታዊ የመሰብሰብ ደረጃ | በየዓመቱ | የቆላማ ቦታዎች ደን ስራ አስኪያጅ | C5.2 |
| | | የነፍሳት የበሽታ ወረርሽኝ | በየዓመቱ ናሙና | የስነህይወት አማካሪ/ የደን ሚንስቴር | |
| በጀት መመደብ | ዓመታዊ | ወጪ | በየዓመቱ | መሪ የፋይናንስ ባለሙያ | P5 |
| | | ለአካባቢው ኢኮኖሚ ያለው አስተዋጽኦ | በየሩብ ዓመቱ | ዋና ስራ አስኪያጅ | P5 |
| የተሳትፎ ዕቅድ | ዓመታዊ | የቅጥር ስታትስቲክስ | በየዓመቱ | ዋና ስራ አስኪያጅ | P3, P4 |
| | | ማህበራዊ ስምምነቶች | በየዓመቱ/ የተሳትፎ ዕቅድ | ማህበራዊ አስተባባሪ | P3, P4 |
| | | ቅሬታዎች | ቀጣይ | የሰው ሀብት ስራ አስኪያጅ | P2, P3, P4 |
| 5-ዓመት የአስተዳደር ዕቅድ | 5-ዓመታት | የዱር እንስሳት ብዛት | ይወሰናል | የአካባቢ ሚኒስቴር | P6 |
| | | ግርድፍ የእንጨት ቁርጥራጭ | ዓመታዊ | የደን ሚንስቴር | P10 |
| | | በነጻነት የሚያድግ/ መልሶ መብቀል | ዓመታዊ ናሙና | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ዘላቂ የደን አስተዳደር ዕቅድ** | 10 ዓመታት | የዕድሜ ክፍል ስርጭት<br>የመጠን ክፍል ስርጭት | አስር ዓመታት | የአካባቢ ሚንስቴር | P6 |
| | | የ10 ዓመት ዓመታዊ ለመቁረጥ የተፈቀደ | ዓመታዊ, አስር ዓመታት | የደን ሚንስቴር/የቆላማ ቦታዎች ደን ስራ አስኪያጅ | C5.2 |
| **የስርዓተ ምህዳር ግልጋሎቶች ምስክር ወረቀት ሰነድ** | 5 ዓመታት | ቅድሚያ ለማረጋገጥ እና ለማረጋገጫ | ቅድሚያ ለማረጋገጥ እና ለማረጋገጫ | ዋና ስራ አስኪያጅ | FSC-PRO-30-006 |

## አባሪ ሰ.    የክትትል ቅድመ ሁኔታዎች (መርህ 8)

1) በ8.2.1 ውስጥ ክትትል የአስተዳደር ተግባራትን ለመለየት እና የአካባቢያዊ ተጽዕኖዎችን ለመወሰን በቂ ነው፤ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፡

    i. የመልሶ መብቀል ተግባራት ውጤቶች (መስፈርት 10.1)፣

    ii. ለመልሶ መብቀል ከስነምህዳራዊ ጋር በከፍተኛ ተስማሚ ዝርያ መጠቀም (መስፈርት 10.2)፣

    iii. ከየትኛውም ከውጭ የመጣ ዝርያ በአስተዳደር አሃድ ውስጥና ውጪ ተያያዥነት ያለው የወራሪነት ወይም ሌላ አሉታዊ ተጽዕኖዎች (መስፈርት 10.3)፣

    iv. ጥቅም ላይ እንዳልዋሉ ለማረጋገጥ በዘረመል የተሻሻሉ ህዋሳትን መጠቀም (መስፈርት 10.4)፣

    v. የድህረ ተከላ እንክብካቤ ተግባራት ውጤቶች (መስፈርት 10.5)፣

    vi. ከማዳበሪያዎች በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖዎች (መስፈርት 10.6)፣

    vii. ፀረ-ተባይ መድሃኒቶችን ከመጠቀም አሉታዊ ተጽእኖዎች (መስፈርት 10.7)፣

    viii. ስነህይወታዊ ቁጥጥር ወኪሎች አጠቃቀም አሉታዊ ተጽእኖዎች (መስፈርት 10.8)፣

    ix. ከተፈጥሮ አደጋዎች ተጽዕኖዎች (መስፈርት 9)፣

    x. የመሠረተ ልማት ፣ የትራንስፖርት ተግባራት እና የድህረ ተከላ እንክብካቤ በብርቅዬ እና አስጊ ዝርያዎች፣ መኖሪያዎች፣ ስርዓተ-ምህዳሮች፣ የመሬት ገጽታ እሴቶች፣ ውሃ እና አፈር ያለው ተጽዕኖዎች (መስፈርት 10.10)፣

    xi. እንጨት መሰብሰብ እና ማውጣት በእንጨት-ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶች፣ የአካባቢያዊ እሴቶች፣ የሚሸጡ የእንጨት ተረፈ ምርት እና ሌሎች ምርቶች እና አገልግሎቶች ላይ ያለው ተጽእኖ (መስፈርት 10.11)፣ እና

    xii. ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ ቆሻሻ  ማስወገድ (መስፈርት 10.12).

2) በ 8.2.1 ውስጥ ያለው ክትትል የደን አያያዝ ተግባራት ማህበራዊ ተጽእኖዎችን ለመለየት እና ለመግለጽ በቂ ነው፤ አስፈላጊ ከሆነም የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

    i. ሕገወጥ ወይም ያልተፈቀዱ ድርጊቶች ማስረጃ (መስፈርት 1.4)፤

    ii. ከሚመለከታቸው ህጎች፣ የአካባቢ ህጎች፣ የጸደቁ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና የግዴታ የአሰራር ደንቦች ጋር መጣጣም (መስፈርት 1.5)፤

    iii. አለመግባባቶች እና ቅሬታዎች መፍታት (መስፈርት 1.6፣ መስፈርት 2.6፣ መስፈርት 4.6)፤

    iv. የሰራተኞችን መብቶች በተመለከተ ፕሮግራሞች እና ተግባራት (መስፈርት 2.1)፤

    v. የፆታ እኩልነት፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና የፆታ መድልዎ (መስፈርት 2.2)፤

    vi. የሙያ ጤና እና ደህንነትን የሚመለከቱ ፕሮግራሞች እና ተግባራት (መስፈርት 2.3)፤

    vii. የምንዳ ክፍያ (መስፈርት 2.4)፤

    viii. የሰራተኞች ስልጠና (መስፈርት 2.5)፤

    ix. ፀረ-ተባይ መድሃኒቶች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ቦታ፣ ለፀረ-ተባይ መድሃኒቶች የተጋለጡ ሰራተኞች ጤና (መስፈርት 2.5 እና መስፈርት 10.7)፤

    x. የነባር ሕዝቦች እና የአካባቢ ማህበረሰቦች እና ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶቻቸውን መለየት (መስፈርት 3.1 እና መስፈርት 4.1)፤

    xi. አስገዳጅ ስምምነቶች ውስጥ ያሉ ውሎችን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ (መስፈርት 3.2 እና መስፈርት 4.2)፤

    xii. የነባር ሕዝቦች እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች (መስፈርት 3.2፣ መስፈርት 3.3 እና መስፈርት 4.2)፤

xiii. ለነባር ህዝቦች እና ለአካባቢው ማህበረሰቦች ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች ጥበቃ (መስፈርት 3.5 እና መስፈርት 4.7)፤

xiv. ነባር ባህላዊ ገጽታዎች እና ከእነሱ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ለነባር ህዝቦች አስፈላጊ የሆኑ እሴቶች መኖራቸው (መስፈርት 3.1፣ መስፈርት 3.5)፤

xv. ባህላዊ እውቀት እና አእምሯዊ ንብረት አጠቃቀም (መስፈርት 3.6 እና መስፈርት 4.8)፤

xvi. የአካባቢ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት (መስፈርት 4.2፣ መስፈርት 4.3፣ መስፈርት 4.4፣ መስፈርት 4.5)፤

xvii. የተለያዩ ጥቅሞችን እና/ወይም ምርቶችን ማምረት (መስፈርት 5.1)፤

xviii. የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶችን መጠበቅ እና/ወይም ማሻሻል (መስፈርት 5.1)፤

xix. የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶችን የመጠበቅ ወይም የማሻሻል ተግባራት፤

xx. እንጨት እና እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶች ዓመታዊ ትክክለኛ እና ታሳቢ ምርት ንጽጽር (መስፈርት 5.2)፤

xxi. የአካባቢ ምርት የማምረት ሂደት፣ የአካባቢ አገልግሎቶች እና የአካባቢያዊ የተጨማሪ እሴት ማምረቻ አጠቃቀም (መስፈርት 5.4)፤

xxii. የረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ዘላቂነት (መስፈርት 5.5) ፤ እና

xxiii. ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች 5 እና 6 በመስፈርት 9.1 ውስጥ ተለይተው የታወቁ ፡፡

3) የ8.2.2 የክትትል አሰራሮች የአካባቢ ሁኔታዎችን ለውጦች ለመለየት እና ለመግለጽ በቂ ናቸው፣ አስፈላጊ ከሆነም የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

i. የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶችን መጠበቅ እና/ወይም ማሻሻል (መስፈርት 5.2) (ድርጅቱ የFSC ስነ-ምህዳር አገልግሎቶችን የይገባኛል ጥያቄዎችን ሲጠቀም)፤

ii. የካርበን ማመቅ እና ማከማቸት ጨምሮ የአካባቢ እሴቶች እና የሥርዓተ ምህዳር ተግባራት (መስፈርት 6.1)፤ በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመከላከል፣ ለመቀነስ እና ለመጠገን ተለይተው የታወቁ እና የተተገበሩ ድርጊቶች ውጤታማነትን ጨምሮ (መስፈርት 6.3)፤

iii. ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች፣ እና እነሱን እና መኖሪያዎቻቸውን ለመጠበቅ የተተገበሩ እርምጃዎች ውጤታማነት (መስፈርት 6.4)፤

iv. ተወካይ ናሙና ቦታዎች እና እነሱን ለመጠበቅ እና/ወይም ወደነበሩበት ለመመለስ የተተገበሩ ድርጊቶች ውጤታማነት (መስፈርት 6.5)

v. በተፈጥሮ የተገኙ ነባር ዝርያዎች እና የስነ-ህይወት ብዝሀነት እና እነሱን ለመጠበቅ እና/ወይም ወደነበሩበት ለመመለስ የተተገበሩ እርምጃዎች ውጤታማነት (መስፈርት 6.6)፤

vi. የውሃ ፍሰቶች፣ የውሃ አካላት፣ የውሃ መጠን እና የውሃ ጥራት እና እነሱን ለመጠበቅ እና/ወይም ወደነበሩበት ለመመለስ የተተገበሩ እርምጃዎች ውጤታማነት (መስፈርት 6.7)፤

vii. የመሬት ገፅታ እሴቶች እና እነሱን ለመጠገን እና/ወይም ወደነበሩበት ለመመለስ የተተገበሩ እርምጃዎች ውጤታማነት (መስፈርት 6.8)፤

viii. የተፈጥሮ ደንን ወደ ሰው ሰራሽ ደኖች ወይም ደን ያልሆነ መለወጥ (መስፈርት 6.9)፤

ix. የተተከሉ የሰው ሰራሽ ደኖች ሁኔታ ከ1994 በኋላ (መስፈርት 6.10)፤ እና

x. በመስፈርት 9.1 ውስጥ ተለይተው የታወቁ ከ1 እስከ 4 ያሉት ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች እና እነሱን ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል የተተገበሩ ድርጊቶች ውጤታማነት፡፡

## አባሪ ሸ. ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታ ዋና ቦታዎች የሚመለከቱ አመልካቾችን ለማዘጋጀት ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ (መርህ 9)

### ሀ. ለብዙሃኑ የተሰጠ ገደብ

የብዙሃን ገደብ ትርጉም ከጥር 1 ቀን 2017 እኤአ ጀምሮ 80% የሚሆነው አጠቃላይ ያልተነካ የደን መሬት ገጽታ ቦታ በደን አስተዳደር አሃድ ውስጥ ሲገኝ ነው። ብዙሃን የሚለው ያልተነካ የደን መሬት ገፅታ ትርጉምን ያሟላል ወይም ይበልጣል፡፡

ለብዙሃኑ የተሰጠ ገደብ ከ 80% በታች ሊመሰረት ይችላል፣ ይህም ከፍተኛ መጠን ያለው የጥበቃ ውጤት በብሔራዊ ወይም ኢኮ-ክልላዊ ታሳቢዎች እና ሲያሳካ ያልተነካ የደን መሬት ገፅታ ትርጉምን ሲያሟላ ወይም ሲበልጥ ነው።

ከ80% በላይ የሆኑ ገደቦች በሀገሮች እና/ወይም በሥነ ምህዳራዊ ክልሎች /eco-regions/ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች በአንጻራዊ ሁኔታ ውስን እና/ወይም የተበታተኑ ሲሆኑ እና/ወይም እኤአ ከ2000 ወዲህ ከፍተኛ መጠን ያለው ያልተነኩ የደን መሬት ገጽታዎች የጠፋባቸው አካባቢዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

አብዛኛው ደረጃ አዘጋጆች በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም በሥነ ምህዳራዊ ክልሎች የተለየ ለብዙሃኑ የተሰጠ ገደብ ሲያዘጋጁ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡

ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች አንጻራዊ ብዛት እና በሰው ተግባራት ምክንያት

1) ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች የመጐሳቆል አደጋ ደረጃን የሚያሳይ ማስረጃ፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

   ሀ. በብሔራዊ ወይም በሥነ ምህዳራዊ ክልሎች ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታዎች አንጻራዊ እጥረት፡፡ ያልተነኩ  የደን የመሬት ገጽታዎች በጣም ሲጠፉ የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

   ለ. እኤአ ከ2000  ጀምሮ በሰው ልጅ ተግባራት የተጐሳቆሉ ብሔራዊ ወይም ሥነ ምህዳራዊ ክልሎች /eco-regions ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታዎች መጠን እና ስለሆነም የተመናመኑ፣ አልፎ አልፎ የሚገኙ ወይም የተበታተኑ ናቸው፡፡ ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታዎች በፍጥነት ሲጎሳቆሉ የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

   ሐ. ከእኤአ 2000  ጀምሮ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* በፍጥነት እንዲጎሳቆሉ ምክንያት የሆኑት የሰው ልጆች እንቅስቃሴ አይነቶች፣ የሰዎች ተግባራት፣ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች አለመነካት ይበልጥ የሚጎዱ ከሆነ የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

   መ. በሰው ልጅ እንቅስቃሴ ምክንያት ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* የመጎዳት አደጋ፡፡ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* ላይ የሚጋረጠው አደጋ እየጨመረ በሄደ መጠን የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

   ሠ. የተለያዩ የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎችን* ክብደት በማወዳደር ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ዋና ቦታዎች* የተጠበቁበት መጠን እና አንጻራዊ ዘላቂነት፡፡ ጥበቃው ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ዋና ቦታዎች አንድነት እና ሌሎች ሥነ ምህዳራዊ ባህሪያትን መጠበቅ ወይም ማሻሻል አለበት*፡፡ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ጥበቃው ይበልጥ ዘላቂ ከሆነ የብዙሃን ገደብ ዝቅተኛ ይሆናል፤

   ረ. ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ውስጥ እና በአቅራቢያ ያሉ ሥነ ምህዳራዊ እሴቶች ተፈጥሮ እና ስርጭት፡፡ የእነዚህ እሴቶች ክምችት ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ውስጥ እና በአቅራቢያቸው የበለጠ ከሆነ፣ የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

   ሰ. ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ውስጥ እና አጠገብ የባህላዊ እሴቶች እና ህጋዊና ልማዳዊ መብቶች ተፈጥሮና ስርጭት፤ እና

   ሸ. ከተጎዱት የመብት ባለቤቶች፣ የተጎዱ እና ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ባህሉን የጠበቀ የተሳትፎ ውጤቶች፡፡

### ለ. ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ለመገምገም እና ለመጠበቅ አመልካቾችን ማዘጋጀት

ደረጃ አዘጋጆች ለመስፈረት 9.1 እና 9.2 አመላካቾችን በሚያዘጋጁበት ጊዜ የሚከተሉትን መረጃዎች ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

ለብዙሃኑ እና ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎችን እንደ ዋና ቦታዎች ለመለየት፣ ለመገምገም እና ለመጠበቅ ውጤቱ በብሔራዊ ወይም በሥነ ምህዳራዊ ክልሎች ደረጃ ተገቢ ና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች መሆን አለባቸው፡፡

ዋና ቦታዎች አለመነካታቸው ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ተግባራት እንዲጠበቁ የታሰቡ ሲሆን ይህም የንግድ ሥራን ለማካሄድ የሚውል የእንጨት ማውጣት፣ የማዕድን ማውጣት እንዲሁም የመንገድ፣ የግድብ እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን ይጨምራል።

1) ዋና ቦታዎችን ለመለየት እና ለመሰየም የተዘጋጁ አመልካቾች የሚከተሉትን ያደርጋሉ፡

ሀ. የተጎዱትን የሙብት ባለቤቶች ነፃ ቅድመ እና መረጃ የተገኘበት ስምምነት የማግኘት ሙብት ማክበር (መሰፈርት* 3.1 እና 4.1) ፤

ለ. የተጎዱት የሙብት ባለቤቶች ዋና ቦታዎችን የመጠቀም ሕጋዊና ልማዳዊ ሙብቶች እንዲከበሩ ማረጋገጥ፤

ሐ. ዋና ቦታዎች በሥነ ምህዳራዊ ሁኔታ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ፣ ተያያዥነት ያላቸው እና ጥቅጥቅ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎችን ክፍሎች መኖራቸውን ማረጋገጥ፤

መ. የዋና ቦታዎች ቅርፅ የውስጥ መኖሪያ ቦታዎቻቸውን ከፍ ለማድረግ የተነደፈ መሆኑን ማረጋገጥ፤

ሠ. ዋና ቦታዎች በስፋት የተያያዙ እና ያልተለወጡ የደን ቦታዎች ላይ ለሚገኙ ብርቅዬ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች እና ሌሎች የዱር እንስሳትና ዕፅዋት መኖሪያ ቦታዎችን እንደያዙ ማረጋገጥ፤

ረ. ዋና ቦታዎች በደን አስተዳደር አሃድ ውስጥም ሆነ በአቅራቢያቸው ያሉ ዋና ቦታዎች መካከል ግንኙነታቸው መጠበቁን ወይም መመለሱን ማረጋገጥ፤ እና

ሰ. ዋና ቦታዎች ከ50 ሺህ ሄክታር በታች እንዳይሆኑ ማረጋገጥ።

2) ዋና ቦታዎችን ለመጠበቅ የተዘጋጁ አመልካቾች የሚከተሉትን ያረጋግጣሉ፡

ሀ. የተጎዱ ባለሙብቶች ዋና ቦታዎች የመጠቀም ሕጋዊና የተለመዱ ሙብቶች ተከብረዋል፤

ለ. የነባር ሕዝቦች ለብዙ ዓመታት ለብቻቸው የተውሰነ ቦታ የሚኖሩ ሕዝቦች እና በደን ላይ ጥገኛ የሆኑ ማህበረሰቦች ከዋና ቦታዎች ጥበቃ ጋር የሚጣጣሙ አማራጭ የአስተዳደር እና የጥበቃ ተግባራትን ለመቅረፅ እና ለመተግበር ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፤

ሐ. በዋና ቦታዎች ውስጥ ህገ ወጥ የዛፍ መቁረጥና ማጓጓዝ፣ በነፋስ መውደቅ፣ መመናመን እና ሌሎች የዳርቻ ውጤት ተፅዕኖዎች መከላከል፤

መ. የመንገድ ግንባታ አስተዳደር እና ከዋና ቦታዎች አጠገብ ያሉ ሌሎች ተግባራት ጥንካሬ በዋና ቦታዎች ውስጥ ህገወጥ የዛፍ መቁረጥና ማጓጓዝ፣ በነፋስ መውደቅ፣ መመናመን እና ሌሎች የዳርቻ ውጤት ተፅዕኖዎች ለመከላከል፤ እና

ሠ. በዋና ቦታዎች ውስጥ የዳርቻ ውጤት ተፅዕኖዎች ለመከላከል የመንገድ ግንባታ እና ሌሎች ተግባራት የሚተዳደሩባቸው ዋና ቦታዎች አጠገብ የሚገኙ ተስማሚ የመከላከያ ዞኖች ስፋት መለየት።

3) ለዋና ቦታዎች ጥበቃ የተዘጋጁ አመልካቾች ዋና ቦታዎች በአለመነካታቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተግባራት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የንግድ ሥራን ለማከናወን የሚያስችሉ ዛፎችን መቆረጥና ማጓጓዝ፣ ማዕድን ማውጣት፣ እና የመንገድ፣ የግድብና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን መገንባት ጨምሮ ፍፁም ያልተነኩ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ፍፁም ያልተነኩ ዋና ቦታዎችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ የአስተዳደር ስራዎች ምሳሌዎች፤ የጥበቃ ቀጠናዎች እንዲሁም የሕግ ጥበቃ ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው የሚችሉ ቦታዎችን ለምሳሌ የተተዉ ቦታዎች፣ መጠባበቂያ ቦታዎች፣ ውሳኔ ያላገኙ ቦታዎች፣ የማህበረሰብ መጠባበቂያ ቦታዎች እና ነባር የተጠበቁ ቦታዎችን ያካትታሉ፡፡

4) ላልተነኩ የደን መሬት ገጽታዎች የተዘጋጁ አመልካቾች እንደ ዋና ቦታዎች ያልተሰየሙ ያልተነኩ የደን መሬት ገጽታዎች ክፍሎች ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ምድብ 2 ለመጠበቅ እና/ወይም ለማቆየት የሚያገለግሉ መሆናቸውን ያብራራሉ፡፡

## አባሪ ቀ. ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስልቶች (መርህ 9)

ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚረዱ ስልቶች የግድ የምርት መሰብሰብን ሊከለክሉ አይችሉም። ይሁን እንጂ አንዳንድ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ ብቸኛው መንገድ እነሱን የሚደግፍ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያለው ቦታን በመጠበቅ ነው።

- **HCV 1 –** የጥበቃ ዞኖች፣ የምርት መሰብሰብ መመሪያዎች፣ እና/ወይም በመጥፋት ላይ ያሉ፣ አደጋ ላይ የወደቁ፣ ብቸኛ ዝርያዎች ወይም ሌሎች የስነ ህይወት ብዝሃነት ክምችቶች እና የሚመረኮዙባቸውን ሥነ ምህዳራዊ ማህበረሰቦች እና መኖሪያ ቦታዎች ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሌሎች ስልቶች የመኖሪያ ቦታዎች እና የዝርያዎች መገኘት መጠን፣ አንድነት፣ ጥራት እና ዘላቂነት መቀነስን ለመከላከል በቂ ናቸው። ዓላማው መሻሻል ከሆነ ለእነዚህ ዝርያዎች መኖሪያ አካባቢዎችን ለማሳደግ፣ ለማስፋት እና/ወይም ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚያስችሉ እርምጃዎች በቦታው አሉ።
- **HCV 2 –** የደን ሥርዓተ ምህዳሮችን መጠን እና አለመነካት ሙሉ በሙሉ የሚጠብቁ ስልቶች እና የእፅዋት እና የእንስሳት አመላካች ዝርያዎችን፣ አመላካች ዝርያዎችን /keystone species/ እና/ወይም ከትላልቅ ያልተነኩ የተፈጥሮ የደን ሥርዓተ ምህዳሮች ጋር የተዛመዱ አንድ ዓይነት ሥነ ምህዳራዊ የሚጠቀሙ ዝርያዎች ቡድን ጨምሮ የእነሱ የስነ ህይወት ብዝሃነት ክምችት ዘላቂነት። ለምሳሌ የተከለሉ ቀጠናዎች እና የተተው ቦታዎች፣ የልተተው ቦታዎች ውስጥ ማንኛውም የንግድ እንቅስቃሴ በማንኛውም ጊዜ የደን መዋቅርን ፣ ጥንቅርን ፣ ዳግም ብቀለትን እና የተፈጥሮ ዑደቶች መረበሽ ንድፍን ሙሉ በሙሉ በሚጠብቅ መልክ እንዲሁም አነስተኛ መጠን ባላቸው ሥራዎች ብቻ የተገደበ ነው። ዓላማው ማሻሻል እንደሆነ ከተገለጸ የደን ሥርዓተ ምህዳሮችን፣ አለመነካታቸውን እና ተፈጥሯዊ ስነ ህይወታዊ ብዝሃነትን የሚደግፉ መኖሪያ ቦታዎቻቸውን መልሶ ለማቋቋም እና እንደገና ለማገናኘት የሚያስችሉ እርምጃዎች ተወስደዋል።
- **HCV 3 –** ብርቅየ ወይም በመጥፋት ላይ ያሉ ሥርዓተ ምህዳሮችን፣ መኖሪያ ቦታዎችን ወይም መጠጊያዎችን ሙሉ በሙሉ የሚጠብቁ ስልቶች። ማሻሻል እንደ ዓላማ ከተገለጸ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ ሥርዓተ ምህዳሮች፣ መኖሪያ ቦታዎችን ወይም መጠጊያዎችን ወደ ነበረበት ለመመለስ እና/ወይም ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎች ተቀምጠዋል።
- **HCV 4 –** በደን አስተዳደር አሃድ ውስጥ ወይም ታችኛው ተፋሰስ ክፍል የሚገኙትን ለአካባቢው ማህበረሰቦች አስፈላጊ የሆኑ የውሃ ተፋሰሶችን /catchments/ እና በተለይ ያልተረጋጋ ወይም ለመሸርሸር የተጋለጡ አካባቢዎችን ለመጠበቅ የተቀመጡ ስልቶች፡፡ ለምሳሌ የተከለሉ ቦታዎች፣ የምርት መሰብሰብ ትዕዛዞች፣ የኬሚካል አጠቃቀም ገደቦች፣ እና/ወይም የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ትዕዛዞች፣ የውሃ ተፋሰሶችን /catchments/ እና የላይኛው ተፋሰስና የላይኛው ተዳፋት ቦታዎችን መጠበቅን ያጠቃላል። ማሻሻል እንደ አላማ ከተለየ የውሃውን ጥራት እና ብዛት ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚያስችሉ እርምጃዎች ተቀምጠዋል፡፡ የ HCV 4 ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የአየር ንብረት ደንብን የሚያካትቱ ከሆነ የካርቦን ማጠራቀሚያ እና ማከማቻን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል ስልቶች ተቀምጠዋል፡፡
- **HCV 5 –** የደን አስተዳደር አሃድን በተመለከተ የማህበረሰቡን እና/ወይም የነባር ሕዝቦች ፍላጎትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስልቶች ከአካባቢው ማህበረሰቦችና ከነባር ህዝቦች ተወካዮችና አባላት ጋር በመተባበር ይዘጋጃሉ፡፡
- **HCV 6 –** ባህላዊ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስልቶች ከአካባቢው ማህበረሰቦች እና ከነባር ህዝቦች ተወካዮች እና አባላት ጋር በመተባበር ይዘጋጃሉ፡፡

## አባሪ በ.    ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ማዕቀፍ (መርህ 9)

**አጠቃላይ ከሁሉ ተሸሎ የተገኘ መረጃ /Overarching Best Available Information (BAI)**

የሚከተሉት ሠንጠረዦች ለሁሉም የ HCVs ወይም ለተወሰኑ የ HCVs ምድቦች ለግምገማዎች፣ ስልቶች እና ክትትል የሚመለከታቸው አጠቃላይ ከሁሉ ተሸለው  የተገኙ መረጃዎች (BAI) ዓይነቶችን ያሳያሉ። BAI SLIMF ላልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ ይሠራል። ለSLIMFs BAI የሚተገበረው በተጠቀሰው ቦታ ነው። እዚህ ላይ አጠቃላይ የ BAI ዝርዝርን የመዘርዘር ዓላማ በቀጣዮቹ ክፍሎች ውስጥ ደጋግሞ መዘርዘር እንዳይኖር ነው። ለእያንዳንዱ ይበልጥ የተወሰነ የ HCV ትርጓሜዎች BAI በሚቀጥሉት ክፍሎች ውስጥ ተካትቷል።

| ብሔራዊ ወይም ክልላዊ የHCV ትርጓሜዎችን ለመለየት እና ለመገምገም ከሁሉ ተሸሎ የተገኘ መረጃ | | SLIMF |
|---|---|---|
| **ሁሉም የ HCV ምድቦች፣ ሁሉም መሰረታዊ ነገሮች** | መረጃ፣ እውነታዎች፣ ሰነዶች፣ የባለሙያዎች አስተያየቶች እና የቦታ ዳሰሳ ጥናቶች ወይም ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ምክክር ውጤቶች በጣም አስተማማኝ፣ ትክክለኛ፣ የተሟላ እና/ወይም ተገቢ የሆኑና በአስተዳደር ተግባራት መጠን እና ጥንካሬ እና ጥንቃቄ በተሞላበት አካሄድ ምክንያታዊ በሆነ ጥረት እና ወጪ ሊገኙ የሚችሉ ናቸው።<br><br>ለደን አስተዳደር አሃድ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት የዳሰሳ ጥናት፣ ፤ አግባብነት ያላቸው የመረጃ ቋቶች እና ካርታዎች፤ ከአገሬው ተወላጆች፣ ከተጎዱት የሙብት ባለቤቶች፣ ከተጎዱት እና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት እንዲሁም አግባብነት ካላቸው የአካባቢና የክልል ባለሙያዎች ጋር ከባህላዊ አግባብነት ጋር የተጣጣመ ተሳትፎ፤ የ FSC መመሪያ ለነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት ተግባራዊነት (2021)፤ ከድርጅቱ ገለልተኛ በሆኑ እውቀት ባላቸው ባለሙያዎች የተገኙ ውጤቶችን እንዲታዩ ማድረግ። | X |
| **HCV 2, መሰረታዊ ነገሮች 1, IFLs** | ግሎባል ፎረስት ዋች ያልተነኩ የደን ገጽታ ካርታዎች (2017) www.globalforestwatch.org፣ ወይም የተጣራ ዘዴን በመጠቀም ይበልጥ የቅርብ ጊዜ እና ትክክለኛ ያልተነኩ የደን ገጽታዎች ምዝገባ ላይ የተመሠረተ ሌሎች ካርታዎች። | X |
| **HCV 5, መሰረታዊ ነገሮች 2, እና HCV 6, መሰረታዊ ነገሮች 3, ነባር ህዝቦችመሠረታዊ እሴቶች** | ከነባር ህዝቦችጋር በባህል ተስማሚ የሆነ ተሳትፎ ለእነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ዋነኛው BAI ነው። | X |
| **HCV 5, መሰረታዊ ነገሮች 2, እና HCV 6, መሰረታዊ ነገሮች 3, ለአገሬው ተወላጆች መሠረታዊ እሴቶች** | ከነባር ህዝቦችጋር በባህል ተስማሚ የሆነ ተሳትፎ ለእነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ዋነኛው BAI ነው። | X |

| ብሄራዊ ወይም ክልላዊ ከፍተኛ ጥበቃ እሴት ትርጓሜዎችን ለማዘጋጀት የተሻለ መረጃ | | SLIMF |
|---|---|---|
| **ሁሉም የ HCV ምድቦች፣ ሁሉም መሰረታዊ ነገሮች** | ስጋቶችን ለመለየት የሚከተሉትን ይጠቀማል፡- መረጃዎች፣ እውነታዎች፣ ሰነዶች፣ የባለሙያዎች አስተያየቶች፣ እንዲሁም የመስክ የዳሰሳ ጥናቶች ወይም ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ምክክር ውጤቶች በጣም አስተማማኝ፣ ትክክለኛ፣ የተሟላ እና/ወይም ተገቢ የሆኑና በአስተዳደር ተግባራት መጠንና ጥንካሬ እንዲሁም ጥንቃቄ በተሞላበት አካሄድ ምክንያታዊ ጥረትና ወጪ በማድረግ ሊገኙ የሚችሉ ናቸው። ከነባር ህዝቦች፣ ከተጎዱት የመብት ባለቤቶች፣ ከተጎዱት እና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከባለሙያዎች ጋር መስተጋብር መፍጠር።<br><br>ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በባህል ተስማሚ የሆነ ተሳትፎ ለእነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ዋነኛው BAI ነው። የህብቶቹ "መሰረታዊነት" እና "ወሳኝ ጠቀሜታ" እንዲሁ በተሳትፎ መወሰን አለባቸው። | X |
| **HCV 5, መሰረታዊ ነገሮች 1, እና HCV 6, መሰረታዊ ነገሮች 2, ለአካባቢው ማህበረሰብ መሠረታዊ እሴቶች** | ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በባህል ተስማሚ የሆነ ተሳትፎ ለእነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ዋነኛው BAI ነው። የህብቶቹ "መሰረታዊነት" እና "ወሳኝ ጠቀሜታ" እንዲሁ በተሳትፎ መወሰን አለባቸው። | X |
| **HCV 5, መሰረታዊ ነገሮች 2, እና HCV 6, መሰረታዊ ነገሮች 3, ለአገሬው ተወላጆች መሠረታዊ እሴቶች** | ከነባር ህዝቦች ጋር በባህል ተስማሚ የሆነ ተሳትፎ ለእነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ዋነኛው BAI ነው። የህብቶቹ "መሰረታዊነት" እና "ወሳኝ ጠቀሜታ" እንዲሁ በተሳትፎ መወሰን አለባቸው። | X |

| ብሔራዊ ወይም አካባቢያዊ የHCV አተረጓጎም ለመከታተል ምርጥ መረጃ | | SLIMF |
|---|---|---|
| **ሁሉም የ HCV ምድቦች፣ ሁሉም መሰረታዊ ነገሮች** | BAI የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡- ከመመዘኛ 3.5፣ 4.5 እና 4.7 ጋር በሚጣጣም መልኩ ከመብት ባለቤቶች ጋር መተባበር፤ ከነባር ህዝቦች እንዲሁም ከተጎዱትና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከባህል አንፃር ተገቢ የሆነ ግንኙነት፤ የሀገሬው ተወላጆች እና/ወይም የአካባቢው ማህበረሰቦች ተወካዮች ጋር ስለመተባበር መረጃ፤ በነባር ህዝቦች እና/ወይም በአካባቢው ማህበረሰቦች የሚደረግ ክትትል፣ እና ከባለሙያዎች ጋር መተባበር። | X |

**HCV 1 – የዝርያ ብዝሀነት /Species diversity/፡ ዓለም አቀፋዊ፣ ቀጠናዊ ወይም ብሔራዊ ደረጃ ላይ ጠቀሜታ ያላቸው ብቸኛ ዝርያዎች፣ እና ብርቅዬ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ ወይም አደጋ ላይ የወደቁ የደረሱ ዝርያዎችን ጨምሮ የሥነ ሕይወት ብዝሃነት ክምችት፡፡**

በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ ያሉ መረጃዎች ለሁሉም ድርጅቶች ይሠራሉ፡፡ የማይጨምረው ለSLIMFs ወይም ለሌሎች ድርጅቶች ተተግብሮ የማይታየው BAI ነው (>SLIMF)፤ ሆኖም ግን ትርጓሜዎች፣ ስልቶች እና የግምገማና የክትትል ዘዴዎች አሁንም ተግባራዊ ይሆናሉ። በተጨማሪም ከላይ የተዘረዘሩትን አጠቃላይ የ BAI ዝርዝሮች ይመልከቱ።

### ሀ. የHCV 1 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች ለ HCV መለያ

| የHCV 1 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች፡- | የመተርጎሚያዎቹን መገኛዎች ለመለየት ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለSLIMF ሊተገበር ይችላል? |
|---|---|---|
| **ዋና ነገሮች 1፡- በዓለም አቀፍ፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጠቃሚ የሆኑ የሥነ ሕይወት ብዝሃነት ክምችቶች** | | |
| **የተጠበቁ ቦታዎች የሚከተሉትን ጨምሮ፡- ብሔራዊ ፓርኮች፣ ብሔራዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የደን ቦታዎች፣ ክልላዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የደን ቦታዎች፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎች፣ የዱር እንስሳት ማቆያዎች /Wildlife resereve/፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የአደን ቦታዎች፣ የማህበረሰብ ጥበቃ ቦታዎች፣ የዩኔስኮ ባዮስፌር መጠባበቂያ ቦታዎች። (EBI; MEFCC, 2018; ሌሎችም)** | ለዝርዝሮች እና ካርታዎች የተጠበቁ አካባቢዎችን ይመልከቱ (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) እና የዩኔስኮ ባዮስፌር መጠባበቂያ ቦታዎችን (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) ይመልከቱ። በተጨማሪም የሚከተሉትን ይመልከቱ: - የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት፣ ብሔራዊ የብዝሀ ህይወት ስልት እና የድርጊት መርሀ ግብር፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና አግባብ ያለው የክልል መንግስት። | |
| **የባሌ ሰንሰለታማ ተራሮች፣ የላይኛውና የታችኛው ከፍታዎች፣ የመና-አንገቱ ደን፣ የሀረና ደን እና ከብሔራዊ ፓርኩ ውጭ ያሉ ሌሎች አካባቢዎችን ጨምሮ። (Kimbrough, 2021; Siegel, 2018; WWF, 2004; WWF, 2000) ከፋ፣ ሸካ እና ያዩ ባዮስፌር መጠባበቂያ ቦታዎች**<br><br>**'የቤተ ክርስቲያን ደኖች' (አካ ቅዱስ ዛፎች)፣ በመካከለኛውና በሰሜናዊው ተራራማ አካባቢዎች ጨምሮ (Aerts et al, 2016)**<br><br>**ሌሎች ገለልተኛ የተቆራረጡ ደን ቅሪቶች፣ ደረቃማ የአፍሮሞንቴን ደን ጨምሮ (Aynekulu et al, 2016)**<br><br>**ከቦታ ወደ ቦታ የሚፈልሱባቸው ቦታዎች፣ የመራቢያ ቦታ፣ ረጅም እንቅልፍ የሚወስዱበት ቦታ /Hibernation areas/ እና ሌሎች ጉልህ ሥፍራ ያላቸው ወቅታዊ የዝርያዎች ክምችት።**<br><br>**በቅድመ ጥንቃቄ አቀራረብ መሠረት ተጨማሪ ግምገማ እስኪደረግ ድረስ ሌሎች በ HCV 1 መታየት ያለባቸው ቦታዎች፡- በቁልፍ የብዝሀ ሕይወት** | ቁልፍ የብዝሃ ሕይወት ቦታዎች (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) | |

| የHCV 1 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች:- | የመተርጎሚያዎቹን መገኛዎች ለመለየት ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለSLIMF ሊተገበር ይችላል? |
|---|---|---|
| ቦታዎች ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ደኖች እና ሌሎች የአካባቢው ነባር ሥርዓተ ምህዳሮች። | | |
| ዋና ነገሮች 2:- በዓለም አቀፍ፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጠቃሚ የሆኑ ብቸኛ ዝርያዎች ክምችቶች | | |
| የተጠበቁ ቦታዎች፣ የባሌ ሰንሰለታማ ተራሮች፣ እና የቤተ ክርስቲያን ደኖች (መሰረታዊ ነገሮች 1 ይመልከቱ)፣ እና AZE ቦታዎች እና የቀይ ቀበሮ ቦታዎች (መሰረታዊ ነገሮች 3 ይመልከቱ):: (Kimbrough, 2021; Siegel, 2018; Foquet et al, 2019)<br><br>ሌሎች ከፍተኛ ክምችት ያላቸው ብቸኛ የእፅዋት ወይም የእንስሳት ዝርያዎች፤ ለምሳሌ ለአደጋ የተጋለጡ፣ አደጋ ላይ ያሉ፣ ከባድ አደጋ ላይ ያሉ ወይም ለመጥፋት የተቃረብ በብቸኛ ዝርያዎች ያለ ብዛት /population/ እና/ወይም በርካታ በብቸኛ ዝርያዎች ያለ ብዛት /population/። የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ የጮቄ ተራራ፣ ሰሜን ተራሮች፣ የሻላ ሐይቅ፣ ጨበራ ጩርጭራ፣ መናገሻ ሱባ፣ የጣና ሐይቅ ባዮስፌር፣ የአርሲ ተራሮች ፓርክ<br><br>በቅድመ ጥንቃቄ አቀራረብ መሠረት ተጨማሪ ግምገማ እስኪደረግ ድረስ ሌሎች ሊታሰብባቸው የሚገቡ በHCV 1 መታየት ያለባቸው ቦታዎች:- በብቸኛ ወፍ ቦታዎች ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ደኖች እና ሌሎች የአካባቢው ነባር ሥርዓተ ምህዳሮች። | ለነዚህ ትርጓሜዎች BAI በመሰረታዊ ነገሮች 1 እና 3 ላይ ይመልከቱ።<br><br>ብቸኛ የሆኑ የእንስሳት ዝርያዎች ዝርዝሮችን ለማግኘት የ IUCN ቀይ ዝርዝር (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) እና የሚመለከታቸው ብሔራዊ ዝርያዎች ዝርዝሮችን ይመልከቱ፣ ከእነዚህም መካከል: - Vivero et al (2005) እና የ EBI የዱር እንስሳት እና እፅዋት ዝርያዎች ዝርዝር፤ የእንስሳት ብዝሀ ሕይወት ዳይሬክቶሬት፣ ብሔራዊ የብዝሃ ሕይወት ስልት እና የድርጊት መርሀ ግብር (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ)<br><br>ብቸኛ ወፍ ቦታዎች (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) | |
| ዋና ነገሮች 3:- በዓለም አቀፍ፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጣቃሚ የሆኑ ብርቅዬ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ፣ አደጋ ላይ የወደቁ ዝርያዎች ክምችቶች | | |
| የዜሮ መጥፋት ጥምረት Alliance for Zero Extinction (AZE) ጣቢያዎች:- የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ (ለ *Capra walie*)፣ ግልገል አባይ ወንዝ (ለ *Nilopegamys plumbeus*) እና የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ (ለ *Crocidura harenna, Tachyoryctes macrocephalus, Altiphrynoides malcolmi, Balebreviceps hillmani* እና *Ericabatrachus baleensis* )።<br><br>ለቀይ ቀበሮ አስፈላጊ የሆኑ ቦታዎች:- ሰሜን ተራራ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ ጓሳ-መንዝ፣ አርሲ ተራሮች፣ ባሌ ተራሮች። (IUCN, 2011)<br><br>ስንቅሌ መጠለያዎች (ቆርኬ)<br><br>በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የጉራ-ፈርዳ ወረዳ እና ከፋ፣ ሸካ ተራራማ አፍሮሞንቴን ደኖች። (Foquet et al, 2019)<br><br>በ IUCN ቀይ ዝርዝር ወይም በብሔራዊ ዝርያዎች ዝርዝር ውስጥ እንደ ተጋላጭ ፣ ለአደጋ የተጋለጡ ፣ ለከባድ አደጋ የተጋለጡ ወይም ለመጥፋት የተቃረቡ ተብለው የተዘረዘሩ የመሬት እና የንፁህ ውሃ ዕፅዋት ወይም | የቦታዎች ካርታ ለማግኘት AZE ይመልከቱ (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ)።<br><br>ብርቅየ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ፣ እና አደጋ ላይ ያሉ ዝርያዎች ዝርዝሮችን ለማግኘት የ IUCN ቀይ ዝርዝር (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) እና የሚመለከታቸው ብሔራዊ ዝርያዎች ዝርዝሮችን ይመልከቱ፣ ከእነዚህም መካከል: - Vivero et al (2005) እና የ EBI የዱር እንስሳት እና እፅዋት ዝርያዎች ዝርዝር፤ የእንስሳት ብዝሀ ሕይወት ዳይሬክቶሬት (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ)<br><br>CITES (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) | |

| |
|---|
| እንስሳት ዝርያዎች ሌሎች በጉልህ መገኘት። የሚከተሉትን መገኘት ጨምሮ፡- በከፍተኛ ሁኔታ ከተዘረዘሩት በየዝርያዎች ያለ ብዛት ውስጥ ከ1% በላይ የሚሆኑት፣ በርካታ ወይም ከዚያ በላይ ከተዘረዘሩት ዝርያዎች፣ እና/ወይም በልዩ ሥነ ምህዳራዊ ቦታ ውስጥ የተዘረዘሩ ዝርያዎች፣ ለምሳሌ፣ ሰፊ ተደራሽነት ያላቸው ሥጋ-በል ዝርያዎች፣ አመላካች ዝርያዎች፣ ጥላ ዝርያዎች /Umberella trees/፣ በጣም አነስተኛ ቁጥር ወይም ክልል ያላቸው ዝርያዎች እና ሌሎች ቅድሚያ ጥበቃ የሚሰጣቸው ዝርያዎች።<br><br>በ CITES የተዘረዘሩ የእንስሳት ወይም የእፅዋት ዝርያዎች ያሉባቸው ቦታዎች። |

**ለ. የ HCV 1 ግምገማዎች**

| የ HCV 1 ትርጓሜ መገኛዎች ለመገምገም ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች | መገኛዎችን ለመገምገም ከሁሉ ተሽለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም የHCV 1 ትርጓሜዎች: ከላይ የተዘረዘሩትን የHCV 1 ትርጓሜዎች መከሰትን ከመለየት ጋር ፣ ከሌሎች የHCV 1 ክስተቶች ጋር ፣ የመጀመሪያው ፣ አስፈላጊው የግምገማዎች አካል ነው።<br><br>ለሁሉም HCV 1: ሌሎች የግምገማ አካላት የ HCV አካባቢዎችን መለየት ፣ የ HCV ሁኔታ እና ለ HCVዎች ስጋቶች ይገኙበታል። ሊያስከትሉ የሚችሉ አደጋዎች የዱር አራዊትን በሕገ ወጥ ማደን፣ በሕገ ወጥ መንገድ የእርሻ ቦታዎችን ማስፋፋት፣ የዱር እንስሳትና የሰው ልጆች ግጭት፣ የእሳት ቃጠሎ፣ በሕገ ወጥ መንገድ ንብ ማለብ፣ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ዛፎችን መቁረጥ፣ እንዲሁም ለእንጨትና ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች ማምረት።<br><br>ለተጠበቁ አካባቢዎች፡- ፖሊሲዎች እና ልምዶች ቦታውን እና ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶቹን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንደሚጠብቁ ያረጋግጡ። (EBI, 2022b; ሌሎች)<br><br>በደን አስተዳደር አሃድ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ሌሎች የ HCV 1 ምሳሌዎችን ለመለየት እና ለመገምገም ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት የሚከተሉትን ይመልከቱ፡- FSC (2020a) እና HCVRN (2017) (ለምሳሌ ምዕራፍ 2 ለ HCV ግምገማዎች የተሻሉ ልምዶችን በተመለከተ እና ምዕራፍ 3.1 HCV 1 መለየት) | በአንቀጽ A ውስጥ ያለውን BAI እና አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ፣ ከነባር ህዝቦችእና ከሙብት ባለቤቶች እና HCV ጥበቃ ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እንደገና መገናኘት።<br><br>በአንቀጽ ሀ ላይ ያለውን BAI እና አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ ፣ እንደገና ማሰማራትንም ጨምሮ | |

ሐ. **HCV 1 ለመጠበቅ እና ለማሻሻል የሚረዱ ስልቶች**

| የ HCV 1 ትርጓሜዎች ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል የሚረዱ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ስልቶች | ለአስተዳደር ስልቶች ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም የ HCV 1 ትርጓሜዎች: - የጥበቃ ዞኖች፣ የምርት መሰብሰብ መመሪያዎች፣ እና/ወይም በመጥፋት ላይ ያሉ፣ አደጋ ላይ የወደቁ፣ ብቸኛ ዝርያዎች ወይም ሌሎች የስነ ህይወት ብዝሃነት ክምችቶች እና የሚመረኮዙባቸውን ሥነ ምህዳራዊ ማህበረሰቦች እና መኖሪያ ቦታዎች ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሌሎች ስልቶች የመኖሪያ ቦታዎች እና የዝርያዎች መገኘት መጠን፣ አንድነት፣ ጥራት እና ዘላቂነት መቀነስን ለመከላከል በቂ ናቸው። <br><br> ለሁሉም የ HCV 1 ትርጓሜዎች: ማሻሻል እንደ ዓላማ ከተለየ ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ዝርያዎች መኖሪያዎችን ለማሳደግ፣ ለማስፋት እና / ወይም ወደ ነበረበት ለመመለስ እርምጃዎች። | | |
| ለተጠበቁ አካባቢዎች፡- የአስተዳደር እና የማስከበር እቅዶችን ማዘጋጀት እና ተግባራዊ ማድረግ፤ ግልጽ የድንበር ወሰን መከለያዎችን ማቋቋም፤ የአካባቢውን ማህበረሰቦች ስለ ቦታዎቹ ሁኔታ ማስተማር፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማህበረሰቡ ላይ የተመሠረተ እቅድ ማውጣት እና አስተዳደርን መጠቀም፤ ያልተፈቀደ አደን እና የዛፍ መቁረጥ መከላከል፤ የማህበረሰቡን ለማገዶ መሰብሰብን ዘላቂነት ወደ አለው ደረጃ መገደብ፤ ከመሬት ወረራ፣ ከግጦሽ፣ እና ለግብርና ህገ ወጥ የመሬት ማፅዳት /illegal clearing/ የመጋለጥ አደጋዎችን እልባት መስጠት። (Siegel, 2018; ሌሎች) | | |
| ለቤተ-ክርስቲያን ደኖች፡- የድንበር ወሰኖችን መከለል እና የደን ቦታን መጋፋትን መከላከል፤ የዛፎችን መቁረጥ መቆጣጠር፤ የግጦሽ ቁጥጥር ጨምሮ ዳግም ብቅለትን መደገፍ። በተጨማሪም የጠፉ ዝርያዎችን መትከል፤ የደንበር ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ እና የደኖችን መጠን እና የመቋቋም አቅም ለማሳደግ መከላከያ ቦታዎችን /buffers/ ማቋቋም፤ በደኖች መካከል የጥምር እርሻ /agro-forestry/ ግንኙነት መስመሮችን ማቋቋም። (Aerts et al, 2016; AFR100) | የግንኙነት ተነሳሽነቶችና ድጋፍ ምሳሌዎች AFR100 ይመልከቱ (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) እና Plant-for-Ethiopia ፕሮጀክት ይመልከቱ። | |
| ለጉራ-ፈርዳ ወረዳ እና በመንግስት ባለቤትነት እና በጋራ በሚተዳደሩ መሬቶች ውስጥ ለሚገኙ ቦታዎች፡- የ2018 የደን አዋጅ ለጋራ አካላት የባለቤትነት/የይዞታ መብትን የሚሰጥበትን ትክክለኛ አፈፃፀም ማረጋገጥ። (Atmadja et al, 2019; Foquet et al, 2019) <br><br> ለብቸኛ እና ለብርቅየ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ ወይም ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች፡- በአካባቢው ማህበረሰቦች እና በነባር ህዝቦችባህላዊ ምርት መሰብሰብ ዘላቂ ደረጃ ለማምጣት ካልሆነ በስተቀር ምንም ዓይነት አደን የሌለበት ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ። ዝርያዎችን የመጠበቅ እቅዶችን ማዘጋጀት እና ተግባራዊ ማድረግ፡- የዱር እንስሳት ስጋ መሰብሰብ ስጋት በሚፈጥርባቸው አካባቢዎች ለባህል ተስማሚ የሆነ የአካባቢ ትምህርት ይጠቀሙ። (Atmadja et al, 2019; Foquet et al, 2019) | | |

| የ HCV 1 ትርጓሜዎች ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል የሚረዱ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ስልቶች | ለአስተዳደር ስልቶች ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለቀይ ቀበሮ አስፈላጊ ለሆኑ አካባቢዎች፡- የግጦሽ እና የቤት ውሾችን መቆጣጠር፤ የቀንድ-ከብት አስተዳዳሪዎች ጋር በመሆን መርዛማነትን መከላከል፤ ወደ መንገዶች እና እርሻ መቀየር ስጋቶችን እልባት መስጠት። (IUCN, 2011; Siegel, 2018) | በ IUCN (2011) ውስጥ ያሉትን ስልቶች ተመልከቱ | |
| ለብቸኛ እና ለብርቅየ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ ወይም ለአደጋ የተጋለጡ የዛፍ ዝርያዎች፡- ዛፎችን ያለፍቃድ ከመሰብሰብ መጠበቅ፣ እና የዝርያዎቹን በሕይወት መቆየት እና ማገገም ለመደገፍ ቦታውን መያዝ/ማስተዳደር። | | |
| የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ተከላካይ አረንጓዴ ኢኮኖሚ (CRGE) ስትራቴጂ፣ የኢትዮጵያ የባዮዲቨርስቲ ስትራቴጂ እና የድርጊት መርሃ ግብር (EBSAP) ፣ የኢትዮጵያ የደን ልማት፣ የጥበቃ አጠቃቀም ፖሊሲ እና ስትራቴጂ (2007) እና የደን ልማት ጥበቃ አዋጅ (1065/2018) ተግባራዊ ማድረግ<br><br>ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት የሚከተሉትን ይመልከቱ: FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ ክፍል 2)። | በ MEF (2015) ውስጥ ያሉትን ስልቶች ተመልከቱ:: የ MEFCC (2018) ሠንጠረዥ 3 ላይ የተጠቀሱትን የመልሶ መተካት /Restocking/ መስፈርቶች ተመልከቱ። | |

**መ. የ HCV 1 ክትትል**

| የ HCV 1 ትርጓሜዎች ክስተቶች ለመከታተል ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች | ለክትትል ክስተቶች ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| መስፈርት 9.4 እና ጠቋሚዎቹን የሚመለከት ክትትል በተጨማሪም HCV ዎች ላይ ውስጣዊ እና ውጫዊ ስጋቶች ላይ የሚከሰቱ ለውጦችን መከታተል ያስቡ። ለአንዳንድ የ HCV ትርጓሜዎች እና ክስተቶች ቀጥተኛ አመልካቾች ለምሳሌ የዕፀዋትና የእንስሳት ዝርያዎች የመስክ ቅኝት ወይም በአውሮፕላን ቁጥጥር መጠቀም አለባቸው። ለሌሎች ደግሞ ቀጥተኛ ያልሆኑ አመልካቾች በቂ እና የበለጠ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ ለምሳሌ የ RTE ዝርያዎች የመኖሪያ መጠን እና ጥራት ለውጦች። | BAI ን ይመልከቱ | |
| የአካባቢው ማህበረሰቦች እና የነባር ህዝቦችሕዝቦች በጋራ መከታተል መቻል አለባቸው፣ ይህም በጫካ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ተፅእኖዎችን እና ሊከሰቱ የሚችሉ ህገወጥ ወይም ያልተፈቀዱ እንቅስቃሴዎችን መከታተልን ያካትታል። የጋራ ክትትል ምሳሌዎችን ለማግኘት በጋያና ውስጥ የሚገኘውን አይዎክራማ ዓለም አቀፍ ማዕከል እና በጋያና ውስጥ የሰሜን ሩፑኑኒ ወረዳ ልማት ቦርድ ይመልከቱ ። | BAI ን ይመልከቱ | |

| የ HCV 1 ትርጓሜዎች ክስተቶች ለመከታተል ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች | ለክትትል ክስተቶች ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| **እንደ SMART የመሳሰሉ የመረጃ አስተዳደር ስርዓቶች ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።**<br><br>**(https://smartconservationtools.org/)**<br><br>**ለክትትል ፕሮግራሞች ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት የሚከተሉትን ይመልከቱ: FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ ፣ ክፍል 3 ፣ በአንቀጽ 1 ውስጥ ያሉ ሀብቶች እና በአንቀጽ 2 ውስጥ ያሉ የክትትል ቴክኒኮች ምሳሌ)። Lucey et al (2023) እና ሌሎች ሊረዱ ይችላሉ ።** | BAI ን ይመልከቱ | |

**HCV 2 – በመሬት ገጽታ ደረጃ ያሉ ሥርዓተ ምህዳሮች እና ሕብር፡፡ በአለም አቀፍ፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጉልህ የሆኑ እና በተፈጥሯዊ ስርጭትና በብዛት በሚገኙበት ሁኔታ ውስጥ በተፈጥሮ የሚከሰቱትን አብዛኛዎቹን ቀጣይ ዝርያዎች የሚይዙ ያልተነኩ የደን መልክዓ ምድሮች እና ትላልቅ በመሬት ገጽታ ደረጃ ያሉ ሥርዓተ ምህዳሮች እና ሕብሮች።**

በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ ያሉት መረጃዎች ለሁሉም ድርጅቶች ይሠራሉ። የተለየ የሚሆነው በ SLIMFs ወይም ለሌሎች ድርጅቶች ተተግብሮ የማይታየው BAI ነው (>SLIMF)፤ ነገር ግን ትርጓሜዎች፣ ስልቶች እና የግምገማና የክትትል ዘዴዎች አሁንም ተግባራዊ ይሆናሉ። በተጨማሪም ከላይ የተዘረዘሩትን አጠቃላይ የ BAI ዝርዝሮች ይመልከቱ።

**ሀ. የHCV 2 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች ለ HCV መለያ**

| የHCV 2 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች:- | የመተርጎሚያዎቹን መገኛዎች ለመለየት ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ዋና ነገሮች 1:- ያልተነኩ የደን የመሬት ገፅታዎች:- | | |
| ያልተነኩ የደን የመሬት ገፅታዎች (IFLs)፡፡<br>የሼካ ባዮስፌር ሪዘርቭ፣ የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ፣ የቦንጋ ደን ሪዘርቭ፣ የካፋ ባዮስፌር ሪዘርቭ፣ የማጃንግ ባዮስፌር ሪዘርቭ | ለ 2017 የ IFL ካርታዎች; Global Forest Watch IFL ይመልከቱ (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) ። | X |
| ዋና ነገሮች 2:- በአለም አቀፍ፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጉልህ የሆኑ እና በተፈጥሯዊ ስርጭትና በብዛት በሚገኙበት ሁኔታ ውስጥ በተፈጥሮ የሚከሰቱትን አብዛኛዎቹን ቀጣይ ዝርያዎች የሚይዙ ትላልቅ በመሬት ገጽታ ደረጃ ያሉ ሥርዓተ ምህዳሮች:- | | |
| ባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ ሴሚን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ ኖኖ ሴሌ ደን፣ ካፍታ-ሺራሮ ብሔራዊ ፓርክ፣ ጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ፣ አሊታሽ ብሔራዊ ፓርክ፣ ሼካ ባዮስፌር ሪዘርቭ፣ ያዮ ባዮስፌር ሪዘርቭ፣ ካፍፋ ባዮስፌር ሪዘርቭ<br>የጂሎ ሙኪታር ደን፣ የዬጎፍ ተፈጥሮአዊ ደን፣ የዎፍ ዋሻ ደን፣ የያዮ ባዮስፌር ሪዘርቭ፣ የሃሬና ደን፣ የጂባት ደን፣<br>በባሌ ተራሮች በሰሜን ምዕራብ እና በደቡብ ምስራቅ ተዳፋት ላይ የሚገኘው የሀረና ጫካ። (WWF, 2004)<br>12500 ሄክታር ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሌሎች በአንፃራዊነት ያልተነኩ የደን አካባቢዎች። (FSC, 2018a)<br>ጉልህ የሆነ እርጥብ መሬት፡፡ ተጨማሪ ግምገማ እስከሚደረግ ድረስ እንደ HCV 2 የሚወሰዱ:- በተከዜ ሸለቆ (ትግራይ)፣ በባሮ-አኮቦ (ጋምቤላ)፣ በኦሞ-ጊቤ (ደቡብ)፤ የአዋሽ ሸለቆ እና የአማራ ክልል የፎጎራ፣ የደምቢያ፣ የበለስ እና የቦርከና ረግረጋማ ቦታዎች፤ በቤኒ-ሻንጉል ጉምዝ ውስጥ የዳቡስ ወንዝ ረግረጋማ ቦታዎች፤ በኢሉባቦር፣ በከፋ እና በወልጋ ዞኖች እና በማዕከላዊ ሸዋ ተራራማ ቦታዎች ረግረጋማ ስፍራ፤ የቁምቢ ረግረጋማ ቦታ፣ የአልፓይን /alpine/ ሐይቆች እና የባሌ ተራሮች፣ የዝቋላ እና የደብረ-ዘይት ክሬተር /crater/ ሐይቆች፤ በአፋር ክልል ውስጥ የዱብቲ፣ የአፋምቦ፣ የገማሪ እና በአፋር ክልል የአቤ ሐይቅ ረግረጋማ ቦታዎች። (EBI, 2022a) | በ EWNHS and WI (2018) ውስጥ የተዘረዘሩትን እርጥባማ-አካባቢዎች እንመልከት። | |

| የHCV 2 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች፡- | የመተርጎሚያዎቹን መገኛዎች ለመለየት ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ሌሎች ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ እርጥበታማ-ቦታዎች /wetlands/። | | |
| **ዋና ነገሮች 3፡- በአለም አቀፍ፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጉልህ የሆኑ እና በተፈጥሯዊ ስርጭትና በብዛት በሚገኝበት ሁኔታ ውስጥ በተፈጥሮ የሚከሰቱትን አብዛኛዎቹን ቀጣይ ዝርያዎች የሚይዙ የሥርዓተ ምህዳር ሞዛይኮች፡-** | | |
| በቅድመ ጥንቃቄ አቀራረብ መሠረት ተጨማሪ ግምገማ እስኪደረግ ድረስ በ HCV 2 መታየት ያለባቸው ነገሮች፡- የባሌ ሰንሰለታማ ተራሮች፣ የጉራ-ፈርዳ ደን እና ሌሎች በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖች የተለያዩ ከፍታዎችን እና የደን እና የደን ያልሆኑ ሥርዓነ ምህዳሮችን ያጠቃልላል። እንዲሁም የሸካ ደን ባዮስፌር ሪዘርቭ እና የማጃንግ ደን ባዮስፌር ሪዘርቭ። (Foquet et al, 2019; NABU, 2022) | ለሼካ እና ማጃንግ የደን ባዮስፌር ሪዘርቭ የዩኔስኮ ባዮስፌር ሪዘርቭ ይመልከቱ (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ)። | |
| በተለይ እንደ ስነ-ህይወታዊ የግንኙነት መተላለፊያዎች አስፈላጊ የሆኑ አካባቢዎች ለምሳሌ የወንዝ ዳር ደኖች እና በተጎሳቆሉ ወይም በተለወጡ የመሬት ገጽታዎች መካከል በደን ቦታዎች መካከል ያሉ ቦታዎች።<br><br>ሌሎች የደን ሥርዓተ ምህዳሮች በአብዛኛዎቹ የሀገር በቀል ዝርያዎች ብዝሃነት ከሚጠቀሙ ሌሎች የእፅዋት ዓይነቶች ጋር በመሬት ገፅታ ደረጃ ጉልህ የሆነ ሞዛይክ ይፈጥራሉ። | የአፍሪካ የደን መሬት ገፅታ መልሶ ማቋቋም ተነሳሽነትን /African Forest Landscape Restoration Initiative/ ያማክሩ (በማጣቀሻዎች ውስጥ AFR100 ን ይመልከቱ)። | |

ለ. የ HCV 2 ግምገማዎች

| የ HCV 2 ትርጓሜ መገኛዎች ለመገምገም ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች | መገኛዎችን ለመገምገም ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም የኤችሲቪ 2 ትርጓሜዎች: ከላይ የተዘረዘሩትን የHCV 1 ትርጓሜዎች ክስተቶች መለያየት ፣ ከሌሎች የHCV 1 ክስተቶች ጋር ፣ የግምገማዎች የመጀመሪያ እና አስፈላጊ አካል ነው ። <br><br> ለሁሉም HCV 2: ሌሎች የግምገማ አካላት የ HCV አካባቢዎችን መለየት ፣ የ HCV ሁኔታ እና ለ HCVዎች ስጋቶች ይገኙበታል ። ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎች የሕገ ወጥ አደን፣ የእርሻ ቦታዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ማስፋፋት፣ የሰው ልጅና የዱር እንስሳት ግጭቶች፣ እሳቶች፣ በህገወጥ መንገድ ንብ ማነብ ህገወጥ የደን መቆረጥ ለእንጨት እና ለህንፃ ግንባታ። <br><br> ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች፣ በእያንዳንዱ የደን አካባቢ ውስጥ ለ RTE ዝርያዎች ፣ በትላልቅ ያልተነኩ ደኖች ላይ ጥገኛ ለሆኑ ሌሎች ዝርያዎች ወይም ከሌሎች የደን አካባቢዎች ጋር ግንኙነት ላላቸው በተለይ ያልተነኩ ወይም አስፈላጊ የሆኑ ቦታዎችን መለየት። ለተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት የ FSC (2020b) ይመልከቱ። | በእንቀጽ A ውስጥ ያለውን BAI እና አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ፣ ከነባር ህዝቦች ሕዝቦች እና የመብት ባለቤቶች እና በHCV ጥበቃ ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባትን ጨምሮ ። <br><br> አጠቃላይBAIን ይመልከቱ | X |

ሐ. HCV 2 ለመጠበቅ እና ለማሻሻል የሚረዱ ስልቶች

| የ HCV 2 ትርጓሜዎች ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል የሚረዱ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ስልቶች | ለአስተዳደር ስልቶች ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም የ HCV 2 ትርጓሜዎች:- የደን ሥርዓተ ምህዳሮችን መጠን እና አለመነካት ሙሉ በሙሉ የሚጠብቁ ስትራቴጂዎች እና የእፅዋት እና የእንስሳት አመላካች ዝርያዎችን እና/ወይም ከትላልቅ ያልተነኩ የተፈጥሮ የደን ሥርዓተ ምህዳሮች ጋር የተዛመዱ ቡድኖች ጨምሮ የእነሱ የስነ-ህይወት ብዝሃነት ክምችት ዘላቂነት። ለምሳሌ የጥበቃ ዞኖች እና ተለይተው የተቀመጡ ቦታዎች፣ ተለይተው የተቀመጡ ቦታዎች ውስጥ ማንኛውም የንግድ እንቅስቃሴ በማንኛውም ጊዜ የደን መዋቅርን ፣ ጥንቅርን ፣ መልሶ ማገገምን እና የተፈጥሮ ዑደት መረበሽ ንድፍ ሙሉ በሙሉ በሚጠብቁ አነስተኛ መጠን ያላቸው ሥራዎች ብቻ የተገደበ ነው። | የ FSC (2020b) ይመልከቱ። | |
| ለሁሉም የ HCV 2 ትርጓሜዎች: ዓላማው መሻሻል እንደሆነ ከተለየ የደን ሥርዓተ ምህዳሮችን አለመነካታቸውን እና ተፈጥሯዊ ስነ-ህይወታዊ ብዝሃነትን የሚደግፉ መኖሪያ ቦታዎችን መልሶ ለማቋቋም እና እንደገና ለማገናኘት የሚያስችሉ እርምጃዎች ተወስደዋል። <br><br> ለ IFLs:- በደን አስተዳደር አሃድ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ያልተነካ የደን መልክዓ ምድር ዋና አካባቢ የተጠበቀ ሲሆን፣ በደን አስተዳደር አሃድ ውስጥ ካለው ያልተነካ የደን መልክዓ ምድር ቢያንስ 80% የሚሆነውን ያጠቃልላል፤ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለማግኘት | በ EWNHS & WI (2018) ውስጥ ያለውን የጥበቃ እና መልሶ ማቋቋም ምክሮችን ይመልከቱ ። <br><br> የአፍሪካ የደን መሬት ገፅታ መልሶ ማቋቋም ተነሳሽነትን /African Forest Landscape Restoration Initiative/ | |

| የ HCV 2 ትርጓሜዎች ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል የሚረዱ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ስልቶች | ለአስተዳደር ስልቶች ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| አመላካች 9.2.5 እና 9.2.7 ን ይመልከቱ። ዋና አካባቢዎችን ሲወስኑ እና ሲጠብቁ የ FSC (2020b) ምስል 7 እና 8 ይከተሉ፡፡<br>ለትልልቅ እርጥበታማ አካባቢዎች፡፡<br><br>የግንኙነት መተላለፊያዎችን መልሶ ለማቋቋም እና ለመጠበቅ መመሪያ እና ድጋፍ ለመስጠት ።<br><br>ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት የሚከተሉትን ይመልከቱ: FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ ክፍል 2) ። | ያማክሩ (በማጣቀሻዎች ውስጥ AFR100 ን ይመልከቱ)። | |

**መ. የ HCV 2 ክትትል**

| የ HCV 2 ትርጓሜዎች ክስተቶች ለመከታተል ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች | ለክትትል ክስተቶች ከሁሉ ተሸለው የተገኙ መረጃዎች | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም የ HCV 2 ትርጓሜዎች: መስፈርት 9.4 እና ጠቋሚዎቹን የሚመለከት ክትትል ። በተጨማሪም በHCV ዎች ላይ ውስጣዊ እና ውጫዊ ስጋቶች ላይ የሚከሰቱ ለውጦችን ለመከታተል ያስቡ። | አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |
| የአካባቢው ማህበረሰቦች እና የነባር ህዝቦችሕዝቦች በጋራ መከታተል፣ በጫካ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ተፅእኖዎችን እና ሊከሰቱ የሚችሉ ህገወጥ ወይም ያልተፈቀዱ እንቅስቃሴዎችን መከታተል ጨምሮ። (ለተጨማሪ መረጃ HCV 1ን ይመልከቱ)<br>IFLs ን ለመቆጣጠር ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት FSC (2020b) ን ይመልከቱ ።<br>ለክትትል ፕሮግራሞች ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት የሚከተሉትን ይመልከቱ: FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ ፣ ክፍል 3 ፣ በአንቀጽ 1 ውስጥ ያሉ ሀብቶች እና በአንቀጽ 2 ውስጥ ያሉ የክትትል ዘዴዎች ምሳሌ)። | አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |

**HCV 3 *ሥርዓተ-ምህዳሮች እና መኖሪያ ቦታዎች ፣ ያልተለመዱ (ብርቅዬ) ፡ ለአደጋ የተጋለጡ ፡ ወይም የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው ሥነ ምህዳሮች፡ መኖሪያ ቦታዎች ወይም መጠጊያዎች (መሸሸጊያዎች) ።***

በቀጣዮቹ ክፍሎች ውስጥ ያሉት ሁሉም መረጃዎች ለሁሉም ድርጅቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ። ልዩነቱ ለ SLIMFs የሚተገበር ሆኖ ያልተገለፀው BAI ነው፡ ሆኖም ግን ትርጓሜዎች፣ ስልቶች እና የግምገማ እና የክትትል ዘዴዎች አሁንም ተፈጻሚ ይሆናሉ። በተጨማሪም ከላይ የተዘረዘሩትን አጠቃላይ BAI ይመልከቱ ።

***ሀ.* የ HCV 3 *ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች ለ* HCV 3 *መለያ***

| HCV 3 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች | የትርጓሜዎቹን ክስተቶች ለመለየት የሚገኝ ምርጥ መረጃ (BAI)፡- | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| **ዋና ነገር 1፡- ፡- ብርቅዬ፣ ለአደጋ የተጋለጡ ወይም የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው ሥነ-ምህዳሮች** | | |
| **የቤተክርስቲያን ደኖች (HCV 1 ይመልከቱ) እና ሌሎች የተቀሩ የአፍሮሞንታን ደኖች በሰሜን ኢትዮጵያ እና በማዕከላዊ እና በሰሜናዊ ተራራማ ቦታዎች ።(Per: Aerts et al, 2008; Aerts et al, 2016; Cardelus et al, 2013)**<br>**በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በቤንች ሸኮ ዞን የሚገኙ የዝቅተኛ ቦታ ደኖች (ቆላማ ደኖች)። (Per: NABU, 2022)**<br>**የአካሺያ-ኮሚፎራ ዘርዘር ያለ ደን (Acacia-Commiphora woodland ) ስነ-ምህዳር፤ ከተጠበቁ አካባቢዎች ውጭ ፣ የሱብ-አፍሮአልፒን (Sub-Afroalpine) ሥነ ምህዳሮች ፣ ኤሪካ-ሃይፐሪክየም ደን ፣ ደረቅ ሁሌም አረንጓዴ ሞንታኔ ደኖች ፣ በምስራቅ ጋምቤላ ክልል ዝቅተኛ ቦታዎች ደኖች ። በተጨማሪም የሞንታን እርጥብ ደን ሥነ ምህዳሮች ወደ ግብርና ፣ ቡና እና ሻይ እርሻዎች በመቀየር እና ውጤታማ ባልሆኑ የተፈጥሮ / ብሔራዊ የደን ቅድሚያ የሚሰጣቸው አካባቢዎች ስያሜዎች ስጋት ላይ ናቸው ።(Per: EBI, 2022b)**<br>**በቅድመ ጥንቃቄው አቀራረብ መሠረት ተጨማሪ ግምገማ እና የመሬት ማረጋገጫ እስከሚሰጥ ድረስ በHCV 3 መታየት ያለባቸው ፤ ቀደምት ደኖች እና ሌሎች ቀሪ የተፈጥሮ ደኖች እና ዘርዘር ያሉ ደኖች ። (Per: Lett, 2019; others)**<br>**በIUCN ቀይ ዝርዝር ውስጥ ያሉ ስነ-ምህዳሮች፣ የተዘረዘሩ ካሉ (ግምገማ እየተካሄደ ነው።) (Per: IUCNRLE, 2022.)** | ለ 2001 የመጀመሪያ ደረጃ ደኖች ካርታ ፣ ግሎባል ፎረስት ዎች (Global Forest Watch) ይመልከቱ<br>የአይዩሲኤን (IUCN) ቀይ ሥነ ምህዳሮች ዝርዝር (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) ። | |
| **ዋና ነገር 2፡- ብርቅዬ ፤ለአደጋ የተጋለጡ ወይም የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው መኖሪያዎች መኖሪያ ቦታዎች** | | |
| **የባሌ ኤምኤንፒ (MNP) ፣ የሰሜን ኤምኤንፒ (MNP) ፣ የቤርጋ እርጥብ መሬት ፣ የአቢጃታ-ሻላ ሐይቆች ኤንፒ (NP) ፣ ጋምቤላ።**<br>**በቅድመ ጥንቃቄ አቀራረብ መሠረት ከላይ በተጠቀሰው ፍሬ ነገር 1 የተዘረዘሩት የ RTE ሥነ ምህዳሮች እና በHCV 2 የተዘረዘሩት እርጥብ ቦታዎች ተጨማሪ ግምገማ እስኪደረግ ድረስ የ RTE መኖሪያ ቦታዎች ሆነው መታየት አለባቸው ።**<br>**ለአደጋ የተጋለጡ ወይም የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው እና/ወይም ለኤች.ሲ.ቪ. 1 (HCV 1) ብዝሃ ህይወት ወይም ዝርያዎች አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች በጣም ውስን የሆኑ፣ መኖሪያ ቦታዎች እና የመኖሪያ ቦታ ባህሪያት** | | |

| HCV 3 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች | የትርጓሜዎቹን ክስተቶች ለመለየት የሚገኝ ምርጥ መረጃ (BAI)፡- | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ዋና ነገር 3፡- መጠጊያ (መሸሸጊያ) | | |
| ገለልተኛ አካባቢዎች በሰው ልጅ ሰፊ መረበሽ ያልደረሰባቸው እና ለሀገር በቀል ዕፅዋትና እንስሳት ህልውና ወሳኝ የሆኑ<br><br>አንዳንድ የHCV 1 እና የHCV 2 ትርጓሜዎች እንደ መጠጊያ (መሸሸጊያ) ሆነው ሊሠሩ ይችላሉ ፣ ለምሳሌ ፣ የቤተክርስቲያን ደኖች ፣ እርጥብ ቦታዎች ፣ ለኢትዮጵያ ተኩላዎች አስፈላጊ የሆኑ አካባቢዎች ፣ የአንዳንድ የተጠበቁ አካባቢዎች ክፍሎች ፣ ቤርጋ እርጥብ መሬት ፣ ጨቤራ ቸርቹራ ፣ አቢጃታ-ሻላ ሌካ ኤንፒ ፣ ያንጉ ዲራሳ ። | | |

## ለ. የHCV 3 ግምገማዎች

| ብሄራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች የኤች.ሲ.ቪ 3 (የHCV ) ትርጓሜ ክስተቶችን ለመለየት | ክስተቶችን ለመለየት የሚገኝ ምርጥ መረጃ (BAI): | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም HCV 3፡ ትርጓሜዎች፡ ከላይ የተዘረዘሩትን የHCV 1 ትርጓሜዎች መከሰት መለየት፣ ከሌሎች የ HCV 1 ክስተቶች ጋር፣ የመጀመሪያው፣ አስፈላጊ የግምገማ አካል ነው።<br><br>ለሁሉም HCV 3፡ ሌሎች የግምገማ ክፍሎች የ የHCV አካባቢዎችን ፣ የHCVs ሁኔታ እና ለ የ HCV ስጋት መኖሩን ያካትታሉ። ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች አደን ፣ የእርሻ ወረራ ፣ የሰው-የዱር እንስሳት ግጭቶች ፣ የዋንጫ አደን ፣ እሳት ህገ-ወጥ የማር መሰብሰብ ምክንያት እና ለእንጨት እና ለህንጻ ግንባታ ህገ-ወጥ የዛፍ መቁረጥ ያካትታሉ።<br><br>በአስተዳደር አሃድ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ሌሎች (HCV 3) ምሳሌዎችን ለመለየት እና ለመገምገም መመሪያ ለማግኘት የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ያስገቡ - FSC (2020a) እና HCVRN (2017) (ለምሳሌ ፣ ምዕራፍ 2 ፣ ለHCV ግምገማዎች ምርጥ ልምዶች እና ምዕራፍ 3.3 ፣ የHCV 3 መለየት) ። | በክፍል A ውስጥ ያለውን BAI እና አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ ፣ ከነባር ህዝቦችእና ከሙብት ባለቤቶች እና ከ HCV ጥበቃ ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እንደገና መገናኘት ።<br><br>በክፍል A ውስጥ ያለውን BAI እና አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ ፣ እንደገና ማሰማራትንም ጨምሮ | |

### ሐ. HCV 3 ለመጠበቅና ለማሻሻል የሚረዱ ስልቶች

| የኤች.ቪ.ቪ. 3 ን (የHCV 3) ትርጓሜዎች ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ስልቶች: | ለአስተዳደር ስልቶች (ለአስተዳደራዊ ስልቶች) የሚገኙ ምርጥ መረጃ (BAI):- | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም HCV 3 ትርጓሜዎች: ያልተለመዱ ወይም ለአደጋ የተጋለጡ ሥነ-ምህዳሮችን ፣ መኖሪያዎችን ወይም መጠለያዎችን መጠን እና ሙሉ በሙሉ የሚጠብቁ ስልቶች። | | |
| ለሁሉም HCV 3ትርጓሜዎች: ማሻሻያ እንደ አላማው ከታወቀ ፣ ብርቅዬ ወይም አደጋ ላይ የወደቁ ሥነ ምህዳሮችን ፣ መኖሪያዎችን ወይም መጠጊያዎችን (መሸሸጊያዎችን) ለማደስ እና / ወይም ለማዳበር የሚወሰዱ እርምጃዎች አሉ። | | |
| ለተቀሩት ተፈጥሯዊ የደን ሥነ ምህዳሮች:- ወደ ግጦሽ፣ ወደ ግብርና እንዲሁም ወደ ቡናና ሻይ እርሻዎች እንዳይሸጋገሩ ማድረግ። የዛፍ መጨፍጨፍና ሌሎች አጠቃቀሞችን ዘላቂ በሆነ ደረጃ መገደብ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጋራ ባለስልጣናት የባለቤትነት/የግዛት መብቶች እንዲኖራቸው የሚፈቅደውን የ2018 የደን አዋጅን ተግባራዊ ማድረግ። (Per: Hesselden, 2016; EBI 2022b; others) | | |
| ለተጨማሪ መመሪያ፣ግምት ውስጥ ለማስገባት: FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ ክፍል 2) ። | | |

### መ. የHCV 3 ክትትል

| የ የHCV 3 ክስተቶች ትርጓሜዎችን ክትትል ለማድረግ ብሄራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች | ክስተቶችን ክትትል ለማድረግ ከሁሉ ተሸሎ የሚገኝ መረጃ (BAI): | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም የ HCV 3 ትርጓሜዎች: መስፈርት 9.4 እና ጠቋሚዎቹን የሚመለከት ክትትል በተጨማሪም በHCV ቫይረሶች ላይ ውስጣዊ እና ውጫዊ ስጋቶች ላይ ለውጦችን ለመከታተል ያስቡ. | በአጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |
| ለአንዳንድ የ HCV ትርጓሜዎች እና ክስተቶች ቀጥተኛ አመልካቾች ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው;; ለምሳሌ የሥርዓተ ምህዳሮች እና መኖሬያ አካባቢን ሁኔታን በተመለከተ የመስክ ጥናቶች ። ለሌሎች ደግሞ ቀጥተኛ ያልሆኑ አመላካቾች በቂ እና የበለጠ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ ለምሳሌ አመላካች ዝርያዎችን መከታተል | በአጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |
| ለክትትል ፕሮግራሞች ተጨማሪ የክትትል መመሪያዎች, የሚከተሉትን ያስቡበት: FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ ፣ ክፍል 3 ፣ በአንቀጽ 1 ውስጥ ያሉ ሀብቶች እና በአንቀጽ 2 ውስጥ ያሉ የክትትል ዘዴዎች ምሳሌ) | | |

**HCV 4 - ወሳኝ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች፡- በወሳኝ ሁኔታዎች ውስጥ የውሃ ተፋሰሶችን መከላከል እና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የአፈር እና የተዳፋታማ ቦታዎች መሸርሸርን መቆጣጠርን ጨምሮ መሰረታዊ የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ።**

በቀጣዮቹ ክፍሎች ውስጥ ያለው መረጃ ለሁሉም ድርጅቶች ይሠራል ። SLIMFs የሚተገበር ሆኖ ያልተገለፀው BAI ለየት ያለ ነው; ሆኖም ግን ትርጓሜዎች ፣ ስልቶች እና የግምገማ እና የክትትል ዘዴዎች አሁንም ተፈጻሚ ይሆናሉ ። በተጨማሪም ከላይ የተዘረዘሩትን አጠቃላይ BAI ይመልከቱ ።

**ሀ. የHCV 4 ብሄራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች፣ ለ HCV መለያ**

| የብሔራዊ ወይም ክልላዊ የ HCV 4 ትርጓሜዎች: | የትርጓሜዎቹን ክስተቶች ለመለየት የሚገኝ ምርጥ መረጃ (BAI)፡- | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| **ዋና ነገር1፡- በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የውሃ ማጠራቀሚያዎች** | | |
| **ማጠራቀሚያ ፣ የላይኛው አባይ ንዑስ ተፋሰስ (ጣና ሀይቅ)፣ አዋሽ ተፋሰስ፣ ገናሌ ዳዋ ተፋሰስ፣**<br>**"የቤተክርስቲያን ደኖች" (HCV 1 ይመልከቱ) እና ሌሎች የአፍሮሞንታን ደኖች። (Per: Aerts et al, 2016; Ferede, 2017; Cardelus, 2013)**<br>**በአፋር፣ በሶማሌ፣ በትግራይ፣ በአማራ እና በቤኒሻንጉል-ጎሙዝ ክልሎች ያሉ ደረቅ ደኖች ዝናብን በመሳብ እና የጎርፍ አደጋን በመከላከል (Per: Atmadja et al, 2019)**<br>**የባሌ ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ እና ግዙፍ፣ እና ሌሎች በደን የተሸፈኑ ተራሮች እና ተፋሰሶች "የውሃ ግንብ" ሆነው ያገለግላሉ። (Per: Siegel, 2018; WWF, 2004; Lett, 2019; Hesselden, 2016)**<br>**ሌሎች ተፋሰሶች፣ የውሃ አካላት እና የውሃ ምንጮች በአካባቢው ማህበረሰቦች ወይም ነባር ህዝቦች የመጠጥ ውሃ፣ መስኖ፣ ወይም ሌላ የዕለት ተዕለት አጠቃቀም ወይም በሌላ መልኩ ለውሃ አቅርቦት ቅድሚያ የሚሰጣቸው። (HCV 5 ይመልከቱ።)** | HCV 5የ BAI ን ይመልከቱ ። | |
| **ዋና ነገር 2፡- ፡ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የተጋላጭ አፈር እና ተዳፋታማ ቦታዎች መሸርሸርን መቆጣጠር፡-** | | |
| **አፍሮሞንታን ደኖች። (Per: Solomon et al, 2019).**<br>**ለአፈር መሸርሸር የተጋለጡ አካባቢዎች፣ ለምሳሌ፣ 15% ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ተዳፋት ላይ ያሉ የደን ቦታዎች፣ እና/ወይም ያልተረጋጋ አይነት የደን አፈር። (በ፡- FSC፣ 2018a)**<br>**የወንዝ ዳርቻዎችን የሚከላከሉ ደኖች እና ዘርዛራ ደኖች ። (Per: FSC, 2018a)** | የአፈር ካርታዎች፣ የአፈር መሸርሸር ካርታዎች፣ የኢትዮጵያ ተፋሰስ ባለስልጣን፣ የአባይ ተፋሰስ ተነሳሽነት፣ የአፈር እና የውሃ ጥበቃ መዋቅሮች | |

| የብሔራዊ ወይም ክልላዊ የ HCV 4 ትርጓሜዎች: | የትርጓሜዎቹን ክስተቶች ለመለየት  የሚገኝ ምርጥ መረጃ (BAI)፡- | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| **ዋና ነገር 3፡- ፡ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ሌሎች የስነምህዳር አገልግሎቶች፡-** | | |
| የካርቦን ማከማቻ እና ማከማቸት ፣ በአፍሮሞንታን ደኖች እና ዘርዘር ያሉ ደኖች  ውስጥ ጨምሮ ። (በ FSC, 2018a እና 2018b)<br><br>የቤተክርስቲያን ደኖች (HCV 1 ን ይመልከቱ) እና ሌሎች የአፍሮሞንታን ደኖች ፣ ለሙቀት እና ለአየር ንብረት ደንብ ፣ ለአበባ ማራቢያ መኖሪያ ፣ ለማገዶ እንጨት ፣ ለከብት መኖ ፣ ወዘተ ። (በ: Aerts et al, 2016; Ferede, 2017; Cardelus, 2013) | | |
| የቡና ደኖች፣ ማለትም በአንፃራዊነት ተፈጥሯዊ የሆኑ የዱር ቡና ዝርያዎች ማከማቻ የሆኑ ደኖች። (በ: Hesselden, 2016; Aerts et al, 2016)<br><br>የአካባቢው ማህበረሰቦች ወይም የነባር ህዝቦችምግብና መጠለያ ለማግኘት የሚተማመኑባቸው ሌሎች ደኖች። HCV 5 ን ተመልከት)<br><br>ሌሎች የሥነ-ምህዳር አገልግሎቶች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ | HCV 5የ BAI ን ይመልከቱ ። | |

**ለ. የHCV 4 ግምገማዎች**

| የHCV 4 ትርጓሜዎችን ለመገምገም ብሄራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች :- | ክስተቶችን ለመገምገም የሚገኝ ምርጥ መረጃ (BAI): | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| **ለሁሉም HCV 4፡ ትርጓሜዎች፡ ከላይ የተዘረዘሩትን የ HCV 1 ትርጉሞች ለይቶ ማወቅ ከሌሎች HCV 1 ክስተቶች ጋር የመጀመሪያው፣ አስፈላጊ የግምገማ አካል ነው።** | በሴክሽን A ውስጥ ያለውን BAI እና አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ ፣ ከአገሬው ተወላጆች እና ከሙብት ባለቤቶች እና HCV ጥበቃ ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እንደገና መገናኘት ። | |
| **ለሁሉም HCV 4፡ ሌሎች የግምገማ አካላት የ HCV አካባቢዎችን፣ (HCV ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች ይገኙበታል ። ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎች የሚያካትቱት የአፈር መሸርሸር፣ የእርሻ ሥራ ወደ ውኃ መስመሮች እና እርጥብ ቦታዎች፣ የመሰረተ ልማት ልማት ናቸው፡፡** | በአንቀጽ ሀ ላይ ያለውን የ BAI እና አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ ፣ እንደገና ሥራን ጨምሮ | |
| **ለሁሉም HCV 4፡ ትርጓሜዎች፡ ከላይ የተዘረዘሩትን የ HCV 1 ትርጉሞች ለይቶ ማወቅ ከሌሎች HCV 1 ክስተቶች ጋር የመጀመሪያው፣ አስፈላጊ የግምገማ አካል ነው።**<br><br>**ለሁሉም HCV 4፡ ሌሎች የግምገማ አካላት የ HCV አካባቢዎችን፣ (HCV ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች ይገኙበታል ። ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎች የሚያካትቱት የአፈር መሸርሸር፣ የእርሻ ሥራ ወደ ውኃ መስመሮች እና እርጥብ ቦታዎች፣ የመሰረተ ልማት ልማት ናቸው፡፡** | በሴክሽን A ውስጥ ያለውን BAI እና አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ ፣ ከአገሬው ተወላጆች እና ከሙብት ባለቤቶች እና HCV ጥበቃ ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እንደገና መገናኘት ።<br><br>በአንቀጽ ሀ ላይ ያለውን የ BAI እና አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ ፣ እንደገና ሥራን ጨምሮ | |

ሐ. **HCV 4 የመንከባከብ እና የማሳደግ ስልቶች**

| የHCV 4 ትርጓሜዎችን ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል ብሄራዊ ወይም ክልላዊ ስልቶች፡- | ለአስተዳደራዊ ስትራቴጂ የሚገኝ ምርጥ መረጃ (BAI): | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ ወይም ከታች ተፋሰስ ለሚገኙ የአካባቢ ማህበረሰቦች እና በክፍሉ ውስጥ ባሉ አካባቢዎች በተለይም ያልተረጋጋ ወይም ለአፈር መሸርሸር ተጋላጭ ለሆኑ የውሃ ተፋሰሶች: እና የላይኛው አካባቢዎችን ለመጠበቅ የጥበቃ ዞኖች ፤ የመሰብሰብ መመሪያዎች ፤ የኬሚካል አጠቃቀም ገደቦች እና / ወይም የመንገድ ግንባታ እና ጥገና መመሪያዎች ። የውሃ ጥራት ማሻሻል እንደ ግብ ሲታይ የውሃ ጥራት እና ብዛት ለመመለስ የሚያስችሉ እርምጃዎች ተወስደዋል ።<br><br>ለአየር ንብረት ቁጥጥር (ደንብ): የካርቦን ማቆያ እና ማከማቻን ለመጠበቅ (ለማቆየት) ወይም ለማሻሻል ስልቶች አሉ ።<br><br>ለቤተ ክርስቲያን ደኖች፡ የHCV 1 ስልቶችን ይመልከቱ።<br><br>ለሌሎች የአፍሮሞንታን ደኖች እና ደረቅ ደኖች;- ወደ ደን ያልሆኑ የመሬት አጠቃቀሞች እንዳይቀየር ይከላከሉ ። (Per: Solomon et al, 2019)<br><br>ለ "የውሃ ማማዎች" እና ሌሎች በደን የተሸፈኑ ተፋሰሶች: የተፈጥሮ የደን ሽፋንን (የባህር ዛፍ ሳይሆን) መጠበቅ እና ማደስ, የከርሰ ምድር ውሃን መልሶ መሙላት እና ወቅታዊ የውሃ ማጠራቀሚያ ተግባራትን ማቆየት እና ማደስ, እና የደለል ፍሳሽን መገደብ. (Per: Lett, 2019; FSC, 2018a and 2018b) | ለተጨማሪ ጉዳዮች፡ FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ፡ ክፍል 2፡) ይመልከቱ።<br><br>ክፍል 2.3.4 ጨምሮ). | |
| ለቡና ደኖች: HCV 3 ስልቶችን ይመልከቱ እና የካኖፒ ሽፋን የሚጠብቅ ባህላዊ የቡና ምርት መሰበሰብን ይደግፉ ። (በ: Hesselden, 2016; Aerts et al, 2016)<br><br>ለተጨማሪ መመሪያ ግምት ውስጥ ያስገቡ፡<br><br>FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ ክፍል 2) ። | | |

**መ. ለHCV 4 ክትትል ማድረግ**

| የ HCV 4 ትርጓሜዎች ክስተቶችን ክትትል ለማድረግ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች: | ክስተቶችን ክትትል ለማድረግ ምርጥ የሚገኝ መረጃ (BAI) | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም HCV 4 ትርጓሜዎች: መስፈርት 9.4 እና ጠቋሚዎቹን የሚመለከት ክትትል ማድረግ ። በተጨማሪም ለኤችሲቪዎች (HCVs) ውስጣዊ እና ውጫዊ ስጋቶች ለውጦች ለመከታተል ያስቡ ።<br>ለውሃ ጥራት እና ብዛት፣ አፈር እና ሌሎች የስነ-ምህዳር አገልግሎቶች: ክትትልን ግምት ውስጥ ማስገባት የሚገባቸው መሰረታዊ ነገሮች የ FSC (2021b) አባሪ B ይመልከቱ።<br>በክትትል መርሃ ግብሮች ላይ ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት የሚከተሉትን ያስቡ፡- FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ ክፍል 3፣ በአባሪ 1 ውስጥ ያሉ ሃብቶች እና በአባሪ 2 ውስጥ ያለው የክትትል ዘዴዎች (ቴክኒኮች) ምሳሌ)። | በአጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |

**HCV-5፡-መሰረታዊ የሆኑ የማህበረሰብ እና የነባር ሕዝቦች ፍላጎት የሚያሟሉ የደን ቦታዎች እና ሀብት (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ የኑሮ መሰረት፤ውሃ፤ጤና፤ እና ሥርዓተ ምግብ) ከማህበረሰቡ እና ከነባር ህዝቦች ጋር ቀጥተኛ ግንኙት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡**

SLIMFs የሚተገበር ሆኖ ያልተገለፀው BAI ለየት ያለ ነው; ሆኖም ግን ትርጓሜዎች ፣ ስልቶች እና የግምገማ እና የክትትል ዘዴዎች አሁንም ተፈጻሚ ይሆናሉ ። በተጨማሪም ከላይ የተዘረዘሩትን አጠቃላይ BAI ይመልከቱ ።

**ሀ. (ከፍተኛ ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖችን HCV-5 ለመለየት የሚያገለግሉ ብሔራዊ እና ቀጠናዊ መገለጫዎች**

| (ከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV-5 አለም አቀፋዊ እና ቀጣናዊ ትርጓሜ | ለከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች ለመለየት የሚያስችል ከደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ | ከደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ በ SLMFP ላይ ያገለግላል፡፡ |
|---|---|---|
| የመጀመሪያ ክፍል- Sመሰረታዊ የሆኑ የማህበረሰብ እና የነባር ህዝቦችን ፍላጎት የሚያሟሉ የደን ቦታዎች እና ሀብት (ለምሳሌ የማህበረሰብ የኑሮ መሰረት፤ውሃ፤ጤና፤ እና ሥርዓተ ምግብ) | | |
| የፍል ውሃ ምንጭ፤( አምቦ፤ወሊሶ፤ሸበሌ፤ሶደሬ) የኮንሶ አፈር እና ውሃ ጥበቃ ስራ፤ የኦሮሞ ኢሬቻ የባህል ስርአት፡ የቦረና ግጦሽ መሬት ( የቦረና መሕበረሰብ)፤ካፋ፤ሸካ እና ኢሉአባቦራ ደን፤ የጉንዶን ባህል<br>የተፋሰስ፤ወንዝ፤ምንጭ፤ሌላ የሚጠጣ ውሀ፤ለመስኖ ምንጭ<br>የማገዶ፣ የጫካ ቡና፣ የእጣን እና ሙጫ ምንጭ ሆኑ የቆላማ እና ደረቅ ደን ( ነጭ እጣን፤ከርቤ እና የአረቢያ እጣን)፤ የደን ማር ፤ መድሃኒት እና የሚበሉ የዱር ፍራፍሬዎች ለደን ማህበረሰብ ኑሮ መሰረት እና የገቢ ምንጭ የሚሆኑ፡፡ ይህ አደን፤ህጋዊ ያልሆነ ደን መሰብሰብን አይጨምርም፡፡<br>(Per: Lett, 2019; Siegel, 2018; Tadese, 2016; Aerts et al, 2016; Atmadja et al, 2019; Ferede, 2017)<br>ይህ ምልከታ ያላየው (ከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV-5፡ ዩ.ኒ.ስ.ኮ የብዝሃሂዎት ቦታዎች እንደ ካፋ፤ያዩ ፤ሸካ ፤ መጃንግ ደን፤ ታና ሃይቅ . (Per: ዋቢ ሰነድ, UNESCO Biosphere Reserves) | ከአከባቢው ማህበረሰብ ጋር የሚፈጠር የባህል ቁርኝት<br>ተጨማሪ የደን ከደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ ከ ካርታ፡ ከባለሞያዎች እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጆች ሊገኝ ይችላል፡፡ | |
| ሁለተኛ ክፍል- Sመሰረታዊ የሆኑ የማህበረሰብ እና የነባር ህዝቦችን ፍላጎት የሚያሟሉ የደን ቦታዎች እና ሀብት (ለምሳሌ የማህበረሰብ የኑሮ መሰረት፤ውሃ፤ጤና፤ እና ሥርዓተ ምግብ) | | |
| የቦረና የግጦሽ ፡ አፋር እና ሶማሌ ዝቅተኛ ቦታዎች፤ የጣና ሀይቅ( የወይጦ ማህበረሰብ)፤ የኢሬቻ ( ተራራ ፤ወንዝና እና ሀይቅ) ሸካ እና ጉዶ ደን ( ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ)<br>ለመጀመሪያ ክፍል- የ(ከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV-5 አለም አቀፋዊ እና ቀጣናዊ ትርጓሜ በተጨማሪ ይመልከቱ ፡ ተወሰኑ የአካባቢው ማህረሰብ በነዚህ አይነቶች የደን እና ተፈጥሮ ሀብት ላይ ጥገኛ ናቸው፡፤ | ከአከባቢው ማህበረሰብ ጋር የሚፈጠር የባህል ቁርኝት<br>ተጨማሪ የደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ ከካርታ፡ ከባለሞያዎች እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጆች ሊገኝ ይችላል፡፡ | |

ለ. ከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች HCV-5 ዳሰሳ

| አለም አቀፋዊ እና ቀጣናዊ የ(ከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV-5 ዳሰሳ እና ምልከታ የሚያገለግሉ አመላካቾች | ለከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች ለመሌት እና ዳሰሳ አመለካች ከደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ | ከደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ በ SLMFP ላይ ያገለግላል |
|---|---|---|
| ሁሉም የከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV-5 ፡ የከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV-5 ብዛት ዳሰሳ እና ልየታ መገለጫዎች እነደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡ ከሌሎች HCV-5 ብዛት ጋር እንደአስፈላጊነቱ ያገልግላል፡፡ | ከአከባቢው ማህበረሰብ ጋር የሚፈጠር የባህል ቁርኝት | |
| ለሁሉም የከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV-5 ሌላ የዳሰሳ ስራ የሚያካትታቸው እና ሁሉንም በጥበቃ ውስጥ የሚካተቱ ባለድርሻ አካላትን ይጨምራል፡<br><br>እነዚህን ለሁሉም የከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ ኢነቨስተሮች ለባህላዊ እና ለአካባቢው ማህበረሰብ እሴቶች ምንም እውቅና የማይሰጡትን፤ የደን እሳት አደጋን እና ደን ምንጣሮን የሚያከናውኑትን ያካትታል፡፡ | ተጨማሪ የደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ ከካርታ፡ ከባለሞያዎች እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅች ሊገኝ ይችላል፡፡ ተጨማሪ የደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ የ ከፍል-ሀን መልከቱ | |
| HCV-5 ትርጉም፤ የአሳታፊ ደን ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ማካሄድ፤ ይህ ካርታ የሚከተለው HCV-5 ቦታዎችን በአስተዳደር እቅድ ውስጥ በማስገባት ባህላዊ እሴት ያላቸውን ቦታዎች ማስጠበቅ፤ የ FPIC ኢኒሼቲቭ ጥበቃ ቦታዎችን ከካርታ በፊት በዳሰሳ መለየት | የአካባቢ ማህበረሰብ እና ነባር ህዝቦች | |
| በቦታው ሌሎች የደን ጥበቃ ስራዎችን ማጠናከር ለምሳሌ የማገዶ እንጨት ለቀማ፤እጣንና ሙጫ እና ሌላ ዘላቂ ጥቅም ሚያስገኙ ስራዎቸን ብዝሃ ሂዎቱን እና HCV-5 በማይጎዳ መልኩ ማካሄድ፡፤ | | |
| HCV-5 ለመጠበቅ ሌላ የዳሰሳ ስራ በማሰብ ማከናወን፤ FSC (2020a) and HCVRN (2017) (e.g., Chapter 2, Best Practice Considerations for HCV Assessments, and Chapter 3.5, Identification of HCV 5). | | |

ሐ. የከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV ለመጠቅ እና ለማሳደግ የሚያስችል ስልት

| አለም አቀፋዊ እና ቀጣናዊ የከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV ለመጠቅ እና ለማሳደግ የሚያስችል ስልት | ለከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች ለመሌት እና ዳሰሳ አመለካች ከደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ | ከደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ በ SLMFP ላይ ያገለግላል |
|---|---|---|
| ለሁሉም የከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV-5 መገለጫዎችን መግለጽ፤<br>ማንኛውንም አካባቢውን የሚጠቅሙ የደን ልማትና ጥበቃ ስራና ስልት የአካባበቢውን ማህበረሰብ እና ከነባር ህዝቦች አሳታፊ በሆነ መልኩ በማኔጅምንት አሃድ ውስጥ መካተት አለበት<br>ማናቸውም የደን ቦታ እና ሃብት ከነባር ህዝቦች ጋር በተመለከተ፡ የደን ልማትና ጥበቃ ስራና ስልት የአባቢውን ህግ ወይም የነባር ህዝቦችን መብቶችን ታሳቢ ባለደረገ መልኩ ይከናወናል፡፡ (Per: IWGI, 2022).<br>በደን ውስጥ ላሉ የጫካ ቡና፡ በደን ልማት ስልት በHCV 3 እና 4<br>ለሙጫና እጣን ምርት ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውሉ የቆላማ ቦታዎች ደን፡ የማድማትና የዛፍ ቆረጣ ወደ ዘላቂ ደረጃ መገደብ፤ እንዲሁም በቂ ዳግም ብቅለትን ያረጋግጡ Per: Atmadja et al, 2019)<br>**ለተጨማሪ ማብራሪያ,ይመልከቱ**: FSC (2020a) and HCVRN (2018) (ለምሳሌ,ክፍል 2). | የአካባቢ ማህበረሰብ እና ነባር ህዝቦች | |

መ. (ከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV-5 የቁጥጥር ስርዓት

| አለም አቀፋዊ እና ቀጣናዊ የከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች) HCV ለመጠቅ እና ለማሳደግ የሚያስችል ስልት | የደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ ለከፍተኛ የደን ጥበቃ እሴት ያላቸው ደኖች ለመሌት እና ዳሰሳ አመለካች | የደን የሚገኝ ምርጥ መረጃ በ SLMFP ላይ ያገለግላል |
|---|---|---|
| ለሁሉም የከፍተኛ የተፈጥሮ እሴት ያላቸው ደኖች HCV-6 ትርጓሜዎች፡ መስፈርት 9.4 እና ጠቋሚዎቹን የሚመለከት ክትትል ማድረግ፡በተጨማሪም ውስጣዊ እና ውጫዊ የሆኑ የ HCV-6 ስጋቶች ላይ የሚከሰቱ ለውጦች መከታተል ያስፈልጋል፡፡ | አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |
| ከአከባቢው ማህበረሰብ ወይም ከነባር ሕዝቦች ጋር የተያያዙ HCV-6 ጉዳዮችን በተመለከተ: በአከባቢው ማህበረሰብ ወይም ከነባር ሕዝቦች ጋር የሚደረግ ክትትል ወይም በባህላዊ ተስማሚ ተሳትፎ ከእነሱ ጋር በመተባበር የተዘጋጁ ዘዴዎችን በመጠቀም ። የአካባቢው ማህበረሰቦች ወይም የነባር ሕዝቦች የማያካሂዱት (የማይተገብሩት) ከሆነ ክትትሉ በእነሱ ማረጋገጥ አለበት ። | አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |
| ለሁሉም HCV-6 ትርጓሜዎች: ክትትል ለማድረግ ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ምክንያቶች የጣቢያዎች እና የተፈጥሮ ሀብት ሁኔታ ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መዳረሻው በቂ መሆን አለመሆኑን ፣ የጣቢያዎቹ ምስጢራዊነት ተገቢ ሆኖ ሲገኝ መከላከሉን እና HCV-6 ክስተቶችን በተመለከተ የትኛውም ግጭት መጠን እና ተፈጥሮን ያካትታሉ ።<br><br>ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት FSC (2020a) እና HCVRN (2018) (ለምሳሌ ፣ ክፍል 3) እና በአንቀጽ 1 ውስጥ ያሉትን መረጃዎች ይመልከቱ ። | አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |

**HCV -6 ባህላዊ እሴቶች የአካባቢ ማህበረሰቦች ወይም የነባር ሕዝቦች ባህላዊ ባህሎች ወሳኝ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ሃይማኖታዊ/ቅዱስ ጠቀሜታ ያላቸው ዓለም አቀፍ ወይም ብሔራዊ ባህላዊ፣ አርኪኦሎጂያዊ ወይም ታሪካዊ ጠቀሜታ ያላቸው እና/ወይም በእነዚህ ከአካባቢ ማህበረሰቦች ወይም ከነባር ሕዝቦች ጋር በመተባበር የተለዩ ቦታዎች፣ ሀብት፣ መኖሪያዎች እና የመሬት ገጽታዎች፤**

በቀጣዮቹ ክፍሎች ውስጥ ያሉት ሁሉም መረጃዎች ለሁሉም ድርጅቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ። SLIMFsየሚተገበር ሆኖ ያልተገለፀው BAI ለየት ያለ ነው; ሆኖም ግን፤ ትርጓሜዎች፣ ስልቶች እና የግምገማ እና የክትትል ዘዴዎች አሁንም ተፈጻሚ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከላይ የተዘረዘሩትን አጠቃላይ BAI ይመልከቱ፡፡

**ሀ. የ HCV 6 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች ለ HCV መለያ**

| የ HCV 6 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች: | : ከሁሉ ተሸለው የሚገኙ መረጃዎች ለትርጓሜዎች ከስተቶች ለመለየት | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ዋና ነገር 1፡- ዓለም አቀፋዊ ወይም ብሔራዊ ባህላዊ፣ አርኪኦሎጂያዊ ወይም ታሪካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች፣ ሀብቶች፣ መኖሪያ ቦታዎችና የመሬት ገጽታዎች | | |
| ሶፉማር / ሼክ ሁሴን) ፣ ሆራ ሀርሴዴ ፣ ላሊቤላ ሮቼዮን ቤተክርስቲያን ፣ አክሱም ፣ ፋሲል ቤተመንግስት ፣ የአፋር ኩንትር ሀዳር አርኪኦሎጂካል ጣቢያ ፣ ሜልካ ፣ ኤኬብሪጂያ ካፔንሲስ (ሼካ) ፣ ፊኩስ ሲኮሞረስ (ኦዳ አሮሞ) ፣ አካሲያ ቶርቲሊስ (ቦሬና) ፣ ጉዶ ፣ ኮዶ ፣ ባህላዊ ጣቢያ ።<br>በባህላዊ፣ በአርኪኦሎጂያዊ ወይም በታሪካዊ እሴቶች የተሰየሙ የዓለም ቅርስ ቦታዎች።<br>ተጨማሪ ግምገማ እስኪደረግ ድረስ ለዓለም ቅርስነት የሚቀርቡ ቦታዎች ባህላዊ ፣ አርኪኦሎጂያዊ ወይም ታሪካዊ እሴቶች በተጨማሪም ታና ሐይቅ ባዮስፌር ሪዘርቭ ፣ የሸካ ደን ባዮስፌር ሪዘርቭ ፣ የካፋ ባዮስፌር ሪዘርቭ ፣ ማጃንግ ደን ባዮስፌር ሪዘርቭ ፣ ያዩ ቡና ባዮስፌር ሪዘርቭ ።<br>ሌሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ወይም በብሔራዊ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸው ባህላዊ ፣ አርኪኦሎጂያዊ ወይም ታሪካዊ ቦታዎች ፣ ሀብት ፣ መኖሪያዎች ወይም የመሬት ገጽታዎች<br>ሌሎች ገና እውቅና ያልተሰጣቸው ዓለም አቀፍ ወይም ብሔራዊ አስፈላጊ የሆኑ የአርኪኦሎጂ ቦታዎች (Per: Walker, 2018; Katz, 2019) | የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ቦታዎች (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) ።<br>የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ቦታዎች (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) እና የዩኔስኮ የባዮስፌር መጠባበቂያዎች (ማጣቀሻዎችን ይመልከቱ) ።<br>የመረጃ ቋቶች እና የባለሙያ ድርጅቶች (የባለድርሻ አካላት እና የባለሙያዎች ዝርዝር ይመልከቱ) ። | |
| ዋና ነገር 2፡- ለአካባቢው ማህበረሰቦች ልማዳዊ ባህሎች ወሳኝ የሆነ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ሃይማኖታዊ/ቅዱስ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች፣ ሀብት፣ መኖሪያ ቦታዎችና የመሬት ገጽታዎች | | |
| ሆራ ሀርሴዴ (የኦሮሞ ኢሬቻ ፣ ጉዶ (የኩዶ ጣቢያ) ፣ አርዳ ጂላ ጌዳ ስርዓት ፣ የኮንሶ ማህበረሰብ መንደር ፣ ሜ ቦኩ ፣ ባህላዊ ፣ ሥነ ምህዳራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ወይም | ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በባህላዊ አግባብነት ያለው ግንኙነት.<br>ተጨማሪ BAI የመረጃ ቋቶችን፣ ካርታዎችን እና ባለሙያዎችን ሊያካትት ይችላል፣ | |
| ለአካባቢው ማህበረሰቦች ሃይማኖታዊ/ቅዱስ ጠቀሜታ አለው።<br>ለሁሉም ትርጓሜዎች | ለምሳሌ የማህበረሰብ ልማት ድርጅቶች | |

| የ HCV 6 ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ትርጓሜዎች: | : ከሁሉ ተሸለው የሚገኙ መረጃዎች ለትርጓሜዎች ከስተቶች ለመለየት | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| **አካል/ክፍል 3፡- ዓለም አቀፋዊ ወይም ብሔራዊ ባህላዊ፣ አርኪኦሎጂያዊ ወይም ታሪካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች፣ ሀብቶች፣ መኖሪያ ቦታዎችና የመሬት ገጽታዎች** | | |
| የቦረና ማህበረሰብ-ያቤሎ፣ የአውራ አምባ ማህበረሰብ-የአውራ አምባ ማህበረሰብ፣ የኮንሶ ማህበረሰብ-ባህላዊ መንደር፣ የጉጂ ማህበረሰብ- ሜቦኩ<br><br>ለነባር ሕዝቦች ባህላዊ ፣ ሥነ-ምህዳራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ሃይማኖታዊ / ቅዱስ ጠቀሜታ ያላቸው ጣቢያዎች ፣ ሀብቶች ፣ መኖሪያዎች ወይም የመሬት ገጽታዎች ።<br><br>ለሁሉም ትርጓሜዎች | ከባህላዊ አግባብነት ጋር በተያያዘ ከነባር ህዝቦች ጋር መግባባት.<br><br>ተጨማሪ BAI የመረጃ ቋቶችን ፣ ለነባር ሕዝቦች የሚወክሉ ወይም አገልግሎቶችን የሚሰጡ ድርጅቶችን እና አርኪኦሎጂስቶችን እና አንትሮፖሎጂስቶች | |

**ለ. HCV 6 ግምገማዎች**

| የ HCV 6 ክስተቶችን ለመገምገም ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች ትርጓሜዎች: | ክስተቶችን ለመገምገም ከሁሉ ተሸሎ የተገኘ መረጃ | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| **ለሁሉም HCV 6: ከላይ የተዘረዘሩትን የ HCV 6 ትርጓሜዎች መገኘትን መለየት ፣ ከማንኛውም ሌሎች የ HCV 6 ክስተቶች ጋር ፣ የግምገማዎች የመጀመሪያ እና አስፈላጊ አካል ነው** | ለኤሌመንት 2 እና 3 ለአካባቢው ማህበረሰቦች እና ለነባር ህዝቦች አስፈላጊ የሆኑ ኤች.ሲ.ቪዎች ከህብረተሰቦች እና ከነባር ህዝቦችጋር በባህላዊ ተገቢነት ያለው ተሳትፎ ዋናው የ BAI ነው ፡፡ ለኤለመንት 1 እና ለኤለመንት 2 እና 3 ተጨማሪ BAI ክፍል A እና አጠቃላይ BAI ይመልከቱ | |
| **ለሁሉም HCV 6: ሌሎች የግምገማ አካላት የሚከተሉትን ያካትታሉ: በ HCV ጥበቃ ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መገናኘት; እና የ HCV አካባቢዎችን መለየት ፣ የ HCVs ሁኔታ እና ለ HCVs ስጋቶች ፡፡ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎች በገጠር አካባቢዎች ያሉ የውጭ ባለሀብቶች የአካባቢውን ህዝብ ባህላዊ እሴቶች ፣ የእርሻ ግጭቶች ፣ የደን ቃጠሎዎች እና የቦታ መዳረሻ ገደቦችን አለማወቅን ያካትታሉ።** | በ A ክፍል ውስጥ ያለው BAI እና አጠቃላይ BA | |
| **ለ 2 እና 3 ንጥረ ነገሮች ለህብረተሰቦች እና ለነባር ህዝቦችአስፈላጊ የሆኑ ኤች.ሲ.ቪዎች-ከአካባቢው ማህበረሰቦች እና ከነባር ህዝቦች ጋር በይነተገናኝ ካርታዎችን ያስቡ ፡፡ በባህላዊ ስሜታዊ ጣቢያዎች ላይ ችግር እንዳይፈጠር በጠቅላላው የኤች.ሲ.ቪ እና የአስተዳደር እቅድ ሂደት መጀመሪያ ላይ ካርታውን ማዘጋጀት ያስቡበት። እንዲሁም ከካርታ እና ግምገማ ሂደት በፊት የ FPIC ውይይቶችን ለመጀመር ያስቡ** | ማህበረሰቦች እና የነባር ህዝቦች፣ ሽማግሌዎችን ወይም ሌሎች አባላትን ጨምሮ ሚስጥራዊነቱ ሊጠበቅባቸው ስለሚገባቸው ቦታዎች እውቀት ሊኖራቸው ይችላል፣ ለምሳሌ፣ የመቃብር ቦታዎች፣ ቅዱስ ቦታዎች፣ ወዘተ | |
| **ገና እውቅና ያልተሰጣቸው የአርኪኦሎጂ ቦታዎች: በአካባቢው ባለሙያዎች፣ በአካባቢው ሽማግሌዎች እና/ወይም በመስክ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚካሄዱ የመስክ ጥናቶች (Per: Walker, 2018)** | | |

### ሐ. HCV 6ን ለማስቀጠልና ለማሻሻል የሚረዱ ስልቶች

| የ HCV 6 ክስተቶችን ለመገምገም ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች ትርጓሜዎች: | ክስተቶችን ለመገምገም ከሁሉ ተሸሎ የተገኘው መረጃ | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ከነባር ህዝቦች እና/ወይም ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በተያያዘ የHCV ክስተቶች: ባህላዊ እሴቶችን ለመጠበቅ ስትራቴጂዎች ከአካባቢው ማህበረሰቦች እና ከነባር ሕዝቦች ተወካዮች እና አባላት ጋር በመተባበር ይዘጋጃሉ<br>ከነባር ሕዝቦች ጋር በተያያዘ የHCV ክስተቶች: ስልቶች ነባር ህጎች የነባር ህዝቦችን መብቶች እውቅና ወይም ጥበቃ ያደርጋሉ ብለው ማሰብ የለባቸውም። (Per IWGI ፣ 2022)<br>ለሌሎች የHCV ክስተቶች (ማለትም በዋነኝነት በዓለም አቀፍ ወይም በብሔራዊ ጠቀሜታ ምክንያት ለተለዩ) ስልቶች በተሻለ መረጃ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ፣ እናም HCV ን ለማቆየት እና / ወይም ለማሻሻል ውጤታማ እንደሆኑ ይቆጠራሉ።<br>For additional guidance, consider: FSC (2020a) and HCVRN (2018) (e.g., Part 2). | የአካባቢው ማህበረሰቦችና የነባር ሕዝቦች | |

### መ. የ HCV 6 ክትትል

| የ HCV 6 ክስተቶችን ለመከታተል ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ዘዴዎች ትርጓሜዎች: | ክስተቶችን ለመከታተል ከሁሉ የተሻለው መረጃ፡ | BAI ለ SLIMFም ይሠራል? |
|---|---|---|
| ለሁሉም HCV 6 ትርጓሜዎች: መስፈርት 9.4 እና ጠቋሚዎቹን የሚመለከት ክትትል በተጨማሪም ለኤችሲቪዎች ውስጣዊ እና ውጫዊ አደጋዎች ለውጦችን ለመከታተል ያስቡ ። | አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |
| ከአከባቢው ማህበረሰብ ወይም ከነባር ህዝቦች ጋር የተያያዙ የHCV ጉዳዮችን በተመለከተ: በአከባቢው ማህበረሰብ ወይም ከነባር ህዝቦች ጋር የሚደረግ ክትትል ወይም በባህላዊ ተስማሚ ተሳትፎ ከእነሱ ጋር በመተባበር የተዘጋጁ ዘዴዎችን በመጠቀም ። በአካባቢው ማህበረሰቦች ወይም በነባር ህዝቦች ያልተካሄደ ክትትል በእነሱ ማረጋገጥ አለበት ። | አጠቃላይ BAI ን ይመልከቱ | |
| ለሁሉም HCV 6 ትርጓሜዎች: ክትትል ለማድረግ ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ምክንያቶች የጣቢያዎች እና ሀብቶች ሁኔታ ፣ አስፈላጊ ከሆን በቂ መዳረሻ ይኑርዎት ፣ የጣቢያዎች ምስጢራዊነት አስፈላጊ ከሆነ የተጠበቀ መሆኑን እና የ HCV ክስተቶችን በተመለከተ የትኛውም ግጭት መጠን እና ባህሪን ያካትታሉ<br>ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት የሚከተሉትን ተመልከት፡-FSC (2020a) and HCVRN (2018) (e.g., Part 3), and the resources in Annex 1)." | See the Overarching BAI | |

**አግባብነት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎች ምሳሌዎች፤**

(ይህ በአጠቃላይ ወይም በተወሰኑ HCV ምድቦች ወይም አካላት ለ **HCV** ግምገማዎች ፣ ስልቶች እና / ወይም ክትትል አግባብነት ሊኖራቸው የሚችሉ የባለድርሻ አካላት እና የባለሙያ ድርጅቶች ዝርዝር ነው ። ዝርዝሩ የተሟላ አይደለም ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ መለወጥ ሊያስፈልገው ይችላል ፣ እና በደረጃ ገንቢዎች ሊዘመን ይችላል። ተጨማሪ ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎች ለተወሰኑ የአመራር ክፍሎች አስፈላጊ ከሆኑ እነሱም መወሰን እና በአመራሮች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው ።)

**የአካባቢ ባለድርሻ አካላት**

- የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት እና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (EWNHS)
- የዓለም ደኖች፣ የምሥራቅ አፍሪካ ጽሕፈት ቤት
- ግሪን ፒስ አፍሪካ
- የዱር እንስሳት ጥበቃ ማህበር
- WWF ኬንያ/ROA አፍሪካ
- የኢትዮጵያ ተኩላ ጥበቃ ፕሮግራም
- ጉሌሌ የዕፅዋት የአትክልት ስፍራ (የአካባቢው ባዮሎጂያዊ ብዝሃነት)
- IUCN የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ ክልላዊ ቢሮ (ESARO)
- የናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ፣ ኬንያ
- ወንዶ ገነት የደን ልማት እና የተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ
- ማህበራዊ ባለድርሻ አካላት እና የማህበረሰብ ልማት ድርጅቶ
- የኢትዮ ዌትላንድስ እና የተፈጥሮ ሀብት ማህበር (EWNRA)
- የኢትዮጵያ ቡና ደን ፎረም (ECFF)
- የደን ልማት ህብረት ስራ ማህበራት
- የደን አርሶ አደሮች ህብረት
- የኮንሶ ልማት ማህበር (KDA)
- የቤተ ክርስቲያን እርዳታ ኮሚሽን (EOC-DICAC)
- ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅቶች፣ ኢትዮጵያ
- የተፈጥሮ እና የባዮዲቨርስቲ ጥበቃ ህብረት (NABU) ።

**ሌሎች አካባቢያዊ ባለሙያ እና ድርጅቶች፤**

- የኢትዮጵያ ተኩላ ጥበቃ ፕሮግራም
- ጉሌሌ የዕፅዋት የአትክልት ስፍራ (የአካባቢው ባዮሎጂያዊ ብዝሃነት)
- የአለም ህብረቱ የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ ክልላዊ ቢሮ (ESARO)
- የናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ፣ ኬንያ
- ዋንዶ ገነት የደን ልማት እና የተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ

**ሌሎች የማህበራዊ ድርጅቶች ባለሙያዎች፡**

- የባህል ቅርስ ምርምርና ጥበቃ ኤጀንሲ

- የአርኪኦሎጂና ቅርስ አስተዳደር መምሪያ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
- የታሪክና አርኪኦሎጂ መምሪያ፣ ናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ፣ ኬንያ
- የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
- የአክሱም ዩኒቨርሲቲ የአርኪኦሎጂና ቅርስ ፕሮግራም

**የመንግስት ድርጅቶች (ኤጀንሲዎች)**

- የአካባቢ፣ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን (EFCCC)
- የኢትዮጵያ የባዮዲቨርስቲ ኢንስቲትዩት (EBI)
- የኢትዮጵያ አካባቢና ደን ምርምር ተቋም (ኢኢአር)
- የኢትዮጵያ ጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ
- የፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን
- የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን (EWCA) ፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
- የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የባህላዊ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን
- የክልል የመንግስት ኤጀንሲዎች

## References


- *(Relevant references may include weblinks or full references for BAI listed above, as well as supporting references for HCV Interpretations.)*
- Aerts et al. 2008. Land rehabilitation and the conservation of birds in a degraded Afromontane landscape in northern Ethiopia.
- Aerts, R., Lerouge, F., November, E. et al. Biodiversity Conservation 17. 2008. https://doi.org/10.1007/s10531-007-9230-2.
- Aerts et al. 2016. Conservation of the Ethiopian church forests: Threats, opportunities and implications for their management. Aerts, R., Van Overtveld, K., November, E., Wassie, A., et al. Science of The Total Environment, vols 551-552. 2016. https://doi.org/10.1016/j.scitotenv.2016.02.034.
- Alliance for Zero Extinction. For a map of sites, see: https://zeroextinction.org/site-identification/2018-global-aze-map/ (at the “country” tab, select “Ethiopia”).
- AFR100. African Forest Landscape Restoration Initiative. See: https://afr100.org/content/building-green-corridors-biodiversity-ethiopia.
- Atmadja et al. 2019. Guidelines on sustainable forest management in drylands of Ethiopia. Atmadja S, Eshete A and Boissière M. FAO. 2019. https://www.fao.org/3/ca3699en/ca3699en.pdf
- Aynekulu et al. 2016. Plant diversity and regeneration in a disturbed isolated dry Afromontane forest in northern Ethiopia. Aynekulu, E., Aerts, R., Denich, M., et al. Folia Geobot, 51. 2016. https://doi.org/10.1007/s12224-016-9247-y

- Buechley et al. 2021. Buechley, E., Giradello, M., Santangeli, A., Ruffo, A., et al. Priority areas for vulture conservation in the Horn of Africa largely fall outside the protected area network. Cambridge University Press. July 21, 2021. https://www.cambridge.org/core/journals/bird-
- conservation-international/article/priority-areas-for-vulture-conservation-in-the-horn-of-africa-largely-fall-outside-the-protected-area network/644A624D7879275496AD5698747F7149.
- Cardelús et al. 2013. Preliminary Assessment of Ethiopian Sacred Grove Status at the Landscape and Ecosystem Scales. Cardelús, C., Scull, P., Hair, J., Baimas-George, M., et al. Diversity, 5. 2013. https://canopymeg.com/wp- content/uploads/2019/01/2013Cardelusetal.Diversity.pdf.
- CITES. For list search, see https://www.speciesplus.net/species.
- EBI. Ethiopian Biodiversity Institute. https://ebi.gov.et/. For the Animal Biodiversity Directorate, see: https://ebi.gov.et/directorates/animal-biodiversity-directorate/. For a list of Biodiversity Centers and Botanical Gardens, see https://ebi.gov.et/directorates/management-members/.
- EBI. 2022a. Webpage on Ethiopian wetlands. Information accessed May, 2022. https://ebi.gov.et/biodiversity/diversity-of-ecosystem/wetland-ecosystem/.
- EBI. 2022b. Webpage on Ethiopian Ecosystems. https://ebi.gov.et/. Information accessed May, 2022.
- Endemic Bird Areas. For a list of areas with links to more information, see: http://www.datazone.birdlife.org/eba/results?cty=68&sn=&fc=&cri=. For a map, see http://www.datazone.birdlife.org/country/ethiopia/ebas or https://www.globalforestwatch.org/map/ (at "Biodiversity Layers," select "Endemic Bird Areas").
- EWNHS & WI. 2018. A First Directory of Ethiopian Wetlands: Descriptions, Ecosystem Services, Causes of Degradation & Recommendations for Restoration and Sustainability. Ethiopian Wildlife and Natural History Society and Wetlands International. 2018. https://africa.wetlands.org/en/download/5026/.
- Ferede. 2017. Integrated Assessment of ecosystem services, stakeholder dependence and incentives for sustainable management of the Chilmo forest, Ethiopia. MSc Thesis in Environmental Science. Ferede, A. Environmental Systems Analysis group, Wageningen University. January, 2017. https://edepot.wur.nl/527704.
- Foquet et al. 2019. Express Biodiversity Survey in Gura-Ferda Forest, Ethiopia. Express Report
- 8. Biodiversity Inventory for Conservation. Foquet, R., Kassie, A., De Beenhouwer, M. Biodiversity Inventory for Conservation. 2019. https://www.binco.eu/wp- content/uploads/2019/04/BES8-Gura-ferda-forest-1.pdf.
- FSC. 2017. FSC Glossary of Terms. FSC-STD-01-002. October 19, 2017. https://fsc.org/en/document-centre/documents/resource/207.
- FSC. 2018. FSC International Generic Indicators. FSC-STD-60-004 V2-0 EN. https://fsc.org/en/document-centre/documents/resource/262.
- FSC. 2018a. The FSC National Forest Stewardship Standard of the Republic of Uganda. Forest Stewardship Council. March 2018. https://fsc.org/en/document-centre/documents/resource/304.

- FSC. 2018b. FSC National Forest Stewardship Standard for Tanzania Mainland. Forest Stewardship Council. July 2018. https://fsc.org/en/document-centre/documents/resource/289.
- FSC. 2021b. Ecosystem Services Procedure: Impact Demonstration and Market Tools. FSC- PRO-30-006 V1-2. *https://connect.fsc.org/document-centre/documents/resource/316.*
- FSC. 2020a. High Conservation Value Guidance for Forest Managers. FSC-GUI-30-009 V1-0 EN. https://fsc.org/en/document-centre/documents/resource/422.
- FSC. 2020b. Intact Forest Landscapes Guidance for Forest Managers. FSC-GUI-30-010 V1-0 EN. https://fsc.org/en/document-centre/documents/resource/424.
- FSC. 2021. FSC Guidelines for the Implementation of Free, Prior and Informed Consent. FSC-GUI-30-003. V2.0. March 9, 2021. https://fsc.org/en/document-centre/documents/resource/332.
- FSC. 2021b. Guidance for Demonstrating Ecosystem Services Impacts. FSC-GUI-30-006 V1-1. October 1, 2021. https://fsc.org/en/document-centre/documents/resource/336.
- FSC. 2021c. Interim National Standard of Kenya. FSC-STD-KEN-01-2021 EN. https://fsc.org/en/document-centre/documents/retrieve/4cff2911-3266-4b3f-a1d9-b3253ce118ba.
- GFW - IFL. For a map of Intact Forest Landscapes, click on “Intact Forest Landscapes” at the “Land Cover” tab at: https://www.globalforestwatch.org/map/. To see IFLs as of 2017, look at both the green areas labeled as “Intact Forest Landscapes” (as of 2020) and the dark brown areas labeled “reduction in extent 2016-2020.” For downloadable data layers for 2016/2017, see:http://intactforests.org/data.ifl.htmland http://data.globalforestwatch.org/datasets/7dc2af9bf4e2404393f673e603aa9351_4
- Global Forest Watch – Primary.Primary Forest map. https://www.globalforestwatch.org/map/ (at “land cover,” select “primary forest”).
- HCVRN. 2017. Common Guidance for the Identification of High Conservation Values. High Conservation Value Resource Network. October 2013, amended September, 2017. https://hcvnetwork.org/library/common-guidance-for-the-identification-of-high-conservation-values/.
- HCVRN. 2018. Common Guidance for the Management and Monitoring of High Conservation Values. High Conservation Value Resource Network. September, 2014, amended April, 2018. https://hcvnetwork.org/library/common-guidance-for-the-management-and-monitoring-of-hcv/.
- Hesselden. 2016. Ethiopia’s vulnerable tropical forests are key to securing future of wild coffee. Commentary at the University of Huddersfield. Hesselden, F. October 10, 2016.
- https://news.mongabay.com/2016/10/ethiopias-vulnerable-tropical-forests-are-key-to-securing-future-of-wild-coffee/.
- Important Bird Areas. For maps, see http://datazone.birdlife.org/site/mapsearch and for custom search: http://datazone.birdlife.org/site/search.
- IUCN. 2011. Strategic plan for Ethiopian wolf Conservation. IUCN/SSC Canid Specialist Group. 2011. https://portals.iucn.org/library/efiles/documents/2011-090.pdf

- UCN Red List. See https://www.iucnredlist.org/search. Searches can be done by country and species' assessment status. Click on each species for basic information on their status, range, threats, etc
- IUCN Red List of Ecosystems. See http://iucnrle.org/assessments/; and http://iucnrle.org/resources/published-assessments/.
- IUCNRLE. 2022. News: Red List of Ecosystems: Advance in Africa. February 23, 2022. https://iucnrle.org/news/red-list-of-ecosystems-advances-in-africa.
- IWGI. 2022. Webpage on indigenous peoples in Ethiopia. International Work Group for Indigenous Affairs. https://www.iwgia.org/en/ethiopia/714-indigenous-peoples-in-ethiopia.html. Information accessed May, 2022.
- Katz. 2019. Archaeologists Uncover Evidence of an Ancient High-Altitude Human Dwelling. Katz, B. Smithsonian Magazine. August 9, 2019. https://www.smithsonianmag.com/smart-news/found-earliest-evidence-high-altitude-home-humans-180972878/.
- Key Biodiversity Areas. For maps, see https://www.keybiodiversityareas.org/sites/search; click on each KBA for more information. Maps are also available by clicking on "Key Biodiversity Areas" at the "Biodiversity" tab at: *https://www.globalforestwatch.org/map/*.
- Kimbrough. 2021. Spiny new chameleon species described from Bale Mountains of Ethiopia. Kimbrough, L. Mongabay. April 6, 2021. https://news.mongabay.com/2021/04/spiny-new-chameleon-species-described-from-bale-mountains-of-ethiopia/
- Lett. 2019. In Ethiopia, women and faith drive effort to restore biodiversity. Lett, C. Mongabay. March 20, 2019. https://news.mongabay.com/2019/03/in-ethiopia-women-and-faith-drive-effort- to-restore-biodiversity/
- MEF. 2015. Study of Causes of Deforestation and Forest Degradation in Ethiopia and the Identification and Prioritization of Strategic Options to Address Those. Ministry of Environment and Forest. 2015. https://reddplusethiopia.files.wordpress.com/2015/05/national-study-on-drivers- of-deforestation-and-forest-degradation-ethiopia-final.pdf
- MEFCC. 2018. National Potential and Priority Maps for Tree-Based Landscape Restoration in Ethiopia (version 0.0): Technical Report. Ministry of Environment, Forest and Climate Change. 2018. https://assets.forest-atlas.org/eth/documentation/MEFCC-Ethiopia-National-Landscape-Restoration_high-res.pdf
- MRG. 2022. Webpage on Ethiopia. Minority Rights Group International. https://minorityrights.org/country/ethiopia/. Information accessed May, 2022.
- NABU. 2022. Webpage on forests in Southwest Ethiopia. https://en.nabu.de/topics/regional-development/forests-for-future.html. Information accessed May, 2022.
- Protected Areas. For an overview map, with links to more information on each area, see: https://www.protectedplanet.net/en/country/ETH
- Siegel. 2018. Pressure Mounting for the Home of Wild Coffee and Ethiopian Wolves. Siegel, N. Mongabay. December 18, 2018. https://news.mongabay.com/2018/12/pressure-mounting-for-the-home-of-wild-coffee-and-ethiopian-wolves/

- Solomon et al. 2019. Ecosystem Service Values Changes in Response to Land-Use/Land- Cover Dynamics in Dry Afromontane Forest in Northern Ethiopia. Solomon, N., Segnon, A., Birhane, E. International Journal of Environmental Research and Public Health. 16(23). 2019. https://doi.org/10.3390/ijerph16234653
- Tadese. 2016. The People of Ethiopia's Forests. Tadese, M.H. Mongabay. November 15, 2016. https://news.mongabay.com/2016/11/the-people-of-ethiopias-forests/
- UNESCO Biosphere Reserves. See: https://en.unesco.org/biosphere/africa#ethiopia.For Kafa Biosphere Reserve, see: https://en.unesco.org/biosphere/africa/kafa. For Yayu Biosphere Reserve, see: https://en.unesco.org/biosphere/africa/yayu. For Sheka Forest Biosphere Reserve, see: https://en.unesco.org/biosphere/africa/sheka. For Lake Tana Biosphere Reserve, see: https://en.unesco.org/biosphere/africa/lake-tana. For Majang Forest Biosphere Reserve, see: https://en.unesco.org/biosphere/africa/majang-forest
- UNESCO World Heritage Sites. For an overview map, see: https://whc.unesco.org/en/list/?search=&id_states=et&order=country. Sites designated primarily for natural values: Simien National Park, https://whc.unesco.org/en/list/9. Sites designated primarily for cultural or archaeological values: Rock-Hewn Churches, Lalibela, https://whc.unesco.org/en/list/18; Fasil Ghebbi, Gondar Region, https://whc.unesco.org/en/list/19; Aksum, https://whc.unesco.org/en/list/15; Lower Valley of the Awash, https://whc.unesco.org/en/list/10; Lower Valley of the Omo, https://whc.unesco.org/en/list/17; Tiya, https://whc.unesco.org/en/list/12; Harar Jugol, the Fortified Historic Town, https://whc.unesco.org/en/list/1189; Konso Cultural Landscape, https://whc.unesco.org/en/list/1333. For proposed sites, see: https://whc.unesco.org/en/tentativelists/state=et; sites include: Bale Mountains National Park; Dirre Sheik Hussein Religious, Cultural and Historical Site; Gedeo Cultural Landscape; Holqa Sof
- Omar: Natural and Cultural Heritage (Sof Omar: Caves of Mystery); Lake Tana Island Monasteries and its Adjacent Wetland Natural and Cultural Heritages; Melka Kunture and Balchit; Sacred Landscapes of Tigray; The Cultural Heritage of Yeha.
- Vivero et al. 2005. Red List of Endemic Trees and Shrubs of Ethiopia and Eritrea. Vivero, J., Kelbessa, E., Demissew, S. IUCN, Fauna & Flora International, and Global Trees Campaign.2005https://globaltrees.org/wpcontent/uploads/2013/10/RedlistEthiopiaEritrea.pdf
- Walker. 2018. Ethiopia must overhaul archaic heritage system to protect ancient treasures. Walker, S. Ethiopia Insight. October, 29, 2018. https://www.ethiopia-insight.com/2018/10/29/ethiopia-must-overhaul-archaic-heritage-system-to-protect-ancient-treasures/
- NBSAP Project. 2005. National Biodiversity Strategy and Action Plan, December 2005Wiki. 2022. Web page on Indigenous Peoples. https://en.wikipedia.org/wiki/List_of_Indigenous_peoples#Horn_of_Africa. Information accessed May, 2022.
- WWF. 2000. DGIS-WWF Tropical Forest Portfolio Newsletter. 2000.
- WWF. 2004. DGIS-WWF Tropical Forest Portfolio Newsletter. May 2004.

## አባሪ ተ.    መዝገበ ቃላት

ለቃላት መደበኛ ትርጓሜዎች በ FSC-STD-01-002 የቃላት መዝገበ ቃላት ውስጥ ተሰጥተዋል። ይህ መዝገበ ቃላት በተቻለ መጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን ትርጓሜዎች ያካትታል። እነዚህ ምንጮች ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት የምግብና ግብርና ድርጅት (FAO) ፣ አለም አቀፍ ብዝሃ ሕይወት ስምምነት ሰነድ እ.ኤ.አ (1992)፤ የ2005 የሚሊኒዬም ሥነ ምህዳር ምልከታ ሰነድ፤ ከአለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት (IUCN)፣ በዓለም አቀፍ የሰራተኛ ድርጅት (ILO) እና የአለም አቀፍ ብዝሃ ሕይወት ስምምነት የመጤ ወራሪዎች ዝርያ ፕሮግራም ድረ-ገጾች ላይ ከተሰጡት የመስመር ላይ መዝገበ ቃላት ትርጓሜዎችን ያካትታሉ። ሌሎች ምንጮች ጥቅም ላይ ሲውሉ እነሱም በዚህ መሠረት ተጠቅሰዋል።

የ ‘በ....ላይ የተመሠረተ’ /Based on/ የሚለው ቃል አገላለጽ ትርጓሜው በዓለም አቀፍ ምንጭ ውስጥ ከተሰጠው ነባር ትርጓሜ የተወሰደ ነው።

በዚህ የቃላት መዝገበ-ቃላት ወይም በሌሎች የ FSC ሰነዶች ውስጥ ካልተገለጹ፣ በአለም አቀፍ አጠቃላይ አመልካቾች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት በአጭሩ አክስፎርድ እንግሊዝኛ መዝገበ-ቃላት ወይም እጥር ምጥን ባለዉ ኦክስፎርድ መዝገበ-ቃላት ውስጥ እንደተገለጹ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

**ዋና ንጥረ ነገር/Active ingredient:** ለፀረ-ተባይ ስራ ሚያገለግል ዋና ግባት (Source: FAO International Code of Conduct on Pesticide Management).

**ከሁኔታዎች ጋር የሚስማማ አስተዳደር /Adaptive management:** አሁን ካሉት እርምጃዎች ውጤት በመማር የአስተዳደር ፖሊሲዎችን እና ልምዶችን ያለማቋረጥ የማሻሻል ስልታዊ ሂደት (Source: FSC-STD-01-001 V5-2, based on International Union for Conservation of Nature (IUCN). Glossary definitions as provided on IUCN website).

**በተጨማሪነት/Additionality:**

በተጨማሪነት ከአስተዳደር አሃድ ውጭ ያሉ/Additionality outside the Management Unit:

- የድርጅቱ ድጋፍ እና/ወይም ሥራ ባይኖር ኖሮ ሊሳካላቸው የማይችል ቀደም ሲል ከተገኘው ወይም ሊገኝ ከታሰበው በላይ ጥበቃ እና/ወይም መልሶ ማቋቋም ውጤቶች
- ካለሆነም ፕሮጀክቶች አዲስ መሆን አለባቸው/Projects must either be new

(ማለትም ፣ ቀድሞውኑ እየተተገበረ ወይም የታቀደ አይደለም) ፣ የተሻሻሉ ወይም የተራዘሙ ስለሆነም የጥበቃ እና / ወይም የመልሶ ማቋቋም ውጤቶች ከተገኙት በላይ የተሻሻሉ ናቸው ፣ ወይም ድርጅቱ ለታሪካዊ ልወጣ ለማስተካከል ዕቅድ ከሌለው ሊገኝ ወይም ሊገኝ የታቀደ ወይም የገንዘብ ድጋፍ የተደረገበት።

**የሚመለከታቸው ባለመብቶች/Affected Rights Holder:** የአስተዳደር ውሳኔዎችን ለመወሰን ነፃ ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት የሚጠየቁ የሕግ ወይም ልማዳዊ መብቶች ያላቸው ነባር ሕዝቦችሕዝቦች/Indegenous people/፣ ባህላዊ ሕዝቦችን እና የአካባቢ ማህበረሰቦችን ጨምሮ ግለሰቦች እና ቡድኖች።

**የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት/Affected stakeholder**: ማንኛውም ሰው፣ የግለሰቦች ቡድን ወይም ድርጅት በአስተዳደር አሃድ ተግባራት ተፅዕኖ የተጋለጠ ወይም ሊጋለጥ የሚችል ነው። ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ, ነገር ግን አይገደቡም (ለምሳሌ  ታችኛው ተፋሰስ ላይ ያሉ የመሬት ባለቤቶች) ፣ በአስተዳደር አሃዱ አከባቢ ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች፣ የግለሰቦች ቡድኖች ወይም አካላት። የተጎዱ ባለድርሻ አካላት ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው:-

- የአካባቢ ማህበረሰብ/Local communities
- ነባር ሕዝቦች/Indigenous Peoples
- ሰራተኞች/ Workers
- በደን ዉስጥ ነዋሪዎች/Forest dwellers
- ጎረቤቶች/ Neighbours
- የታችኛው ተፋሰስ የመሬት ባለቤቶች/ Downstream landowners
- የአከባቢዉ አቀናባሪዎች/ Local processors
- በአከባቢዉ የሚገኙ ንግዶች/ Local businesses
- የመሬት ስሪት እና የመጠቀም መብት ያላቸዉ፣ የመሬት ባለቤቶችን ጨምሮ/ Tenure and use rights holders, including landowners
- የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላትን ወክለው እንዲንቀሳቀሱ የተፈቀደላቸው ወይም ሕጋዊ ድርጅቶች /ለምሳሌ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣ የሰራተኛ ማህበራት ፣ ወዘተ/ Organizations authorized or known to act on behalf of affected stakeholders, for example social and environmental NGOs, labour unions, etc.

(Source: FSC-STD-01-001 V5-2).

**አዎንታዊ እርምጃ/ Affirmative action:** እንደ ትምህርት እና ሥራ ውስጥ እኩል ዕድልን ለማረጋገጥ ንቁ እርምጃዎችን በመውሰድ ያለፈውን መድልዎ ለማስተካከል የሚፈልግ ፖሊሲ ወይም ፕሮግራም። (Source: FSC report on generic criteria and indicators based on ILO Core Conventions principles, 2017).

**መጤ ዝርያዎች/Alien species**: ከዚህ ቀደም ከተፈጥሮአዊ ስርጭቱ ወይም አሁን ካለው ስርጭቱ ውጭ የመጡ ዝርያ፣ ንዑስ ዝርያ ወይም ዝርያዎች ሊራቡ የሚችሉም ማናቸውም የተክል ክፍሎች፣ ጋሜቶች፣ ዘሮች፣ እንቁላሎች ወይም ቁርጥራጮች ይገኙበታል፡፡ (Source: Convention on Biological Diversity (CBD), Invasive Alien Species Programme. Glossary of Terms as provided on CBD website)

**ተፈጻሚነት ያለዉ ሕግ/Applicable law**: ለድርጅቱ እንደ ህጋዊ ሰው ወይም ለንግድ ድርጅት በአስተዳደር አሃዱ ውስጥ ወይም ለእሱ ጥቅም የሚተገበሩ መንገዶች እና የ FSC መርሆዎችን እና መመዘኛዎችን አፈፃፀም ተጽኖ የሚያሳድሩ ሕጎች። ይህ ህጋዊ ህግን (በፓርላማ የፀደቀ) እና የችሎት ህግን (የፍርድ ቤት ትርጓሜዎች) ፣ ተዳዳኝ ደንቦችን ፣ ተዳዳኝ የአስተዳደር ሂደቶችን እና በሌሎች ህጋዊ መሳሪያዎች ላይ ሁል ጊዜ ህጋዊ ቅድሚያ የሚሰጠውን ብሔራዊ ህገ-መንግስትን (የሚኖር ከሆነ) ያጠቃልላል። (Source: FSC-STD-01-001 V5-2).

**ዉሃ የሚፈልቅበት አለት/Aquifer**: አንድ ስብስብ ፣ የቡድን ስብስቦች ፣ ወይም የስብስብ ክፍል በቂ የሆነ የተሞላ የሚያሳልፍ አካል የያዘ ሲሆን በዚያ ክፍል ውስጥ እንደ የውሃ ምንጭ ሆኖ ኢኮኖሚያዊ እሴት እንዲኖረው ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃ ወደ ጉድጓዶች እና ምንጮች የሚፈስ ።

(Source: Gratzfeld, J. 2003. Extractive Industries in Arid and Semi-Arid Zones. World Conservation Union (IUCN).

**የተሻለ መረጃ /Best Available Information፡-** መረጃ፣ እውነታዎች፣ ሰነዶች፣ የባለሙያዎች አስተያየቶች፣ እና የመስክ ዳሰሳ ጥናቶች ወይም ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ውጤቶች በጣም ተዓማኒነት ያላቸው፣ ትክክለኛ፣ ሙሉ እና/ወይም አግባብነት ያላቸው እና በተመጣጣኝ ጥረት እና ወጪ ሊገኙ የሚችሉ፣ እንደ ልኬቱ እና ጥንካሬ ተገገር የአስተዳደር ተግባራት እና የጥንቃቄ አቀራረብ።

**አስገዳጅ ስምምነቶች/ Binding Agreement:** አባል ሃገራት ወይም ባለድረሻ አካለትን ተገዥ የሚያደርጉ በጽሁፍ ወይም በሰነድ ተዘጋጅተው ወይም በቃላለት ስምምነት በህግ የሚተገበሩ አሰራሮች፡፡

**ሥነ ሕይወታዊ መቆጣጠሪያዎች /Biological control agents:** የሌሎችን ተሕዋሳት ብዛት ለማስወገድ ወይም ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ ተሕዋሳት። (Source: Based on FSC-STD-01-001 V4-0 and World Conservation Union (IUCN). Glossary definitions as provided on IUCN website).

**የሥነ ሕይወት ብዝሃነት/Biological diversity :** ከሁሉም ምንጮች የመጡ ሕያዋን ፍጥረታት ልዩነት፤ ይህም ከምድር፣ ከባህር እና ከሌሎች የውሃ ሥነ ምህዳሮች እንዲሁም የተለያዩ ሥነ ምህዳራዊ ውስብስብ አካላትን ያጠቃልላል፤ ይህም በዝርያ ውስጥ፣ በዝርያዎች መካከል እና በሥነ ምህዳሮች ብዝሃነት ያጠቃልላል። (Source: Convention on Biological Diversity 1992, Article 2).

**ጸረ ተባይ መድሃኒት/Chemical pesticide/፡** በሰው ሰራሽ የተሰራ ፀረ ተባይ መድሃኒት(Source: FSC-POL-30-001 V3-0).

**ልጅ/ Child /:** ማንኛውም ግለሰብ ከ 18 አመት በታች ሆነ (ILO Convention 182, Article 2).

**የጋራ ድርደር/Collective bargaining/:** በሥራ ፈጣሪዎች ወይም በአሠሪዎች ድርጅት እና በሠራተኞች ድርጅት መካከል በጋራ ስምምነቶች አማካይነት የቅጥርና የሥራ ስምሪት ሁኔታዎችን ለማስተካከል በፈቃደኝነት የሚደረግ ድርድር። (ILO Convention 98, Article 4).

**ሚስጥራዊ መረጃ/Confidential information/:** የግል እውነታዎች፣ መረጃዎች እና ይዘቶች ለህዝብ ይፋ ቢደረጉ ለድርጅቱ፣ ለንግድ ፍላጎቱ ወይም ከባለድርሻ አካላት፣ ደንበኞች እና ተፎካካሪዎች ጋር ላለው ግንኙነት አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ

**በመርሆች እና መስፈርቶች እና ህጎች መካከል የሚፈጠሩ ተቃርኖዎች /Conflicts between the Principles and Criteria and laws/**: መርሆዎቹን እና መስፈርቶቹን እና ህግን በአንድ ጊዜ ማክበር የማይቻልባቸው ሁኔታዎች (Source: FSC-STD-01-001 V5-2).

**መገናኛ/ Connectivity/:** ኮሪዶር፣ አውታረ መረብ ወይም ማትሪክስ ምን ያህል የተገናኘ ወይም በቦታ ውስጥ ቀጣይነት ያለው እንደሆነ የሚለካ መለኪያ ነው። ክፍተቶች አነስተኛ ሲሆኑ ግንኙነቱ ከፍ ያለ ይሆናል። ከመዋቅራዊ ትስስር ፅንሰ-ሀሳብ ጋር የተዛመደ; ተግባራዊ ወይም የባህሪ ትስስር የሚያመለክተው አንድ አካባቢ ለሂደቱ ምን ያህል እንደተገናኘ የሚያስ ነው ፣ ለምሳሌ እንስሳ በተለያዩ የመሬት ገጽታ አካላት ውስጥ ሲንቀሳቀስ፣ የውሃ ትስስር በሁሉም ዓይነት የውሃ ሥነ-ምህዳሮች የተለያዩ ክፍሎች መካከል በከርሰ ምድር ውሃ እና በምድር ላይ በሚፈስ ውሃ በኩል ቁሳቁሶች እና ኦርጋኒኮች ተደራሽነት እና መጓጓዣን ይመለከታል። (Source: Based on R.T.T. Forman. 1995. Land Mosaics. The Ecology of Landscapes and Regions. Cambridge University Press, 632pp).

**የጥበቃ ቦታዎች መረብ/Conservation Areas Network/:** ከአስተዳደር አሃዱ ንዑስ ክፍሎቹ ዋና እና በአንዳንድ ሁኔታዎች ብቸኛ ዓላማው ጥበቃ ነው፤ እነዚህ አካባቢዎች ወኪል ናሙና ያላቸው አካባቢዎች፣ የጥበቃ ዞኖች፣ የጥበቃ አካባቢዎች፣ የግንኙነት አካባቢዎች እና ከፍተኛ የጥበቃ ዋጋ ያላቸው አካባቢዎች ናቸው።

**ጥበቃ/ መከላከል /Conservation/Protection/:** እነዚህ ቃላት የተለዩ የአካባቢ ወይም የባህል እሴቶችን ለረጅም ጊዜ ለማቆየት የታቀዱ የአስተዳደር ተግባራትን ሲያመለክቱ በተለዋጭነት ያገለግላሉ። የአስተዳደር ተግባራት ከዜሮ ወይም አነስተኛ ሥራ እስከ የተወሰኑ ተገቢ ሥራዎች እና እነዚህን የተለዩ እሴቶች ለማቆየት የተነደፉ ወይም ለማቆየት የሚስማሙ ተግባራት ሊሆኑ ይችላሉ። (Source: FSC-STD-01-001 V5-2).

**የጥበቃ ዞኖች እና የከለላ ቦታዎች/Conservation zones and protection areas/ :** በተፈጥሮ አካባቢያዊ ወይም ባህላዊ እሴቶቻቸው አንፃር በዋነኛነት ዝርያዎችን፣ መኖሪያዎቻቸዉን፣ ስነ-ምህዳሮችን፣ የተፈጥሮ ባህሪያትን ወይም ሌሎች ቦታ-ተኮር እሴቶቻቸውን ለመጠበቅ የተሰየሙ እና የሚተዳደሩ የተወሰኑ አካባቢዎች ወይም ለክትትል ፣ ለግምገማ ወይም ለምርምር ዓላማዎች ሌሎች የአስተዳደር ተግባራትን ሳይከለክል። ለመሠረታዊ መርሆዎች እና መመዘኛዎች ዓላማዎች፣ እነዚህ ቃላት በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ ይውላሉ፣ አንዱ ሁልጊዜ ከሌላው የላቀ የጥበቃ ወይም የጥበቃ ደረጃ እንዳለው ሳያሳዩ። ለእነዚህ ቦታዎች 'የተከለለ ቦታ' የሚለው ቃል ጥቅም ላይ አይውልም, ምክንያቱም ይህ ቃል በብዙ አገሮች ውስጥ በብሔራዊ ደንቦች የተሸፈነ ህጋዊ ወይም ኦፊሴላዊ ሁኔታን ያመለክታል። በመሠረታዊ መርሆዎችና መስፈርቶች መሠረት የእነዚህ አካባቢዎች አስተዳደር ንቁ ጥበቃን እንጂ ተለዋዋጭ ጥበቃን ማካተት የለበትም። (Source: FSC-STD-01-001 V5-2).

**መለወጥ/Conversion/:** በሰው ተግባራት ምክንያት የተፈጥሮ የደን ሽፋን ወይም ከፍተኛ የጥበቃ ዋጋ ያላቸው አካባቢዎች ዘላቂ ለውጥ። ይህም በከፍተኛ የዝርያ ብዝሃነት፣ የመኖሪያ አካባቢ ብዝሃነት፣ መዋቅራዊ ውስብስብነት፣ የስነ-ምህዳር ተግባራዊነት ወይም የኑሮ እና ባህላዊ እሴቶች በማጣት ሊታወቅ ይችላል። የመለዉጥ ትርጓሜው ቀስ በቀስ የደን መመናመንን እንዲሁም ፈጣን የደን ለውጥን ይሸፍናል። (Source: FSC-POL-01-007 V1-0).

- **በሰዎች ተግባር የሚከሰት/** Induced by human activity/**:** እንደ አውሎ ነፋስ ወይም የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ባሉ የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ከሚከሰቱ ከባድ ለውጦች በተቃራኒው። እንዲሁም በተፈጥሮ በተቀጣጠሉ እሳቶች ውስጥም ተግባራዊ ይሆናል፣ የሰው ተግባራት (ለምሳሌ የአፈር መሬቶችን ማፍሰስ) የእሳት አደጋን በእጅጉ ጨምሯል። እንዲሁም ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ እሳት በሚነሳበት ጊዜም ተፈጻሚ ይሆናል፣ የሰው ልጅ ተግባራት(ለምሳሌ ረግረጋማ ቦታዎችን ማድረቅ) የእሳት አደጋን በእጅጉ ይጨምራል።

- **ዘለቂ የሆነ የተፈጥሮ ደን ሽፋን ለዉጥ/ Lasting change of natural forest cover/:** ቋሚ ወይም የረጅም ጊዜ የተፈጥሮ ደን ሽፋን ለውጥ። የደን ሽፋን ወይም የደን መዋቅር ጊዜያዊ ለውጦች (ለምሳሌ በ FSC የደንብ ማዕቀፍ መሠረት መሰብሰብ እና ዳግም ተከላ) እንደ ልወጣ አይቆጠሩም።

- **ዘላቂ ከፍተኛ የአከባቢ እሴት ያላቸው ቦታዎች ለዉጥ/ Lasting change of High Conservation Value (HCV) areas /**፡የማንኛውም የከፍተኛ ጥበቃ እሴቶች ቋሚ ወይም የረጅም ጊዜ ለውጥ። በHCV የተያዙ አካባቢዎች ላይ አሉታዊ እና ዘላቂ ተፅዕኖ የማያሳድሩ ጊዜያዊ ለውጦች (ለምሳሌ እንደ መርህ 9 መሠረት መሰብሰብ እና ከዚያ በኋላ መልሶ ማቋቋም/ማልማት) እንደ ዘላቂ ለውጥ አይቆጠሩም።

- **መሰረታዊ የሆነ የዝርያ መመናመን/**Significant loss of species diversity/: የዝርያዎች መጥፋት ከፍተኛ ነው የሚባለው ብርቅዬ ዝርያዎች፣ ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች ወይም ሌሎች በአካባቢው አስፈላጊ የሆኑ፣ ቁልፍ እና/ወይም ዋነኛ ዝርያዎች ከቁጥር አንፃር ወይም ከዝርያዎች ብዛት አንፃር ሲጠፉ ነው። ይህ ደግሞ መፈናቀልንም ሆነ መጥፋትንም ያመለክታል።

**ማስታወሻ-** ኃላፊነት የተሞላበት የደን አስተዳደር ዓላማዎች(ለምሳሌ የደን መንገዶች፣ የመንሸራተቻ መንገድ፣ የእንጨት መጫኛ ቦታ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ ወዘተ) ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ አጋዥ መሰረተ ልማቶች ማቋቋም እንደ ልውጥ አይቆጠርም።

**የመቀየሪያ ገደብ (Conversion Threshold):** የተፈጥሮ ደን ሁኔታዎችን እና/ወይም ከፍተኛ የጥበቃ ዋጋ ያላቸው ቦታዎችን መልሶ ማግኘት ያለቀጥታ ጣልቃገብነት ሊሳካ በማይችልበት ደረጃ መመናመን እና/ወይም መመንጠር የተከሰተበት ደረጃ። (Source: FSC-POL-01-007 V1-0) ።

<u>ማሳሰቢያ:</u> የቀጥተኛ ጣልቃገብነት ምሳሌዎች የውጭ ዝርያዎችን በማስወገድ ብቻ ያልተገደቡ ናቸው፣ ያሉትን ቅሪት የሆኑ አገር በቀል እፅዋትን አካላዊ ጥበቃ፣ የደረቀ አፈርን እንደገና ማርጠብ፣ ተገቢ የሆኑ የሀገር በቀል ዝርያዎችን እንደገና ማስተዋወቅ እና ነባር ተስማሚ መካነህይወት ወይም እንደገና የተቋቋመ ለአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸው ዝርያዎችን መልሶ ማስተዋወቅ፡፡

**ዋና ቦታ (Core area):** የእያንዳንዱ ያልተነካ የደን መሬት ገጽታዎች ክፍል በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ባህላዊ እና ስነ-ምህዳራዊ እሴቶችን እንዲይዝ ነው። ዋና ቦታዎች የኢንዱስትሪ ተግባራትን ለማስቀረት የሚተዳደር ነው። ኮር ቦታዎች ያልተነካ የደን መሬት ግጽታዎች ፍቺ ያሟላሉ ወይም ይበልጣል።

**መስፈርት (Criterion (pl. Criteria))**: በመርህ መሠረት (የደን ባላደራነት) መፈጸሙን ወይም አለመፈጸሙን ለመዳኘት የሚረዳ ዘዴ ነው። /Source: FSC-STD-01-001 V4-0/

**ወሳኝ (Critical)**: የወሳኝነት ወይም የመሠረታዊነት ፅንሰ-ሀሳብ በመርህ 9 እና HCVs የማይተኩ እና በዚህ HCV ላይ የሚደርሰው መጥፋት ወይም ከፍተኛ ጉዳት ለተጎዱ ባለድርሻ አካላት ከባድ ጭፍን ጥላቻ ወይም ስቃይ ከሚያስከትልባቸው ጉዳዮች ጋር ይዛመዳል። የስነ-ምህዳር አገልግሎት* ወሳኝ ነው ተብሎ ይታሰባል (HCV 4) የአገልግሎቱ መስተጓጎል በአካባቢ ማህበረሰቦች ደህንነት፣ ጤና ወይም ህልውና ላይ፣ በአካባቢ፣ HCVs ላይ፣ ወይም ጉልህ የሆኑ መሠረተ ልማቶች (መንገዶች፣ ግድቦች፣ ህንፃዎች ወዘተ) ስራ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያመጣ ወይም ስጋት ሊፈጥር ይችላል። እዚህ ላይ የወሳኝነት ጽንሰ-ሀሳብ የሚያመለክተው ለተፈጥሮ ሀብቶች እና ለአካባቢያዊ እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እሴቶች አስፈላጊነት እና ስጋት ነው። (Source: FSC-STD-01-001 V5-2)

**ወሳኝ የቁጥር ጥግግት (Critical population density):** በተባይ ክምችት ውስጥ ከፍተኛው ተቀባይነት ያለው የግለሰቦች ብዛት ወይም መጠጋጋት፣ ከዚህም በላይ ተባዩ የአስተዳደር አላማዎችን ማሳካት አደጋ ላይ ይጥላል። የወሳኙን የቁጥር ጥግግት ግምገማሲደረግ ከተጎጂው አካባቢ የተገኙ የታሪክ መዛግብትን፣ ተባዮችን አይነት (ነፍሳት፣ አረም፣ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን፣ ወዘተ) እና የተባዮቹ ቁጥር ከጥግግቱ ጋር በተያያዘ እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል፣ በተጨማሪም በአነስተኛ ቁጥር ብዛት ሁኔታ ውስጥ የቁጥር ጥግግት እና የእድገት ምጣኔ አዎንታዊ ግንኙነት (በመስመር የሚተከሉ ዛፎች ተጽዕኖ) ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። (Based on: International Code of Conduct on the Distribution and use of Pesticides 2006)።

**በባህል ተስማሚ [ስልቶች] (Culturally appropriate [mechanisms]):** ከልማዶች፣ እሴቶች፣ ስሜቶች እና ዒላማ ታዳሚዎችን የአኗኗር ዘይቤዎች ጋር የሚስማሙ ቡድኖችን ለመድረስ የሚረዱ ዘዴዎች/አቀራረቦች።

**ልማዳዊ ህግ (Customary law):** እርስ በርስ የተያያዙ የባህላዊ መብቶች ስብስቦች እንደ ልማዳዊ ህግ ሊታወቁ ይችላሉ። በአንዳንድ ክልሎች ልማዳዊ ህግ በህግ አውጪዎች በጸደቀው ህግ ጋር እኩል ነው፣ በተወሰነው የብቃት ክልል ውስጥ ህጋዊውን ህግ ለተወሰኑ ብሄሮች ወይም ሌሎች ማህበራዊ ቡድኖች ሊተካ ይችላል። በአንዳንድ ክልሎች ልማዳዊ ህግ ህጋዊ ህግን ያሟላ እና በተለዩ ሁኔታዎች ውስጥ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ (Source: Based on N.L. Peluso and P.Vandergeest. 2001. Genealogies of the political forest and customary rights in Indonesia, Malaysia and Thailand, Journal of Asian Studies 60(3):761–812) ።

**ልማዳዊ መብቶች (Customary rights):** ከረዥምና ተከታታይ የተለመደ ወይም ልማዳዊ ድርጊቶች የሚወጡ መብቶች፣ ሳያቋርጥ የሚደጋገሙ፣ እንደዚህ ባሉ መደጋገም እና ያለሚረጥ በመቀበል፣ በጂኦግራፊያዊ ወይም ሶሽዮሎጂያዊ ክፍል ውስጥ የህግ ሀይል አግኝተዋል። (Source: FSC-STD-01-001 V5-2)

**መመናመን (Degradation):** በተፈጥሮ ደን ውስጥ ወይም ከፍተኛ የጥበቃ እሴት አካባቢ የዝርያውን ስብጥር በጉልህና በአሉታዊ ጉዳቶች የሚፈጠሩ ለውጦች፣ አወቃቀሩ እና/ወይም ተግባር እና ስነ ምህዳሮች አቅም ምርት ለመስጠት፣ ብዝሃህይወቱን ለመደገፍ እና/ወይም የስነምህዳሩን ግልጋሎቶች ለማቅረብ ያላቸውን አቅም ይቀንሳል፡፡ (Source:  FSC-POL-01-007 V1- 0) ።

**ቀጥተኛ ተሳትፎ (Direct involvement):** ተጓዳኝ ድርጅት ወይም ግለሰብ ተቀባይነት ለሌላቸው ተግባራት የመጀመሪያ እጅ ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታዎች (Source: FSC-POL-01-004 V2-0)

**አድልዎ/ Discrimination:** የሚያካትተው- ሀ) በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በብሄራዊ ማንነት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በፆታዊ ዝንባሌ ላይ የተመሰረተ ልዩነት፣ ማግለል ወይም ምርጫ፣ ይህም በስራ ወይም በሙያ ውስጥ የእድል ወይም እኩልነትን የሚሽር ወይም የሚጎዳ ውጤት ያለው፣ ለ) ሌላው አድልዎ የተመሰረተ ልዩነት፣ ማግለል ወይም ምርጫ፣ ይህም በስራ ወይም በሙያ ውስጥ የእድል ወይም እኩልነትን የሚሽር ወይም የሚጎዳ ውጤት ያለው በሚመለከታቸው አባል ከተወካይ ቀጣሪዎች እና የሠራተኞች ድርጅት ጋር ከተነጋገረ በኋላ እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር (ከ ILO ስምምነት 111 አንቀጽ 1 የተወሰደ)። በኮንቬንሽን 111 ላይ በተገለጸው ትርጉም ላይ 'የፆታ ዝንባሌ' ተጨምሯል፣ ምክንያቱም እንደ ተጨማሪ የመድልዎ አይነት ተለይቷል።

**ክርክር (Dispute):** ለIGI ዓላማ ይህ የአስተዳደር ተግባራትን ወይም ከFSC መርሆዎች እና መስፈርቶች ጋር መጣጣምን በተመለከተ ለድርጅቱ ቅሬታ ሆኖ የቀረበ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ቅሬታ የሚያቀርብበት ምላሽ የሚጠበቅበት ነው። (Source: based on FSC-PRO-01-005 V3-0 Processing Appeals)

**ከፍተኛ ቆይታ ያለው ክርክር (Dispute of substantial duration):** በFSC ስርዓት ውስጥ አስቀድሞ የተወሰነው የጊዜ ሰሌዳዎች ከሁለት እጥፍ በላይ የሚቆይ ክርክር (ይህ ቅሬታው ከደረሰ ከ6 ወራት በኋላ ነው፣ በ FSC-STD-20-001 ላይ የተመሰረተ) ።

**ከፍተኛ መጠን ያለው ክርክር (Dispute of substantial magnitude):** ለአለም አቀፍ አጠቃላይ አመላካቾች ዓላማ፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ክርክር ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሚያካትት ክርክር ነው፡

- የአገሬው ተወላጆች እና የአካባቢ ማህበረሰቦችን ህጋዊ ወይም ባህላዊ መብቶች ይነካል;
- የአመራር ተግባራት አሉታዊ ተፅእኖ ሊቀለበስ ወይም ሊቀንስ የማይችል ከሆነ;
- አካላዊ ጥቃት;

- የንብረት ውድመት;
- ወታደራዊ አካላት መገኘት;
- በደን ሰራተኞች እና ባለድርሻ አካላት ላይ የማስፈራራት ድርጊቶች።

ይህ ዝርዝር በደረጃ አዘጋጆች መላመድ ወይም መስፋፋት አለበት።

**ተገቢ እሳቤ (Due consideration):** በሁኔታዎች ውስጥ ተገቢነት ያለው በሚመስል መልኩ ይህን የመሰለ ክብደት ወይም ጠቀሜታ ለአንድ የተወሰነ ነገር ለመስጠት እና ይህ ማስተዋልን ያካትታል (Black's Law Dictionary, 1979)

**ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት (Economic viability):** በአንፃራዊነት ራሱን የቻለ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ክፍል ሆኖ የማደግ እና የመትረፍ ችሎታ። ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ሊጠይቅ ይችላል ግን ከትርፋማነት ጋር ተመሳሳይ አይደለም (Source: Based on the definition provided on the website of the European Environment Agency) ።

**ሥነ ምህዳራዊ-ክልል (Eco-regional):** በጂኦግራፊያዊ ልዩነቶችን ያጠቃለሉ ዝርያዎች፣ ተፈጥሯዊ ማህበረሰብ እና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ያሉበት ትልቅ የመሬትወይም የውሃ ክፍል (Source: WWF Global 200. http://wwf.panda.org/about_our_earth/ecoregions/about/what_is_an_ecoregion/) ።

**ሥርዓተ-ምህዳር (Ecosystem):** ተለዋዋጭ የሆነ የእፅዋት፣ የእንስሳት እና የጥቃቅን ህያዋን ማህበረሰቦች እና ሕያው ያልሆኑ አካባቢያቸው እንደ ተግባራዊ ክፍል መስተጋብር ይፈጥራል (Source: Convention on Biological Diversity 1992, Article 2) ።

**ሥርአተ ምህዳራዊ ተግባር (Ecosystem function):** ከሁኔታዎች እና ሂደቶች ስብስብ ጋር የተዛመደ ውስጣዊ የሥርአተ-ምህዳር ባህሪ (እንደ ዋና ምርታማነት፣ የምግብ ሰንሰለት፣ ባዮኬሚካላዊ ዑደቶች ያሉ)። የሥርዓተ-ምህዳሩ ተግባራት እንደ መበስበስ፣ ምርት፣ የንጥረ-ምግብ ኡደት እና የንጥረ-ምግቦች እና የሀይል ፍሰቶች ያሉ ሂደቶችን ያካትታሉ። ለ FSC ዓላማዎች፣ ይህ ፍቺ እንደ የዘረመል ፍሰት እና የችግር ድርጊት፣ የመልሶ ማቋቋም ዑደቶች እና የስነምህዳር ልማት (ስኬት) ደረጃዎችን የመሳሰሉ ሥነ-ምህዳራዊ እና የዝግመተ ለውጥ ሂደቶችን ያጠቃልላል። (Source፡ Based on R. Hassan, R. Scholes and N. Ash. 2005. Ecosystems and Human Well-being: Synthesis. The Millennium Ecosystem Assessment Series. Island Press, Washington DC; and R.F. Noss. 1990. Indicators for monitoring biodiversity: a hierarchical approach. Conservation Biology 4(4):355–364) ።

**ሥርአተ ምህዳራዊ አገልግሎቶች (Ecosystem services):** ሰዎች ከስርዓተ ምህዳሮች የሚያገኙት ጥቅሞች፡፡ እነዚህን ያካትታል፡ እንደምግብ፣ የደን ውጤቶች እና ውሃ ያሉ አገልግሎቶችን መስጠት፤ እንደ ጎርፍን፣ ድርቅን፣ የመሬት መራቆት፣ የአየር ጥራት፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና በሽታ የመሳሰሉ አገልግሎቶች መቆጣጠር፤ እንደ አፈር መፈጠር እና የንጥረ ነገሮች ዑደት ኢጋዥ አገልግሎቶች፤ እና ባህላዊ አገልግሎቶች እና ባህላዊ እሴቶች እንደ መዝናኛ፣ መንፈሳዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ሌሎች ቁሳዊ ያልሆኑ ጥቅሞች፡፡

(Source: Based on R. Hassan, R. Scholes and N. Ash. 2005. Ecosystems and Human Well-being: Synthesis. The Millennium Ecosystem Assessment Series. Island Press, Washington DC) ።

**ድንገተኛ ሁኔታ (Emergency):** ድንገተኛ ወረራ ወይም የተባይ ወረራ ለመቆጣጠር አፋጣኝ እርምጃ የሚፈልግ፣ ይህም ለስርዓተ-ምህዳሩ የረዥም ጊዜ መረጋጋት፣ የሰው ልጅ ደህንነት ወይም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን አደጋ ላይ የሚጥል ነው።

በእቅድ፣ ክትትል ወይም የተቀናጀ የተባይ መቆጣጠሪያ ስርዓትን በመተግበር የሚተነብዩ ክስተቶች እና ሁኔታዎች ዑደቶች እና ሁኔታዎች እንደ ድንገተኛ አደጋ ሊቆጠሩ አይችሉም።

ለFSC ፀረ ተባይ ማጥፊያ ፖሊሲ ዓላማ፣ የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ሁኔታዎች አፋጣኝ እርምጃዎችን ይጠይቃሉ እና በትንሹ አደገኛ አማራጭ ሊቆጣጠሩ አይችሉም። (Source፡ FSC-POL-30-001 V3-0)

**ቅጥር እና ሙያ (Employment and Occupation):** የሙያ ሥልጠና ማግኘትን፣ የሥራ ቅጥርን እና ልዩ ሙያዎችን ማግኘት እና የሥራ ውል እና ሁኔታዎች ያካትታል. (ILO Convention 111, Article1.3)፡፡

**መሳተፍና/ተሳትፎ (Engaging /engagement):** ድርጅቱ ፍላጎት ያላቸውን እና/ወይም የተጠቁ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ የሚያቀርብበት፣ዓላማቸውን፣ ምኞታቸውን፣ ግምቶቻቸውን፣ፍላጎቶቻቸውን፣ መብቶቻቸው እና እድሎቻቸው በአስተዳደር ዕቅድ ጅማሮ፣ ትግበራ እና ማደስ ላይ የሚገናኙበት፣ የሚያማክሩበት እና/ወይም የሚያቀርቡበት ሂደት (Source: FSC-STD-01-001 V5-2)።

**የአካባቢ እና የማህበራዊ ስጋት ግምገማ (Environmental and social risk assessment (ESRA):** በደንብ የተገለጸ እርምጃ ሊከሰት የሚችለውን ወይም ትክክለኛ የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅእኖን የመተንበይ፣ የማጥናት እና የመገምገም ሂደት፣ አማራጮችን በማመዛዘን እና ተገቢውን የመቀነስ፣ የአስተዳደር እና የክትትል እርምጃዎችን መንደፍ። በFSC ፀረ-ተባይ ፖሊሲ አውድ ውስጥ፣ ከኬሚካል ፀረ-ተባይ አጠቃቀም ጋር ይዛመዳል (Source: FSC-POL-30-001 V3-0)።

**አካባቢያዊ የስነህይወት ክትትል (Environmental bio monitoring):** ሁኔታን እና በሥርዓተ-ምህዳር፣ የብዝሃ-ሕይወት አካላት እና የመሬት ገጽታ ላይ ያሉ ለውጦችን የመከታተል እና የመገምገም ተግባር፣የተፈጥሮ አካባቢዎችን፣ ብዛታቸውን እና ዝርያዎችን ጨምሮ። (Source: Encyclopaedia of Toxicology (Third Edition, 2014)).

**የአካባቢ ጉዳት (Environmental harm):** በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነትበሰዎች እንቅስቃሴ ምክንያት አካባቢን የማራቆች ሀይል ምክንያት በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚደርሰው ማንኛውም ተጽእኖ (Source፡ FSC-POL-01-007 V1-0)

**የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (Environmental Impact Assessment (EIA)):** የታቀዱ ፕሮጀክቶች ሊሆኑ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተጽኖዎችን ለመለየት፣ አማራጭ አቀራረቦችን ለመገምገም እና ተገቢውን የመከላከል፣ የመቀነስ፣ የአስተዳደር እና የክትትል እርምጃዎችን ለመንደፍ እና ለማካተት ጥቅም ላይ የሚውል ስልታዊ ሂደት (Source: based on Environmental impact assessment, guidelines for FAO field projects. Food and agriculture organization of the United Nations (FAO). Rome,-STD-01-001 V5-2)

**የአካባቢ እሴቶች (Environmental values) ፡** የሚከተሉት ስነ-ህይወታዊ እና የሰው አካባቢ አካላቶች ስብስብ፡-

- የስርዓተ-ምህዳር ተግባራት (የካርቦን ማሰባሰብ እና ማከማቻን ጨምሮ);
- የህይወታዊ ልዩነት;
- የውሃ ሀብቶች;
- አፈሮች;
- ከባቢ አየር;
- የመሬት አቀማመጥ እሴቶች (ባህላዊ እና መንፈሳዊ እሴቶችን ጨምሮ)።
- የእነዚህ አካላት ትክክለኛ ዋጋ የሚወሰነው በሰው እና በህብረተሰቡ ግንዛቤ ላይ ነው (ምንጭ፡ FSC- STD-01-001 V5-2) ።

**እኩል ዋጋ ላለው ሥራ ለወንዶች እና ለሴቶች ሠራተኞች እኩል ክፍያ (Equal remuneration for men and women workers for work of equal value) ፡** በጾታ ላይ የተመሰረተ አድልዎ ሳይደረግበት የተቀመጡትን የደመወዝ መጠኖች ያመለክታል (ILO Convention 100, Article 1b).

**አቻ (Equivalent) ፡** ለሥነ-ምህዳራዊ አቻነት፣ አንድ ዓይነት የተፈጥሮ ደን ወይም ከፍተኛ የጥበቃ ዋጋ እንደወደመ ተመሣሣይ ወይም ተጠብቆ ይቆያል።

ለማህበራዊ መፍትሔ፣ እኩልነት በነጻ፣ በቅድሚያ፣ በመረጃ የተደገፈ ስምምነት (FPIC) ከሚመለከታቸው የመብት ባለቤቶች የሁሉም ማሕበራዊ ጉዳቶች ተፈጥሮ፣ጥራት እና መጠን እንዲሁም ወደፊት ሊመጡ ስለሚችሉ ጥቅማ ጥቅሞች ነፃ ግምገማ እና ስምምነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። እኩልነት የወደፊቱን የማህበረሰብ ደህንነት ለማረጋገጥ የሚቻለውን ምርጥ አማራጭ ማቅረብን ይጨምራል። (Source: FSC- POL-01-007 V1-0)

**የእግላይ ዞን (Exclusion zone) ፡** ኬሚካላዊ ፀረ-ተባዮች ጥቅም ላይ የሚውሉበት ቦታ እና ፀረ-ተባይ መድሃኒቶችን በሚጠቀሙበት ጊዜ እና በኋላ ሰዎች ወደ ውስጥ እንዳይገቡ የሚከለከሉት ተቀባይነት የሌለው የመጋለጥ አደጋን ለማስወገድ ነው. የተጋላጭነት ስጋት ተቀባይነት

ወዳለው ደረጃ (የዳግም የመግባት ጊዜ) እስኪቀንስ ድረስ የማግለል ግዛት በሥራ ላይ ይቆያል።

**ውጫዊ ነገሮች (Externalities) ፡** በነዚ ተግባራት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ በሌላቸው ባለድርሻ አካላት ወይም በተፈጥሮ ሃብት ወይም አካባቢ ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አወንታዊ እና አሉታዊ ተፅእኖዎች በአብዛኛው ወደ መደበኛ የወጪ ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ውስጥ በማይገቡበት ሁኔታ የነዚያ ተግባራት ምርቶች የገበያ ዋጋ ሙሉውን ወጪ ወይም ጥቅሞችን እንዳያንጸባርቁ (Source: FSC-STD-01-001 V5-2)።

**ፍትሃዊ ካሣ (Fair compensation)** ፡ በሌላ አካል ከሚሰጠው የአገልግሎት መጠን እና አይነት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ ወይም በአንደኛው አካል ላይ ከሚደርሰው ጉዳት ጋር የሚመጣጠን።

**ማዳበሪያ (Fertilizer) ፡** ማዕድን ወይም የህያው አፈር ንጥረ ነገሮች፣ በብዛት በተለምዶ N፣ P2O5 እና K20፣ በአፈር ላይ የሚተገበረው የእፅዋትን እድገት ለማሳደግ ነው።

**የጭረት ሙከራ (Fibre Testing) ፡** ድፍን እንጨትና ጭረት ላይ የተመሰረቱ ምርቶችን ቤተሰብ፣ ዝርያ፣ ዝርያ እና አመጣጥ ለመለየት የሚያገለግል የእንጨት መለያ ቴክኖሎጂዎች ስብስብ።

**የትኩረት ዝርያ (Focal species) ፡** የመሬት ገጽታው የሚከሰቱትን ዝርያዎች መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ መገኘት ያለባቸውን ባህሪያት የሚገልጹት ዝርያዎች መስፈርቶችን በቋሚነት ለማስቀጠል (Source: Lambeck, R.,J. 1997. Focal Species: A multi-species Umbrella for Nature Conservation. Conservation Biology Vol 11 (4): 849- 856.)።

**የግዳጅ ወይም የግዴታ ሥራ (Forced or compulsory labour) ፡** ከማንኛውም ሰው የሚቀጣው ሥራ ወይም አገልግሎት በማናቸውም ቅጣት መሠረት የተነገረው ሰው ራሱን/ራሷን በፈቃደኝነት ያላቀረበ ሲሆን (ILO Convention 29, Article 2.1)

**ደን (Forest) ፡** በአብዛኛው በዛፎች የተሸፈነ መሬት (Source: FSC-STD-01-001 V5-0. Derived from FSC Guidelines for Certification Bodies, Scope of Forest Certification, Section 2.1 first published in 1998, and revised as FSC-GUI-20-200 in 2005, and revised again in 2010 as FSC-DIR-20-007 FSC Directive on Forest Management Evaluations, ADVICE-20-007-01).

**መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የሠራተኛ ድርጅት (Formal and informal workers organization) ፡** ማህበር ወይም የሠራተኛ ህብረት፣ በሕግም ሆነ በድርጅቱ ወይም በሁለቱም ዕውቅና ያለው፣ የሠራተኛ መብቶችን የማሳደግ ዓላማ ያለው እና ከድርጅቱ ጋር በሚደረገው ግንኙነት በተለይም የሥራ ሁኔታን እና ካሳን ሰራተኞችን ለመወከል በሚመለከት፡፡

**የተበታተነ (Fragmentation) ፡** መኖሪያ አካባቢዎችን ወደ ትናንሽ ቦታዎች የመከፋፈል ሂደት፣ ይህም የመነሻ መኖሪያ መጥፋትን፣ የግንኙነት መጓደልን፣ ትናንሽ መኖሪያ ቦታዎች ስፋት መቀነስ እና የትናነሽ ቦታዎች መበጣጠስ ይጨምራል። በተለይ በደን የተሸፈኑ መልክዓ ምድሮችን ወደ አገር በቀል ዝርያዎች መጥፋት ከሚያስከትሉት ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱ መከፋፈል እና አሁን ላለው የመጥፋት ቀውስ ዋና መንስኤዎች አንዱ ነው ተብሎ ይታሰባል። ያልተነኩ የደን መሬቶችን በተመለከተ

